
# ከቡስካ በስተጀርባ

## ድንግል ውበት

ከፍቅረማርቆስ ደስታ



t.me/OLDBOOKSPDF

# ከቡስካ በስተጀርባ

## ድንግል ውበት

ከ

ፍቅረማርቆስ ደስታ

አዲስ አበባ – 1987 ዓ.ም

t.me/OLDBOOKSPDF

© ፍቅረማርቆስ ደስታ፥ 1987

ፖ.ሣ.ቁ. 6350
አዲስ አበባ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Reserved

በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ታተመ።
Printed by Educational Materials Production and Distribution Agency

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ለኅትመት በማብቃት ረገድ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዶክተር አሉላ ፓንክረስት፥ ለአቶ ጌታቸው ዘኪና ለአቶ መሐመድ አድረስ ÷ በተለይ ደግሞ ለጃፓን አንትሮፖሎጂስቶች ለዶክተር ማሳዮሺ ሺጌታ ÷ ዮኪኦ ሚያዋኪና ለሒሮሽ ማቱሱዳ እንዲሁም ለፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ደራሲው

የኮምፒዩተር ለቀማና የገጽ ቅንብር — ኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት
Computer typesetting and design — Ethiopia Book Centre

t.me/OLDBOOKSPDF

# 1

ባኞ ቤቱ ውስጥ ጠብ ጠብ ከሚለው የውኃ ድምፅ በተጨማሪ ላይ ላይ የምትተነፍስ ሴት ድምፅ ይሰማል። የመታጠቢያ ገንዳው ውኃ እስከ ወገቡ የደረሰ ሲሆን ካርለት ውኃው ውስጥ ጋደም ብላ ቀኝ እግሯን ገንዳው ከንፈር ላይ በማስቀመጥ ከግርጌዋ ያለውን የውኃ ማሞቂያ በተመስጦ ትመለከታለች። ከውኃ ገንዳው በስተቀኝ የእጅ መታጠቢያው ከፍ ብሎ ደግሞ በክፍሉ ሙቀት ሳቢያ የሚያዠው መስተዋት አለ። የመታጠቢያ ክፍሉ ጠበብ ያለ ቢሆንም ንጹሕና ዘመናዊ ነው። ከመግቢያው በር በስተግራ ካለው የቆሻሻ ልብስ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ካኔተራ፣ ሱሪና ጃኬት ተቀምጧል። ከሱ በላይ ሰፋና ረዘም ያለ በነጭና ሐምራዊ ቀለም የተዥጎረጎረ ፎጣ ተንጠልጥሏል።

ካርለት የገንዳውን ውኃ ቀይራ ሰውነቷን በንጹሕ ውኃ ከተለቃለቀች በኋላ ከገንዳው ውስጥ ወጥታ በጥቁርና ነጭ ቀለም የአጥር ሥዕል ከተሣለበት ጸጉራማ ምንጣፍ ላይ ቆመች። እርጥቡ ጸጉሯ ትከሻዋና ደረቷ ላይ ተለጥፏል። ከጸጉሯ ወደ ግንባሯ እየተንኳለለ የሚወርደው ውኃ በቅንድቧ ሥር እየሰረገ ተለቅና ሰርጉድ ያለውን ዓይኗን ያራጥባል። በደረትና ትከሻዋ አካባቢ ቁጥር ቁጥር ያለ የውኃ እንክብል ከመታየቱም ባሻገር ከሴት ብልቷ ላይ ካለው ስስ ጸጉር ላይ ደግሞ በውርጭ ሰሞን ሳር ላይ የሚታየውን የመሰለ ትንንሽ የውኃ ነጠብጣብ ይታያል።

ካርለት ወደ መስተዋቱ ቀረብ እንዳለች ገፅታዋ ከሚያዠው መስተዋት ውስጥ ተከፋፍሎ ታያት። መስተዋቱን ተወት አድርጋ በእጆቿ ጡቶቿን ጨበጥ ጨበጥ አደረገቻቸው። ቀኝ እጇ ቀኝ ጡቷ ላይ ሲቀር ግራ እጇ ግን ወደ ታች እየተንከላወሰ ጉዞ ጀመረ–ወደ ሴት ብልቷ። እጇ የደረሰበትን በዓይኗ ተመለከተችው።

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by

ከሰፊው የመስተዋት መስኮትና ላዩ ላይ ከተንጠለጠለው ነጭና ቡና ዓይነት መጋረጃ አልፎ አልፎ ዧ ብሎ የሚያልፍ የመኪና ድምፅ ይሰማል። በክፍሉ ውስጥ ካሉት ሁለት አልጋዎች መካከል አንድ ኮመዲኖ አለ። ኮመዲኖው ላይ «ሶኒ» የሚል ምልክት ካለበት ሬዲዮ ካሴት ውስጥ ከዛሬ ሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት በፊት በሞዛርት የተቀነባበረው ፒያኖ ሶናታ የሙዚቃ ስልት ድምፁን ሰለምለም – ሞቅ ሞቅ– ሰለምለም...እያደረገ ይንቆረቆራል። ከመስኮቱ ጠርዝ አካባቢ ሁለት ሶፋና አንድ ጠረጴዛ ያለ ሲሆን ጠረጴዛው ላይ ከግማሽ በላይ የተጠጣለት የማር አረቄ ይታያል።

ስቲቭ ማርቲን የአደረው «የዞረ ድምር» ዓይኖቹን ከርቸም ያለ እንቅልፍ አጋድሞታል። በአዲስ አበባው ሒልተን ሆቴል በተዘጋጀው የቡፌ ግብዣ ላይ ሦስት ወንበር እንዲያዝላቸው በማዘዝ ሁለቱ የፍቅር ጓደኛሞች ከኪሎ ሆራ ጋር በመሆን ምሽቱን ከምግብ ጉዝጓዙ በኋላ መጎንጨቱንና በአፍሪቃውያን ሙዚቃ መውረግረጉን እስከ እኩለ ሌሊት ሲያስኬዱት ቆይተው ነው ሁለቱ ፍቅረኛሞችና ኪሎ ሆራ «መሥመርህን ለይ» የተባባሉት።

ካርለት እና ስቲቭ የሥራ ቦታቸው በጣም የተራራቀና የትራንስፖርትም ችግር ያለበት በመሆኑ ተመልሶ ለመገናኘት ቢያንስ የሦስት ወር ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። በፍቅር አባዜ ለተያዙት ለእነዚህ ወጣቶች ደግሞ ጊዜው የትየለሌ ነው–ሩቅ። ስለ መለያየታቸው እንጂ ስለ መገናኘታቸው የማይተማመኑት ፍቅረኛሞች በወሲብና በፍቅር ጨዋታ ሰዓታቸውን በሚገባ ለመጠቀም በአንድ ወጥ ስሜት ጥረዋል። ድብቅነት በሌለው ንጹሕ የፍቅር ጨዋታ ልባቸውን ስልትና ቃናው በሚጣፍጥ ቅላፄ እያስጨፈሩ ራሳቸውን በመሆን በፍቅር ባሕር ከመዋኘት አልፈው ዘቅጠውበት አድረዋል።

ካርለት እንደምንም በድኗን ከስቲቭ እቅፍ መንጭቃ ተነሥታ ወደ ባኞ ክፍሉ በመሄድ ገላዋን ተጣጥባ ስትጨርስና በፎጣ ገላዋን ስታደራርቅ ከስቲቭ ረዘም ላለ ጊዜ የመለየቷን፣ የፍቅርና ወሲብ ጥመኛ የመሆኗን ትርዒት በእዝነ ልቦናዋ ስትቃኝ ፍርሃትና ጭንቀት መንፈሷን ሰንገው ያዙት። ተፈጥሯዊ ስሜቷ መኪና አይቶ እንደማያውቅ ፈረስ አእምሮዋን ጥሎ በረገገባት።



t.me/OLDBOOKSPDF

አንገቷን ዘንበል በማድረግ መጀመሪያ ጡቶቿን ከዚያም እምብርቷንና ሰርጓዳ ወገቧን፣ ለስላሳ ጭኖቿን ስትመለከት ስሜቷን በአእምሮዋ ለመቆጣጠር ተሳናት። ካርለት ስሜቷን ልትጫኑው ስላልፈለገች በግዴለሽነት የመታጠቢያ ክፍሉን በር በርግዳ ስትወጣ ስቲቭ ቀኝ እግሩን አጠፍ አድርጎ ጭኖቹን በመበርገድ ተንጋሎ ተኝቷል።

ካርለት ስቲቭን ስታየው የሆነ ስሜት በመላ አካሏ ቅጽበታዊ መተረማመስ ፈጠረና ፍቅር አመንጭ ሕዋሳቶቿ ተከፋፍተው ወደ ፊት ገፈተሯት። አእምሮዋም በስቲቭ አካል ላይ ቀስቱን ደገነ– የልግጠም፣ ይውጋኝ ፍልሚያ። «ግንኮ የስቲቭ ስሜት እንደኔ ላይሆን ይችላል? ስሜቴን መቆጣጠር መቻል አለብኝ። ሊደከመ ውም እኮ ይችላል!» ብላ አሰበች። ታስብ እንጂ መንቀሳቀሷን አላቆ መችም፤ የሚገፋፋት ስሜት ወደፊት አዳፋት፤ ተጠጋችው። ካርለት ያሰቡትን ለማድረግ መወሰን የሚሳንበት ወቅት መሆኑ ገብቷታል።

«ስቲቭ» አለች የእጅ ጣቶቿን ወደ ቡናማው ጸጉሩ እየሰገሰገች። ቦንብ ቢፈነዳ እንኳን የሚነቃ የማይመስለው ፍቅረኛዋ የእሷን ውብ ድምፅ ሰምቶ ዓይኖቹን ሲገልጥ የሚወደው ምስል እርቃን ሥጋውን ከአጠገቡ ቆሞ ሲያይ፣ «እ...» ብሎ ዓይኖቹን ገለጠ።

«ፍቅር የሚጣፍጠው ሲልሱት ሳይሆን ሲግጡት፣ ኩርሽምሽም አድርገው ሲውጡት፣ ከአካል ጋር ሲዋሐድ፣ የተፈጥሮ ቦታውን ሲይዝ፣ ደባቂና ተደባቂ ሲሆን እንጂ በቃላት ድርደራ አይደለም» ብላ የምታምነው ካርለት ለስቲቭ፣ «ና» የሚል ምልክት በእጇ አሳየችው። ያ እጇ ሁሌም ከሚያስደስተው አካሏና ውስጣዊ እሷነቷ እንደሚያደርሰው ያውቃልና ተከተለው።

በጣም ደክሞታል፤ ከካርለት እጆችና የፈገግታ ኃይል ግን ራሱን ሊለይ አልተቻለውም። ስለዚህ ወደ ተጠራበት አቅጣጫ ተጓዘ። ጉዞው ራቀበት፤ ከተጠራበት አካል ቶሎ ደርሶ ለመደሰት በጣም ጓጉቷል። ካርለት ባኞ ቤት ውስጥ እንደገቡ ገፍትራ ለብ ካለው ውኃ ውስጥ ከተተችው። ሣቀ፤ ሣቀች። ሁለመናቸው ተሣሣቀ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጭኖቿን ተመርኰዞ አንጋጦ ሲያይ የገነትን በር ያየ መሰለው። ታዲያ የዚያን ውብ ስፍራ በር ከፍቶ የማይገባ ማን አለ? በየጅማቱ ሥር ተበታትኖ የነበረው ኃይል ዘቅዝቆ ወደ ብልቱ ሲንዶለዶል ተሰማው። ያ — የተበታተነ ኃይል እንኳን የተፈቀደለትን፣ ሌላ ጠንካራ በር እንኳ ጥሶ የሚያስገባ ኃይል እንዳለው አመነ።

«እወድሃለሁ! ፍቅርህን አልጠግብም! ስግብግብ ነኝ። እንድትለቀኝ አልፈልግም...» የሚል ድምፅ የሰማ መሰለው። የቃላት ምልልስ ወቅቱ አለመሆኑን በመረዳቱ ግን እግሮቿን እየዳሰሰ ተነሣ! ሁለቱ አካሎች ተዋሐዱ። ፍጡር ካለ ክንፍ ወደሚንሳፈፍበት፣ ወደ ሰማየ ሰማያት ተነጥቆ የገነትን ውበት ወደሚጎበኝበት፣ ማራኪ መዓዛ፣ ውብና እንከን የለሽ ተፈጥሮ ወደሚታይበት፣ እውነተኛ የፍቅርና የደስታ ዜማ ወደሚዜምበት ዓለም ተያይዘው ነጐዱ! በሩ ተከፍቶ ተዘጋ።

* * *

ካርለት አልፈርድ በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ በሶስዮሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ካገኘች በኋላ በዩኒቨርሲቲው የአንትሮፖሎጂ ዲፓርትመንት አባል በመሆን በወቅቱ ታዋቂ በነበሩት አንትሮ ፖሎጂስቶች የተዘጋጁትን ጽሑፎችና ዲስኩሮች ተከታትላለች።

ከአሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን በተለይም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ እመርታን ካሳየበት ከዛሬ መቶ ሃምሳ ዓመት ወዲህ እየተዋጡ የመጡት ቅርሶች፣ የተናቁት ባህሎችና ለከፍተኛ ውጤት ሊያበቁ የሚችሉት የአርኪዮሎጂና የሌሎችም ጥናቶች የምሁራትን አእምሮ ይበልጥ በመሳባቸው እንደ ጀርመን፣ እንግሊዝ፣ ጣሊያን፣ አሜሪካና ጃፓን የመሳሰሉት ምሁራን ትኩረት እንደ ሰጡት እንግሊዛውያንም ምሁራንም በመስኩ እጅግ ተስበው ነበር።

በእርግጥ፣ የአንትሮፖሎጂ ጥናት የማይዳስሰው የሕይወት ክፍል እንዳለመኖሩ ሁሉ ጥናቱና ምርምሩ ችግርና ሰቆቃ የበዛበት በመሆኑ ብዙዎቹን ቢያስደነግጥም፣ ጥቂት በሙያው የተመሰጡና እራ ሳቸውን መሥዋዕት ያደረጉት ግን ከራሳቸው የሕሊና እርካታ በተጨ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግሪ ለሰው ልጆች ደኅንነትና ጥቅም ያደረጉት አስተዋፅኦና ለዓለ ማችን ይበልጥ መቀራረብ የተጫወቱት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው።

ካርለትም በወባ በሽታ ተይዘው የሞቱትን፣ የአውሬ ሲሳይ የሆኑትን፣ በነፍሰ ገዳይ የተገደሉትን...ስትሰማ፣ በዚህ ውጣ ውረድ በበዛው የሙያ መስክ ለመሰማራት ማሰቧ እራሷን ለመከራና ችግር መዳረግ ይሆናል ብላ በመገመቷ የተሳሳተ የሕይወት መሥመር የተከተለች መስሏት ሰግታ ነበር። እንዳጋጣሚ ሆኖ ግን፣ እርቃ ሳትሄድ የተለያዩ የጥናትና ምርምር ጽሑፎችን ስታነብና ከተመራማሪዎች አንደበት የሚወጣውን ንግግር ስታዳምጥ፣ የነበራትን ጥላቻ ለመመርመር ተገደደች።

መኖርና መሞት የሰው ልጅ አይቀሬ ዕጣ ፈንታ ቢሆንም፣ ዓላማ ያላቸው ሰዎች አለመሞታቸውን የሚያረጋግጡት በእስትንፋሳቸው መኖር ሳይሆን ለሕብረተሰቡ በሚያበረክቱት መልካም የሥራ ውጤት መሆኑን ስለምታምን፣ እሷም በሕይወት መኖሯን የማስመከር፣ በተለይም ሰው ሠራሽ ጾታዊ ግድቡን የማፍረስ ተልዕኮ እንዳላት ገባት።

ካርለት ዕድሜዋ አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆን፣ አባቷ ቻርልስ አልፈርድ በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ መምህር በመሆን እ.ኤ.አ እስከ 1955 ዓ.ም ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ስለ ደቡብ አፍሪካ የነጮችና ጥቁሮች ቋንቋና ኢትኖግራፊ ጥናት በማካሄድ በርካታ ጽሑፎችን ያቀረቡና ለንደን በሚገኘው የአንትሮፖሎጂስቶች ማዕከል ፕሮፌሰር የነበሩ ናቸው።

ካርለት በወርቃማው የወጣትነት ዘመኗ እንደማንኛውም የታላቋ ብሪታንያ ወጣት ሁሉ ብርቅዬ በሆኑ አልባሳት አጊጣ ከአገሯ አልፋ ፈረንሳይን፣ ጀርመንን፣ እስፓኝን፣ ካናዳን...በማካለል ተዝናና ታለች። ካርለት በእናቷ ትብብር ፒያኖና ቫዮሊን የሙዚቃ መሣሪያዎች አጨዋወት የተማረች ቢሆንም ከሙዚቃው ይልቅ ስሜቷ ወደ ፎቶግራፍ ማንሣት ጥበብ ስላጋደለ የፎቶግራፍ ጥበቡን ጀመረች፤ ሆኖም በዚህም ብዙ ሳትገፋ ተወችው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት ምርጫዋን ለማስተካከል ተስኗት ከፊል ጊዜዋን በመዝናናት ስታሳልፍ አባቷ ቻርልስ ዘመኑ ያቀረበላትን ማዕድ ባርከው ሲለግሷት፣ በወቅታዊው እፍ–እፍ ስሜቷ ውስጥ ጣልቃ ባይገቡም እንኳን ሕሊናቸው በወደፊት የልጃቸው ዕጣ ሕይወት መባዘኑ አልቀረም። ሜዲትራኒያንንና የሰሃራ በረሃን አቋርጠው በመጓዝ ስላዩት ተፈጥሮ፣ ባህልና ይዘው ስለተመለሱት የጥናትና ምርምር ውጤት ሲያወጓት፣ «እባክህ አባዬ የወሬ ርዕስህን ቀይርና ይልቁንስ ሽርሽር ይዘኸን ውጣ...» ስትላቸው፣ ምንም እንኳን ስሜታቸውን በገጽታቸው ባይገልጹትም ውስጥ ውስጡን ያማቸው ነበር። ያም ሆኖ ግን ልጃቸውን ጥናታቸውን ወደ አከናወኑበት ደቡብ አፍሪካ ሲወስዷት እግረ መንገዳቸውን በተፈጥሮ ሀብታቸውና ቅርሳቸው የሚያደንቋቸውን አገሮች ኢትዮጵያን፣ ኬንያንና ዝንቧቡዌን አስጐበኟት።

እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም ፕሮፌሰር ቻርልስ በአደረባቸው የልብ ካንሰር ሕመም ምክንያት ፒጃማ ለብሰው ቤት መዋል ከጀመሩና እልፈተ–ሕይወታቸው በግል ሐኪማቸው ከተረጋገጠ ማግስት ጀምሮ ስለ አባቷ የተጻፉ አስተያየቶችና አድናቆቶች የገዛ አባቷን ገድል እንደምትመረምር ጋበዟት።

ካርለት ለመጀመሪያ ጊዜ ካሸለበችበት በመንቃት የአባቷን ወርቃማ ሥራዎች ለመረዳት ተጣጣረች። ጥረቷ የዘገየና ፀሐይ ከጠለቀ በኋላ በመሆኑ ግራ ብትጋባም፣ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ዓላማቸውንና ያደረጉትንም አስተዋፅኦ ተገነዘበች። ያ–ወቅት በእርግጥ የወጣትነት ቡረቃዋን ገትታ፣ ዘላቂውን የሕይወት ድርሻዋን፣ የምትከተለውን ዓላማ ያጤነችበት፣ የረጋው ፍላጎቷ ማዕበሉ ተጠናክሮ የዋዠቀችበትና በመጨረሻም መልሕቋን በመወርወር ለውሳኔ የበቃችበት ወቅት ሆነ።

ወርቃማው ጸጉሯ፣ ድሎት ያወረዛው ፊቷና መካከለኛው ቁመናዋ በጅምናስቲክ በተገነባው ቅርፅዋ እየተረዱ የብዙ ወንዶችን



t.me/OLDBOOKSPDF

ልብ ያሸፈቱ ቢሆኑም፣ ተባባሪ የውበት አለኝታዎቿ አቅመ–ቢስ ሆነውባት እፏም በፍቅር ቡጢ ጥርሷ እስኪነቃነቅና እንባዋ እስኪጐርፍ ድረስ አፍቅራ ተመናቅራለች። እንዲያውም ይህ ልምዷ የተመኙትን ሁሉ ማግኘት አለመቻሉን፣ ፈላጊና ተፈላጊ መተላለፍ የሚያበዙ መሆናቸውንና የፈለጋት እንዲያገኛት በተቻለ መጠን መገኘት የሚያስችላትን ቦታ ፈልጋ እንድታገኝ ረዳት።

ካርለት፣ በሕይወቷ ሽንፈት ደጋግሞ እንደሚያጋጥማት ታምናለች፤ የምትፅናናበት ግን በፍላጎቷ ወደ ውድድር መድረክ መቅረቧና ከማን ከማን ጋር እንደምትወዳደር ማወቋ ነው። «ከተወዳ ዳሪዎቹ ሁሉ ጅሉ ሰው በውድድሩ ተካፍሎ ለማሸነፍ በመጣጣር አልሳካልህ ብሎ የተሸነፈው ሳይሆን፣ መወዳደሩንና ተወዳዳሪዎቹን ሳያውቅ ለድል የበቃው ነው» ማለት ታዘወትራለች።

ካርለት የማንችስተር ዩኒቨርሲቲ የአንትሮፖሎጂ ዲፓርትመንት አባል ሆና የማስተር ዲግሪዋን ካገኘች በኋላ፣ ለቀረው ጥናቷ ቀደም ሲል አባቷ ካሳይዋት አገሮች ኢትዮጵያን መረጠች። በማከታ ተልም ኢትዮጵያ ነክ የሆኑ የጽሑፍ፣ የፊልምና የስላይድ መረጃዎ ችን በየጕራንጕሩ ሁሉ እያነፈነፈች ከተመለከተች፣ በተለይም ስለ ኢትዮጵያ ዕውቀት ካላቸው አማካሪዋ ከፕሮፌሰር ጆን ፒደርሰን ጋራ በወደፊት የጥናት ቦታዋ ላይ በስፋት ከተመካከሩ በኋላ በእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪካ አንትሮፖሎጂስቶች የጥናት ድርጅት አባል ሆነች። ከዚያም በደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ማኅበረሰቦች ውስጥ በሐመር ማኅበረሰብ ባህል ላይ ጥናቷን ለመጀመር ከአማካሪዋ ጋር ተስማሙ። ልታከናውን ላሰበችው ጥናትም የእርዳታ ሐሳብ ለድርጅቱ አቀረበች። ድርጅቱም የጠየቀችውን በጀት አጸደቀላት። ካርልት፣ በዚህ በጀት ብቻም ሳትወሰን ለዓለም የሴቶች ኮሚቴም ተጨማሪ በጀት እንዲሰጣት ጠየቀች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 2

ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምርና ከሌሎች ተቋማት ለጥናቷ አስፈላጊ የሆኑትን ውጤቶች ካነበበችና ከግለሰቦች ጋር ሐሳብ ለሐሳብ ከተለዋወጠች በኋላ እግረ መንገዷን ሊረዳት የሚችል የክልሉ ተወላጅ አድራሻ፣ የጥናትና የጉዞ ፈቃድ አውጥታ ወደ ጥናት ቦታዋ ከመጓዟ በፊት ምሽቱን በአዲስ አበባው ሒልተን እንግሊዝ ኤምባሲ ከሚሠራውና ለተወሰኑ ወራት በአዲስ አበባው ቆይታዋ ጠረኑን ከለመደችው ጓደኛዋ ጋር እቅፉ ውስጥ ስትንቀሳቀስ አድራ እንደገና ገላዋን ታጠበችና ልብሷን ለባብሳ ወጣች።

በአስተሳሰቧ፣ በግልጽነቷና በውበቷ የነሆለለው ስቲቭ አለባበሷን፣ ከሰዓታት በፊት ፍቅር አመንጪ የነበረው አካሏ ተለውጦ ለሥራ መዘጋጀቷን ሲያይ እሱ ፍቅር ከፈጠረው የደስታ ዓለም ከነበረበት ፈጽሞ ሳይንቀሳቀስ እሷ ግን ገስግሳ ወደ ገሐዱ ዓለም በመመለሷ በፍጥነቷ ተደንቆ በተመስጦ ሲመለከታት ቆየና፣

«የኔ ቆንጆ አሁንም ታምሪያለሽ» አላት።

«ማግሬን እርሳው» አለችው።

«ለምን?»

«ከጥቂት ሰዓታት በፊት እኔም እረስቸዋለሁና።»

«የኔ ቆንጆ፣ ታዲያ ምን እንድልሽ ትፈልጊያለሽ?»

«የጉጉትን ዘዴ፣ የንስርን ማስተዋል፣ የአንበሳን ልብ፣ የኢዮብን ትዕግሥት፣ የአባትሽን ተስፋ አይቆርጤነትና አእምሮ ይስጥሽ በለኝ» ብላ፣ ጉንጩን ሳም አደረገችው።

ስቲቭ አስተያየቱን ጠለቅ አድርጎ ሲያስተውላት ቆየና፣ «አሁን አንችን የመሰለ ውብ ከእነዚያ ዘላኖች...» ሊናገር የፈለገውን ሳታስ ጨርሰው አፉን በአመልካች ጣቷ ከደነችው።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ማፍቀር ያለብህ እኔን ብቻ ሳይሆን ፍላጎቴንም እንዲሆን እፈልጋለሁ። ትልቁ ውበት ደግሞ ሥራ መሆኑን አትዘንጋ» አለች ውና ሌላ ቃል ሳይለዋወጡ ለቁርስ ከፍሉን ቆልፈው ወጡ።

* * *

ፈርጠም ያለ፣ የቀይ ሽንኩርት ቅርፅ መሳይ አፍንጫ ያለው፣ ዳጉስ ብሎ ቀላ ያለውን ከንፈሩን ሲገልጥ ነጫጭ ፍልጥ ጥርሶቹ የሚያማምሩና ከሸበላው ቁመናው ጋር የተስተካከለ አቋም ያለው ከሎ ሆራ ለየት ያለ ባሕርይ ይታይበታል።

ቁጥብነቱን፣ ጅንንነቱን፣ ጥርጣሬውንና ብቸኝነት መውደዱን ያዩ ጓደኞቹ፣ «ነብሮ» ይሉታል—የዩኒቨርሲቲ ጓደኞቹ። ቀልድ፣ ቧልት ከጀመሩለት እንደ ቆሰለ ጎሽ በንዴት ጦፎ ይፎገራል። ከሰው ጋር ደጋግሞ እንደ መጣላቱ ግን ኃይሉን ተማምኖ ተማቶ አያውቅም። ሁለቴ ሦስቴ ቃጥቶ—ቃጥቶ ማንም በማይገባው ቋንቋ አኩተምትሞ ዘወር ይላል። ታዲያ ብዙዎቹ አዳልጧቸው ቀልድ ብጤ ጀማምረው በዚያ ፈርጣማ ጡንቻው በሰነዘረ ቁጥር ጠረመሰን እያሉ አንዴ ከተሳቀቁ፣ «እርም» ብለው ይሸሹታል። ስለዚህ ምን እንደሚያበሽቀው፣ ያለፈው ሕይወቱ ምን እንደሚመስል፣ ብቸኝነቱ ከመቼ ወዲህ እንደ ጀመረው ከፍቶ ማየት የሚችል ሰው አልተገኘም—ግለቱ ስላላስቀረበ።

የተማሪን ቆብ አውላቂ መምህራን በለመዱት ቧልት «ጢብ—ጢብ» ሊጫወቱበት ይዳዳቸውና እንደ ከለመዳሪ የሚነፋውን ከንፈሩንና እሳት ተፊ ትናንሽ ዓይኖቹን ሲያዩ በተለይም በአንቀሳቀሰው ቁጥር እንደ አሎሎ የሚንከባለለውን ጡንቻውን ሲመለከቱ፣ «በቸር አውለኝ» ብለው አቅጣጫቸውን ሲቀይሩ ዓመታት ተቈጠሩ።

ከሎ ሆራ የአራተኛ ዓመት የሶሲዮሎጂ ትምህርቱን ሊያጠናቅቅ በተቃረበበት ወቅት በቀጭን ወገቧ ጂንስ ሱሪዋን በቀላል «ቲ—ሸርት» አስተካክላ ለብሳ፣ የተጉነጉነ ረዥም ጸጉሯን ወገቧ ላይ እያላጋች፣ ቶሎ ቶሎ በመራመድ ጫማዋን ቀጭ—ቋ—ቀጭ—ቋ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያደረገች የምትገሰግሰው ወጣት ከዩኒቨርሲቲው ፖስታ ቤት ወረድ ብሎ ከሚገኘው ኮሪደር ጫፍ ላይ ቁጭ ብሎ እግሩን እያወዛወዘ፣ ጠጠር ወደሚወረውረው ጥቁር ወጣት ተጠግታ፣ «ይቅርታ! ከ—ሎ ሆራ ነህ አይደለም?» ብላ ጠየቀችው፣ በእንግሊዝኛ።

«አዎ ነኝ» አለ ከሎ፣ ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ።

«ካርለት አልፈርድ እባላለሁ። እንግሊዛዊት አንትሮፖሎጂስት ነኝ። ስለ ሐመር ሴቶች ጥናት ለማድረግ ዓላማ አለኝ። አንተም የሐመር ተወላጅ መሆንህን ከዲፓርትመንትህ ኃላፊ ጠይቄ አረጋግጫለሁ» አለችና ንግግሯን በመግታት ትኩር ብላ ተመለከተችው። ከሎ ሆራ፣ የመርበትበት ስሜት አሳየና ከተቀመጠበት ፈጥኖ ተነሣ። ላብ ከወደግንባሩና ቅንድቡ አካባቢ ችፍፍ—ችፍፍ ሲል ከንፈሩ አመድ የነሰነሱበት መሰለ።

«ሶ፥ ለምን ፈለግሽኝ?» አላት በተቆራረጠ ድምፅ።

«እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ» አለችው፣ በዓይኗ እየመረመረችው።

«እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ?» ብሎ አባባሏን ደገመና ለትንሽ ጊዜ የመመሰጥ ሁኔታ አሳይቶ፣

«አዝናለሁ፣ ልረዳሽ አልችልም» አላት።

ካርለት፣ የከሎ ሰውነት ሲለዋወጥና ከብስጭቱ ጋር ሲታገል ያስተዋለች መሰላት፤ ስለዚህ ወጣቱ ከሷ ያለበለዚያም ራሱ ከራሱ ጋር ያልተግባቡት ወይንም ለእሷ ግልጽ ያልሆነላት ሌላ ምክንያት እንዳለው በመረዳቷ ተጨማሪ ጥያቄ ሳታነሣ፣ «አመሰግናለሁ። ነገር ግን ጊዜ ወስደህ ካሰብከበት በኋላ ሐሳብህን ከቀየርክ ‹አይ.ኢ.ኤስ› ልታገኘኝ ትችላለህ። ካለዚያም ስልክ ቁጥሬን ልሰጥህ እችላለሁ» ብላ፣ ፍጹም ልብ በሚነካ ፈገግታ የአድራሻዋን ካርድ ሰጥታው፤ «ደኅና ሁን» እያለች፣ እጇን አውለብልባለት ሄደች።

ከሎ ሆራ ወደ መቀመጫው ሲመለስ፣ የሚሰበቀውን ወገቧንና ጀርባዋ ላይ ከብሰል — ከብሰል የሚለውን ጉንጉን ጸጉሯን ሲመለከት ሐሳቡ ሸፈተበት። ከዓይኑ እስክትሰወር ድረስ በመደመም ሲመለከታት ቆየና ከጥቂት ደቂቃ በፊት የነበረበትን ድንገተኛ ሁኔታ ለማስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታወስ ሞከረ። «ሐመር...ጥናት...ውብ እንግሊዛዊት...የሐሳብ ፍጥጫ፤ የተዳፈነ እሳት ጭረት...እሳት ጫሪ አንትሮፖሎጂስት...ወጣትና ውብ...ዳሚት» አለ፤ እጆቹን ከተቀመጠበት ደረጃ ጋር እያላተመ።

* * *

ልቡ የአዶከበሬ አታሞ ይመስል እየተነረተ፤ ሰውነቱ ፀሐይ እንዳቆረናው የበረሃ ባልጩት ድንጋይ እያተኮሰ፤ እንቅልፍ ሲመኝ ግን ሲነቃ፤ ዕረፍትን ሲሻ፤ ሲንጠራወዝ፤ ሲገለባበጥ፤ በሐሳብ ሲድህና ፎቀቅ–ፎቀቅ ሲል አድሮ ዋለ።

ብዙ አወጣ አወረደ፤ ያለፈ የልጅነት መጥፎ ትዝታውንም አስታወሰ። አሁን ሊያደርግ የማይፈልገውን እንዲያደርግ ግብዣው ቀርቦለታል። ሌላው ቀን አልፏል። ለዛሬ ሥሩ ትናንት ነው። ትናንት ደግሞ እሱ የመከራ ጽዋውን የጨለጠበት ወቅት ነው። ዳግመኛ ሬት ሊያወርድ የሚችል ጉሮሮ የለውም። ስለዚህ በትናንት ቂም ያረገዘው አእምሮው አጓርቶና ድብልቅልቁ ወጥቶ እንዲሟሟና እንዲተን ይፈልጋል። ችግሩ እንዳሰበው ለማድረግ አቅሙ አለ ወይ ነው።

የልጅነት ጊዜው መጥፎ ትዝታ ጥርሱን አግጥጦ፤ ጥፍሩን በማሾል፤ የታባክ ይለዋል። ይኸኔ እንደ ልጅነቱ ልጅ ይሆንና በጭንቀት እየተንቦራቸ ይርበተበታል። ሊጮህ ይፈልግና ድምፁ አልወጣልህ ይለዋል። ትናንት ከገደል ውስጥ ወጥቷል፤ ዛሬ ግን ወደ ገደል ተገፍቶ ለመግባትና ለመሞት ዝግጁ አይደለም። መሞትም አይሻም–ለምን?

እንግዲህ ችግሩ ያለው በትናንትናና በዛሬ መካከል ነው። ልጅ ከነበረው ከሎና አሁን በአካልና በአእምሮ ካደገው ከሎ መካከል አንዱ ሽሽቱን ማቆም፤ አለበለዚያም፤ «በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ» እንዲሉ፤ በፍርሃት ላይ የጅብን ፍርሃት እያከለ ወደ ኋላ ሳያይ የሕይወትን ሩጫ መሸምጠጥ አለበት።

ትንሹ ከሎ ማምለጥ፤ መሸሽ ይፈልጋል–ከሐመር። ትልቁ ከሎ ደግሞ ልቡ ከሁለት ቦታ ተንጠልጥሎበታል። ከሎ ውሳኔው ሲከብደው ካርለት ከተወችለት ካርድ ላይ በብዕር የተጻፈውን ስልክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁጥር ተመልክቶ ስልክ ደወለ። «ሔ—ሎ ከሉ» አለችው እንደ ሕፃን ተቁነጥንጣ።

«...ደህና ነኝ» አላት።

«ምነው ልትገልጽልኝ የምትፈልገው ጉዳይ አለ?» አለችው።

«ለመሄድ ፈቃደኛ ነኝ» አለ ከሉ።

በእርግጥ በአካልና በአእምሮ ያደገውን ከሉ ከዚያ የግፍ ጽዋ ከጨለጠው እንቦቀቅላ እሱነቱ ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ይፈልጋል። ማን ያውቃል ይህ የቀረበለት ግብዣ ሰበብ ሊሆን ይችላል። በሌላ ጐኑ ደግሞ ትምህርቱን ከልምድ ጋር ማቆራኘት ያስችለዋል።

ማንም የሚያውቃት ትንሿ ሣር አዋዝታ፣ ሰርስራ ፈርጣማ ጡንቻ ብቻውን የማይችለውን ድንጋይ ሰንጥቃ ብቅ ትላለች፣ ታድጋ ለች። ሊታመን በማይችል ሁኔታ ትንሿ ሣር ድንጋይ በስታ ሕያው ስትሆን አይቷል። ችግሩ ግን እንዴት የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ የሕሊና ጥያቄ ደግሞ መመለስ እንዳለበት ያምናል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የዚያች የሥነ—ስብእ ተመራማሪ ሶምሶማ ረጋጭ ዳሌ ቀልቡን ገፎታል። ስለዚህ ይህ ዕድል እንዳያመልጠው «ዊዝድሮዋል» ለመጠየቅ ቢወስንም በስልክ በሰጠው የመሄድ ፈቃደኝነት ግን መደንገጡ አልቀረም።

«በጣም አመሰግናለሁ። ይህ ለኔ ትልቅ ዜና ነው። ግን...» ከሉ ሐሳቧን ሳያስጨርሳት፣ «ለጊዜው እንድታነሽብኝ አልፈልግም። ሐመር አካባቢ ሄጄ ልረዳሽ ግን ፈቃደኛ ነኝ» አላት። ቀጥሎ ያኩተመተመውን ግን አልተረዳችውም። የመከፋት ስሜቱን ግን በድጋሚ አጤነች።

ካርለት የስልኩን እጀታ እንደ ያዘች በሐሳቧ፣ «ጥሩ፣ የጓዳው ሲደርስ ይከፈታል፤ ዋናው ፈቃደኛ መሆኑ ነው» አለችና፣ «ታንኪው ...አ... አመሰግናለሁ...» አለች ፍንድቅድቅ ብላ፣ «ኢ—ህ» ብሎ አጸፋውን መለሰላት። የሱ የልብ ፈገግታ የመጨረሻው ኮታ ይኸው ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት፣ ደስታዋን እየተቆጣጠረች ስትመጣ ለከሎ ሆራ ቀጠሮ ከመስጠቷ በፊት ስልክ እንደምትደውል ገልጻለት ለተወሰነ ጊዜ እንዲጠብቃት ከይቅርታ ጋር ጠየቀችው። ከትንሽ ደቂቃ በኋላም፣ ሒልተን ሆቴል ልትጋብዘው እንደምትፈልግና የሴት ጓደኛውንም ይዞ ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ኢትዮጵያ ሆቴል እንዲመጣ ነገረችው።

ከሎ፣ የስልኩን እጀታ ካስቀመጠ በኋላ፣ «የእኔ ተፈጥሯዊ ግለት የሚበርደው...የምን ሴት ጓደኛ? እንኳን የሴት፣ ለወንዱስ ጓደኛ መቼ! እኔ ያሰብኩት...እሳት ጫሪ አንትሮፖሎጂስት... ዳሚት» ብሎ አጉተመተመ።

ከሎ ከሶሲዮሎጂ ይልቅ የሳይኮሎጂ ትምህርት እጅግ ይመስጠዋል። በተለይ የሲግመንድ ፍሮይድ፣ «ሰው በተፈጥሮው ‹ወሲባዊና ሞገደኛ ነው› የሚለው እምነቱ፣ ብዙውን የሕይወት ክስተቶች ቁልጭ አድርጎ ያሳየዋል።

የሰው ልጅ ባህላዊ ገዴታዎች ባይኖሩበት ኖሮ በወደዳቸው ሴቶች ላይ ጉብኘውን ሳያፍር ዘሎ ከተጓዳኙ ጀርባ ላይ እንደሚወጣ የ‹ዙ› ጎሪላ ዝንጀሮ፣ ወይንም ጭንቅላት ነክሶ እንስቷ ጀርባ እንደሚኮፈስ አውራ ዶሮ ይሆን ነበር። ሆኖም አንደበት በባህላዊ ዜጥ ተሸብቦ፣ ልብ እየዘለለ ሲፈርጥ፣ ውጫዊ አካል ግን አገር ሰላም ነው እያለ ጥሩንባውን ይነፋል። ስለዚህ ስሜት ውሃ ይከለስበትና እንዲከስል ካለያም እንዲሸጎርበት ይደረጋል።

ከሎ፣ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ልቡ የከጀላትን ሴት ለማግኘት እንዳይሞክር የባህል ተጽዕኖ እንደተቀየደች በቅሎ ኮድኩዶታል፤ በስጨት ብሎ ኃይል እንዳይጠቀም ደግሞ ባህልና ሕግ እጁን ጠፍሮታል። ስለዚህ ተፈጥሮን በተፈጥሮ ሕግ እንዲገዛ ከማድረግ ይልቅ ከትውልድ ትውልድ በሚተላለፍ የባህል ገመድ ተጠፍሮ እርካታ አልባ ሆኗል– የሚፈልገውን ሳያጣ። ከሎ ወደደም ጠላ በዚህ ባህላዊ ክርን እየተደቆሰ ነው።

ከሎ ሆራ ሒልተን ሆቴል ለመሄድ ከካርለት ጋር ከተቀጣጠረበት ኢትዮጵያ ሆቴል ሲገባ ከበስተግራ በኩል ካለው ተንቀሳቃሽ የብረት



t.me/OLDBOOKSPDF

አጥር ላይ እየተጠላለፈ ከወጣው ሐረግ ስር አሾልኮ ሲያይ፣ ካርለት ፈገግ ብላ እሱን ለመቀበል ከመቀመጫዋ ስትነሣ ከጎኗ ሙሉ ቡላ ሱፍ፣ በነጭ ሸሚዝ ላይ ቀይ ክራቫት ያሰረ የውጭ ዜጋ አብሯት ሲነሣ ተመለከተ። ካርለት ከሎን ከጨበጠችው በኋላ ከጎኗ ወደ ቆመው ሰው እያመለከተች ጓደኛዩን ላስተዋውቅህ አለችው። የውጭ ዜጋው «ስቲቭ» ብሎ እንገቱን በማወዛወዝ እጁን ዘረጋለት። ከሎ በልቡ፣ «ዳሚት» ብሎ፣ የፈረንጁን ጣቶች ጨፍልቆ ያዘ። ያኔ ስቲቭ፣ «አ» ብሎ ቀኝ እግሩን አነሣ። ይቅርታ መጠየቅ ያለመደው ከሎ ግን ለቆት ወደ ካርለት ዞረ።

ካርለት በተለይ ከሎን እንዲቀመጥ ጋበዘ፣ «ምን ትጠጣለህ?» አለች። ከሎ ተፈጥሮ ባሕርይው ሆኖና ሲጠየቅ ቶሎ መመለስ አይወድም። ስለዚህ ሶፋው ላይ በመቀመጥ ዝም ብሎ ዓይን–ዓይኗን ተመለከታት። «አምላኬ!» አለችና ጥርሷን ሳታሳይ ፈገግ አለች።

«ለስላሳ»አለ ከሎ ጥቂት ከጠበቀችው በኋላ። ስቲቭ እጆቹን ትከሻዋ ላይ አድርጎ ከኢንግላንድ ስለ ደረሰው ደብዳቤ ያወራታል። እሷ ግን የከሎ ዝምታና የስቲቭ ቅብጥብጥነት አልስማማሽ አላት። የመድረክ ተዋናይ የመሰለችው ወጣት ሁለት ባሕርያቸው፣ «አራምባና ቆቦ» የሆኑ ሰዎች ማስተናገድ በሁለት መሰላል የመውጣት ያህል ከበዳት።

ሒልተን ሆቴል ከሄዱም በኋላ ስቲቭ እቅፉ ውስጥ ሸጎጥ አድርጎ ሲደባብሳት ከሎ ለንቦጩን ይነፋባታል። ስቲቭ ያየውን ሁሉ ሲያደንቅ፣ ከሎ ያየውን ሁሉ ዳሚት ይላል። ሰው ሁሉ ለዳንስ መድረኩ መሃል ሲገባ፣ ከሎ ቁጭ ብሎ ቢራውን ያንቀረቅራል፤ ሌላው ዕረፍት ሲወስድ ደግሞ እሱ በመደነሻው መሃል ቆሞ ሲያኩተመትም ሌሊቱ ተጋምሶ ወደሚያድርበት ሰፈር ሲያደርሱት ምንም ሰላምታ ሳይሰጣቸው ወጥቶ ጉዞ ጀመረ። ካርለት ከስቲቭ «ቢ.ኤም.ደብሊው» መኪና ወርዳ ስትሰናበተው ዘወር ብሎ አይቶ፣ «ኢ–ህ» ብሏት ሄደ። ሁለቱ ፍቅረኛሞችም እርስ በእርሳቸው በአድናቆት ተያይተው ቀሪው የሌሊት ትዕይንት ወደሚታይበት የመኝታ ክፍላቸው ከነፉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 3

ሁለት ሳምንት አለፈ። ካርለትና ከሉ የየራሳቸውን የጉዞ ዝግጅት ሲያደርጉ ሰነበቱ። ከሉ ሐመር ሲሄድ የሚያነባቸው ልብወለድና ታሪክ ነክ የአማርኛ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ በእንግሊዝኛ የተጻፉ ልብወለድና የሳይንስ መጻሕፍትን እየገዛ ከፊሉንም እየተዋሰ አዘጋጀ።

በተለይም ካርለት ኮተቷ በዛ። በማስታወሻዋ በዝርዝር ከያዘችው አስፈላጊ የምግብ ዓይነቶች የታሸገ የዓሣ፣ የአሳማ፣ የከብት ሥጋ፣ የድንች፣ የዱባ፣ ያጃ ሾርባ፣ የፓፓያ፣ የብርቱካን፣ የአናናስ ጭማቂ፣ ኃይል ሰጪ ንጥረ–ነገር የበዛበት ብስኩት፣ ደረቅ ብስኩት፣ የቆርቆሮ ቢራ ወዘተ. ከመድኃኒት ዓይነትም ክሎሮኪን፣ ፓልዱሪን፣ ኒቫኩይን ለወባ መከላከያ፣ ሌሎች፣ «አንቲባዮቲክስ» መድኃኒቶችንና የመጀመሪያ ሕክምና ኪት፣ ኮዳክ ፊልሞች፣ ባትሪ ድንጋዮች፣ ሶፍቶች ወዘተ. በአራት የፕላስቲክ ሣጥኖች ደረደረች። ካኖንና ፔንታክስ ካሜራዋንና የተለያየ መጠን ያላቸውን ሌንሶች በእጅ በሚንጠለጠለው ቦርሳዋ፣ ካኪ ሱሪዎች፣ ካኔትራ፣ ውስጥ ሱሪ፣ ፎጣ፣ ጡት ማስያዣ፣ ስሊፒንግ ባግ፣ ግራጫ መልክ ያለው ሹራብ፣ በአየር የሚሞላና ሌላ ተጣጣፊ ፍራሽ፣ ሳሙና፣ ኦሞ፣ ከሁለት መቶ ሃምሳ ዓመት በፊት በሞዛርት የተቀነባበሩ የፒያኖ ሶናታና የፒያኖ ኮንቸቶ፣ የቤቶቪን ሲንፎኒ፣ ከሦስት ጊዜ በላይ የወርቅ ዲስክ አሸናፊው ድምፃዊ የቢሊ ጆይል፣ ከሦስት መቶ ዓመት በፊት የነበረውና የሲንፎኒ አባቱ የሃይደን እንዲሁም ሌሎቹን የባሮክ ክላሲካል፣ ሮማንቲክና ዘመናዊ የሙዚቃ ካሴቶችን፣ ማስታወሻ፣ ብዕር፣ መጻሕፍትና መጽሔቶች በአራት ማዕዘኑ የብረት ሣጥን ውስጥ ከተተች። ለሽፍን ላንድ–ክሩሰር ቶዮታ መኪናዋም በሁለቱም ታንከር ነዳጅ ሞላች። አምስት ጀሪካን ናፍጣም ለመጠባበቂያ ያዘች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት ለሦስት ወራት የሚያስፈልጋትን ቁሳቁስ ካሟላች በኋላ ቀሪውን ዕቃዋንና ገንዘቧን ስቲቭ በሰጣት ክፍል ውስጥ አስቀመጠች። ለአንዳንድ ወጪ ብላ የያዘችውን ሦስት ሺህ አምስት መቶ የኢትዮጵያ ብርም በሹራቧ ውስጥ በሰፋችው ስውር ኪስ፣ አንገቷ ላይ በምታንጠለጥለው የጨርቅ ቦርሳና ብረት ሣጥኑ ውስጥ አከፋፍላ ያዘች።

ሰኞ ጠዋት ልክ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ አራት ኪሎ ሞቢሉ ጎን ካለው ሉቅ በር ላይ በቀጠሯቸው ተገናኙ። ካርለት ልጥፍ የኋላ ኪስ ያለው ካኪ ሱሪ፣ ተረከዙ ፕላስቲክ የሆነ ሸፍን ባለማሰሪያ ጫማ፣ ቡና ዓይነት ቲ—ሸርት ለብሳ፣ አንገቷ ላይ አነስ ያለ ነጭ ፎጣ ጣል አድርጋ፣ ከመኪናው በመውረድ የከሎን «ዩ—ኤስ—ኤ» የሚል ወስፋት የነፋው የሕፃን ሆድ መስሎ የተወጠረ ቦርሳ የኋላ በሩን ከፍታ በዕቃ ከሞላው መኪና ውስጥ በአንድ በኩል ባለው ክፍት ቦታ አስገባችና ወደ መኪናው ውስጥ ገቡ። ካርለት የውኃ ኮዳዋን፣ ዳቦ የያዘ ላስቲኳን አቀረበችና ከከሎና እሷ መካከል ካለው የካሴት ሣጥን የሞዛርትን ፒያኖ ሶናታ ወደ መኪናው ቴፕ አስገብታ ማስታወሻዋን በማውጣት የተነሡበትን ሰዓት መዘገበች። ከዚያም ፈገግ ብላ፤ «መሄድ እንችላለን?» አለችው።

«ኢ—ሀ» አላት ከሎ፣ ዝግጁ መሆኑን አንገቱን በማወዛወዝ እየገለጸ። ካርለት፣ ቀኝ እጇን ማርሹ ላይ በማስቀመጥ፣ በግራ እግሯ ፍሪሲዮኑን እረግጣ፣ የመኪናውን መስተዋት አየት—የት በማድረግ በአራት ኪሎው የድል ሐውልት ወደ ቀኝ ታጥፈው፣ በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት አድርገው ቁልቁል ወደ መስቀል አደባባይ ወረዱ። ከዚያም በደብረ ዘይት መንገድ ወደ ቃሊቲ፣ አቃቂ፣ ዱከም ተጉዘው ደብረ ዘይት ከተማ ሲደርሱ ወደ ግራ ታጥፈው ሁለት ኪሎ ሜትር በመጓዝ መኪናዋን ሆራ ሆቴል አቁመው ለቁርስ ወደ ውስጥ ገቡ። በስተጀርባ፣ ከሐይቁ ትይዩ የመርከብ ላይ መናፈሻ ከሚመስለው ስፍራ ሆነው የተለያዩና ቁር—ቁር እያሉ በመዘመር የሚበሩ አዕዋፍን እያዩ ቁርሳቸውን ተመግበው ወጡ። ካርለትና ከሎ ሆራ በሞጆ ታጥፈው፣ ወደ ሻሸመኔ ጉዟቸውን ተያያዙ። ካርለት፣ በመንገዱ ግራና ቀኝ የግራር፣ የጥድ፣ የኮሶ፣ የዝግባ...ዛፎችንና የተለያዩ ቀለም ያላቸውን እፅዋት እያየች፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚገኙት ከሃያ በላይ አዕዋፋት ውስጥ የምታያቸውን በመልክና በቅርፃቸው ለማወቅ በጆን ጂ ዊሊያምስና በኖርማን አርሎት የተጻ ፈውን የአዕዋፍ ምስል፤ ቀለም ባሕርይና የሚገኙበትን አካባቢ እያ የች ተጓዙና ለምሳ በስምጥ–ሸለቆ ካሉት ሐይቆችና የመናፈሻ ቦታ ዎች አንዱ ወደሆነው ወደ ላንጋኖ ከመንገዱ ወደ ግራ ታጥፈው ገቡ።

ላንጋኖ ሆቴል ምግብ ቤት ብዙ የውጪ ሀገር ዜጎች፤ አፍሪ ቃውያንና ኢትዮጵያውያን ክብ እየሠሩ በመጫወት ይመገባሉ። ከሆ ቴሉ ውጪ በቀላል ድንኳን ጥግ፤ በዋና ውስጥ ሱሪና ጡት ማስያዣ ሆነው የፀሐይ ክሬም ሰውነታቸውን የሚቀቡና ሐይቁ ዳር ለዳር የሚዋኙ ሴትና ወንዶች ይታያሉ። ጥቁርና ነጭ ሕፃናትም በመዋኛ ፕላስቲክ ውኃውን በማንቦራጨቅ እየተንጫጩ ይጫወታሉ።

ከሎና ካርለት ከምግብ ቤቱ ትይዩ የፀሐይ ጃንጥላው ውስጥ ተቀምጠው ቡናቸውን ሲጎነጩ ቆዩና ካርለት የሐይቁን ዳር ትርምስ አሸጋግራ ስትቃኝ ቆይታ፤ «ሐይቅ ዳር ስሆን እረካለሁ፤ አገሬ ውስጥ ከጓደኞቼና ቤተሰቦቼ ጋር ያለሁ ስለሚመስለኝ የደስታ ስሜት ይሰማኛል። በአውሮፓ፤ ብዙዎች መዝናኛዎች የሚገኙት ባሕር ዳርቻ ነው። ብቻ...» ካርለት ከሎ ሆራን በጎን ተመለከተችው።

«ኢ–ሀ» አላት፤ እግሮቹን ወደፊት በመዘርጋት ሰውነቱን ለጥጦ። ካርለት የከሎ ሆራ ጠባይ ደንቋታል፤ ግን አልከፋትም። በቀላሉ ከምትግባባቸው ሰዎች ይልቅ አስቸጋሪ ባሕርይ ያላቸውን ታከብራለች። ሁሉም ሰው ሊረዳው የሚችል ባሕርይ ያላቸው ሰዎች ለሷ አያረኳትም። እረቀቅ ያለ ባሕርይ ያላቸውን ግን አእምሮዋን አስደንሳ፤ መላ ፈጥራ፤ የተለያየ ስልት በመጠቀም እንደ ግል ሬዲዮና መክፈት መዝጋት እንደ መቻል የምትረካበት ነገር የለም። ለዚህም ካርለት፥ «ዘመናችን የሚመርጠው ልዩና ውስብስብ አስተሳሰብ ያላቸውን ነው። ምክንያቱም የነገው ፈጠራና ብሩህ ሕልም ህላዊነት በመዳፋቸው መሃል ያለው ከእንዚህ ዓይነት ግራ አጋቢ ባሕርይ ካላቸው ሰዎች ነው» ብላ ታምናለች።

ከሎ ቅንና ተባባሪ ሰው መሆኑን፤ ነገር ግን ይህን ባሕሪውን የሚገልጽ የቃላት ድርደራ ችሎታ የሚጎድለው መሆኑን



t.me/OLDBOOKSPDF

ተገንዝባለች። ካርለት ከሉን የተለያዩ ነገሮችን እያወራች፣ እየጠየቀች የቱ እንደሚያስደስተው፣ የቱ አፍንጫውን እንደሚ ያስነፋውና ጥንካሬውን ከደካማ ጎኑ ለመለየት ምርምሯን ስለ ቀጠለች አንድ ወጥ በሆነው የሥውር ባሕርይው ዋሻ ለመግባት ትልቁን የድንጋይ መዝጊያ ማንቀሳቀስ ጀምራለች።

«አዎ! የከሉ ባሕርይ ራሱ መጠናት የሚገባው ነው። እሱን ለማጥናት ግን አስፈላጊውን ቁልፍ ማዘጋጀት አለብኝ» አለች ካርለት፣ ከሻሸመኔ ከተማ ወጥታ የአርባ ምንጭን መንገድ ስትይዝ። ከሻሸመኔ ትንሽ ራቅ ብለው የአስፋልቱ ጉዳና አልቆ ኮረኮንቹን መንገድ ሲጀምሩ ግን መኪናዋ እየተገሜጨች ስትንሰጠሰጥና ከፊት ለፊቷ ያሉትን መኪናዎች ስታልፍና ከእሷ ተቃራኒ የሚያልፋት መኪናዎች የሚያነሡት አቧራ መኪናዋ ውስጥ እየገባ ማፈን ሲጀምር፣ ካርለት መኪናዋን አቁማ፣ ጸጉሯን በመሸብለል፣ ቆብ ደፋችበትና መኪናዋን በማንቀሳቀስ ከመሪው ጋር መታገል ጀመረች።

ካርለት፣ መኪናዋን በሰዓት ከሥልሳ እስከ ሰማንያ ኪሎ ሜትር በሚደርስ አማካኝ ፍጥነት እያሽከረከረች እንደተጓዙ ከፊት ለፊታቸው አንድ እስከ አናቱ ድረስ የታረሰና የተለያዩ እፅዋት ያሉበት ተራራ ተመለከቱ። ከተራራው ግርጌ ራቅ–ራቅ ያሉ መንደሮች ሲኖሩ፣ በየመንገዱ አካባቢ ሙዝ፣ እንሰት፣ ጥድና ባሕር ዛፍ ይታያል። ከመንደሮች ራስጌና ግርጌ እንዲሁም ግራና ቀኝ የበቆሎ፣ የጤፍ...አዝርእት ተመለከቱ። ካርለት የአካባቢው ልምላሜና በኮርቻ ፈረስ በሶምሶማ ግልቢያ የምታያቸው ሰዎች ስላስደነቋት፣ «አ! ልምላሜ የተላበሰ ግራኪ ነው። ምን የሚባለው አካባቢ ነው?» ብላ ከሉን ጠየቀችው።

«ወላይታ።» አጭር መልስ መለሰላት።

«ወ–ይ–ታ» አለች፣ መጥራቱ ከብዷት።

«ወላይታ–ወ–ላ–ይ–ታ» አላት፣ ፊደሉን እየቆጠረ። ከዚያም ስለ ማኅበረሰቡ ቋንቋ፣ ባህል ጠየቀችው። ካርለት በከተማው ስታልፍ እንደተለመደው አዋቂ ወንዶችና ሴቶች እጃቸውን አውለበለቡላት፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ሕፃናት፣ «ፈረንጅ» እያሉ ጨፈሩላት። መኪናዋን ስታቆም ከበቧት፣ እጇን ለመያዝም ተሯሯጡ።

ካርለትና ከሉ ወላይታን ካለፉ በኋላ ምዕራብ አባያ ላይ በቅርጫት የተከመረ ፓፓያ፣ ገና ያልቀላ አረንጓዴ ሙዝ ከነመያዣው፣ ሎሚው ተደርድሮ ተመለከተች። በተለይ አርባ ምንጭ ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው ባገኟት ላንቴ ከተማ ያዩት ሙዝ አንዱ ለሦስት የሚበቃ ሆኖ አገኘችው። መኪናዋን ስታቆም፣ «ሙዝ፣ ፓፓያ፣ ሎሚ» እያሉ የመኪናውን መስኮት ከበቡ።

ካርለት አንዱን ቁና ሙዝ ተቀብላ ዋጋውን ጠየቀች። አንድ ብር የሚሸጠውን ሁለት ብር አሏት፤ አንዱን ቅርጫት ፓፓያ ጠየቀች። ሦስት ብር አሏት። «አምላኬ!» አለች የነገሯት ዋጋ ትክክለኛ ስለ መሆኑ ከሉን ጠይቃ ካረጋገጠች በኋላ።

በዓለም ላይ ተበልቶ ተጠጥቶ ከአንድ ዶላር በታች የሚጠየቅባት አገር እሷ እስከምታውቀው ድረስ ኢትዮጵያ ብቻ ናት። ከምር ሙዝና ፓፓያ ዋጋቸው አንድ ዶላር እንኳ አይሞላም። ኢትዮጵያ ውስጥ ተበልቶ፣ ተጠጥቶ የሚከፈለው አገሯ ለወንበር ተብሎ ከሚከፈለው ያነሰ ነው። አውሮፓ ውስጥ ትኩስ ፓፓያና ሙዝ ዋጋቸው የዋዛ ስላልሆነ፣ ለማግኘት ከባድ ነው። እንዲያውም አንድ ጃፓናዊ ጓደኛዋ ጃፓን አገር ትኩስ ፓፓያ መብላት የሚችሉት ሚሊየነሮች ናቸው ብሏታል። ይህን ስታስብ፤ «ኢትዮጵያ ውስጥ ፍራፍሬ ይሸጣል ከማለት ይልቅ፣ ይታደላል ቢባል እውነትነት ይኖረዋል» አለች።

ካርለትና ከሉ ወደ አርባ ምንጭ ጥቅጥቅ ባለው የግራር፣ የጥድ፣ የብርብራ ዛፍና ሌሎችም እፅዋትና በሰፊው የጥጥ እርሻ መካከል አልፈው ሲደርሱ አምስት መቶ ኪሎ ሜትር መጓዛቸውን የሚገልጽ በነጭ ላይ ጥቁር የተጻፈበት የቆመ ድንጋይ ተመለከቱ። የአርባ ምንጭ ከተማ የአባያንና ጫሞን ሐይቅ እግሩ ስር አድርጎ የተከተመ ከተማ ሲሆን መንገዶቹ አስፋልት ቢሆኑ ውበቱ ይጐላ ነበር።

ካርለትና ከሉ ከአዲስ አበባ አርባ ምንጭ አሥራ አንድ ሰዓት ተጉዘው ደረሱ። ከዚያም በከሉ መሪነት በቀለ ሞላ ሆቴል ሁለት



t.me/OLDBOOKSPDF

አልጋ ከያዙ በኋላ ካርለት ልብሷን ለማውለቅ እንኳ ሰንፋ ከነልብሷ ሻወር ቤት ገባች። ከሉ ሆራ ምናልባት መኪና ማሽከርከር ቢችል ኖሮ እሷ የደከመችበትን ጉዞ ሳያርፍ ሦስቴ ሊያመላልስ የሚችል ኃይል እንዳለው አምናለች።

ምሽት ላይ ካርለትና ከሉ ከሆቴሉ በስተጀርባ ካለው መዝናኛ ቦታ ቁጭ ብለው ከአርባ አራት ምንጭ በላይ አለው! የአንበሳ መኖሪያ ነው የሚባለው ጥቅጥቅ ያለ የአበሻ ጥድ፣ ግራር፣ ዋንዛ፣ ሾላ፣ አጋምና ሌሎችን እፅዋት ይዞ ከወዲህ ተራራውን ተለጥፎ፣ ከወዲያ የጫሞ ሐይቅን ከጎንና ጎን ተመርኩዞ፣ ከርቀት ሰንሰለ ታማውን የጉጂ ተራራ ዘብ አቁሞ ሲታይ የተፈጥሮ ውበት የሚደነቅ በት ሞዴል ሆኖ የጉብኚውን የተሰላቸ አእምሮ ያድሳል። ይህን የተፈጥሮ ውበት ሲያዩ እንኳን ካርለት ከሉም የእርካታ ስሜት አሳየ። የተፈጥሮ ውበት ሕሊናን አበረታችና ፈዋሽ ነዋ!

ካርለት ከሐይቆች ለሚነፍሰው ነፋስና ዓይኗ ለሚታኘው ውበት አእምሮዋን በርግዳ ከፍታ አካሏን ካዝናናች በኋላ ከሉን፣ «አንተ ቀዝቃዛ ቢራ እየተጎነጨህ ልትዝናና ትችላለህ። እኔ ግን ማረፍ እፈልጋለሁ» በማለት ቀያይ ብር አስቀምጣለት ሄደች። በእርግጥ ካርለት ከመኝታው ይልቅ መናፈሱንና ቀዝቃዛ ቢራውን መጎንጨት አሰኝቷት ነበር። ይሁን እንጂ ከሉ በእሷ ላይ ያለውን ስሜት በትክክል ማረጋገጥ አልቻለችም። ለነገሩ ጨዋታውን ለዓይነት ያህል ወስዳ ከሉን ማዝናናት ትችል ይሆናል! ፍርሃቷ ግን ለጥናቷ እንቅፋት መፍጠር ወይም እንዲፈጠር ማመቻቸት አትፈልግም። ከሉ ሆራም ለማያገኘው ነገር ጉሮሮውን በማጮህ የስሜት ችግር ውስጥ እንዲገባ ስላልፈለገች ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች።

ከሉም ያንን ስብቅብቅ ወገብና ዳንኪራ ረጋጭ ዳሌ የማግኘት ሕልሙ እንደማይሳካ በማሰብ፣ «ዳሚት» እያለ ሲቆዝም ቆየና ቢራውን ደጋግሞ ጨልጦ፣ ወደ መኝታ ክፍሉ ሄደ።

ማክሰኞ ዕለት በእንቅስቃሴ አልባው የጫሞ ሐይቅ ዳር ጥርሱን ያገጠጠ አዞ ሲንሳፈፍ፣ ከላይ ጥፍሩን ያሾለ አሞራ ዓሣ ለማጥመድ ሲያሽቆለቁል፣ በተራራው አናት የፈነጠቀው የፀሐይ ብርሃን ውጋገን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከውኃው ነጸብራቅ ጋር ተዋሕዶ የዓሣ ሽታ፣ የእፅዋት መዓዛ፣ ከአዕዋፍ ዝማሬ ጋር ቅንብሩ እንደተዋጣ ሙዚቃ መንፈስን በሚሰርቅበት ወቅት «ስቴሽን ዋገን» መኪና ጥግጥጉን የከብት ሽንት በመሰለው ጠመዝማዛ መንገድ እየተሹለከለከ ከነፈ።

ዘመን አመጣሹን የግብርና ዘዴ በተፈጥሯዊ ጥበብ ተጠቅሞ የአፈርን የእሸሻለሁ አትሸሽም የእርከን ሥራ ውጤት ካርለት ስታይ መሰጣት። ስለ ኮንሶ የእርከን ሥራ ባህልና የረጅም ዘመን የመጠቀም ችሎታቸው መጻሕፍት አንብባለች። ተራራማው አካባቢ ላይ የሚኖረው የኮንሶ ሕዝብ በእርከን ሥራ ዘዴ አፈርን በመንከባከብ የረጅም ጊዜ ተጠቃሚ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከዚህም በተጨማሪ ክልሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሸማ ሥራ ጥበብ የተጀመረበት መሆኑን ተረድታለች።

በቆሎ፣ ማሽላ፣ ለመድኃኒትና ለውኃ ማጣሪያ ለክልሉ ሕዝብ የሚያገለግለው የአለኮ ዛፍና ሌሎችም አዝርዕቶች፣ ችፍግ ብለው አዝመራውንና እፅዋቱን ሊያሳይ በሚችል መንገድ ቋጥኝ ጥግ የተሠራው መንደር እንግዶችን እይታቸውን ቶሎ መንቀል አያስችላቸውም።

አልፎ አልፎም ከመንገዱ ግራና ቀኝ ከእንጨት የተሠሩ የሰው ምስሎች ከመቃብር ላይ ተተክለው የሚታዩ ሲሆን ይህም ዘመን አመጣሹ የመቃብር ሐውልት ከመምጣቱ በፊት ኮንሶዎች የእንጨት ምስል ቀርፀው መትከላቸው ቀድመው የሠለጠኑ እንደነበሩ ዓይነተኛ ምስክር ሲሆን፥ ከዚህም በተጨማሪ ሥራ ወዳድነትና ጥረት ለኮንሶ ሕዝብ እንደ ቋንቋው ከልጅነቱ ጀምሮ የሚማረው ነው።

ካርለት ኮንሶንና አካባቢውን በቀስታና በአፅንኦት እየቃኘች ከተማው ደረሱ። ካርለትና ከሎ ከመንገዱ በስተቀኝና በስተግራ ፊት ለፊት ካሉት ብቸኛ ምግብ ቤቶች በግራ በኩል ወዳለው ለምሳ ገቡ። ካርለት አርባ ምንጭ ሆቴል በተለይ ሜካ ውስጥ ያሉት የመኝታ ክፍሎችና የጽዳት ሁኔታቸው አሳቋታል። የምግብ ዝርዝሩም አነስተኛና የለመደችው ባለመሆኑ ግራ ተጋብታ ነበር። የኮንሶው የምግብ ዝርዝር ግን ለእሷ እንግዳ ነው። አማራጭ ብሎ ነገር የለውም! ያለው አንድ ዓይነት ምግብ ሲሆን እሱም ሚስቶ ብቻ ነው — አበቃ!



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት፣ «አምላኬ!» ብላ ተደንቃ ለመብላት ተጣጣረች። ሆኖም ግን ከጉሮሮዋ አልወርድልሽ አላት። ስለዚህ ባልቀዘቀዘ ኮካ ወደ ውስጥ ለማስገባት ሞከረች። ከሎ ግን ደስ ብሎት ጥርግ አድርጎ በላ።

ከከተማው ወጥተው አቀበት፣ ቁልቁለቱን ወርደው ሲጓዙ አሁንም ካርለት በተፈጥሮ ውበት እየተደነቀች ከመኪና መሪ ጋር ስትታገል ቆየችና፣ «ከሎ ይህች ሀገር ልምላሜ፣ ውበትና ጥሬ ሀብቱ ሳያንሳት፣ ቀድማ ነቅታ ምነው ተመልሳ ተኛች። የእንቅልፍ ‹መድኃኒት› ማን አዋጣት? የውስጥ ይሆን የውጭ ሐኪም?» አለችው ምስጥ ብላ። ከሎ በሳንባው የታመቀውን አየር ወደ ውጭ እያንቦለቦለ፣ ፊቱን ቅጭም አድርጎ፣ «ሁለቱም-ሁለቱም ሐኪም ነው ካርለት» አላት። መኪናዋም አቀበቱን ለመውጣት ድምጽዋን ቀይራ ማቃሰት ጀመረች። በመሪው በኩል ያለው ጎማ ግን ፍትጊያውን መቋቋም ስላቃታው ተነፈሰ። ከዚያም «ስኮርት» ጎማ ቀይረው ጥቂት እንደሄዱ ደግሞ በጭቃ ተያዙ።

ሰማዩ ጎሽቶ፣ ብርቅርቅታው እንደ ርችት እየተንጣጣ፣ ዶፍ ዝናቡ መዝነብ በመጀመሩ እንኳን መኪናዋን ከተያዘችበት ጭቃ ለማውጣት መሞከር ቀርቶ በሩን ለመክፈት እንኳን ተሳናቸው።

ዝናቡ አካባቢውን ሲወቃው ቆይቶ ቁልቁል ወደ በረሃው በመውረዱ እየቆየ-እየቆየ አካባቢው ሲገልጥ ወርደው መኪናውን ሲመለከቱ የመኪናው ደረትና መሬቱ ተቃቅፈዋል። መኪናውን ለማንቀሳቀስ መሬቱ መቆፈር፣ ድንጋይ መጨመርና በሰው ኃይል ወደ ላይ ማንሣት ያስፈልግ ስለነበር ካርለትና ከሎ ለሁለት ሊወጡት የማይችሉት ችግር በመሆኑ አድረው የአካባቢውን ሰው ትብብር ለመጠየቅ ተስማምተው ድንኳኖቻቸውን መንገድ ዳር ተከሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 4

ከሎ ከተቀመጠበት ስፍራ ላይ ጉልበቱን ሰብሰብ አድርጎ በመታቀፍ ከንፈሩን እያኘከ የሚተነፍገውን የወይጦ በረሃ የእፅዋት ሽታ ይምጋል፤ ከየጉድባው ወጥተው ድብልቅልቅ በሚያደርግ ድምፅ የሚያገሱት አንበሶች፣ በቀጭንና ወፍራም ድምፅ ጨለማን ተገን አድርገው ድምፃቸውን በነፃነት የሚያስተጋቡትን የአራዊት ትርምስ እያዳመጡ ሁለቱም በሐሳብ ተውጠው ቆዩ።

ከዋክብት ሰማዩ ላይ ሆጨጭ ብለው ብርሃናቸውን ብልጭ ድርግም ሲያደርጉ፣ ገና የተወለደች ጨረቃ ካለአቅሟ ግዙፉን ጨለማ ከዝሆን ጋር እንደሚታገል ዝንብ በብርሃን ድል ለማድረግ ከተራራው አናት ወደ መሃል ሰማይ ስትገሰግስ፣ በበረት የታጎሩት ከብቶች እያመነዢኩ ሲያቃስቱ፣ ካርለትም ሆዷ እየተሸበረ፣ በምትፈጥረው ወኔ ግን እራሷን እየደለለች እንደ ከብቶች ላይ ላይ እየተነፈሰች ታቃስታለች።

የወይጦ በርሃ በተለይም በቀትር ላይ ሙቀቱ እንደ ደመራ እሳት ይጋረፋል። የአራዊቱና የእፅዋቱ አካል ሳይቀር በሙቀቱ ስለሚቀረና አካባቢው ለየት ባለ ሽታ ይታፈናል። በዚህ ወቅት እንግዳ ሰው እንደ ውሻ እያለከለከ የሚስበው አየር ፍለጋ አፍንጫውን እንደ አንቴና አቁሞ ያንጋጥጣል። ሆኖም ግን የፀማይ ማኅበረሰብ፣ ሰጎን፣ አንበሳ፣ የሜዳ ፍየል፣ ጉርኑክና የመሳሰሉት እንስሳት በደስታ ተዝናንተው ይኖሩበታል።

የወይጦ በረሃ ግለት እየቀነሰ ሲመጣ የፀማይ ማኅበረሰብ አባላት ከማሳ፣ ከወንዝ፣ ከከብት ጥበቃ፣ ከአደን፣ ከማር ቆረጣ፣ ከመንገድ...ወደየመንደሩ ሲከት፣ ከተለመደው ውጭ ነጭ መኪና፣ ጸጉሯ ረዘም ያለ ነጭ ሴት፣ ልብስ የለበሰ ጠይም ከተሜ መንደራቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ድንኳን ከትመው አገኛቸው። በዚያን ወቅት፣ ድፍን የፀማይ ኗሪ ስልክና ሌላ መገናኛ ባይኖርም የሰማው ላልሰማው መልእክቱን በቃል እያስተላለፈ፣ ቤት ለቤት የሚውሉ ሽማግሌና ባልቴቶች ሳይቀሩ «ነጭ በቆሎ» የመሰለችውንና ብልጭልጭ ቅራቅንበ የተቀረቀበባትን መኪና፣ ለማየት ጎረፉ።

በካርለት ጸጉርና እጅ ላይ ብዙ የፀማይ «ተመራማሪ» እጆች አረፉበት፤ እንደ አንበሳ ጐፈሬ የለሰለሰ ጸጉር፣ እንደ እብነ በረድ የነጣና የለሰለሰ ገላ፣ የትንባሆ አጢያሽ የመሰለ ጥርስ ሲመለከቱ፣ «ይህች ሰው ምንድ ናት?» ብለው ሲደነቁ ቆዩ። ከመካከል አንዱ፣ «ፈረንጅ ናት» አለ፣ ነቃ ያለው።

«ፈረንጅ...ኡ—» አሉ፣ በአድናቆት አፋቸውን እየያዙ።

«አሃ—ፈረንጅማ ከሆነች ያች በፍየልና ማር ከነጋዴ የምንለውጣት የሽጉጥ ጥይት የመሰለችው የፈረንጅ መድኃኒት ትኖራ ለች» ተባባሉ እርስ—በእርሳቸው። ከሉ ሆራ ፀማይኛ አይችልም! አንዳንድ ፀማዮች ግን ሐመርኛ ስለሚችሉ መድኃኒቷን እንድትሰጠን ጠይቅልን አሉት፥ ለምልክት አንድ የ«ቴትራሳይክሊን» እንክብል እያሳዩት። ፀማዮች ካርለትና ከሉ ቋንቋቸውን ባለመቻላቸው በተለይ ሴቶችና ጎረምሶች ግራ ገብቷቸዋል፣ «ሆሆይ—ለካ እናንተዬ ፀማይኛም የማይችል ሰው አለ!» ብለው ተሳልቀዋል።

በዚህ መልክ ራቁታቸውን የሆኑ ሕፃናት፣ ጎረምሳና አዋቂ ወንዶች፤ ግልድም ያገለደሙ፣ ከወገባቸው በታች የለበሱት ቆዳ መሬት ለመሬት የሚጎተት ትንሽ እንጨት ያለበት ሴቶች ካርለትን እንደ ጉድ ተመለከቷት። እሷም እነሱን በተመስጦ እየተመለከተች የሁለት ወገን ጉዶች ካለ ቋንቋ በጥቅሻ ሲነጋገሩ፣ አንዱ ሌላውን ለመግባባት ሲጣጣር ቆይተው የምሽቱ የአራዊት ትርምስና ጨለማ ሳያሸብራቸው በየአቅጣጫው በመሄድ ቀስ በቀስ ተበታተኑባት።

ካርለት፣ ከአዲስ አበባው ሒልተን ሆቴል ወደ አርባ ምንጩ በቀለ ሞላ ሆቴል፣ ከአርባ ምንጩ ሆቴል ወደ ድንኳን አዳር እየወረደች፤ የምትበላውም መጠኑና ዓይነቱ በጣም እየቀነሰ ቢመጣም፣ በጣም የተቸገረችበት ጉዳይ ሌላ ነበር። እስከ አሁን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳስተዋለችው ፀማይ መንደር ውስጥም ሆነ መንገድ ላይ ሽንት–ቤት አላየችም። ለመጸዳዳት ወደ ጫካ ሲገቡ ተመልክታለች። እሷ ደግሞ ጫካ ሄዳ መጸዳዳቱን ሕሊናዋ ሊቀበለው አልቻለም። በጉዞዋ ባሳለፈችው ቆይታ በሶፍት እየተጸዳዳች በማቃጠል፣ እየተጠቀመች ነው። ሐመር ስትሄድ ግን በዚሁ መልክ መቀጠል የሚቻላት አይሆንም። ሽንት ቤት አስቆፍራ እንዳትጠቀም ለአካባቢው እንግዳ ሁኔታ በመፍጠሯ መልካም ግንኙነት ላይኖራት ነው። ስለዚህ ሊታይ በማይችልና መጠነኛ ጥልቀት ባለው ጉድጓድ መጠቀሙን እያሰበችበት ነው።

በእርግጥ እንኳን ካደጉበት ባህል ውጭ ለተወሰነ ጊዜ ከተከተሉት ባህል ለየት ወዳለ ሲገባ የመጨነቅ ስሜት መፈጠሩ የነበረ ነውና ካርለትም የኢንግላንድ ዘመናዊነት፣ የለንደን ከተማ፣ ማንችስተር የሚገኙት እያቶቿ፣ የወንድና ሴት ጓደኞቿ፣ መዝናኛ ዎች፣ የጭፈራ ቦታዎች ቀርተው ራቁታቸውን ከሚሄዱ ጥቋቁር ሰዎች፣ ከከብቶች በረት፣ ከፍየልና በጎች ጋጥ አካባቢ መሆንዋ ሕልም እንጂ እውን ሊመስላት አልቻለም።

ካርለት ወደ ኢትዮጵያ ለጥናት ከመምጣቷ በፊት የአገር ቤቱን ሕይወት ለመለማመድ ወደ ስፓኝ በመሄድ «የስፓኝ በር» ተብላ በምትታወቀው የሁልቫ ከተማ የበጋ መዝናኛዋን በማድረግና ከወንድ ጓደኛዋ ጋር በብርቱካንና የሱፍ ማሳ አቅራቢያ ተቀምጣ ፀሐይ ላይ ብዙ መቆየት፣ ብርድና፣ ብቸኝነትን ለመለማመድ ሞክክራ ነበር። ያን ጊዜ የወደፊት የጥናት ቦታዋ በአሥር እጅ ከዚያ ሊለይ እንደሚችል ብትገምትም አሁን ግን ዘጠና ዘጠኝ እጅ ያላሰበችውና ያልገመተችው ዓይነት ሆነባት።

ካርለት እንዲህ በሐሳብ ጉና ስትንጨዋለል፣ እያንቋረረ የሚከፈተውን የከሎን ጉሮሮ ስትሰማ ከሰመመኗ ተመለሰች። ከዚያም ዓይኗንና ሕሊናዋን ወደ እሱ መለሰች።

እስከ አሁን ከከሎ ጋር ባደረገችው ቆይታ ካላናገሩት የማይ ናገረው ጥቁሩ ወጣት በራሱ ፍላጎትና አነሳሽነት፣ ሊያወጋት መዘጋጀቱ ሳያስደንቃት አልቀረም።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሚንጊ ነኝ» አለ ከሎ ድንገት።

«ምን?» አለች ካርለት፥ የጠቀሰው ቃል አልገባሽ ብሏት።

«ሚንጊ ማለት በሐመር ቋንቋ ገፊ ማለት ነው» አሁንም የባሰ ተደነጋገረች፤ ስለዚህ፣ እንዲግባቡ ለማድረግ ገለጻውን ሰፋ አድርጎ ጀመረ።

«ሕፃን ልጅ በሽማግሌዎች ፈቃድ ይወለዳል።»

«ካለ ሽማግሌ ፈቃድ መውለድ አይቻልም? ለመውለድ የሽማግሌዎች ፈቃድ እንዴት ይጠየቃል? ሽማግሌ የተባሉት ልዩ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ናቸው?» ካርለት ልጅ ለመውለድ ሲያስፈልግ የሐኪም፣ ካስፈለገም የሥነ–አእምሮ ጠቢብ ምክር ሊጠየቅ እንደሚችል ታውቃለች። ይህም ቢሆን ችግር ያለባቸውና በማኅበራዊ ጠንቅ ውስጥ እንዳይዘፈቁ የሰጉ ሰዎች የሚፈጽሙት እንጂ ለማንኛውም ዜጋ የተደነገገ ሕግ አይደለም። ሆኖም፣ ሽማግሌ የተባሉት ለየት ያለ ችሎታ ያላቸው ይሆናሉ ብላ ገመተች።

«አንችን ለማስረዳት ለኔ ከባድ ነው። በኋላ ቀስ በቀስ ልታውቂው ትችያለሽ። ሽማግሌ የተባሉት ግን በዕድሜና በልምድ ተደማጭነት ያላቸው ሲሆኑ ማንም የሐመር ማኅበረሰብ ሴት ባሏ ጥሎሽ ጥሎ እሱ ዘንድ ካመጣት በኋላ አንድ ቅል አሸዋና አንድ ቅል ወተት ይዛ ወደ ክልሉ ሽማግሎች ዘንድ ትሄድና ትመረቃለች። ከዚያም ወተቷን ትሰጥና አሸዋውን የያዘውን ቅል ቤቷ አምጥታ ግርግም ላይ ታንጠለጥለዋለች። ከዚያ፣ ከባሏ ጋር የግብረሥጋ ግንኙነት አድርጋ ፅንስ ከፀነሰች፣ ወደ ሽማግሎች ሄዳ መፀነሷን ታስታውቃለች። አንዴ መፀነሷን ሽማግሎች ከሰሙ፣ ባሏና እሷ ፅንሱ አድጎ ከተወለደ በኋላ ጥርስ ማብቀል እስኪጀምር ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አይፈጽሙም።»

«እ! እስከ መቼ?» ካርለት በጣም ገረማት፤ ለምሳሌ እሷ ከስቲቭ ከተለያየች ጥቂት ቀናት ሆኗታል። ግን ብዙ ጊዜ የቆየች ያህል የወሲብ ረሃብ እየሞረሞራት ነው፣ «እርግዝናስ እንዴት



t.me/OLDBOOKSPDF

ግንኙነትን ይከለክላል? ያውም ልጅ ተረግዞ፣ ተወልዶ፣ ጥርስ እስኪያበቅል እንዴት ይቻላል?» በማለት ተደነቀች።

«የሐመር ወንዶች ሚስት የሚያገቡት ሀብታም ለመሆን ነው። ማንም የሐመር ወንድ ሚስት ሲያገባ ለጥሎሽ ከብት፣ ፍየል፣ በግ፣ ማር ለሙሸኛው አባት ይከፍላል። ለጥሎች የሚከፈለውን የገንዘብ ጥሎሽ የሚያሟላ የሐመር ወንድ ከሁለት በላይ ሚስቶችን እንደ ሀብቱ መጠን ሊያገባ ይችላል። ብዙ ሚስት የማግባት ዕድል ያገኘ ደግሞ ቶሎ ሀብታም ለመሆን አጋጣሚው የሰፋ ነው። ምክንያቱም ሴት ከተወለደች አባቷ የከፈለውን ጥሎሽ ታስመልሳለች። ወንድ ልጅ ከተወለደም ልጁ የአባቱ መከታ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ሲጐረምስ ከአጎራባች ማኅበረሰቦች ከብት ዘርፎ ያመጣል፤ አድኖ ሥጋ ያበላል። በአጠቃላይ ብዙ ሚስት ያለው ብዙ ልጅ ሊኖረው ስለሚችል የሀብቱ መጠን የበዛ ይሆናል። ስለዚህ ማንኛውም የሐመር ወንድ ሀብታም ለመሆን ጥርሱን እየነከሰ ከሁለት በላይ ሚስት ያገባል።

«እ! ታዲያ በባልና ሚስቱ መካከል ፍቅር የለም ማለት ነው?» ካርለት በአስደናቂ ወሬው ተመስጣ መልሱን ለመከታተል አቆበቆበች።

«ፍቅር አለ፣ የለም ማለት ይከብዳል። በሐመር ባህልና ደንብ ባል ለሚስቱ የፍቅር ምልክት ማሳየት፣ ማውራት፣ ተቃቅፎ መተኛት አይፈቀድለትም። ወንድ አንበሳ ነው—ኩሩ። እንዲያውም በወጉ መሠረት በተገናኙ ቁጥር ፊቱን ማዞር፣ መቆጣት፣ መደብደብና ወንድነቱንና የበላይነቱን ማሳየት ይጠበቅበታል። ለምሳሌ ባል ጥሎሹን ከፍሎ ከጨረሰ ወይም ካገባደደ በኋላ ሚስቱን እናቱና የመንደሩ ሴቶች ሄደው ያመጧታል። ሙሽራዋ ጸጉሯን ትላጭና ቅቤና ከሰል ሰውነቷን ተቀብታ ቆጥ ወይም በሐመርኛ «ሻላ» ላይ ከባሏ ተደብቃ ለሦስት ወራት ትቀመጣለች። ሁሌም ባሏ ሲመጣ ቆጥ ላይ ወጥታ ካልተደበቀችና ፊት ለፊት ካገኛት ይደበድባታል። ተው ባይ የለውም፤ ባህል ነው።

«ቆጥ ላይ ለሦስት ወራት ስትቀመጥ የሥራ ድርሻዋ ሌሊት ሌሊት እየተነሣች የፍየልና በጎችን በጠጥ መጥረግና ሸፈሮ ቡና



t.me/OLDBOOKSPDF

አፍልታ፣ ከመንጋቱ በፊት ሌሎች ሴቶችን ቀስቅሳ መደበቅ ነው። ቅቤና ከሰል ሰውነቷን በየጊዜው የምትቀባውም ለባሏ ውብ ሆና እንድትቀርብ በማለት ነው።

«ሦስት ወር ከሞላት በኋላ ሙሽሪት ባሏ ከሚተኛበት ቁርበት ግርጌ በቆሎ በተን ታደርጋለች። የተበተነው በቆሎ ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝግጁ ነኝ ማለት ሲሆን ሁኔታውን የተረዱ ቤተሰቦቿም አካባቢውን ተወት አድርገው ይሄዳሉ። በዚህን ጊዜ ባል እየተጀነነ ሄዶ ይተኛል። ሙሽራይቱም ቀስ እያለች ሄዳ ከጀርባው ጋደም ትላለች። ከግንኙነት በኋላ ደግሞ ሚስት እንደ አስፈላጊነቱ ጥሬዋን ቀምሳ ትሄዳለች። ባል ከመኝታው ሲነሣም ሚስቱ ከፊት ለፊቱ ተንበርክካ አንገቷን በመቀልበስ እጇን ዘርግታ ትንባሆ ትሰጠዋለች። ባልም ፊቱን ዙሮ ተቀብሏት ይወጣል። ስለዚህ፣ በሐመር ባህል ወንድ ምን ቢወዳትም የፍቅር ምልክቱ ቁጣና ዱላ ነው።»

ካርለት በሕሊናዋ አንድ ነገር ለማመሳሰል ሞከረች፤ የከሎን ጅንንነት ምንጭ የተረዳች መሰላት። የጣማት ታሪክ እስኪያልቅ ግን ሌላ ነገር ማሰብ አልፈለገችም። ስለዚህ፣ «ከዚያስ?» አለችው፣ እሱም ጨዋታውን ቀጠለ።

«እናም መውለድ እንድትችል በሽማግሌዎች ከተመረቀች በኋላ ጨረቃንና ከዋክብትን በማየት አልፎ አልፎ ግንኙነት ያደርጉና ማርገዟን በሽማግሌዎች በኩል ባል ካረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ ልጅ ወልዳ፣ ልጁ ጥርስ እስከሚያበቅል ድረስ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አይፈጽሙም። ሽማግሌዎች ሳይመርቋት ብታረግዝ ግን «ውታ» (ያልተፈለገ) ተብሎ እንድታስወርድ ይደረጋል።

«ባሏ ስሜቷን አይጠብቅማ? ማለቴ ስሜቷ አያስቸግራትም? እንዴት ሁለቱም ለረጅም ወራት ስሜታቸውን ሊቆጣጠሩ ይችላሉ? አ! ልጅ ተወልዶ ጥርስ እስከሚያበቅል? ለምንስ ደግሞ...» ካርለት ለምትሰማው ነገር ምክንያት ፈጥራ ራሷን ለማሳመን ቸገራት። ወሲብ ለእሷ የትክክለኛ ሕይወት ትርጓሜ ነው። ሕይወት ያለ ፍቅር፣ ፍቅር ደግሞ ያለ ወሲብ ከሁሉም የከፋ መራራ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

«የሐመር ወንዶች ‹ኢቫንጋዲ› በተባለው የምሽት ጭፈራ ባል ካላገቡ ልጃገረዶች ጋር ስለሚጫወቱ ስሜታቸውን የማርካቱ ዕድል አላቸው። ማንኛውም ለጭፈራ የደረሰች ልጃገረድ ካለገደብ በኢቫንጋዲ መካፈልና የግብረሥጋ ግንኙነት መፈጸም መብቷ ነው። ያውም በግዴታ ሳይሆን በራሷ ፈቃድ። ክብረ ንጽሕናሽን አስወሰድሽ፣ ባለግሽ ብሎ አተካራ የሚገጥማት ሰው በወደፊቱ ሕይወቷና ሕልውናዋ አያጋጥማትም። ብታረግዝም ልምድ ባላቸው ሰዎች ፅንሱን በማስወረድ፣ እጮኛ እያላት ቢሆንም እንኳ መዝናናቷን ትቀጥላለች። አንድ ወንድ ሚስት ለማግባት የሚጠየቀው ጥሎሽ የዋዛ ስላልሆነና በሁለትና ሦስት ዓመት ለመክፈል ስለሚከብድ ከምላ ጎደል የወጣትነት ጊዜዋን ባል አልባ ሆና ስለምታሳልፍ፣ ልቧ ካማረው ኮረምሳ ጋር ስታዜም፣ ስትጨፍር፣ ስትዳራ ትታያለች።

«ባሏ ጥሎሹን ከፍሎ ከጨረሰና ሚስት ወደ ባሏ ከሄደች በኋላ ግን የባሏ የግል ንብረት በመሆኗ በራሷ ፍላጎት ሳይሆን በባሏ ትእዛዝ መኖር ትጀምራለች። በምሽት ጭፈራ አትካፈልም፤ በጨሌና አንባር እንደ ልጃገረድነቷ ወቅት አታጌጥም፤ የምትለብሰው የፍየል ቆዳ ጭኖቿን እንዲያሳይ ሆኖ መሰፋቱ ይቀራል፤ ጸጉሯን በ‹አሰሌ› አፈር ከቅቤ ጋር ቀላቅላ እየተቀባች መኖር ትጀምራለች። ሚስት ለባሏ የምታደርገው ቢኖር ከባድ ሥራ መሥራትና ልጅ መውለድ ብቻ ይሆናል።

«ወንዱ ግን አገባም አላገባም በጭፈራ መካፈልና ልጃገረድ ማሽኮርመም ይችላል። ጥሩ የወላድ ቤተሰብ ካገኘም ለሚስትነት ጥሎሽ በመክፈል የራሱ ያደርጋታል። ጥሎሽ መክፈሉን ከቻለ፣ ሁለትና ከዚያም በላይ የማግባት ዕድሉ የሰፋ ይሆናል። እንዲያውም የመጀመሪያ ሚስቱ ብቻዋን ሥራውን ሁሉ ለመሥራት ስለሚከብዳት ረዳት ለማግኘት እንዲያገባ ታደፋፍረዋለች። ስለዚህ ሚስት ወደ ባሏ ከሄደች በኋላ ብታረግዝ ከወንድ (ከባሏ) ጋር ግንኙነት የምታቋርጠው ሴቷ እንጂ ባል ካለገደብ መዝናናት ይቻለዋል። ካለ ሽማግሌ ፈቃድ የተወለደ ግን እንደ እርኩስ ስለሚቈጠር የማደግ ዕድል አያገኝም። የማስወረድ ዘዴውም ልምድ ያላቸው ሰዎች በማኅፀን ውስጥ ያለውን ፅንስ – ጭንቅላት ከውጭ



t.me/OLDBOOKSPDF

በኩል በመዳሰስ ሲያገኙ ጭንቅላቱን በሁለት አውራጣታቸው ወ[...]
ውስጥ ደጋግመው በመጭመቅ...» ሲል ካርለት ፊቷ በስሎ የተበላ[...]
ቲማቲም መሰለ፣ ከንፈሮቿ ተንገረበቡ፣ መላ አካሏ ራደ።

ከሎ ግን ንግግሩን ቀጠለ፣ «...እንድታስወርድ ይደረጋል! ከተ[...]
ወለደም ሕፃኑ ጫካ ይጣላል። ስለዚህ አንድ የሐመር ሴት በሽ[...]
ግሎች ፈቃድ ማርገዟ ከታወቀ በኋላ ከባሏ ጋር ግንኙነት ሳታደር[...]
ፅንሱ አድጎ መውለጃዋ ሲደርስና ምጥ ቢይዛት በአካባቢዋ የሚኖሩ[...]
ሴቶች ይሰበሰቡና እጅና እግሯን ጥፍር አድርገው ይዘው፣ አፍ[...]
ጫዋን ያፍኗታል። ይህም ልጁ የእናቱን ማኅፀን ለቆ ተፈትል[...]
እንዲወጣ ይረዳል» ሲል ካርለት ፍርሃት መላ አካሏን አንገጫ[...]
ገጨው። እሷም እንደታፈነች ሁሉ ልቧ ዘለለባት።

«ውልጃ ባፈና? በምጥ ላይ ሌላ ምጥ?» ከሎ ግን ጨዋታውን ቀጠለ።

«እንግዲህ እንደ ነገሩ ታርሳ ራቁቱን ለተወለደው ሕፃን መታ[...]
ፊያ፣ ፎጣ፣ ሙቀት፣ ጂኒ ጃንካ ሳያስፈልገው የቡና ውኃ በማጠጣት
አቀባበል ይደረግለታል። ልጁ ቁሩንና ሙቀቱን ተቋቁሞ አደግ እያለ
ሲመጣ ግን እናቱ ከማማጡ በላይ ትጨነቃለች። አባትም ውስጥ
ለውስጥ ይሳቀቃል።

የሚጮኸው ጅብ ሆድ ዕቃዋን፣ የከሎ ወሬ ደግሞ ሕሊናዋን
አተረማመሰባት። ትሰማዋለች! የምትሰማው ግን ለማወቅ ሳይሆን
በቃ ከአቅሟ በላይ የሆነ ‹አስፈሪ ነው› ብላ መናገር ተስኗት ነው።
ደንታ ቢሱ ከሎ ግን ጨዋታውን ቀጠለ።

«በሐመር ማኅበረሰብ ላም፣ በሬ፣ በግ...ጥርስ የሚያበቅሉት
በታችኛው ድዳቸው ስለሆነ ‹ቅዱስ› ሲባሉ አህያ፣ ፈረስ፣ ጅብ...
ጥርስ የሚያበቅሉት በላይኛው ድዳቸው በመሆኑ ‹እርኩስ› ይባላሉ።
የሰው ልጅም የመጀመሪያውን ‹የወተት ጥርስ› ማብቀል የሚገባው
እንደ ቅዱሳን እንስሳት በታችኛው ድዱ መሆን ሲኖርበት፣ እንደ
እርኩሳን እንስሳት በላይኛው ድዱ ካበቀለ ከእርኩሳን እንስሳት እንደ
አንዱ ስለሚቆጠር ለማኅበረሰቡ አይበጅም! ቢያድግም አባቱን
የሚጋፋ፣ የሚገድል፣ የሚበጠብጥ ስለሚሆን ገሬ ወይንም በአካባ
ቢው አጠራር «ሚንጊ» ተብሎ ይጣላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጥርስ እንደማብቀሉ ሁሉ መውለቁ ላይም በቅድሚያ መውለቅ የሚገባው በታችኛው ድድ የበቀለው ጥርስ መሆን ሲገባው፣ በላይኛው ድዱ የበቀለው ጥርስ ቀድሞ ከወለቀ ሚንጊ ነው ተብሎ አሁንም ይጣላል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ሕፃኑ የታችኛው ጥርሱ ከመውለቁ በፊት በአጋጣሚ እንኳ ወድቆ ወይንም በሌላ መንገድ የላይኛው ጥርሱ ቢወልቅ ሚንጊ ተብሎ ከማኅበረሰቡ እንዲወገድ ይደረጋል።» ከሎ ሆራ «ኢ—ህ» አለና፣

«እና እኔም እንደነገርኩሽ ሚንጊ ነኝ» አላት።

«ታዲያ አንተ ‹ሚንጊ ነህ› ተብለህ ተጥለህ ነበር?» ካርለት፣ ካለማብራሪያ መልሱን በአሉታ ወይንም በአወንታ እንዲመልስላት በሕሊናዋ እየተማጸነች ጠየቀችው።

«አዎ!» ብሎ፣ ጭንቅላቱንና ትከሻው ላይ በጦር የተወጋውንና በድንጋይ የተፈነከተውን አሳያት። ከዚያ ቀና ብሎ ጨለማውንና ከዋክብቱን ተመለከተና እንዴት አድርገው እንደ ጣሉት ጨዋታውን ሲቀጥል ካርለት በሕሊናዋ «ከሎ ለእኔም የሚያዝን አንጀት ይኑርህ እንጂ» በማለት፣ እየተብሰከሰከች የማይቀርላትን ጨዋታ ለመስማት ጉንጯን በጣቶቿ ደግፋ፣ ዓይኖቿን በማፍጠጥ ዓይን ዓይኑን ተመለከተችው።

«እኔ የተወለድኩት ሐመሮች ተሰባሰቡበት ከሚባለው የቡስካ ተራራ ስር ላላ ከተባለው መንደር ነው። እናቴ በንቲ ኃይሎ ትባላ ለች። አባቴ ደግሞ ሆራ ሸላ ይባላል። እናቴ ለአባቴ አምስተኛ ሚስት ስትሆን፣ አምስት ልጆችም ወልዳለታለች። እናቴ፣ በልጅነቴ ሁል ጊዜ በምትለብሰው ቆዳ ሸፈን አድርጋ ከሰውነቷ ጋር ትለጥፈኝና ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ቆይታ፣ «ጨዋንዛ» በሚባል ሸካራ ቅጠል ጥርሴን ትሞርድልኝ ነበር። በወቅቱ ባይገባኝም ኋላ ኋላ ግን የተጣልሁበትን ምክንያት ስሰማ የጥርስ አበቃቀሌ ሁኔታ በትክክለኛው መንገድ ማለትም መጀመሪያ በታችኛው ድዴ፣ ቀጥሎ በላይኛው ድዴ ነበር አሉ የበቀለው። ይሁን እንጂ፣ አንድ ጊዜ ጥጃ ለመመለስ ስሮጥ ወድቄ የላይኛው ጥርሴ አንዱ ወለቀ፣ አንደኛው ተሸረፈ። እንዳበቃቀሉ ሁሉ፣ በቅድሚያ የታችኛው ድዴ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

የበቀለው ጥርስ መውለቅ ሲገባው፣ የላይኛው ጥርሴ ቀድሞ በመውለቁ፣ ለአደጋ ተጋለጥሁ። እናቴ፣ በሸካራው የጨዋንዛ ቅጠል ጥርሴን ስትሞርድልኝ የነበረው ለካ የታችኛው ድዴ ጥርስ ቀድሞ የወለቀ ለማስመሰል ኖሯል።

«ይሁን እንጂ፣ ጥረቷ ከንቱ ነበር። ወድቄ ሳለቅስና ጥርሴ ወልቆ ያዩኝ ሰዎች ለሽማግሎች መንገራቸው አይቀሬ ነበር። እናም አንድ ቀን አባቴ ባልነበረበት ወቅት፣ ሚንጊ የተባሉ ልጆችን የሚጥሉ ሽማግሎች ወደ እኛ ጎጆ መጡ። እናቴ፣ ከርቀት እንዳየቻቸው ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ ሰውነቴን እንቦሳዋን እንደምትልስ ላም እየሳመችና እየላሰች አለቀሰች።

«ከእናቴ ጋር በተለያየ አጋጣሚ እንለያይ ነበር። ከብቶች በድርቅ ጊዜ እርቀው ሲሄዱ፣ ወደ ማሳ፣ ለገበያ ወዘተ...ስትሄድ ሁለትና ሦስት ቀናት፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ከዚያም በላይ እንለያያለን። ታዲያ ስንለያይ እናቴ ታለቅሳለች፤ እኔ ግን የእሷ ሁኔታ ቢረብሸኝም ቶሎ ወደ ጨዋታዬ እመለስ ነበር። የዛን ቀን ሽማግሎች፣ «ጥርሱን አስወልቀን እናምጣው» ብለው፣ በጠንካራው እጃቸው ትንሿን እጄን በጨመቁ ቁጥር ግን እንባዬ ሳያቋርጥ ይንገፈገፍ ነበር።

«እናቴ ሽማግሎች ጥርሱን አስወልቀን እናምጣው ብለው ሲጠይቋት ካለምንም ተቃውሞ ገፋ አድርጋ አሳልፋ ብትሰጠኝም፣ ትከሻዋን በሁለት እጆቿ አቅፋ፣ ድምፅዋን አጥፍታ፣ አምርራ ስታለቅስ ለአደገኛ ሁኔታ እንደተጋለጥኩ ገመትሁ። ሆኖም ግን፣ ምን እንደሚደርስብኝና ለምንስ እንደምቀጣ አላወቅሁም ነበር።

«ሁለቱ ሰዎች ከመንደራችን እያራቁ ሲወስዱኝ እናቴ እጇን እያርገበገበች ስታለቅስ ትታየኝ ነበር። እንዲያውም እስከ አሁን ድረስ እንኳ ሰው እንደ እሷ ስፍስፍ ብሎ ሲያለቅስ አይቼም አላውቅም።

«ከመንደራችን ብዙ ርቀን ወደ ጫካው ውስጥ እስከንገባ ሽማግሎች ምንም ሳያወሩኝ ሄድንና የሆነ ገደል አጠገብ ስንደርስ ከፊት ለፊታቸው ወደነሱ ሳልዞር እንድቆም ነገሩኝ። እኔ ግን፣ ያሉኝን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመፈጸም ስላልተቻለኝ ዘወር ስል፣ አንደኛው ሽማግሌ ጦሩን ወደ ትከሻዬ ሲሰድ ተመለከትኩኝ። ከዚያ በኋላ ሰውነቴን ሲወጋኝና ለመጮህ ስሞክር፣ ገፍትረው ወደ ገደሉ ከተቱኝ። ገደሉ ውስጥ የነበረው ድንጋይ ደግሞ እራሴን ተረተረኝ፤ ደም ፊቴን አለበሰው፤ የሞት ሞቴን ግን የእናቴን፣ የወንድሜን፣ የአባቴን...ስም እየጠራሁ ጮሁ። የደረሰልኝ ግን አልነበረም።

«ስለዚህ፣ ጉድጓድ ውስጥ እንደሆንኩ ስንጉር ውዬ አድሬ፣ ጠዋት ላይ ድምፄ ተዘጋ። ረፈድፈድ ሲል የሰው ድምፅ ሰማሁ። የሰማሁት ድምፅ ግን የሰው ቢሆንም ቋንቋው የማውቀው ሐመርኛ አልነበረም። ለመጣራት ብሞክርም ድምፄ እምቢ አለኝ።

«የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ፣ አንዷ በልቅሶ የተዘጋውን ድምፄን ሰምታ ኖሮ፣ አብረዋት ከሐመር ቆቁ ከተማ የመጡትን ሴቶች ጠርታ በድንጋጤ ተያይዘው ሄዱ መሰለኝ ድምፃቸው ጠፋብኝ። ብዙ ቆይቼ ግን፣ እንደገና የወንዶችና ሴቶች ድምፅ ተሰማኝ። ከወላጆቼ ጋር ሳለሁ፣ እነዚያን መሳይ ሰዎች ወደ መንደራችን ሲመጡ፣ በፍርሃት ፈርጥጬ እሮጥ ነበር። ሆኖም ግን፣ የማልፈራቸው የኔ ወገኖች ስለጨከኑብኝ መሰለኝ፣ አለባበሳቸውንና ቋንቋቸውን የማላውቃቸው ሰዎች ከጉድጓድ ውስጥ አውጥተው የሚበላ ሲሰጡኝና ሲያሳክሙኝ፣ አንድም ተቃውሞ አላሰማሁም።

«ይኸውልሽ፣ ከወላጆቼ ጋር ዳግመኛ ሳንገናኝ፣ ከነዚያ ካስጠጉኝ ሰዎች ጋር በመሆን ለትንሽ ጊዜ እንደቆየሁ፣ የመንግሥት ሠራተኛ የነበሩት እረዳቶቼ ወደ ጂንካ ሲቀየሩ፣ እኔም አብሬ ጂንካ ከተማ ሄድኩ። እዚያም ትምህርት ቤት አስገቡኝና ትምህርቴን በመከታተል ከሞት ተርፌ ለዚህ በቃሁ።

«ከወላጆቼና ከአካባቢዬ ከተለየሁ በአሥራ ሦስት አመቴ፣ የመሰረተ ትምህርት የተማሪ አስተማሪ ሆኜ የዘመትኩት ትውልድ ቦታዬ ሲሆን፣ ወደዚያው የትውልድ አካባቢዬ ስሄድ በመልኬ ሁሉም አወቁኝ። አባቴ ቢሞትም እናቴንና ወንድም እኅቶቼን ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

አገኘኋቸው። መጀመሪያ ፍጹም ልቀርባቸው አልፈለግሁም ነበር በኋላ ግን እናቴ፣ «የልጄን ዓይን ምነው ባየሁት» እያለች፣ መኖሯ ከሰማችበት ጊዜ ጀምሮ ታለቅስ እንደነበረና ወንድሞቼም ፍየል ቅቤና ማር እየሰጡ ሲቀርቡኝ፣ የእናቴም በሕሊናዬ የተዳፈነ የእናትነት ፍቅሯና ወደ ሞት አፋፍ እንደ በሬ ስነዳ አቅም አጣ የተንሰፈሰፈችውን በማስታወስ ባህሉ እንጂ እነሱ ተፈጥሮአዊ ጥላ የሌላቸው መሆኑን በማሰላሰል፣ ይቅር ለማለት ሞከርኩ።

«በመካከሉ ግን፥ ባይገርምሽ፥ በጦርና በድንጋይ ወግረው ገፍትረው ገደል የከተቱኝን ሽማግሌች ገና ሳያቸው፣ በቆምኩበት በፍርሃት ራድሁ፤ እጄን ይዘው እንደገና ወደ ሞት ሊወስዱኝ ‹ጥርሱን አስወልቀን እናምጣው› ያሉ መሰለኝና ሸሸሁ። ስለዚህ ከትውልድ ቦታዬ በመሸሽ ቱርሚ ከሚገኙት ጓደኞቼ ጋር በመቆየት ግዳጄን ፈጽሜ ተመለስኩ። የረሳሁትን ቋንቋ ግን በአራት ወራት አቀለጣጥፌ መናገር ቻልኩ።

«አሁንም ቂም ያረገዘው አእምሮዬ ገና ያልሻረና ፍርሃቴም ከሕሊናዬ ያልተወገደ ቢሆንም፣ አንቺ ግን እንሂድ ስትይኝ እሺ አልኩሽ» ብሎ ንግግሩን አቆመ።

ካርለት፣ በተለይ በመጨረሻ ላይ የተናገረው ነገር ቢያስደነ ቃትም፣ ምስጋናም ማቅረብ እንደሚኖርባት ብታምንም፣ ሰውነቷ በሞላ ይንቀጠቀጥ ስለነበር ስሜቷን ለመቆጣጠር አቅም እንደ ተሳናት ስለ ተረዳች ጸጥ ብላ ወደ ድንኳኗ ገባች። ከዚያም፣ ዓይኖቿን ጨፍና ከሉ ያወራትንና የአውሬዎችን ጩኸትና ግሳት ላለማሰብና ላለመስማት ትጣር እንጂ፣ በሐሳቧ እንደገና ወደዚያው እየተመለሰች ተዘፈቀች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 5

ዲመካና ቁርሚ ሁለቱም የሐመር አውራጃ የገጠር ከተሞች ናቸው። ለቆላማው የሐመር ክፍል ቁርሚ፣ ለደጋማው ደግሞ ዲመካ አማካዮች ሲሆኑ፣ ሁለቱም ደረቅና ቁጥቋጦ የበዛበት መሬት ያላቸው ናቸው። ቁርሚ መንገድ ዳር ያለ ከተማ ሲሆን፣ ከዲመካ ይልቅ ሁለት ትናንሽ ምግብ ቤቶች፣ ወደ አምስት የሚደርሱ ሻይና ቂጣ መሸጫ ቤቶች፣ ሁለት በመጠን ከፍ ያሉና ትናንሽ ሳሙና፣ ባትሪ–ድንጋይ፣ ክብሪት...የሚሸጥባቸው መንገድ ላይ የሚዘረጉ ሱቆች አሉ። በተለይም በገበያ ቀን ከተማዋ ደመቅ–መቅ ብላ ትታያለች። ገበያ ውስጥ ለመጠጥ ቦርዴና የአበሻ አረቄ፣ ግልድም የሚሆን ከጥጥ ተሠርቶ ከኮንሶ በነጋዴዎች የሚመጣ ሳዳጎራ፣ ጨሌና አንባር፣ በቆሎና ማሽላ ዓይነተኛ ሸቀጦች ናቸው። ቁርሚ፣ በከብት እርባታና በቁፋሮ ምርት ለሚተዳደረው የሐመር ሕዝብ ድል ያለች ከተማ፣ ታምሮና ተውቦ የሚታዩባት፣ ጐረምሳና ሴቱ አብሮ መሸታ ገብቶ የሚደባበስባት፣ የተጣላ የሚታረቅባት፣ ሽማግሎች ተሰባስበው የሚመከሩባት፣ ብርቅዬ ከተማ ናት–ለሐመሮች።

ዲመካ ግን፣ ከዋናው መንገድ ወጣ ብላ፣ ሰቀላ ቤቶች በአራት ማዕዘን ተሰትረው የሚታዩባት ከተማ ናት። በየሰቀላ ቤቶች ፊት–ለፊትና በስተኋላ የግራር፣ የብርብራ...ዛፍ ያለ ሲሆን ከከተማው ግርጌ፣ ከወንዙ ጥግ በሚሰዮናውያኑ የተተከለ በፀሐይ ብርሃን በሚንቀሳቀስ መስኖ የለማ የፍራፍሬ፣ የበቆሎና ሌሎችም ወቅታዊ አዝርእቶች የሚታይ ሲሆን፣ ከጎን በኩልም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ሕንፃና ጋራዥ፣ ዲመካን አንድ ዓይና ከመሆን አድኗታል። የገበያ ቀን፣ በየሰቀላ ቤቱ ጠጅ የሚሸጥ ሲሆን፣ ምግብ ቤት ግን ከናካቴው የለም። ደግነቱ፣ እንግዳ ብርቅ በመሆኑ ጋባዥ ብዙ ስለሆነ እግር የጣለው ሰው ሕቅ ብሎ ሲያዝን አይሰማም። በተረፈ ገበያ ውስጥ ያለው ሸቀጥ ከቁርሚ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱንም ከተሞች



t.me/OLDBOOKSPDF

ቡስካ ስር ካሉት ላላና ሻንቆ እስከ ሚኖ፣ ሚርሻ፣ ሚጎ፣ አንኳ
መንደር ድረስ የሚያገናኛቸው የማኅበረሰብ ሕይወት የሆነው የከስ
ወንዝ ነው። ከብቱ፣ ፍየሉ፣ በጉ፣ ሰው፣ አዕዋፍ...ሁሉም ፕመ
ይቈርጥበታል።

ካርለትና ከሎ ሆራ ከዲመካ ወጣ ብላ ከምትገኘው የሻን
መንደር መኖር ከጀመሩ ሁለት ወራት አለፋቸው። የከልሉ ኗሪዎ
ከሎ ሆራን እንዳዩ፣ «የሆራ ሻላ ልጅ» እያሉ፣ ሰላምታና ስጦ
አጕረፉለት፤ ቆዳ ለባሽ እናቱና እኅቶቹም ደረታቸውን በመድቃ
የደስታ እንባ እያነቡ አስተናገዱት።

ካርለት፣ በቆይታዋ የተለያዩ ልምዶችን አገኘች። ከዘመናዊው
ሕይወቷ እንደ ባንዲራ ወርዳለች፤ ይህን አጋጣሚዋን ግን በግላ
ትርጕሟ እንደ መጥፎ ከመውሰድ ይልቅ እንደ ጥሩ አጋጣ
በመውሰዷ የሚሰማት ስሜት የደስታ ስሜት ነው። ይህ ደግሞ
ማኅበረሰቡን ለመቅረብና ለመርዳት እንድትጣጣር አድርጓታል።

ስለዚህ፣ ካርለት የከሎ ሆራን እናትና እኅቶች፣ የአካባቢውን
ሴቶችና ወንዶች ለመቅረብ የቋንቋ ትምህርቷን በማጠናከር ልትግባ
ሞክራለች። ቢሆንም ግን፣ በወደፊቱ ጥናቷ ላይ ከፍተኛ እንቅፋት
እየሆንባት የመጣው በሴቶች ላይ ያለው ባህላዊ ተፅዕኖ እንደ ጋለ
ብረት ምጣድ አላስጠጋሽ አላት።

በማኅበረሰቡ፣ ሴት ሣቂታ ወንድ ኵስታራ ነው። ሴት በልጃ
ረድነቷ የአባቷ፣ ባል ከአገባች ደግሞ የባሏ ጥገኛ ናት። ስለዚህ
በልባዊ ሡራት የተሞሉት የሐመር ወንዶች ካርለት ሴት ሆና እንዴት
ባሏን ወይንም አባቷን ጥላ ወደ እነሱ እንደ መጣች በጣም
አስገርሟቸዋል። ሽማግሎች እንዲያውም፣ «ይእ! እሷ ምን
ታድርግ? አባቷ ወይም ባሏ፣ ብቻዋን መልቀቃቸው ከቶ ምን ያሉ
ነፈዞች ቢሆኑ ነው» ብለው አውግዘዋል።

ስለሆነም፣ ካርለት የጥናት ኮተቷን ይዛ ለጥያቄ ቀረብ ባለቻቸው
ቍጥር የደስታ ገጽ ስለማታይባቸው ለተወሰነ ቀን ግራ ተጋብታ
ነበር። አንድ ቀን ግን ወንዶች ሊያደርጉት ባሰቡት ስብሰባ ለመካፈል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሄደች። ገላጣ ስፍራ ላይ ካለ ትልቅ ግራር ጥላ ሥር፤ የሸንቆ መንደር ሽማግሌ፤ አባወራ፤ ጐረምሶች ተሰብስበዋል። ከወገብ በላይ ራቁት ሆነው፤ ቆዳቸው የተሸበሸበ፤ ጸጉራቸው ገለል ብሎ ሽበት ጣል—ጣል ያደረገበት አዛውንት በሁለት ወገን ጦር የተሰካበት ብትር ይዘው፤ መሬቱን ወጋ ነቀል እያደረጉ ወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀሱ ንግግር ሲያደርጉ ሁሉም ጸጥ ብሎ በተመስጦ ሲያዳምጥ፤ ካርለት ስብሰባውን ለመካፈል ጓጉታ ቀስ እያለች ተጠግታ ልትቀመጥ ስትል ሁሉም ዘወር ብለው አይዋትና በስብሰባው መካፈል እንደማትችል ነገሯት።

ካርለት፣ ወንዶችን ለመቅረብ አለመቻሏ ብቻ ሳይሆን፣ ሴቶችም ምሥጢራቸውን ሊገልጹላት ባለመቻላቸው ግራ ተጋብታ ቅር ተሰኘች። በተለይ ደግሞ፤ ለመሳተፍ ጓጉታለት በነበረው የወንዶች ስብሰባ ልትካፈል ባለመቻሏ ጥልቅ ኀዘን ከመስማት አልፎ ለወደፊቱ አደርገዋለሁ ብላ የደከመችለት ጥናት ሊሳካ አይችልም ብላ ሠጋች።

ስለዚህ፤ ዓይኗ ቁንዶ በርበሬ መስሎ እስኪቀላ ድረስ እያለቀሰች፤ «ክሎ! ለምን ወንዶች ጥያቄዎቼን ለመመለስ ፈቃደኛ አይሆኑም? ለምንስ በስብሰባቸው እንዳልካፈል ይከለክሉኛል? በዚህ ዓይነት ጥናቴንስ እንዴት ማድረግ እችላለሁ?» ብላ ጠየቀችው።

«በሐመር ማኅበረሰብ ሴት ወንድን ለመርዳትና ለማገልገል የተፈጠረች ጸጋ ናት። ለወንዶች ትንባሆ ታዘጋጃለች፤ ልጃገረድ ከሆነችም ታርሳለች፤ የከብቶችን በረት ታጸዳለች፤ ሕፃናትን ትንከባከባለች፤ ምግብ ታበስላለች...እንጂ ከወንድ ጎን ተቀምጣ ስለ ማኅበረሰቡ ችግር በመነጋገርና በመምከር መፍትሔ መፈለግና ጦርነት መግጠም አትችልም።

«ካርለት፣ አንቺ ወንድ ብትሆኚ ኖሮ ምንም ችግር ላያጋጥምሽ ይችል ነበር። ሆኖም ግን አንቺ ሴት ነሽ። ለሐመር ሴቶች የወጣው ደንብ ማንኛዋንም ሴት ያጠቃልላል፣ ብለው ስለሚያምኑ በስብሰባቸው እንድትካፈይ አለመፍቀድ ብቻ ሳይሆን፣ የምትጠይቂያቸውንም ሙሉ በሙሉ ለመመለስ ፈቃደኛ አይሆኑም። እኔም ይህ ችግርሽ እጅ ሰባራ ሊያደርግሽ እንደሚችል እየተሰማኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

መጥቷል። ምናልባትም ችግሩ ግልጽ ከሆነልሽ የግልሽን መፍትሔ ውሰጂ» አላት።

ካርለት ፈጽሞ ያልጠበቀችውን መልስ በማግኘቷ በባህላዊ ልዩነቱ በጣም ተሸማቀቀች። በአሁኑ የጥናት አያያዟ በእርግጥም ለመቀጠል አለመቻሏ ቁልጭ ብሎ ታያት። በአእምሮዋ አውጥታ አውርዳ የወሰነችው ውሳኔ፣ እስከ አሁን ያደረገችው ጥረትና ጉዞ፣ ጥሩ የድንጋይ ምት እንዳረፈበት መስተዋት ከሽ ብሎ ሊሰበር የተቃረበ መስሎ ታያት። ያ ችሎታዋንና ጥንካሬዋን የሚያስመሰክረው፣ ማንነቷን የሚያረጋግጠው፣ ብቃቷን ማያዋ መስተዋት እንዲሰበር ግን ጭራሽ አትፈቅድም። በዚህም ተባለ በዚያ፣ የጀመረችውን ከግቡ ለማድረስ ሕሊናዋ እሷን ወደፊት መግፋት አለበት። ሰዎች ከጎሪላና ከእፉኝት፣ ከአንበሳና ከተኩላ ጋር በሐሩርና በረዶ መኖር መቻላቸውን አስመስክረዋል። እሷም ዓላማዋን ከግቡ ለማድረስ ተጣጣሬና ጠንካራ ለመሆን ከራሷ ጋር ተማማለች። ግን ምን መላ ትምታ? ለተወሰነ ቀን ካለ ዕረፍት በዚህ ጉዳይ ላይ ስታስብ ከቆየች በኋላ ምንም እንኳ የችግር ኮተቱን ዓይኗን ጨፍና አላይም ብትልም፣ የሚያጋጥማት ሥቃይ ከባድ መሆኑን አውቃ ቀበቶዋን አጠበቀች።

ከዚያም፣ ያሰበችውን መላ ለመጀመር ያስችላት ዘንድ ባል አለማግባቷን የሚገልጽ ወሬ ለአገኘችው ሁሉ አወራች። ወሬው ተዛምቶ በየመንደሩ መዳረሱን ስታረጋግጥ ደግሞ ጉረምሶች፣ ወጣት ባለትዳር ወንዶች፣ ያላገቡና ባለ እጮኛ ልጃገረዶች ምሽትን ተገን አድርገው ወደሚቦርቁበት የምሽት ጭፈራ «ኢቫንጋዲ» ለመካፈል ነኢማ ከምትባለው የከሎ ሆራ እኅት ጋር ስትሄድ ምንም ተቃውሞ ሳይደርስባት ቀረ።

ካርለት ለጭፈራ እንግዳ አይደለችም። እንዲያውም አሳምራ የመደነስ ትምህርትና ልምድ አላት፤ ኧረ ነበራት ማለት ይሻላል። በምሽት ጭፈራው (በኢቫንጋዲ) ግን የምታምቧትር ሕፃን ሆነች። በኢቫንጋዲ ከአምስት ዓይነት በላይ የጭፈራ ስልቶች ሲኖሩ ስልቱ በዘፈቀደ መወዛወዝ ሳይሆን አንድ ወጥና ደረጃ በደረጃ የወሲብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስሜትን ሊቀሰቅስና ሊያጋግል በሚችልበት ዘዴ የተቀነባበረ መሆኑን ካርለት ቀስ በቀስ በሚገባ አጤነች።

መጀመሪያ ወንዶች ብቻ እየዘለሉ ሰውነታቸውን ያሟሙቃሉ፤ ቀጥሎ ወንዶች አባራሪ ሴቶች አቅጣጫ ቀያሪ እየሆኑ ይሾራሉ፤ ከዚያ የወንዶች ጭን በሴቶች ጭን ስር ያልፍና ውስጥ ሱሪ አልባ ገላዎች አንዱ «ጀነሬተር» ሌላው «ኦፕሬተር» ይሆንና በሚፈጠረው የኤሌክትሪክ ምገድ ሲናጡ ሁለቱም ተያይዘው ወደ ጫካ ይሠወራሉ። ጭፈራ...ግለት...ጫካ...እርካታ ብቻ–አበቃ፤

ካርለት፣ ከነኢማ የጭፈራውን ስልት እንደ ለመደች ለተወሰነ ጊዜ የመጨነቅ ስሜት ይሰማት እንጂ ቀስ በቀስ ተካነችበት። ቀጭን ወገቧና ዳጐስ ያለው ዳሌዋ፣ ከእግርና እጆቿ ጋር ተዋሕደው በጨረቃ ብርሃን ጫካን ተገን አድርገው ሾሩ።

ይሁን እንጂ መቼም «አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በያዝሽ» ነውና ይፈጠራል የማትለው ስሜት፣ በዳንሱ ስልታዊ እንቅስቃሴ ይፈጠርባት ጀመር። በተለይ አንድ ምሽት፣ ጎሽና ቀጭኔ ገዳይ የሆነውና በተኳሽነቱ የሚደነቀው ደልቲ ገልዲ ልክ እንደ ማንኛዋም ሴት ወደ ጭፈራ ጋብዛው፣ ጥቁሩና ለስላሳው ጭኑ፣ በነጩና ለስላሳ ጭኗ ስርጎ ገብቶ፣ የወንድ ብልቱ የሴት ብልቷን አካባቢ አሸትሽት ሲያደርግላት፣ ምገዱ ከፋኛ ናጣት። ያኔ በደብዛዛዋ የጨረቃ ብርሃን ደልቲን አሻቅባ በማየት እጆቿን ወደ ማጅራቱ ስትሰድ፣ እሱ ግን እጇን አስለቅቆ ወደ ዋንዛና ግራሩ ጫካ ሲሄድ ተከተለችው። ደልቲ፣ ለምን ጫካው ውስጥ እንደ ገባ ምክንያቱ ባይገባትም፣ ወዲያው ግን ፍላጎቱና ፍላጎቷ ተጠቃቅሰው ፊቷን ዞራ እንድትቀርበው አደረጋት።

* * *

ካርለት እስከ ጠዋቱ አራት ሰዓት ከድንኳኗ ሳትወጣ ተኝታ አረፈደች። ለሐመር ሴቶች አንድ በኢቫንጋዲ ጭፈራ ስትውረገረግ ያደረች ሴት በድካም ተኝታ ብታረፍድ ማንንም አያስደንቅም ነበረና ከመኝታዋ እንደ ተነሣች የተለየ ሁኔታ ከአካባቢው ኗሪዎች አላየችም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት፣ ሰውነቷ ውልቅልቁ የወጣ ያህል ቢሰማትም፣ የማታዐ ትዕይንት ግን ወለል ብሎ ታያት። ከልቧ ጨፈረች! በሙሉ ፈቃደኝነት ስሜቷን ለግሳ እሷም ስሜቷን አረካች። ደልቲ ገልዲና እሷ በአንድ ዓይነት ቋንቋ ለመግባባት አልሞከሩም። እሷም ሆነች እሱ ራሳቸውን ሆነው፣ በራሳቸው ቋንቋ ቢነጋገሩም፣ አንዱ ሌላዉ ያለውን ለመረዳት አልተሳነውም። የተፈጥሮ ስሜት በተፈጥሮ «ኮድ» ካለምንም ችግር መገለጽ ስለሚችል ግራ አልተጋቡም፤ ያጋሉት ብረት ምጣድ ሳይቀዘቅዝ ግን ስሜታቸውን ለማርካት ሁለቱም የሚወዱትን ጥብስ ጠበሱበት።

ካርለት፣ የብዙ ወንዶችን እጅ ተንተርሳለች። ደልቲም ቢሆን፣ የብዙ ሐመር ልጃገረዶችን ወገብ አቅፏል። በመካከላቸው ፈላጊና ተፈላጊ አልነበረም። ተጠጋጉ፣ ተነካኩ! ሁለቱም ሞተር አስነሥና አብረው ነጐዱ! ካሰቡት ደረሱ—አበቃ!

የሐመር ወንዶች የአልኮል ፈረስ አይደሉም። መጫወት፣ መዝናናት ግን ባህላቸው ነው። የስሜታቸው ባለቤት ሆነው ይጀምራሉ። የስሜታቸው ባለቤት እንደሆኑ ይጨርሳሉ። የፍትወት ፍላጎታቸውን ለማርካት ኃይልን አይጠቀሙም። ይህን ደግሞ ካርለት ራሷ አይታ አረጋግጣለች። በጭፈራው ስሜቷን እንዲያረካ የከጀለ ችው ሰው ቢኖራትም የመጀመሪያዎቹን ስሜት አነሳሽ የጭፈራ ስልቶች ከሌሎች ወንዶች ጋር ጨፍራለች። የመጨረሻዋ ስልት ጊዜ ግን ተሽቀዳድማ ደልቲ ገልዲን ጋበዘችው። በዚያ ቁመናው ወገቡ ላይ ካገለደመው ሳዳጉራ በስተቀር ምልምል ራቁቱን «አና» በተባለው አፈር ሰውነቱን አዥጐርጉሮ፣ ከንዱ ውስጥ የጠቀለለውን አንባር እያብለጨለጨ፣ አየሩን ግራና ቀኝ እየቀዘፈ፣ በመዝለልና በማሽብሸብ፣ በፈገግታ ጠጋ ብሎ እጁን ትከሻዋ ላይ፣ ጭኖቹን ጭኖቿ ውስጥ ሲያስገባ፣ ካርለት ድንጋዩ እንዳለቀበት ባትሪ ሐሳቧ ብዥ ብዥ አለባት! ስሜቷ ገመዱን በጥሶ በረረ! ለመያዝ ሞከረች! ግን በምን ኃይሏ! መላ ሰውነቷ እየተልፈሰፈሰ፣ ዓይኗ እየተስለመለመ፣ በተወዛወዘች ቍጥር ሰውነቷ እንደ ጀርመን ካቴና ይበልጥ እየተጣበቀ ሲሄድ ተሰማት።

ቢያንስ ደራሽ ስሜቷን ለማሳለፍ አስባ ነበር። ስሜቷንም ለመከታተል ጓጉታ ነበር። ግን ምን ይሆናል፣ ወጥመድ ውስጥ የገባ



t.me/OLDBOOKSPDF

አውሬ ሆነች። ስለዚህ፣ የወሲብ ስሜቷን ለመቆጣጠር ተስኗት ቀድማ ስሜቷን አጣች፤ ተሸነፈች። በተመራማሪዋ ላይ አዲስ ተመራማሪ ተፈጠረባት።

ወደ ጫካ ሲወስዳትም ወደ መኝታ ቤቷ የምትሄድ እንጂ፣ ወደማታውቀው ጫካ የምትጓዝ አትመስልም ነበር። ከዚያም እንኳን ኃይለ ቃል፥ አንዲት ቃል ሳይተነፍስ የውስጥ ሱሪዋን ያወለቀችም እሷ ናት። ካርለት፣ ትክክለኛው ጭፈራ ሰዎችን እርቃናቸውን እንዲ ወዛወዙና ሰላማዊ የመጠላለቅ ዋናን እንዲፈጽሙ የማድረግ ኃይሉን ተረዳች። እና፣ በጭፈራው ስሜት አነሣሽነት፣ ቅንብርና በሐመር ወንዶች የሴቶችን ስሜት አዳማጭነት ተደነቀች።

ካርለት አንድ ከራሷ ልትደብቀው ያልፈለገችው እውነት ደግሞ የደልቲ ገልዲን የስሜትና አካል ጠንካራነት ነው። በትናንቱ ምሽት ዕድሜ ልኳን ያልተሰማት ልዩ ደስታ ማግኘቷም ሌላው ያስደነቃት ጉዳይ ሆነ። ሥልጣኔ ካላዘመነው የተፈጥሮ ቦታና ሰው፣ እውነትስ አዲስ ግኝት ሲገኝ ማን እማይደነቅ አለ?

መላ የስሜት ሕዋሶቿን በአንድ ቍልፍ ነካክቶ፣ አንዱንም ሳያስከፋ፣ ሁሉንም እንደ ባሕርይው አስደስቶ፣ የሚያዝናና ወንድ በሕይወቷ አንድ ወቅት አጋጥሟታል። የዚህኛው የወሲብ ጥንካሬ ግን ለጉድ ነው። ይህ ጥንካሬው ግን ከአመጋገቡ ይሆናል ብላ ገምታለች፤ የከብት ደምና ወተት ቀላቅሎ መጠጣት፣ ቅል ሙሉ ማር፣ ከማሽላ የተሠራ ምግብ፣ የበሰለ ሥጋ፣ የዱር ፍሬና ቅጠላ ቅጠል መብላት ለጥንካሬው አስተዋጽኦ እንዳለው አመነች።

በምሽት ጭፈራው የተካፈሉት ወንዶችና ሴቶች ከደልቲ ገልዲ ጋር ወደ ጫካ ስትጓዝ አይተዋታል። ሆኖም ግን፣ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በጥላቻ ዓይን አላዩዋትም። ስለዚህ ማኅበረሰቡ ለቅናት ያለው ግምት አስደንቋታል። ይህ ሁሉ አስገረማት፤ ከተኛችበት ሳትነሣ ከልቧ በሣቅ ተንከተከተች–ካርለት።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 6

ሦስት ወራት አለፈ። ካርለት በሐመር ቆይታዋ ብዙ ልምድ አካበተች፤ ያልጠበቀችውንም እርካታ አገኘች።

ካርለት ከሎን ወደ ዲመካ፣ ቱርሚና ጂንካ ከተማ ሲሄዱ እግረ–መንገዷን መኪና ማሽከርከር ስላስለመደችው መረዳዳት ጀምረዋል። ካርለት በሐመር ኑሮዋ ዕቃዋን፣ ገንዘቧን ለማስቀመጥ የምትተማመነው በመኪናዋ ውስጥ ነው፤ በተለይም ሙዚቃ ለማዳመጥ መኪናዋ ከፍተኛ ጥቅም ትሰጣታለች። በነዳጅ በኩል እስከዚያ ወቅት ድረስ ችግር አላጋጠማትም፤ ካስፈለጋት ግን ጂንካ ከተማ ናፍታ ማግኘት እንደምትችል ተረድታለች።

የሐመር ሰማይ ጥርት ያለና አልፎ አልፎ ብን ያለ የጥጥ ባዘቶ መሳይ ዳመና ይታይበታል። የዝናቡ ወቅት፣ እምብዛም የሚያስተማምን ባይሆንም፣ ድንገት እያጓራ የሚያጋሽብ ጥልመት ዳመና ከታየ «አህያ» የማይችለው ዝናብ፣ መዓቱን ያወርደዋል። በዚህ ወቅት የዕጽዋት ቅጠሎች እንደ በረዶ ብን–ብን እያሉ ሲወድቁ ከብቶች ጅራታቸውን ሽጉጠው፣ ጆሮአቸውን ይጥላሉ።

በዚህ ወቅት፣ የከሰኬ ወንዝ ከአሸዋ በላይ ዛፍ ቅጠሉን እያተራመሰ፣ ባሕርይውን ይቀይርና በመደንፋት፣ እየተነሣ ይፈርጣል። በዚያን ጊዜ ከሰኬ ወንዝና የሐመር ማኅበረሰብ፣ ከብቱ፣ ፍየሉ፣ በጉ ይኰራረፋሉ፤ «አትድረስብኝ» አንመጣብህም ይባባላሉ።

አንድ ጊዜ፣ ካርለትና ከሎ መዝነቡን ሳያውቁ ከጂንካ ወደ ሻንቆ ሲሄዱ፣ ከሰኬ ወንዝን በመኪና ገብተው ሊሻገሩ ሲሉ መኪናዋ በአሸዋው ተያዘች። እነሱም ከመኪናቸው ወርደው በዶማና አካፋ ለማውጣት ሲሞክሩ። «ፉ–ፉ–ፉ...» የሚል ድምፅ ሰሙ። ቀና ሲሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደረቱን ገልብጦ፣ የሚጣደፍ ደራሽ ውኃ ተመለከቱ። ካርለትና ከሎ ብርክ ይዟቸው እንደ ሕፃን ልጅ ተንቦራቹ። ውኃው ግን ገሰገሰ።

ካርለትና ከሎ ዳር ላይ ሊደርሱ ሲሉ ውኃው ሲያጠናግራቸው ተንገዳገዱ፤ ሳያስቡት እጅ ለእጅ መያያዛቸው ግን በሟቸውና ለትንሽ አመለጡ። ደራሽ ውኃው መጀመሪያ መኪናዋን እያነቃነቀ ፈተሻት፣ ቀጥሎ በጎኗ፣ ከዚያም በጭንቅላቷ አቆማት።

«አምላኬ!» አለች፣ ካርለት መኪና የሚያገለባብጠው ውኃ እኑ ሱን ቢያገኝ እንዴት ብትንትናቸውን እንደሚያወጣቸው እያሰበች።

ዛፉ «ቋ–ቀሽ–ቀሽቀሽ...» ይላል፤ ግንድና ቅጠሉ ብቅ–ጥልቅ ይጫወታሉ፤ ውኃው፣ ሣር ቅጠሉን ያግበሰብሳል። መኪናዋ ጎማዋ ሲታይ ቆይታ በጎኗ ተጋደመች። ደራሽ የውኃ ሙላቱ ግን ለማንም በሚያስገርም ሁኔታ እየቀነሰ፣ እየቀነሰ መጣና ጸጥ አለ። ካርለትና ከሎ መኪናዋን ማውጣት ባለመቻላቸው፣ በየቦታው የተገነደሰውንም ግንድ ለብቻቸው ማነቃነቅ የማይሞከር በመሆኑ፣ የሻንቆን መንደር ኗሪ በእግር ሄደው ጠርተው፣ በስንት ችግር መኪናዋን ሊያወጡ ቻሉ። ስለዚህ፣ ሐመር ላይ ዝናብ ሲዘንብ ከስኬ ሰው፣ ከብት፣ መኪና ሳይቀር ስለሚወስድና ስለሚያሰምጥ ምሉን አያጣም፤ ከብቱን፣ አራዊቱን፣ ሰውን...ድንገት ጠልፎ በመዋጥ የቆየ ልምድ አለው። ካርለትና ከሎ በቆይታቸው የተለያዩ ዕጽዋትንና ጥቅማ ቸውንም ተረድተዋል። ወንጌና ሴቴ ቃጫ ለገመድና ቤት ሥራ፣ ጠዬ ለዱላ፣ ሌልሜ ለቤት ሥራ፣ ፌጦ ለመፋቂያ፣ ኩንኩሮ ለተለ ያየ ጥቅም፣ ፊላና ሰንበሌጥ ለቤት ሥራ እንደሚውሉ ተረድተዋል። በተረፈ ጨው ሊንባ፣ እንኮይ፣ ዘምባባ፣ አጋም፣ ጨዋንዛ፣ ግራር ወዘተ የሐመርንና የአጐራባቾችን መሬቶች አስውበው ሲመለከቱ፣ ከመንፈስ እርካታው በተጨማሪ አንዳንዶቹን መጠቀም ችለዋል።

ካርለትና ከሎ ሻንቆ፣ ላላ፣ ወሮ፣ ዴንባይቴ፣ ዲመካ፣ ቱርሚ፣ ሚኖ፣ ሚርሻ፣ ሜን፣ አንትዴ...መንደሮች ሲዘዋወሩ ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር ከሚገናኙበት አንዱ ሸፈሮ ቡና (የቡና ገለባ) የሚፈላበት ወቅት ነው። የሐመር ቡና የሚፈላው በጀበና ሳይሆን በትልቅ እንስራ ነው። ቡናው የሚጠጣው ንጋት ላይ ጀምሮ እስከ ረፋዱ ድረስ ሲሆን፣ ያደረሰው ሁሉ መጠጣት ይችላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ጊዜ ታዲያ፣ ካርለትና ከሉ ሻንቆ መንደር ለመጀመሪያ ጊዜ ቡና ሊጠጡ ሄደው፣ አይጊ የተባለችው የመንደሩ ኗሪ ቤቷ ለመጡት እንግዶች በሾርቃ (ከትልቅ ቅል ላይ በተከፈለ) መጠጫ ለሁሉም እንግዳ ስታድል፣ ለሁለቱም ሰጠቻቸው። ካርለት አንዱን ሾርቃ እንደምንም ጨርሳ ‹ተገላገልኩ› ብላ፣ ሾርቃውን ለአይጊ አቀበለቻት። በሐመር ባህል ሾርቃውን ቡናውን ለምትቀዳው ካቀበሉ ድገሚኝ እንደማለት በመሆኑ፣ አይጊ ቡናውን በሾርቃ ሞልታ ለካርለት ሰጠቻት፤ «አምላኬ!» አለች ካርለት የመጀመሪያው ቋቅ ሊላት ደርሶ፣ ሁለተኛውን ስታስታቅፋት።

ካርለት፣ ቡናውን መጠጣት ከበዳት። ቁጭ አድርጋ ትታ እንዳትሄድ፣ ባህሉን መናቅ እንዳይሆንባት ሠግታ ስትጨነቅ ቡናውን በያዘው ሾርቃ ላይ ዝንቦች እየገቡ ተንሳፈፉ። ካርለት፣ «ጥሩ አጋ ጣሚ» ብላ፣ እየሣቀች፣ «ዝንብ ገባበት» በላቸው አለችው ከሉን፣ «ድፊው» ይሉኛል ብላ። እነሱ ግን፣ «ጠጭው ምንም አይልሽም፣ ይሄ የወተት እንጂ፣ የቆሻሻ ዝንብ አይደለም» አሏት። ካርለት፣ ሌላ አማራጭ ስላልነበራት የሚንሳፈፉትን ዝንቦች «እፍ» እያለች ቡናውን ጠጥታ ጨረሰች።

ካርለት በሐመር ኑሮዋ በጣም የከበዳት ችግሯ ግን የሐመሮች የጊዜ ዕውቀት አለመኖር ነው። ካለፕሮግራሟ፣ በተለይ በገበያ ቀን ዲመካ፣ ቱርሚ፣ ቀይ–አፈርና ጂንካ በመኪናዋ እንድትወስዳቸው ይጠይቋትና መኪናዋ ውስጥ ዱቄት፣ ፍየል፣ በግ፣ አረቄ፣ ማርና ቅቤ ስለሚጭኑ ሁሌ ትሳቀቃለች። አንዳንዴም አፍ አውጥታ፣ «አልሄድም» ትላለች።

ካርለት ምግብ፣ ደብዳቤ፣ መጽሔት፣ ከቤተሰብ ጋር የስልክ ግንኙነት ለማድረግ አዲሳባ ስትሄድም፤ በጉዞው ከሉ ሆራ መኪና ማሽከርከር ቢረዳትም ወንዝ እየሞላ፣ ጭቃ ሲይዛቸው ትማረራለች።

ካርለትና ከሉ ወደ አዲሳባ ሲሄዱ አልፎ አልፎ የሚላኩት መልእክት የተወሰነ ሲሆን አቡጀዲ፣ የላስቲክ ጫማ፣ ሽፈሮ ቡና፣ ሽጉጥ መሳይ መድኃኒት «ቴትራሳይክሊን ወይም ክሎሮፌኒኮል» ዋነኞቹ ናቸው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት ሐመር ሦስት ወር ቆይታ አዲሳባ እንደሄደች፣ ከስቲቭ ጋር ተገናኙ። ስለ ሐመር ሕይወቷ፣ ስላየቻቸው ነገሮች፣ ስላጋጠማት ችግርና ስለ ወሰደችው የመፍትሔ እርምጃ አጫወተችው።

ስቲቭ ከነገረችው ሌላ፣ ካርለት አንገቷና እጇ ላይ ያለውን ነገር ከማየቱም ባሻገር፣ ሳታቋርጥ ስታክ ተመለከታት። ከዚያም፣ «የኔ ፍቅር፣ ይህን ያህል ለምን ራስሽን ለችግር ታጋልጫለሽ?» አላት ስቲቭ።

«ችግር ስትል ምን ማለትህ ነው?»

«ይህ ደረሰብኝ እያልሽ ያወራሽኝ ሁሉኮ ጋሪ ላይ የተጫነ ጭነት ሳይሆን፣ አንች የተሸከምሽው ችግር ነው?» አላት።

«ስቲቭ፣ አንድ ሰው የምኖረው ትርጉም ያለው ሥራ ለመሥራት ነው ካለ፣ ሕይወቱም ትርጉም ያለው ይሆናል። ሌላው ደግሞ ‹የምኖረው ለመሞት ነው› ካለ በውስጡ እውነትነት አለው። ሕይወቱ ግን፣ ትርጉም አልባ ይሆንበታል።

«ማንኛውም አጋጣሚ በየግላችን አእምሮ አመዛዝነን፣ መክረን፣ እናወጣ–እናወርደዋለን፣ ቀጥሎ ጥሩ ወይም መጥፎ ትርጉም እንሰጥና ተግባሩ ላይ ያን አጋጣሚ እንጠላዋለን ወይም እንወደዋለን።

«አንዱ መኖርን ጥሩ ሥራ ለመሥራት እንደሆን ተረድቶ ሲጥር፣ ሌላው ደግሞ መኖሩ ለመሞት መሆኑን አውቆ ተስፋው ይኰሰምናል።

«እኔም፣ ገጠመኙን ማውራቱ ለአንተ ፍርሃትን ሲፈጥርብህ፣ ለእኔ ግን ፍቅር ስላሳደረብኝ፣ አብሬያቸው መኖሩን እመርጣለሁ» አለችውና ዝም ብላ ቆይታ፣ «አየህ ስቲቭ፣ ከርቀት ጠቦ የሚታይህ ድልድይ፣ ስትደርስበት ግን ሰፊ ነው» ብላ ጉንጩን ቆንጠጥ አድርጋ፣ ከከሎ ጋር ጉዞዋን ቀጠለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 7

«በአባቴ ቆዳ ላይ ተኝተህ፣ ኩርኩፋህን እየበላህ፣ ሸፈሮ ቡናህ እየጠጣህ፣ ቀና ብለህ የቦርጆን (የአምላክን) ከዋክብት ተመልከት፤ አሸጋግረህ የሐመር ተራራዎችን ቃኝ። በእበትና አፈር እያጌጥክ፤ የባንኪሞሮን ንቦች እየተንከባከብክ፣ ማሩን ብላ፤ የአበቦችን መዓዛ አሽትት።

«ጠላቶቻችን ከተራራው ግርጌ ናቸው። የአባቴ አጥንት ስለሚ ወጋቸው፣ ጠረኑ ስለሚያስበረግጋቸው፣ አይመጡብህም። ሾልከው ከገቡ ግን እበቴን ተቀብቼ፣ ንቤን በብብቴ ይዤ፣ ሁለት አፍ ጦሬን በመያዝ፣ አንተን አስከትዬ እሄድላቸዋለሁ። የሀገሬ አዕዋፍና አውሬ፣ ያኔ ይጠግባሉ።

«ፀሐይ ከወደቀችበት ነገ ትነሣለች፤ ጨረቃን ገፍትራ ጥላ ቦታዋን እስከትይዝ ግን ታጋሽ ሁን። ጨለማን ተገን አድርገህ ተንኮል አትሥራ። ከስኬ ከአሸዋ በላይ እስኪሞላ፣ የሰማይ ውኃን እየጠበቅህ ጓሮህን እንድትቆፍር ልጃገረድህን እዘዝ።

«እጅህንና እግርህን በምላስህ እሠር፤ የአባቴን ደንብና ባህል አክብር፤ የታላላቆችህን ትእዛዝ ተቀበል፤ ለጠላቶችህ የማትፈራ፤ ወፍ በጥይት የምታስቀር፣ ጀግና ሁን። ካለበለዚያ፣ የአባቴን ደንብ ሽረሃልና ደረቴን አስጌጥብሃለሁ (እገድልሃለሁ)።

«ተጫወት፣ በአባትህ ሚዳና ተራራ ተዘዋወር፤ ከልጃገረዶች ጋር ዝለል፤ ወተትና ደም ጠጣ፤ ውለድ፤ ከብትህን በበረት ሙላ፤ ...የኔ ልጅ ጨርሻለሁ» ብለው የሚጠጡትን ሸፈሮ ቡና «ፕስስ...» እያሉ፣ በአራቱም ማዕዘን ያማትቡና የልጃቸውን ራስ ዝቅ አድርገው የሸፈሮ ቡናውን ውኃ፣ «ፕስስ...» እያሉ ያርከፈክፉበታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ደልቲ ገልዲ፣ አባቱ ገና ከመሞታቸው በፊት ምርቃታቸውንና አደራቸውን በገሐድ አሳያቸው። ለምሳሌ ደልቲ ገልዲ ማጎ በረሃ ከጓደኞቹ ጋር ወርዶ ካለምንም ስንቅ ለተወሰነ ጊዜ በረሃብ ቢሠቃይም፣ ከዚያ በኋላ ግን ሚዳቋም፣ ውድንቢትም፣ ድኩላም፣ እየገደሉ፤ ቋንጣውን በፀሐይ በማድረቅ እየተመገቡ ታላላቅ አራዊት ሊገኙበት ከሚችልበት አካባቢ በመዘዋወር ሰንብተው፣ አንድ ቀን ከማጎ ወንዝ ውስጥ ተነክረው እንዳሉ የአራዊት ዳና ሰሙ። ከውኃው እየሮጡ በመውጣት ድምፁን ከሰሙበት አቅጣጫ በተቃራኒ ካለው ጫካ ውስጥ አደፈጡ። ሆኖም ግን፣ መሣሪያቸው ወዲያ ማዶ በመሆኑ ሲመኙት የነበረው ዕድል አመለጣቸው። የመጣው የጎሽ መንጋ ካለብዙ ችግር፣ እርስ በርስ እየተጠባበቀ በመጣበት አቅጣጫ ሄዶ ተሠወረባቸው።

ደልቲም ሆነ ሌሎች ጓደኞቹ ወደ አደን ከመምጣታቸው በፊት ብዙ የአራዊት ጠባይ ተነግሯቸዋል። ጎሽ ከቈሰለ፣ የአቈሰለውን ሰው እንደማይለቅ፤ ያንን ሰው ባያገኘው እንኳን ዝንብ ቈስሉን እየበላ እንዳያስቸግረው ከወንዝ ውስጥ እየገባ እንደሚያደፍጥና ሌላ ሰው ካገኘ ብጥስጥሱን በእልክ እንደሚያወጣው ሰምተዋል። ስለሆነም፣ ጎሽን ለመግደል ብልቱን ለይቶ መምታት እንደሚያስፈልግ፣ በመን ጋው ላይ ከመተኩስም፣ ከመንጋው የተለየውን መግደል እንደ ሚሻል፣ ተመክረዋል።

ማታ ማታ አንበሳና ነብር እንዳይተናኰላቸውም እሳት ማቀጣ ጠል እንደሚገባና እሳቱ ብዙ ጭስ እንዳይኖረውና ጫካውንና አውሬዎችን የሚጠብቁት ዘበኞች አደጋ እንዳያደርሱባቸው እንዲጠነቀቁ፤ እባብ በተለይም የጠገበ ዘንዶ፣ አንዳንዴ ግንድ መስሎ እንደሚጠቀለልና ድንገት ቁጭ ካሉበት ለአደጋ እንዳይጋለጡም ተመክረዋል። አቅጣጫ ጠፍቶባቸው በተለይ በውኃ ጥም እንዳይጠቁም ልምምድና ውኃ የማያስጠማ መፋቂያ እንዲይዙና በጨረቃና በከዋክብት አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ፣ ተነግሯቸዋል። በተለይ ደግሞ፣ ሲጓዙ በጋራና በዘዴ እንዲሆንና በተናጠል እንዳይጓዙ፣ ችግር ሆኖ ከተጠፋፉም እንቅልፍ ለመተኛት ሲፈልጉ ከመጋደም ይልቅ ቁጭ ብለው አንገትን ወደ ታች በመቅበር እንዲተኙ፤ ከብትም ሆነ ሰው ላይ ጥላው ሲያርፍ ወገብ የሚያጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምመው አሞሯ ሲበር ሲታይ መደበቅና ከጥላው መራቅ ማስፈለጉን፣ የግድ የሚቀርብ ከሆነም ተዙሶ ማባረር የሚሻል መሆኑን ተመክረዋል። በተረፈ አራዊት ከጠፉ የጀግንነታቸው ማረጋገጫ ስለማይኖር ሴትና ወንዱን መለየት ስለማይቻል ዕድል ቀናኝ ብለው በብዛት መግደልና ማስደንበርም እንዳይፈጽሙ አደራ ተብለዋል።

ስለዚህ፣ የጎሹ መንጋ ተመልሶ ሄዶ ከአካባቢያቸው መራቁን አረጋግጠው ከተደበቁበት ብቅ ሲሉ ሲሉ፣ ሴትና ወንድ አንበሳ ወደ ውኃው ሲመጡ አዩ፤ ወዲያው ደንግጠው ተመልሰው ተደበቁ። በቁጥቋጦው ውስጥ ከርቀት ሲመለከቱ ደግሞ፣ ግንድና ቅጠሉ ሲርመሰመስ ተመለከቱ። ከዚያ አንበሶቹ እነሱ ወደ ተደበቁበት አቅጣጫ ሲመጡ፣ ሁሉም ወሽመጣቸው ተበጠሰ። ባዶ እጅ ከአንበሳ ጋር መግጠም መቼም አይቻልም። ያውም ከሁለት አንበሳ። አንበሶቹ ከኋላ ግንድና ቅጠሉን እያተረማመሱ የሚመጣውን አውሬ በጥርጣሬ እያዩ ስለሚሸሹ ደግነቱ እነሱን ፈርተው የሚንቀጠቀጡትን አላስተዋሉም። ስለዚህ፣ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ግንድና ቅጠሉ በሚሰባበርበትና በሚንሿሿበት አቅጣጫ ሲመለከቱም፣ ለቍጥር የሚታክት ዝሆን ተመለከቱ። ስለ ዝሆን ደግሞ የሰሙት አለ። ዝሆን ከፍተኛ የማሽተት ችሎታ አለው። እስከ ብዙ ርቀት ጠረን ማሽተት ይችላል። ምናልባት ደግነቱ ነፋሱ ወደነሱ አቅጣጫ ስለሆነ ጠረናቸው ላይደርሰው ይችላል። እንሽሽም ተባብለው ነበር። ግን፣ ከዚህ የዝሆን ረገጣና ወገራ ቢያልፉ፣ ከዚያ ደግሞ የአንበሳ ክንድና የጎሽ ቀንድ ይጠብቃቸዋል። ሁሉም ያው እንዳቅሙ ሰባብሮ፣ መጨረሻው ሞት ነው። ስለዚህ መሸሹ እንደማያዋጣ አመኑ።

የዝሆን መንጋው በኩንቢው ውኃውን ሰውነቱ ላይ እየረጨ፣ ውኃው ውስጥ ለብዙ ሰዓት ቆየ። አንድ ዝሆን እንዲያውም፣ ድንጋይ ተደግፎ የተቀመጠውን ምንሽር ጠመንጃ ወደ ላይ በኩንቢው አንሥቶ አይቶ መልሶ አስቀመጠው። የሱ ማደኛ መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ ወደ አመድነት ይለውጠው ነበር፤ ነገር ግን አላወቀም። ስለዚህ ጠላቱን አንሥቶ መልሶ አስቀመጠው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ደልቲና ጓደኞቹ ይህንና ይህን የመሳሰለውን ችግርና አደጋ አሟልጠው፣ ቀንቲቸው ከታላላቅ አራዊት ውስጥ ከገደሉ ደግሞ በማኅበረሰባቸው የሚያገኙት የጀግንነት ክብርና ሙገሳ፣ ልብን የሚያልል። ከወንድነት ማረጋገጫውም ውስጥ ዋናው በጠላትነት የሚያዩትን የማኅበረሰብ አባል መግደል ሲሆን ከዚያ የሚቀጥለው ደግሞ አውራሪስ፣ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ጎሽ፣ ቀጭኔ...መግደሉ ነው።

በሌላ ቀን ደልቲ ገልዲና ጓደኞቹ አደናቸውን እንደ ጀመሩ፣ ከመንጋ የተለዩ ጎሾችን ተመለከቱ። ሁሉም በየተራ እያነጣጠረ ተኮሰ። የቀሩት ጎሾች ሲሸሹ፣ ሦስት ጓደኞቹ ብቻ ሦስት ጎሽ ገደሉ። ከነዚያ ውስጥ ደግሞ የመጀመሪያው ገዳይ ደልቲ ገልዲ ሆነ። የገደሉትን ባልገደሉት ላይ ጀግንነት ተሰማቸው፤ አቅራሩ፤ ፎከሩ።

ለአደን በሄዱ በሦስተኛው ሳምንታቸው ደግሞ ከርቀት የቀጭኔ መንጋ ተመለከቱ፣ ቀጭኔ ከርቀት ማየት ስለሚችል እንዲህ በዋዛ ግደን ስለማይቻል እምብዛም ተስፋ አጡ። ገልዲ ግን፣ በየት እንደሄደ ጓደኞቹ እንኳ ሳያዩት ከቀጭኔዎቹ እይታ ውጭ በመሆን ሥራቸው ድረስ መጠጋት በመቻሉ፣ በምንሽር ጠመንጃው አንዱን ቀጭኔ በሁለት ጥይት ወርቹን በጥሶ አንበረከከው። ጓደኞቹ ሲመጡ ከቀጭኔው ጀርባ ላይ ወጥቶ ጠበቃቸው።

ደልቲ ገልዲ፣ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የጎሽና የቀጭኔ ገዳይ ሆነ። ወደ መንደራቸው ሲመለሱም የመንደሩ ልጃገረዶች ለገዳዮቹ፣ በተለይም ለጎሽና ቀጭኔ ገዳዩ፣ ጨሌያቸውን በአንገቱ አጠለቁለት። በየዘመዶቹም እያቅራራና እየፎከረ ሲሄድ በግና ፍየላቸውን እያረዱ፣ ጀርባው ላይ ደሙን አፈሰሱለት። ለወራት ያህል ምግቡ ደምና ወተት፣ ሥጋና ማር ሆነ። በዚህ ደግሞ፣ አባቱ ልጃቸው እሳቸው እንኳን ያልቀናቸውን የጎሽና ቀጭኔ ገዳይ በመሆኑ ኩሩበት።

ብዙም ሳይቆይ ደልቲ ገልዲ በሐመርና በሙርሲ ማኅበረሰቦች መካከል በተፈጠረው ግጭትና ጦርነት እንደ ጉርኑክ እየዘለለ በመዋጋት፣ ሁለት ሙርሲ ገድሎ መዛሪያቸውን በመማረኩ፣ ደረቱን በመተልተል፣ ራሱን በቀይና በነጭ አፈር በማስጌጥ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

በአንገቱ ከደረደረው ጨሌና በእጆቹ ካጠለቃቸው አንባሮች ሌላ፣ በወገቡ በታጠቀው ዝናርና መያዣዋ በሚያንጸባርቀው ቤልጅግ ጠመንጃ ከአካባቢው ኗሪ ልዩ ክብር ተጎናፀፈ፤ የመንደሩ ልጃገረዶች ቀርቶ ከመንደሩ ራቅ ያሉትም ልጃገረዶች ሳይቀሩ በዝናውና በቁመናው በመመሰጥ፣ የመጀመሪያውን እፍታ በየጫካው አጉረፉ ለት። ከሙርሲ ማኅበረሰብ በዘረፋቸው ከብቶችም መጫሪያ ገዛና በረቱን በከብት ሞላ። ሁለት ሚስት አግብቶ፣ የአባቱን ምኞትም አሟላ። አባቱም ምንም እንኳን ከዳሰነች ማኅበረሰብ ጋር በተደረገው ጦርነት ቢሞቱም፣ የአባቱ ደም መላሽ ለመሆን ቻለ።

ደልቲ ገልዲ ስሙ እየገነነ ሲሄድ፣ የእሱም ልብ እያበጠ ሄደ። መቼም ሲመጣ በላይ በላይ ነውና፣ የላላና ሻንቆን መንደር ሰዎች ከብት እየሰበረ ያስቸገረ አንበሳ ለማደን ሁሉም በቡድን በቡድን ጫካ ሲገባ፣ እሱ ግን፣ «በእኔ በኩል ብቻዬን እበቃለሁ» ብሎ፣ ከነመጫሪ ያው ለአደን ተሰማራ። ሁሉም ቦርጆን (አምላክን) እየተማፀነ፣ የአንበሳው ገዳይ ሆኖ እንደ አባያ በሬ ለመንጐማለል ሲመኝና ፍለጋው ሲጧጧፍ ውሎ የጥይት ተኩስ ተሰማ፤ ወዲያው አንበሳው ተገደለ ተባለና ገዳዩ ማን እንደሆነ አንዱ ሌላውን ሲጠይቅ፣ «ደልቲ ገልዲ፣ የተኛ አንበሳ አልገድልም ብሎ ‹ጎፈር› ብሎ ቀስቅሶ አስነሥቶ፣ አጓርቶ ወደ እሱ ሲዘልበት በሚያስደንቅ ፍጥነት መጫሪያውን አቀባብሎ፣ በሁለት ጥይት፣ ልሳኑን ዘጋው» ተባለ።

ልጃገረዶች፣ «ይኸዋ አላልኩሽም!» ሲባባሉ፣ «ኧረ እሱ ምኑ ነው ይሄን ያህል!» እያሉ ያናንቁ የነበሩት ጐረምሶች እንኳን ሳይቀሩ፣ አንገታቸውን ደፉለት፤ እረኞች፣ ልጃገረዶች በስሙ ዘፈኑለት፣ ሌላው ቀርቶ የመፎከሪያ በሬው ከሌሎች ከብቶች በልጦ ተንጐማለለ። ደልቲ ገልዲ፣ ከግዙፉ የቡስካ ተራራ ይበልጥ ገዝፎ መታየት ጀመረ። በዚህ ሰሞን ነበር ሁለት እንግዶች ወደ መንደራቸው የዘለቁት።

* * *

ደልቲ ገልዲ በራሱ የሚተማመን ጀግና በመሆኑ በዚህ ዓለም ላይ ከእሱ በላይ ሰው ያለ አይመስለውም። ስለሆነም፥ የሚፈልገውን



t.me/OLDBOOKSPDF

አጣለሁ የሚል ቅንጣት ታህል ፕርጣሬ የለውም። በስሙ ሲዘፈንና ሲዘመር፥ ጥርሱን እየፋቀ በርኳታው (መቀመጫው) ላይ ቁጭ ብሎ ወይንም ጋደም ብሎ መዝናናት ነው።

ጀግንነት ከሀብት ጋር ገና ዕድሜው ሳይገፋ፥ «ቤት ለእንቦሳ» ሲል «እንቦሳ እሠር» ብሎ፥ ተቀብሎታል። በእርግጥ እያንዳንዱ የሐመር ጓዳ ላጠቃላይ ማኅበረሰቡ ግልጽ ነው። ተካፍሎ መመገብ፥ ተሰባስቦ መጨፈር፥ ተከባብሮ መኖር፥ ጠላትን በጋራ ማጥቃትና መደናነቅ የማኅበረሰቡ ወግና ልማድ ነው። ደልቲ ገልዲም የዚህ ባህ ላዊ ኑሮ ተሳታፊና ተገዥ በመሆኑ ኃይሉን ተማምኖ ሌላውን የሐመር አባል ማጥቃትም ሆነ ንብረት መቀማት ክብሩን ለውርደት፥ ሀብቱን ለጥፋት ስለሚያበቃ ከልጅነቱ ጀምሮ ክብርንና መብትን በጥንቃቄ መያዙንና ተከባብሮና ተመካክሮ መኖርን ሊዘነጋ አልቻለም።

ዶልቲ ገልዲ፥ በዚያን ሰሞን ወደ መንደራቸው የመጣችውን እንግዳ የተመለከታት በኩራት ነበር። የለበሰችውን ጨርቅና የምትሸተው ቃና ከአካባቢው ልጃገረዶች ጠረን የተለየ በመሆኑ ራቅ ብሎ ነው ያስተዋላት።

«እንደ ሐመር ሴቶች ቆዳ የማትለብሰውና ጭኖቿን የማታሳየው ምናልባት የሚያሳፍር ነገር ቢኖርባት ይሆናል» ብሎ፥ ከመገመቱም በላይ የሴትነት ጠረኗን የዋጠው ሽታ አስጠልቶት ነበር። በተደጋጋሚ ቀናት እንዳያትም በሚኰርፍ ነገር መተጣጠቧ ብልግናዋን ከማረጋ ገጡም በላይ መጥፎ ጠረኗን ለማጥፋት መሆኑን አምኖበታል።

የሐመር ልጃገረዶች በውኃ አይታጠቡም። «ብልታቸውን ውኃ ከነካው መካን ይሆናሉ» ስለሚባል፣ በጣም ነውር ነው። ይህችኛዋ እንግዳ ግን አልፎ አልፎ ብቻ ሳይሆን ዘወትር ስትተጣጠብ ያያታል። «መካንነቷ መቼም የማይቀር ነው። ግን ሴት ሆና ስትተጣጠብ የማታፍር ምኒቱ ባለጌ ናት?» እያለ ኮንኗታል። ሌላውም እንደሱ በድርጊቷ ጠልቷታል።

ሆኖም እሱ የጀግኖች ጀግና ነው፤ እንዲህ ዓይነቷን ባለጌ ልክ የማግባቱ ኃላፊነት ከሱ ትከሻ ላይ የወደቀ ነው። ስለዚህ፣ እንግ ዳይቱን በግርፋትም ቢሆን ሥነ–ሥርዓትን ሊያስተምራት ይችላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ለማድረግ ደግሞ፣ እሷን ማግባት አለበት። ካለበለዚያ ዝንጧንም እሽ ማለት ላይችል ነው። ደግሞኮ የሱ ሚስቶች በመልካቸው ጥቋቁሮች ናቸው፤ ስለዚህ ነጭ ሚስት ያስፈልገዋል። ሀብቱ እንደሆነ የትየለሌ ነው፤ ሦስት በረት ከብት፣ በየጋጡ ብዛት ያለው ፍየል፣ በየጫካው ለቍጥር የሚታክት ቀፎ አለው። በዚያ ላይ የቀጭኔ፣ የጎሽ፣ የአንበሳና የሰው ገዳይ ነው።

ስለዚህ፣ ይህችን ባለጌ ለማረቅ እንዲችል እሷን የራሱ የሚያደርግበት በቂ ሀብት አለው። እና፣ የሚጠየቀውን ጥሎሽ ከፍሎ የሱ ንብረት ካደረጋት በኋላ ቢቀጣት ጠያቂ የለበትም። ለዚህ ሁሉ ግን፣ ሚስቱ እንድትሆን ማድረግ እንዳለበት አመነ። አብሯት የመጣው ከሎ ሆራ እንደሆነ ምንም እንዳልሆነ አረጋግጧል።

አንድ ቀን ካርለትና ከሎ ሆራ ሲጨዋወቱ ደልቲ ገልዲ፣ «ነጋያ» ብሎ አጠገባቸው ለመቀመጥ ይዞት በሚዞረው በርኮታ ላይ መሣሪያውን ጭኖቹ መሃል አድርጎ ተቀመጠ። ከዚያም፣ «ባል አለሽ?» ብሎ በቋንቋው ጠየቃት። ይሉኝታና ፍርሃት የሐመርን ተወላጅ ሲያልፍም አይነካካውም። ደግሞስ ሰው ሰው ነው። ያውም እሱ ጀግናው። ከሎ ሆራ ያለውን ለካርለት ተረጐመላት።

«የለኝም» አለችው። ካርለት በቀኝ እጇ ግንባሯ ላይ የተበታተነውን ጸጉር ወደ ኋላዋ እየመለሰች።

«አባትሽ ስንት ከብት አለው?» አላት፣ ደልቲ።

«ከብት የለውም፣ ፕሮፌሰር ነበር። ስለዚህ ደመወዙ...» ፕሮፌሰር፣ ደመወዝ ያለችው ሊገባው አይችልም። ከባለጌ የሚጠበቅ ተራ የተራ ነገር ይሆናልና ስለሱ ማሰብ አያስፈልግም።

«ቀፎና ፍየልስ?» ጠየቀ ደልቲ።

«የለውም» አለች። አባቷ ደሃ ቢሆን ነው ማለት ነው ወደዚህ የላካት ብሎ አዘነላት። በሐመር ማኅበረሰብ ሀብት ማለት ከብት፣ ፍየል፣ ቀፎ ነው። ከዚህ ውጭ ደመወዝ፣ ቪላ፣ መኪና ብሎ ሐተታ፣ የሚገባው የለም።


t.me/OLDBOOKSPDF

ደልቲ ገልዲ በክልሉ የሀብት ሁሉ ባለቤት አባወራው እንደሆነ አሳምሮ ያውቃል። ስለዚህ፣ እንግዳዋን ስለ እናቷ መጠየቅ አያስፈልግም። ደግሞ ሴትን፣ «ሀብት አላት ወይ?» ብሎ መጠየቅ ነውር ነው። የእንግዳዋን አባት ሁኔታ እንደሆነ ጠይቆ፣ ድህነቱን ተረድቷል።

ደልቲ ገልዲ በእሱና በእንግዳዋ አባት ሀብት መካከል ያለው ልዩነት የሰማይና የምድር ያህል ሰፍቶ ታየው። ለምግብ ማቅረቢያ፣ ለመኝታ የምትጠቀምበት፣ በተለይም ማታ ማታ «ፋ» የምታደርገው መብራትና ብልጭልጭ ቅራቅንቦዋ፣ ከሱ ንብረት አንፃር ሲታይ ጠጠርና ተራራን ማወዳደር ቢሆንም፣ አባቷ ሀብቱን ለምን ለእሷ እንደተወላት ግራ ገብቶታል። የሱ ወገን የሆኑት የሐመር ሴቶች የግሌ የሚሉት ሀብታቸው የሚለብሱት ቆዳ፣ ጨሌና አንባራቸውን ብቻ እንደሆነ ጥርት አድርጎ ያውቃል።

ያም ሆነ ይህ ግን፣ እንግዳዋን አግብቶ በግርፋት መግራት እንዲችል ሊያገባት መፈለጉን ለሽማግሎች ማማከር አለበት። ሽማግሎች የሚሉት ባይታወቅም ብልግናዋን ገልጾ ሊገራት እንደሚፈልግ ሲነግራቸው እነሱም ይህን ስለሚረዱ ተቃውሞ እንደማይኖራቸው ተማምኗል። አንድ ግን ግራ የገባው ጉዳይ አለ። ጋብቻውን ሽማግሎች ቢቀበሉት «ልጅቱን ለማግባት፣ አባቷ የት ተገኝቶ በሽማግሎች ይጠየቃል? ጥሎሹንስ እንዴት ወስዶ ከችግሩ ይላቀቃል?» ብሎ አሰበ።

ይህ ከሆነ በኋላ ግን፣ ብዙም ሳይቆይ ደልቲ ገልዲና ካርለት በምሽት ጭፈራ ተገናኙ። ካርለት ያ አስደናቂ ጥያቄ ሲጠይቃት የነበረው ወላንሳ እየዘለለና እያሸበሸበ ሲደንስና ሲሥቅ፣ ደጋግማ ስታየው ሁሉን ነገር በተለይም ስለሱ የሚባለውን ሁሉ አስታወሰች። ስለዚህ፣ ዛሬ ይህን ስሙ በሐመር ሰማይ ላይ የሚንሳፈፍ ሰው ማንነት ማወቅ አለባት።

ያም ሆኖ ግን ካርለት ስሜቷ ለሁለት ተከፈለባት። በአገሯ ምን ዓይነት ውበትና ጠባይ ያላቸው ወንዶች በሴቶች እንደሚፈቀሩ፣ ከሞላ ጎደል ታውቃለች። እሷም ብትሆን በአፍላው የወጣትነት ጊዜዋ የነበራት የስሜት ቅብጥብጥነትና በምታፈቅረው ወንድ ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታጠምደው የነበረውን መረብ አስታወሰች። ሆኖም ይህ ሰው እዚያ ከምታውቃቸው ሰዎች በብዙ መልኩ ይለያል። ለነገሩ የደልቲ ውበት ጭጋግ ለብሶ ይታያል፤ ያውም ይኖራል ብላ ያልገመተችው ውበት።

የሐመር ልጃገረዶችን ሕሊና ያማልላል ተብሎ የሚደነቀውን ልበ–ሙሉ ወንድ ጭጋጉን በታትና ሥነ–ውበቱን በትክክል መቆጣጠር አለባት። የለንደኑ፣ የቦኑ፣ የማንቸስተሩ...ወጥመዷ ያለውን የመያዝ ችሎታም መፈተን ይኖርባታል።

እንደ ባልጩት ድንጋይ የለሰለሰውን ገላውንና በጨረቃ የሚያንፀባርቁት ጥርሶቹን ባሰበች ቍጥር ጥርት–ጎላ እያሉ ታይዋት። ስለዚህ፣ ማራኪውና የመጨረሻ ዓይነት የጭፈራ ምት መጀመሪያው ጊዜ መቃረቡን ስታውቅ፣ ሐሳቧን ተግባራዊ ለማድረግ ለሩጫ እንደሚዘጋጅ ሯጭ አደፈጠች።

ያን የወቅቱን ወላንሳና ቀብራራ ሐመር ጠብቃ ለዳንስ ስትጋብዘውና እያኮበኮበ፣ አየሩን በመቅዘፍ ቀርቦ ጥቁሩ ጭኑ ከነጩ ጭኗ ሲተሻሽ፣ ሸካራና ጠንካራ እጆቹ ትከሻዋን ሲይዙ፣ ስሜቱ በስሜቷ ውስጥ ሲሟሟ፣ ያለችበትን ቦታና ሰዎችን በመዘንጋት የሚያቃጥል፣ የሚነዝርና በሰመመን የሚያሰጥም ስሜት እንደ ተሰማት፣ ከራሷ ቍጥጥር ውጭ ሆነች። ስለዚህ፣ ሁሉን ነገር ዘንግታ ተንጠራርታ አንገቱን በማቀፍ ከንፈሯን ከከንፈሩ ጋር ለማላተም ተጣጣረች፤ ደልቲ ግን፣ በጠንካራ እጆቹ እጇን ያዝ አድርጎ፣ የዳንሱን ቦታ ጥሎ፣ ወደ ጫካ ይዟት ገባ፤ ጥቁሩና ነጭ አባይ ጫካ መሃል ተገናኙ።

ደልቲ ገልዲ ከእንግዳዋ ጋር ግንኙነት ከፈጠረ ጊዜ ጀምሮ፣ በተለይም በጭፈራ ቦታ፣ በሁለቱም መፈቃቀድ ግንኙነት ማድረጋቸው ቢቀጥልም በእንግዳዋ ላይ የሚያየው ባሕርይ ይበልጥ ግራ እያጋባው መምጣቱ አልቀረም። የእንግዳዋ ሰውነት እጅግ ለስላሳ ከመሆኑ የተነሣ እንኳን ተገርፋ ሲነኩት የሚላጥ ይመስላል። እጅና እግሯ በአጠቃላይ ሁለመናዋ መለስለሱ አስገርሞታል። «እንዴት ነው ይህች ሰው ሳታርስ፣ ሳትፈጭ፣ የከብቶችን እበት ሳትጠርግና እንጨት ሳትለቅም ነው የኖረችው!» በማለት ተደንቋል።


t.me/OLDBOOKSPDF

# 8

አንድ ወቅት ሐመሮች ግብር አንከፍልም ብለው አመፁ። ቢቻል በስምምነት ካልተቻለ በኃይል እንዲያስገብሩ አፄ ኃይለ ሥላሴ የሠለጠነ ወታደር ወደ ሐመር ይልካሉ። በዚያ ወቀት፣ ሐመሮች ባላሰቡት ጊዜ ጥያቄውን በወታደር መልእክተኛ ይጠየቃሉ። ሆኖም ግን ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለጻቸው ውጊያ ተጀመረና የሐመሮች ሕይወት የሆነው የከስኬ ወንዝ ከምላ ኀደል በወታደሮች ተያዘ። ሐመሮች በለመዱት ክልል ከቋጥኝ ቋጥኝ እየዘለሉ ኋላ ቀር በሆነው መሣሪያ ጠንክረው ቢዋጉም በመትረየስና በተሻለ መሣሪያና ስንቅ በመምጣት በከስኬ ወንዝ አሸዋ ጉድባ ሠርቶ ጥይት የሚያዘንብባቸውን ኃይል መቋቋም ተሳናቸው።

በዚህ መልክ ጥቂት ቀን እንደ ቆዩ በውኃ ጥምና ስንቅ ማጣት ሐመሮች እየተጠቁ የመላ ያለህ ሲባል ለአውሬ አደን የመጣ መንገደኛ በጦርነት ለእነሱ በመርዳት ሲታኰስ ሰነበተ። ልብ ያላሉት እንግዳ ወታደሩ የመሸገበትን ሲያስተውል በወንዙ ጠርዝና ጠርዝ ባሉት ዛፎች ብዙ ቀፎዎች ተሰቅለው በማየቱ ዒላማውን እዚያ ላይ በማድረጉ ከቀፎው ተረብሸው የሚወጡት ንቦች ወታደሩን ጒድጓዱ ድረስ በመግባት ቁም ስቅሉን ስላሳዩት ከምሽጉ እየዘለለ ለመውጣት ተገደደ። ሐመሮች ከምሽጉ የሚወጣውን ወታደር ከላይ እየቀለቡ ሲያስቀሩ እንደ ቆዩ የእሩምታ ተኩስ ቀልጦ፣ በተኩሱ ሽፋን ወታደሮች በመሸሻቸው ከስኬ ወንዝን ማስመለስ ተቻለ። ግጭቱም ሳይደገም በእርቅ አለቀ።

ሐመሮች ያን ጸጉረ ልውጥ መንገደኛ ከምት አትርፈውታል። እሱም በተራው ይከፍለዋል ብለው ከጠበቁት በላቀ ሁኔታ ውለታ ውን መለሰላቸው። ስለዚህ መንገደኛውን ክብት በመስጠት እንደ አባት የሚመርጠው ሽማግሌ፣ ዘመዶች የሆኑ ልጃገረዶች



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚገርፋለትና ሚስት እንደሚያገባ፣ እንደ አንድ የሐመር አባልም እንደሚቈጠር በመግለጽ ስለ ለሙኑት መንገደኛው ትንሽ ካቅማማ በኋላ ሆድ የባሰውና ተስፋ የቈረጠ ስለነበር ተስማማ።

መንገደኛው፣ አመጣጡ ከወደ መንዝ ነው። ለስሙ ዘሩ የባላባት ይሁን እንጂ እሱም ሆነ ቤተሰቦቹ የነጡ ድሆች ነበሩ። ስለዚህ ቋት ለማይሞላው ሕይወቱ ደፋ ቀና እያለ፣ በእርሻ ቀንና ምሽት ሲባዝን ኖረ። ከልጅነቱ ጀምሮ ሠርቶ ከሚከበረው፣ ገሎ የሚደነቀውና ከበሬታን የሚያገኘው ሲልቅ ሲያይ ኖሯልና ጀግና ተብሎ መከበሩና ወገኖቹንም ማስከበሩ ሕሊናውን እያሸፈተበትና ልቡን እያቆመበት መጣ። በተለይ ወደ ደቡብ ተጕዘው የአንበሳ፣ የጎሽ፣ የዝሆን...ገዳይ እየተባሉ የሚመለሱት፣ በአካባቢው ያላቸውን ከበሬታ ሲመለከት አንዳንዴም ከብት ውኃ ለማጠጣት ወይም ልብሱን ለማጠብ ወደ ምንጭ ውኃው ወረድ ባለ ቍጥር፣ የገዳይ ሚስት ተራ ሳትጠብቅ ገብታ ውኃውን ቀድታ እንስራዋን በመሸከም፣ ቀሚሷን ሳብ ሳብ አድርጋ እያንጐራጐረች ሞንደል ሞንደል እያለች ስትሄድ፣ ተራ ጠባቂ ሴቶች፣ «...ኧረ ኤዲያልኝ...አኮራታ...ወይ ነዶ...የኛዎቹማ ወንዶች ምድጃ ለምድጃ፣ ‹ሽሮው ቀጠነ› ይበሉ...አይ ሱሪ እቴ...ኧረ እንዲያው ወይ ነዶ! አንሶ አሳናሽ...ሙቅ ሁላ» ሲሉ አንገቱን ደፍቶ ሲሰማ አንጀቱ እየተኰማተረ፣ ልቡ የገበታ ውኃ እየሆነ፣ ቤቱም ቤት አልመስለው እያለ ‹ከርሞ...ቆይ ከመንፈቅ ወዲያ...እሄዳለሁ» ሲል ኖሮ፣ እንደሱ ልባቸው ከኮበለለው ጋር ዘጠኝ ሆነው ስንቃቸውን ቋጥረው በድብቅ ጕዞ ጀመሩ፤ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ።

ከጕዞው ሦስት ዓመታት በፊት መሆኑ ነው፤ ጥር ላይ ይሄው መንገደኛ በአጎቱ ልጅ ሠርግ ጊዜ ነጠላውን አጣጥፎ ሲያስተናግድ የደም ገንቦ የሆነች ዓይን አፋር ወጣት ለዘፈን እንድትገባ ስትለመን ማስተናገዱን ትቶ ትዡር ብሎ ተመለከታት። ልጅቱ አንገቷን ሰበር አድርጋ፣ ነጠላዋን ከትከሻዋ አውርዳ ወገቧ ላይ ስታደርግ፣ እሱ ደግሞ አንገቱን ሰገግ አድርጎ፣ እሷን ለማየት ተንጠራራ። ከበሮው ድል...ድል...ድል እያለ ሲመታና ጭብጨባው ቀልጦ፣ «...እንዴነሽ ገዳዎ...» ሲባል፣ ወጣቷ እግሯንና እጇን በስልት እያንቀሳቀሰች፣ ስታሸበሽብ ቆየችና፣ «አሆ...ዎ» ብሎ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

አቀንቃኙ፣ «ደርብ፣ ምታ...» ሲል፣ ልጅቷ እንደ ባሕር ቀጤማ ትውረገረግ ጀመር።

ይህ መንገደኛ በልጅቷ ውበትና እንቅስቃሴ ተደንቆ፣ በመፍዘዝ ሲመለከታት እንደ ቆየ፣ አንዳች ነገር ልቡን ነሸጠውና ዘሎ ዘፈኑ ውስጥ ሲገባ፣ ጭብጨባው ቀለጠ። ልጅቷም ልቧ ሞላ። ሁለቱም ገጠሙ። መንገደኛው እስክስታውን እየወረደ ያያታል፤ እሷ ግን ዓይኗን እያስለመለመች ትውረገረጋለች። እሱ ቀስ በቀስ እየፈዘዘ መጣ፤ መወዛወዙን አቆመና ባለበት ቆመ፤ ልጅቷ እስክስታ የገጠማትን ሰው ምት ዓይኗን ገልጣ ለማየት ስትሞክር ቆሟል። ትኩር ብላ ትመለከተችው።

ከዘፈኑ ከወጡ በኋላ ያኀቱን ሠርግ ረሳ፤ ማስተናገዱንም ተወው። ልጅቷ በሄደችበት ሁሉ የሚከተል ያሳደገችው ውሻ ሆነ። ሲነካት ስትሸሸው፣ ሲቆነጥጣት ስታመናጭቀው ቆዩ። እሱ ግን በማመናጨቋ የሚበረግግ አልሆነም። ይባስ ብሎ ሌሎችን ጐረምሶች እየገላመጠ ሲከታተላት እንደ ቆየ፣ ለሽንት ወጣ ስትል አብሮ ተከትሏት ወጣና ስትመለስ አድፍጦ ያዛት፤ ወዲያው ወደ ታዛው ይዟት ወደቀ። አንገራገረች በኋላ ግን...

ከዚች ወጣት ጋር ግንኙነታቸው በስርቆሽ ቀጥሎ እንደ ሰነባበቱ ወላጆቿ ለሁለተኛ ባል ዳሯት። ሲፈልግ፣ ሲያስፈላልግ ከርሞ፣ አንድ ቀን ድንገት ከቅዳሜ ገበያ ሲመለስ ተገናኙ። ያለፈውን ፍቅሯን ያውቃልና ገና ሲያያት ልቡ ሞላ፤ ናፍቆቱ አገረሸበት። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፤

«...እህሳ» ሲላት።

«አሁንማ የጀግና ሚስት ነኝ...የገዳይ ባለቤት» ብላ፣ በኩራት መንፈስ ፊት ነስታው ከሄደች ወዲህ እሱም፣ «ገዳይ መባል አለብኝ» ብሎ፣ ውሳኔውን አጠናከረ።

ረጅሙን ጉዟቸውን የጀመሩት በእግር ሲሆን፣ በመጀመሪያዎቹ የጉዞ ቀናት መንገዱ ተገፍቶላቸው ነበር። በኋላ ግን፣ ቀስ በቀስ ጉዟቸው የኤሊ ጉዞ ሆነ። ውኃ ጥሙ፣ ረሃቡ፣ ድካሙ ጥንዝል



t.me/OLDBOOKSPDF

ቢያደርጋቸውም፣ በተለይም ወይጦና ተልተሌ በረሃ ላይ ሲጓዙ አቅጣጫቸውን በመሳት በአዙሪት ኃይል ወደ መጡበት ሲመለሱ ከቆዩ በኋላ በአጋጣሚ በቅሎ ከጫኑ መንገደኞች ጋር ተገናኙ። ያጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ የሚሄዱበት አካባቢም አንድ በመሆኑ አንድ ላይ መጓዝ ጀመሩ።

ነጋዴዎች አቅጣጫ እንዳይጠፋባቸው በመኝታ ጊዜ እግራቸውን ወደ መጡበት፣ እራሳቸውን ወደሚሄዱበት አቅጣጫ ከማድረጋቸው ሌላ፣ አቅጣጫቸውንም ለማወቅ ባላ እየተከሉ ምልክት በማድረግ፣ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ባኮ ከተባለው ከተማ በሦስተኛ ወራቸው ደረሱ።

ባኮ ከደረሱ በኋላ፣ ለአውሬ አደን መምጣታቸውን በመግለጽ ከባህላዊ አሳዳኞች ጋር ተገናኙ። አሳዳኞች ሁለት ምንሽርና አንድ ቤልጅግ ጠመንጃ ያላቸው ሲሆን፣ መንገደኞቹም የተለያየ ቍጥር ያለው የምንሽርና የቤልጅግ ጥይቶችን ከመያዛቸው ባሻገር የማርትሬዛ ብር ይዘው ስለመጡ፣ ከአሳዳኞች ጋር በቀላሉ ተግባብተው ወደ በረሃ ወረዱ።

ምንም እንኳ ከማኅ ወንዝ ሲርቁ በውኃ እጦት ቢቸገሩም፣ አውሬ እያደኑ ጥብሱንም፣ ጥሬውንም፣ ቋንጣውንም፣ አልፎ አልፎም በሶውንም እየተመገቡ ችግሩን እየተቋቋሙ ቆዩ።

በመጨረሻም ባመጡት ጥይትና በተውሶ መሣሪያ እንደ ዕድላቸው ጎሽም፣ አንበሳም፣ አውራሪስም በመግደል ተጠባብቀው ለሁለት ወር ከሳምንት በረሃ ቆዩ።

ሁሉም ቀንቷቸው አውሬውን ከገደሉ በኋላ፣ የነገው የጀግንነት ገድል ታሪክ በየቀያቸው ሲያስተጋባ ወንዱ አንገቱን ሲደፋ፣ ሴቷ አይታቸው ስትሽኮረመም፣ ሽማግሎች ‹ጀግና ነው! ወንድ…› እያሉ ሲያወድሷቸው፣ ሚስቶቻቸው ከአካባቢው ሴቶች ልዕልና አግኝተው ሲያንጐራጕሩላቸው እየታያቸው፣ በደስታ እየሸለሉና እያቅራሩ የመልስ ጕዞ አደረጉ። ከዚያም፣ ካሳዳኞች ጋር የመለያያ ግብዣ አልጋ ከተባለው መንደር አቅራቢያ አደረጉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጨረሻም፣ መንገደኞች ከያዙት ጥይትና ማርትሬዛ ብር ከውላቸው ተጨማሪ ለአሳዳኞች ሸልመው፣ ተቃቅፈው በመሳሳም ተመራርቀው ተለያዩ።

አሳዳኞች ግን፣ የባኮን አቀበት ጉዞ እንደ ተያያዙ የጠጡት ሙጠጥ ለአደን የመጡት ሰዎች የያዙትን ጥይትና ብር እንዲያስታውሱና እንዲጐመጁ አደረጋቸው። መንገደኞቹ ከአልጋ መንደር ያስመጡትን የአበሻ አረቄ እየጠጡ ሲያቅራሩ ቆይተው በያሉበት በመጠጥ ኃይል ተዳከመው ሲተኙ፣ ሁለቱ አሳዳኞች ተዙስ ከፍተው ሰምንቱን ገደሏቸው። አንዱ ግን እንደ ነብር አጓርቶ፣ አንዱን አሳዳኝ ከነጠመንጃው በማነቅ ከመሬት ደባልቆ ጥይቱን በጆሮግንዱ ለቀቀበት። ከዚያም ከሁለተኛው ጋር እየተታኰሰ አባረረው።

ይሁን እንጂ፣ ከትንሽ ጊዜ በፊት አብረውት የነበሩት ሁሉ አልቀው፣ በዘጠኝ አስከሬን መከበቡን ሲያውቅ ፍርሃት አናወጠው። ሰማይ ምድሩ ዞረበት። «እየዩም ሲዳላ ነውና» እንባው ነጠፈ። ተስፋው ጨለመ፤ ጀግንነቱን ረሳው። የቀረው አማራጭ ምን እንደሆነ አያውቅም። ሙት መሃል ቢሆንም እሱም ከእንግዲህ ሙት ነው። ስለዚህ ዝም ብሎ ወደ ጫካው ሸሸ። ብርሃን ወዳላየው ጨለማ ገባ።

ብቸኛው መንገደኛ፣ የት እንደሚሄድ ቀርቶ የት እንዳለ እንኳ አያውቅም። ብቻ መጓዝ ሆነ፣ «ወደ መንዝስ እንግዲህ በምን አባቴ እሄዳለሁ? እንዴትስ ብዩ የዘመዶቼን ዓይን አያለሁ? ምንስ የጣቸው እላለሁ? ኸረ እኔንም ጅቡ ይብላኝ፤ ካለ ምስክር የቀረሁ ከንቱ ነኝ» እያለ፣ አቅሙ እስከቻለ ተጓዘ።

መንገደኛው በመጨረሻ ሲደከመው፣ «አይ ሞኝነቴ አሁን እንዲህ መልፋቴ ግን እንዲገለኝ ፈልጌ ይሆን? አውሬው በላኝ፣ ረሃብ ገደለኝ፣ ሰው ገደለኝ ሳልተርፍ ምን አስፈራኝ? እንዲያው እኮ ይገርማል፤ ያለሁበትንና የምሄድበትን አላውቅ፤ እና መሞቴን አረስቼ ለመኖር ምን አቃዠኝ፣ ያሻው ይገላግለኝ» ብሎ፣ መተኛቱን ያስታውሳል። ሲነቃ ግን፣ ጥቋቁር ጠብደሎች ከበውታል። መሣሪያ አንግተዋል። ጦር፣ ጨቤ፣ መጥረቢያ የያዙም ይታዩታል። አማትቦ መልሶ ዓይኑን ከደነ። ሰዎቹ ግን ጠቆም ጠቆም እያደረጉ እንዲነሣ



t.me/OLDBOOKSPDF

አደረጉት። ሁሉንም በየተራ አያቸው! እንኳን የሚያውቀው ሊኖር፣ የሚሉትም አልገባውም። በሐሳቡ፣ «እንግዲህ መሞቴ ላይቀር በምን እንግደልህ በመሣሪያ ነው፣ በጦር እያሉ እስኪጠይቁኝ ነው የምጠብቀው? ስታገላቸው እሞታለሁ» ብሎ ግብግብ ገጠመ። ትንሽ ታግሎ ቢያስቸግራቸውም፣ ከመሬት ደባልቀው ጉሮሮው ላይ መሣሪያ ደገኑበት። መንገደኛው፣ «ለካ የመጨረሻው ዕድሌ በጥይት መሞት ኖሯል!» ብሎ ዓይኖቹን ጨፈነ።

ሐመሮች መሣሪያና ጥይት ከምንም ነገር በላይ ይወዳሉ። ተኳሾችም ናቸው። በማንም ላይ ግን ቃታ በድንገት አይስቡም። የሚገድሉትን ሰው ማንነት ለይተው ማረጋገጥ አለባቸው።

የሚገድሉት «ቢታው» እንዲገድሉ የፈቀደላቸውን ነው። ቢታ ማለት ጥንት የነበረ ሲሆን፣ ሲወለድ በግራ ብብቱ ንብ፣ በቀኝ ብብቱ እበት ይዞ የተወለደና ከቦርጆ (አምላክ) ጋር ማኅበረሰቡን የሚያገናኝ ቅዱስ ሰው ነው፣ ብለው ስለሚያምኑ ቢታው ካወጣላቸው ደንብ ዝንፍ ሳይሉ ለዓመታት የኖሩ ናቸው።

እንግዳው የሙርሲ፣ የማሌ...ማኅበረሰብ አባል ቢሆን ኖሮ ቢታው እንዲገድሉ የፈቀደላቸው ስለሆነ ይገሉት ነበር። እንግዳው ግን የተለየ ነው። ስለዚህ ሳይገሉት ቀሩ። እንዲያውም የደከመ ሰውነቱን የከብት ደምና ወተት በማጠጣትና ፍየልና በግ በማረድ፣ ያን እየሰበቁ መረቁን እንዲጠጣና ሥጋውንም እንዲበላ በማድረጋቸው፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያገግም አደረጉት።

ከዚህ በኋላ ግን፣ ሐመሮች ከመንግሥት ወታደሮች ጋር ባደረጉት ጦርነት ለእነሱ አብሮ ተዋጋ። መዋጋትም ብቻ ሳይሆን፣ በሉ ስልት ከእልቂት አዳናቸው። ለዚህም ለፈጸመው ትብብር ከብት ዘሎ፣ ልጃገረዶች ተገርፈውለት ሚስት አገባ።

የዚህ እንግዳ ሰው ስም አንተነህ ይመር ይባል እንጂ ከብት ሲዘል መጀመሪያ እግሩ የረገጠበት ትንሽ ጥጃ ቀለሟን በማየት ጋልታምቤ ተባለ።

ጋልታምቤ ከሐመር ማኅበረሰብ አባል ከሆነችው ሚስቱ አንዲት ሴት ልጅ ወልዶ፣ ቋንቋውን፣ አለባበሱን፣ አመጋገቡን ተለማምዶ ደስ ብሎት የሚኖር ሰው ሆነ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጋልታምቤ ሃያ ዓመት ሙሉ ሐመር ውስጥ ሲኖር የተቸገረበት፣ የተለየበት አንዳችም ሁኔታ የለም። ከቋንቋው ልዩነት በስተቀርም ይህ ነው የሚባል የጎሳ ልዩነት እሱ ከሚያውቀው የተለየ የለም።

በሐመር ማኅበረሰብ ችግርን በሽማግሎች ምክክርና በማኅበረሰቡ ነፃ ውይይት መፍታት እንጂ፣ ችግርን በተናጠልና በኃይል መፍታት በኗሪዎች በሙሉ የተወገዘ ነው።

ተመካክሮ፣ ተከባብሮ፣ ተፈቃቅሮ፣ ደካማና ጠንካራው ካለሥጋት የሚኖርበት ማኅበረሰብ በመሆኑ እንግዳው ጋልታምቤ እንኳን እሱ ለልጅ ልጆቹም ከዚያ የተሻለ ዓለም አይመርጥላቸውም።

* * *

የሐመር ዕጽዋት ለምልመው፣ ንቦች ከአበባ ወደ አበባ እየተዘዋወሩና እየዘመሩ ሲቀስሙ፣ ከብቶች ጨሌ ሳራቸውን እያመነዠኩ ሲያገሱ፣ እንቦሶች ቃጭላቸውን እያቅጨለጨሉ ሲቦርቁ፣ ልጃገረዶችም ማሳውን እያረሱ ሲያዜሙ፣ ልጆች እራቁታቸውን ሆነው በቀስት ጫካ ለጫካ ተሪ ለመግደል ሲሯሯጡ በሚውሉበት፣ ጐረምሶች ሹልሹላ፣ ሹርባ...ጸጕራቸውን እየተሠሩ «አኖ» በተባለው አፈር ሰውነታቸውን በማሸርጐርጐር ለማታው ጭፈራና ድሪያ ሲዘጋጁ፣ የብልታቸውን ጸጕር እየተላጩ በመኸር ጊዜ የሚዘፍኑትን ዘፈን ሲያዜሙ በሚውሉበትና ሐመር የከቱን የተፈጥሮ ሕይወት ለብሳ ኗሪዎቿን በምታስፈነጥዝበት ወቅት ድንገተኛ ሁኔታ ታየ።

ካርለት አልፈርድ ሰቀላ ቤት አሠርታ መኖር ከጀመረች ዘጠኝ ወር አለፋት። ከሷ በስተግራ ከሃያ ሜትር ላይ የከሎ ከብ ጎጆ አለ። በግቢያቸው የዱር አበባ፣ ቦዬ፣ ጉደሬ በቅሏል። ከነሱ ግቢ ራቅ ብሎ አለፍ አለፍ በማለት የሐመሮች መኖሪያ ይታያል። ካርለት ቤቷ ሆና ፀሐይ ስትወጣ ከፊት ለፊት፣ ስትገባ ደግሞ ከበስተኋላ ሆና ልታያት ትችላለች።

በእርግጥ በፖስት ካርድ ፀሐይ ስትወጣና ስትገባ አስደናቂ ፎቶዎችን ተመልክታለች። ሕይወት ያላት የሐመሯ ፀሐይ ግን ምሽት



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ በተለያዩ ቀለማት ተውባ እንደ ዕንቁ እያንፀባረቀች አካባቢውን ቀይ፣ ቢጫ፣ ሐምራዊ ድብልቅልቅ ቀለማትን ስትለዋውጥ ስታያት ግን በሕይወቷ ካየችው ውብ ነገር ይልቅ፣ በሐሳቧ የቀረፀችው የገነት ውበት ይታያታል።

ታዲያ፣ በጣም ተመስጣ የአካባቢውን ውበት ስትመለከት፣ ውበትን በትክክል ለማስቀመጥ፣ መጨመር የምትፈልገውንም ጨምራ ለመርካት፣ ከአንትሮፖሎጂስትነቷ ይልቅ ባለቅኔ ወይንም ሠዓሊ መሆን ያምራታል።

ካርለት ያጣችው ነገር የለም አይባልም። የዋና ቦታ አላገኘችም፤ ኑሮዋ ዘመናዊ አይደለም። ያም ሆኖ ግን በሚያውዳት የተፈጥሮ መዓዛ፣ በስሜት በምትውረገረገው የምሽት ጭፈራ፣ ባየችውና በቀረበችው ቊጥር ጥልቅ እሳቤን የሚጠይቃት የተፈጥሮ ምሥጢር፣ በንጹሕ ሕሊና የምታነባቸው መጻሕፍት የደስታ ሚዛኗን ይጠብቁላታል።

አሸጋግራ የምታየው የሐመር ሰንሰለታማ ተራራ፣ መሸት ሲል ከየዋሉበት ብቅ ብቅ የሚሉት ሰዎችና እንስሳት፣ ስታንቀላፉ የዋለችው መንደር፣ ሞቅ ሞቅ ደመቅ ስትል፣ ሁሉም ከፀሐይ ውበት ጋር ውሕደት፣ ቅንብር ሲፈጥሩ ስሜቷ ይረካል። እንዲያውም ከዚህ ለየት ላለ ያልተበረዘ ተፈጥሮ ያላት ፍቅር፣ «ምነው እናቴ፣ ወንድሜ፣ እኅቴና ስቲቭ ይህን ባዩ» ብላ፣ ቅን ሐሳብ እንድታልም ያደርጋታል።

አንድ ቀን ግን፣ የተለመደ ትርዒቷን ስትመለከት፣ በግምት የአሥራ አምስት ዓመት ልጃገረድ፣ ከጥቁር ፍየል ለፍቶ የተሠራውን ቆዳ ዙሪያዋን በነሐስና ጨሌ አስጊጣ ለብሳ፣ አንገቷ ላይ በደረ ደረችው ጨሌ ራሷን አሰማምራ፣ ዳሌዋንና ቀጥ ብለው ግጥም ያሉ ማራኪ የእግር ቅርፅዋን ስታይ ካርለት አፏን በአድናቆት ከፈተች።

«በእርግጥ በጣም ቆንጆና ለየት ያለች ነች፤ መቼም አይቻት እንደማላውቅ እርግጠኛ ነኝ» እያለች በባለ ሌንሱ ካሜራዋ ደጋግማ ከርቀት አነሣቻት። ልጃገረዷ ካለምንም ሥጋት ወደ ካርለት ሰቀላ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀርባ ሰላም ብላ ክርስትን ቆም ብላ ካየቻት በኋላ ጸጉሯን በጣቶቿ እሷም በተራዋ እየነካካች አድናቆቷን በግልጽ ገልጣ ልትሄድ ስትል ክርስት፤ «ወይ አምላኬ፤ አምላኬ! ኧረ ጥርሶቿስ እንዴት ያምራሉ!» አለችና እንድትቀመጥ ጋበዘቻት። ልጃገረዷ ግን፤ የክርስትን የቤት ውስጥ ሁኔታ አንገቷን አስገብታ ቃኝታ በድጋሚ ፈገግ ብላ፤ «ደህና ሁኚልኝ» ብላ ሄደች።

ከሎ ሆራ የሐመሯን ውብ ቀደም አድርጎ ይመለከታት ነበርና ውበቷ ደንቆታል። በተለይ ወደ እሱ ቤት አቅጣጫ ስትመጣ ልቡ መዝለል፤ ሐሳቡ መተረማመሱን ጨመረ። ከሎ ሆራ እስከ ዛሬ ታይቶበት የማያውቅ መርበትበትና ድንጋጤ ታየበት።

ልጃገረዷ፤ «ደህና ዋልህ» ብላው፤ ከተከፈተው የጎጆ ቤት መስኮት ላይ ተንጠልጥላ ስታይ እግሮቿ፤ ጭኗ፤ ዳሌዋና የሚሳበው ወገቧ ከሎን በሲቃ አፈኑት። ልጃገረዷ፤ የሚተኛበትን መኝታና ዕቃዎቹን ተመልክታ ስትወጣ የሱም ልብ አብሮ ተከተላት።

እሷ እንደምታውቀው በማንኛውም የሐመር ቤት የሚገኝ ለመተኛ ቁርበት፤ ለመመገቢያና ለመጠጫ ቾርቃ (ከቅል የተሠራ) እንስራ (ለሸፈሮ ቡና ማፍያ) ነው። ከነጪ ቤትና እንደ ሐመሮች መልክ ያለውና ጨርቅ ለባሹ ቤት ግን አይታው የማታውቀው ዕቃ አለ። በኮተቱ ብዛት ትገረም እንጂ አልተደነቀችም። እንዲያውም ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑት ቁርበት፤ ቾርቃ፤ እንስራ ቤታቸው ውስጥ ባለመኖሩ ተደንቃለች።

ከሎ ቤቱ በር ፊት ለፊት ሆኖ ጠበቃት። በሐመር ባህል ደንብ ልጃገረድ ክቡር ናት፤ ካለፍላጎቷና ሳያገባባ መታገል የውርደት ውርደትና ነውር ነው። ልጃገረድ እንደሚሰበር ዕቃ የሚጠነቀቁላት፤ እንደ ሕፃን ልጅ ፍላጎቷን የሚያከብሩላት መሆን ይገባል።

ልጃገረድ የምትፈልገውን ወንድ ቀጠሮ ትሰጠዋለች። ያውም ከተመቻት ነው። ካለበለዚያ፤ ካለ እሷ ትብብር አፈቀርኩ፤ ወደ ድኩ፤ በዚህ ወጥቶ በዚያ ወርዶ፤ ምን ሲባል ያን አይተሽ፤ እያሉ መጓዘዝ በባህሉ አይታወቅም።


t.me/OLDBOOKSPDF

በሐመር ማኅበረሰብ ልጃገረድ ቀሳሚ ንብ፣ ወንዶች አበባ ናቸው። ባል ካገባች በኋላ ግን ሴት የባል ዕቃና ንብረት ናት።

ስለዚህ ልጃገረዷ ካለፍላጎቷ የሚደርስባት ችግር እንደሌለ ስለምታውቅ ከሎን አልፈራችውም። ከሎ ሆራ ግን ድንገት «እጅ ወደ ላይ» እንደተባለ ሰው ደንዝዟል። ካርለት የሁለቱን ሁኔታ ከርቀት በጉጉት ትመለከታለች። ልጃገረዷ ሰላምታ አቅርባለት መንገዷን ስትቀጥል፣ ከሎ በባህሉ ኰራ ብሎ መታየት ሲገባው ተርበተበተ።

ሰንበት ብሎ ሲያስበው ራሱን ቢታዘብም በሕይወቱ በጣም አደገኛ ወጥመድ ላይ የወደቀበት ጊዜ ያ መሆኑን ራሱ ለራሱ አመነ። ልጃገረዷ ግን ዳግመኛ ወደ መንደሩ አልተመለሰችም።

ሆኖም ከሎ፣ «ከየትኛው መንደር ይሆን የመጣችው? እጮኛ አላት ይሆን?» እያለ፣ በሐሳቡ መዋለሉ አልቀረም።

* * *

«...የሐመር ወንዶች ቢያፈቅሩም ፍቅራቸውን በግልጽ ማሳየት ነውር ነው። ቢሆንም ልጃገረድን መዳራት ነውርነት የለውም» ብሎ፣ ከሎ የነገራትን ካረለት አስታወሰች።

ከሎ ሲቆዝምና ሐሳብ ሲያበዛ፣ ካርለት በፍቅር ሰመመን መዋጡን በመረዳቷ፥ «ከሎ ያችን ልጃገረድ እውን አፍቅሮ ይሆን? ፍቅሩንስ በምን መልክ ይገልጽ ይሆን? ባህላዊውን ወይስ ዘመን አመጣሹን ይሆን የሚጠቀመው? ኧረ ኅብረተሰቡስ ምን ይሰማው ይሆን?» በማለት፣ ካርለት በጥንቃቄና በተመስጦ ማሰቧን ቀጠለች።

«ምን ዓይነት ድንቅ ነገር ነው!» ሁሉም ነገር ምሥጢር ሆኖባት ተገረመች። ስሜት ረቂቅ ነው! አይጨበጥም። ስሜት በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ ቢኖረውም፣ አካባቢም በስሜት ላይ ጫናው ከባድ ነው። ማፍቀርና መፈቀር ተፈጥሯዊ ነውና ማንም ከዚህ ስበት ሊያመልጥ አይችልም። ችግሩ ከፍቅር ቀጥሎ ግንኙነቱ በምን መልክ መሆን



t.me/OLDBOOKSPDF

ይናርበታል ነው። እኒህ ሁለት ሥረ–ግንዳቸው አንድ የሆኑ፣ አካባቢያቸው ግን ለውጥ ያለው ሰዎች እውነት እንዳሰቡት ቢፋቀሩስ?»

አዲሱን ምርምሯን በተለያዩ መንገዶች ተጠቅማ ማወቅ ይናርባታል። «ከሎ ከልጃገረዷ ጋር ፍቅር ቢይዘው ልብስ በመልበሱ ልትንቀው ትችል ይሆን? አውሬ ወይንም የጎሳው ጠላት የሆነውን ሰው አልገደለም፤ ክብት የለውም። ስለዚህ ዘመናዊዋም ሆነች ቆዳ ለባሿ ሴት ክብርና ዝናን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ፈላጊ ስለሆነች ላትቀርበው ትችላለች።»

«ከሎም ቢሆን ልጃገረዷን ለማግባት ኡክሊ ሆኖ በየዘመዶቹ መዞር፣ ከብት መዝለልና ለኮይታ (ጥሎሽ) የሚሰጠው ከብት፣ ፍየል፣ በግና ማር ማግኘት አለበት።

«ደግሞ ከሎ ትምህርቱን ጨርሶ በዘመናዊ ሥራ መሰማራት ይፈልግ ይሆናል። እንደዚያ ካሰበ ደግሞ ቢያፈቅራት እንኳን ስሜቱን ማዳፈን መቻል አለበት ማለት ነው። ምን የጨነቀ ነገር ነው።

«ከሎ እንዳጫወተኝና እኔም እንዳረጋገጥኩት፣ ራሱ ከሎ ሚንጊ ተብሎ የተጣለ፣ ከሐመር ማኅበረሰብ የተወገደ ነው። በእርግጥ፣ የተጣለ ሳይሞት አድጎ ወደ ማኅበረሰቡ ቢመለስ ችግር አያመጣም። ወደ ማኅበረሰቡ ለመመለስ ግን ደንብ ተሠርቶ በሥነ–ሥርዓቱ መሆን አለበት። እሱ ደግሞ ሥነ–ሥርዓቱን አላሟላም።

«አጣብቂኝ ይሏል ይህ ነው። ፍቅርና ችግር–ችግርና ፍቅር የበዛበት ሕይወትስ ሳንካ መቼ አጥቶት ያውቃል?» እሷ ግን የሁለቱ ግንኙነት ቢጠናከር ነፍሷ ነው። የወንድን ፍቅርና ጋብቻ በሱ፤ የሴቷን ደግሞ በሷ ለማረጋገጥ ከቻለች ተልዕኮዋ ተሳክቶ ወደ አሰበችበት እርከን እንደምትደርስ ተስፋ አድርጋለች።

ከሎም በበኩሉ፣ ቀንና ሌሊት በድንገተኛ ገጠመኙ እንዳለመ ነው። በውኑም ሆነ በሕልሙ ሲያለቅስና ሲደሰት ማሳለፍ ልማዱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኗል። የተጫረው የፍቅር እሳት ብርሃን ሕሊናውን ማፍካቱን አሊ ማለቱን አይፈልግም። የተፈጠረው ፍቅር ቢያስጐመዠውም፣ እንደ ደሴት ዙሪያውን የከበበውን ችግር ግን ዋኝቶ ሊዘልቀው አልቻለም።

«ይቅርብኝ መቻል አለብኝ፤ ራሴን በድንገተኛ የፍቅር እሳት እንጫርሬ ስሥቃይ መኖር አልፈልግም፤ ጸጸቱም ሰው አያረገኝም» በማለት፣ ከራሱ ጋር ይማከራል። በሌላ ጎኑም ዙሩ አካሄዱ፣ ከብና የደስ ደስ ያለው ፊቷ፣ ግጥም ብለው የሚያንፀባርቁት እግሮቿና ኩራ ያለው ዳሌዋ በተለይ ፈገግታዋና ዓይኖቿ በዓይነ ሕሊናው ሲታየው ተመልሶ ወደ አዲሱ የፍቅር ማጥ ይንከራል።

«የራስህ ጉዳይ! ገና ያን ሁሉ የባህል ደንብ ፈጽመህ፤ ራቁትህን ዞረህ...በልኮ አትጃጃል! ራስህን መለወጥ፣ ማሻሻል ሲገባህ ውጤቱን ልታየው የተቃረብከውን አዲስ ሕይወት ይበልጥ ወደ ላይ በመሳብ ማየት ሲኖርብህ እንዴት ወደ ታች ለመንሸራተት ታስባለህ፣ ጅላ ጅል» እያለ ሕሊናው በወቀሳ ያራውጠዋል።

«እኔኮ የማይገባኝ በገንዘብ የሚገዛ ሕይወት ለኔ ምኑ ነው? የናት አባቴ ባህልና ደንብ ባላድግበትም የተወለድሁበት ነው። ሕይወትን እንደ ሸቀጥ ለመግዛት ብር ፍለጋ እስከ ዛሬ የለፋሁትስ መቼ አነሰኝ» በማለት ሊፈላሰፍም ይቃጣል። ወጣም ወረደ ግን ተቃራኒ ሐሳቦቹ የሱ የራሱ ቢሆኑም ሁለቱም ያሳምኑታል፤ በአንድ በኩል ደህና ነገር አሰብኩ ሲል በሌላ በኩል የመጣው ያኛውን እውነትነቱን ያደበዝዘበታል፤ ከሎ ዳኛ አልባ በሆነና ድንግዝግዝ ባለ ተመጣጣኝ ሐሳብ ተወጠረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 9

ከሻንቆና ከላላ የተሰባሰቡት ሽማግሎች በደልቲ ገልዲና በካርለት ጋብቻ ላይ ሸንጎ ከመቀመጣቸው በፊት በኅብረተሰቡ አጋጣሚ ላይ ትንበያ መስጠት ይችላሉ የተባሉት፣ «ጫማ ጣዮች» ደጋግመው ጫማ በመጣል ጋብቻው ስለ መሥመሩ አስተያየታቸውን ሰጡ።

ከጫማ ጣዮቹ ቀጥሎ ደግሞ ፍየል ታርዶ «ለአንጀት አይታዎች» ቀርቦ ጋብቻውን በተመለከተ እነሱም አስተያየት እንዲሰጡ ተጠየቁ። እነሱም ተጋቢዎቹ ልጅ ስለ መውለድ አለመውለዳቸው ሊታያቸው ባለመቻሉ ሦስት ፍየል ከታረደ በኋላ፣ «ጋብቻው ቀና ነው» በሚል ብቻ አድበስብሰው ተውት።

በእርግጥ፣ ይህ ጉዳይ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ያወያየ ሲሆን፣ በተለይም በሽማግሎቹ ዘንድ ጋብቻውን በመጠራጠር በቀጠሮ በተለያየ ጊዜያት ለመወያየት አስቻላቸው።

ካርለት አንጀት አይታዎች በሰጡት አስተያየት መደናገጧና መደነቋ አልቀረም። በሐመር ማኅበረሰብ መካን ሴት ፈላጊ እንደ ሌላት ታውቃለች። አንድ ሴት ለአባቷ ጥሎሽ ተከፍሎ ባሏ ዘንድ ከሄደች በኋላ ልጅ ሳትወልድ ብትቀር ባሏ እሷን መልሶ ታናሿን፣ ካለበለዚያም ቅርብ ዘመዷን ያገባል። ያም ሆኖ ካልተሳካለት፣ ልጅ መውለድ ካልቻለች ላባቷ የከፈለውን ጥሎሽ ያስመልሳል። ሴቷም፣ «መካን የሆነችው በውኃ ብልቷን ታጥባ ይሆናል» ተብላ ትጠረጠራለች። መካን ሴት የተገኘችበት ቤተሰብም እንደ መጥፎ ቤተሰብ ስለሚቈጠር ጋብቻ የሚፈልገው ሁሉ ይሸሻል። ይህ ደግሞ አባት በልጆቹ ጥሎሽ ያገኘው የነበረውን ከብት፣ ፍየል፣ በግ፣ ማር ያስቀርበታል። ከዚያም ተጨማሪ፣ ምናልባት አባትየው ሦስት ሴት ልጆች ቢኖሩት የመጀመሪያ ልጁን ጥሎሽ ተቀብሎ ቢድርና መካን



t.me/OLDBOOKSPDF

ብትሆን ሁለተኛዋን፣ ሁለተኛዋም መካን ከሆነች ሦስተኛዋን፣ ሦስተኛዋ መካን ከሆነች የዘመድ ልጅ...በመስጠት ምክሮ ካልተቻለ ግን የተቀበለውን ጥሎሽ ይመልሳል።

«ስለዚህ አንደኛ ነገር እኔ በውኃ ስተጣጠብ ስለሚያዩ መካን ትሆናለች የሚል ግምት መጀመሪያውንም ነበራቸው። ሁለተኛ ደግሞ አንጀት አይታዎችና ጫማ ጣይዎች ልጅ ልወልድ አለመቻሌን ለማኅበረሰቡ አስታውቀዋል። ሌላው ግን የኔው የራሴ ጉዳይ ነው። ለጥንቃቄ እንዳላረግዝ የሕክምና መከላከያ አለኝ። ስለዚህ ልወልድ አለመቻሌን አውቀዋለሁ። እነሱም ባለመውለዴ እጅግ በጣም አምነዋል። ግንኮ እንዴት? የፍየል አንጀት ከኔ ጋር ምን አገናኘው?» ካርለት፣ ራሷ ለራሷ ሐሳቧን አካፍላ ራሷን ጠየቀች።

ካርለት በእውነቱ ከሆነ ጥሎሽ ከደልቲ ገልዲ ማግኘት አትሻም። ጥሎሽ አያስፈልግም ብትል ግን የሱ የግል ንብረትነቷ ማረጋገጫ አጣ ማለት ነው። ጋብቻው ከዚህ ሁሉ ቢቀርስ እንዳይባል ደግሞ እሷ ባህላዊ ግድቡን ጥሳ ጥናቷን ለማካሄድ፣ ደልቲ ደግሞ ባለጌዋን እንግዳ የራሱ አድርጎ በግርፋት ሥነ–ሥርዓትን ሊያስተምራት ቈርጧል።

በግልና በተናጠል የላላና ሻንቆ ኗሪ ሲመክርና ለሽማግሎቹ የመሰለውን አስተያየት ሲሰጥ ሰንብቶ፣ በመጨረሻ ሽማግሎቹ በጥልቅ ከተመካከሩ በኋላ:-

«እንግዳዋ ምንም እንኳ በመልክና በቋንቋዋ ከእኛ ብትለይም የቦርጆ (የአምላካችን) ፍጡር ናት። እኛን ብላ፣ እኛን መርጣ መጣች እንጂ ግሌ፣ በና፣ ዳሳነች፣ ሙርሲ...ምድር ልትሄድ ይቻላት ነበር። በእውነት ከሆነ ብልግናዋ የበዛ ነው። ይህ ደግሞ የሷ ስሕተት ሳይሆን፣ ያባቷ ስሕተት ነው» ብለው ጋብቻውን ለመቀበል ወሰኑ።

በመቀጠልም፣ «ይህች እንግዳ አባቷ በቅርብ ባለመኖሩ ደልቲ ገልዲ የሚከፍለውን ጥሎሽ የሚቀበል አባትና ጥሎሹን የሚወስን ሰው የላትም። ስለዚህ እሷ የፈለገችውን ሰው በአባትነት ትምረጥ። ከእንግዲህ በኋላ የምትለብሰው፣ ጠረኗ እንደ ሐመር ልጃገረዶች


t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሆነና እስከ አሁን የፈጸመችውን ስሕተት እሷም ራሷ ስለምታውቅ ለወደፊት የፍየል ቆዳ ለፍቶና ተሰፍቶ እንድትለብስ፣ በወሉና አንባር በማጌጥም ጸጉሯን አጠር አድርጋ አስቈርጣ ሹርባ እንድትሠራና በእግሯ እንድትሄድ» ብለው ተስማሙ።

«ባባቷ በባንኪ ሞሮ ደንብ መሠረትም ጥሩ ሴት ለመባል አባት ብላ ለምትመርጠው ወንድ ልጅ ወይም በዘመዱ ወንድ ልጅ የከብት ዝላይ ወቅት በባራዛ አርጩሜ ዱላ ቻይ መሆኗን ለማስመስከር ለትሸማቀቅ ፀንጋዞች (ባዕዳን) በሚባሉት ጒረምሶች እንድትገረፍና በጀርባዋ ላይ የሚቀረው የግርፋት ምልክት ለሽማግሌዎችና ለአካ ባቢው ሰው እንዲታይ በግልጽ እንድትተወውና እንድታጌጥበት» ተባብለው ተማመኑ።

ከሎ ሆራ የሽማግሌዎችን ሁኔታና አጠቃላይ ውሳኔያቸውን ለካርለት ሲነግራት ጥርሷ እስኪፋጭ ድረስ ተንቀጠቀጠች። መናገር ተሳናት። በእውነቱ ለተመለከታት የማንኛውንም ሰው አንጀት የምትበላ ሲሆን፣ በሌላ በኩልም ጋብቻ ለመፈጸም ማሰቧ የግብዝነት ተግባር ነው ሊያሰኝ የሚችል ነበር።

ካርለት ከከሎ ተለይታ ሰቀላዋ ውስጥ ገብታ ምን እያደረገችና ወደፊትስ ምን ሊያጋጥማት እንደሚችል ስታስብ፣ እንባዋ እየተንፎለፎለ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ከዚህ ቀደም የኖረችበት ዓለም እውነት አሁን ባለችበት መሬት ላይ ሳይሆን ከሌላ ፈለክ (ፕላኔት) የመጣች እንግዳ ፍጡር የሆነች መሰላት። ሽማግሌዎቹ ካቀረቡላት ቅድመ ሁኔታና ባህላዊ የውጣ ውረድ ጒዞ ይልቅ በትንሿ የመርፌ ቀዳዳ ሾልኮ ማለፍ እንደሚሻል ገመተች።

እሷ የምታውቀው ሕይወትና አሁን ያለችበት ዓለም የሰማይና የምድር ያህል ይራራቃል ተብሎ በርቀት ልዩነት ብቻ የሚለካ ሳይሆን፣ ፈጽሞ ሊተያይ የማይችል ሆድና ጀርባ ሆነባት።

ግርፊያ...ቆዳ መልበስ...በባዶ እግር መሄድ...አለመታጠብ ልት ረዳው፣ ልታምነው፣ ልትሰማው የማትፈልገው ጒዳይ ነው። ስለሆነም ይህን ፈጽሚ ማለት፣ በሷ ላይ ትልቅ ችግር መፍጠር ብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይሆን ይቅር የማይባል ግፍ እንደ መፈጸም ያክል ነው። አባባሉን፣ እንኳን በተግባር በቃል ልትሰማው ከበዳት።

ታላቁ የሴቶች እንቅስቃሴ ለመላው አውሮፓ ሴቶች ያጎናጸፈው መብት ብናኙ እንኳን ወደማይገኝበት መጥቃ መገኘቷ፣ ከመላ ሴቶች ጎን ተነጥላ ወደ ዘንዶ አፍ የመወርወር ያህል ሆኖ ተሰማት።

ስለዚህ ለምን ወደዚህ ጣጣ ራሷን እንደዶለች ማሰላሰል ጀመረች። ካርለት ፍዝዝ፣ ትክዝ እያለች ቀስ በቀስ አንገቷን ወደ ሰማይ በማስገግ ወደ አውሮፓ በሐሳብ ተጓዘች።

እናቷ ሚስስ አልፈርድ፣ ታናሽ እኅቷ ሴሻ አጠገቧ ቢኖሩላት ኖሮ ጭንቀቷን ገልጻላቸው ተያይዘው ያለቅሱ ነበር። ግን ምንስ ብላ ልትገልጽላቸው ነው?

«እኔ እራሴ እንኳ ሁኔታዎች ከቍጥጥሬ ውጭ ሆነውብኝ መላ ብዩ የፈጠርኩት እንጂ እነሱማ መጀመሪያውንስ እንዴት ሊረዱኝ ይችላሉ? እናቴና እኅቴ እንዳፈቅር ገፋፍተውኛል። ለታናሽ እኅቴም የግብረ–ሥጋ ግንኙነት ምን ዓይነት የደስታ ስሜት እንደሚፈጥር የነገርኳት እኔ ነኝ። ጋብቻ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ከባድ ነገር መሆኑን እንደሆነ የእንግሊዝ አገር ወጣት በየትምህርት ቤቱ፣ በቲያትርና ሲኒማው የሚያውቀው የአደባባይ ምሥጢር ነው።

«የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፍቅር ዋነኛው ቅመም ቢሆንም በራሱ ግን ፍቅር አይሆንም። ያልተፈለፈለ፣ እዶሮ እቅፍ ውስጥ ያለ እን ቍላል እንደ ማለት ነው። እንቍላሉ ነፍስ ሆኖ ከመፈጠሩ በፊት እን ስቷ ዶሮና አውራው መገናኘት አለባቸው። የሰዎች ግንኙነት ደግሞ ከዚህ በላይ ነው። በሐሳብ መጣጣምና መግባባት ያስፈልጋቸዋል።

«የደልቲ ገልዲ ጥንካሬው ከግንኙነቱ ላይ ነው። እንደ እንግሊዝ አገር ወንዶች ሳይልፈሰፈስ በጥንካሬ ጀምሮ በጥንካሬ ይጨርሳል። ሆኖም ግን ያ ብቻውን ለእኔ በቂ አይደለም። ልዘረዝረው የማልፈ ልገው ሚሊዮን ፍላጎት ይቀርብኛል። የሕፃንነት ዘመኔ በመፈጸሙ በአሻንጉሊት ልረካ የምችልበት ጊዜ አልፏል። ሦስት እግር የሌለው በሬ በአንድ ጠንካራ እግር ብቻ መንቀሳቀስ አይችልም። ስለዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔም ወደማላውቀው የሕይወት አዘቅት ውስጥ መግባት የለብኝም። እስከምችለው ጥናቴን ለማከናወን እጥራለሁ። ከአቅሜ በላይ የሆነውን ደግሞ መተው እንጂ ከአቅሜ በላይ ወደሆነ ችግር ከተዘፈቅሁ፤ ከገባሁበት ተመልሼ መውጣት ይሳነኝና በዚያው እቀራለሁ። ለእኔ ደግሞ ይህ የሞት ሞቴ ነው።» ካርለት ድርጊቷን አማረረች።

«አንድ አንትሮፖሎጂስት ጥናቱን ለማከናወን የባህል ለውጦችን፤ ችግሮችን የመቋቋም ኃይል ሊኖረው ይገባል። ወደ ጥናቱ መስክ የተሰማራ ባለሙያ ከማንኛውም ነገር ሁሉ በላይ መወሰን የሚችል መሆን አለበት። የዘወትር እምነቱም «ሊሆን የማይችል ነገር የለም» የሚለውን ከልብ መቀበል ነው። ከዚያ በኋላ ልምዱንና ፍላጎቱን በማረቅ ሊያጠናው የፈለገውን መስሎ ሳይሆን፤ ሆኖ መኖርን የማወቅ ክህሎት ሊኖረው ይገባል።» ከአባቷና ከሌሎችም ምሑራን የሰማችውን አስታወሰች።

የአንድ አንትሮፖሎጂስት ጥናት ጠዋት ተጀምሮ ቀትር ላይ የሚጠናቀቅ ሳይሆን፤ የረጅም ጊዜ ልፋትን፤ ችግርን፤ ሥቃይን የሚጠይቅ አቀበት ቁልቁለት የሚያስኬድ፤ በአዞ ጀርባ የሚያስ ከባልል፤ በመርፌ ቀዳዳ የሚያሾልክ፤ አልፎም እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት የሚከፈልበት ሙያ ነው።

ጥናታቸውን ከግብ ለማድረስ ስንቶች የሕይወት መሥዋዕትነት የከፈሉለት፤ የእባብ አንገት እስከ መጨበጥ፤ ከጎሪላ ጋር እስከ መጎዳኘት፤ ጭው ባለ በረሃ እስከ መኖር፤ አካለ ስንኩል እስከ መሆን ድረስ የበቁበት ሙያ ነው። ካርለትም ሁለት መንገድ ቀርቦላታል። ጥናትን ማካሄድ ወይንም መተው። ጥናቷን ከተወች በሕይወቷ ሊመለስ የማይችል ሽንፈት በፍላጎቷ መቀበሏ ነው። ከዚህ በኋላ ስለ እነሱ ማውራት እንጂ እሷ የተናቀች፤ የተዋረደች መሆኗ ነው። ስለ እነሱ እያወሩ ኖሮ ማለፍ ደግሞ ትልቁ የሞት ሞት መሆኑን ታምናለች።

ጥናቷን ለመቀጠል ካሰበች ደግሞ ለዓላማዋ ስኬታማነት የሚቀርቡላትን ጥያቄዎች መመለስ፤ ችግሮችንም መፍታት አለባት። የሐመርን ባህል ጥሳ ገብታ፤ ድብቁን፤ ሽሽጉን ሕይወት ገሐድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማውጣትና ሴቶች ከወንዶች፣ ማኅበረሰብ ከቤተሰብ ጋር ያላቸውን ቀረቤታና የነሱን ሚና ሕሊናዋ በሚቀበለው እውነታ ለዐሐይ ለማብቃት ፆታዋ የፈጠረባትን ገደል ድልድይ ሠርታ መድረስ አለባት።

ለዚህ ችግር መፍትሔው ደግሞ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ ራሷን ለመሥዋዕትነት መሠዊያው ላይ ማጋደም መቻል አለባት። ይህም ብቻ ነው ሁለተኛው ዕድሏ።

«ይሆናል ያልተባሉት ነገሮች ሆነው የሰው ልጆችን እርካታ አጕናጽፈዋል። እንደ «አይቻልም» በዚህ ዓለም ላይ የቀለለ መልስ የለም። እኔስ ይቻላል አስቤ ለምን በአይቻልም እሳቤ ተሸናፊ እሆናለሁ። እውነትስ ሰው ሊሆነውና ሊፈጽመው የማይችል ነገር ምን ሊኖር ይችላል? እኔ መበርታት ያለብኝ መሞከሩ ላይ ነው። በፍላጎቴ ወደ አድካሚው ውድድር ከገባሁ በአሸንፋለሁ ባይነት መወዳደር ይጠበቅብኛል። የዘወትር እምነቴም ይኸው ነው። ስለዚህ ቆዳ ለመልበስ፣ በእግር ለመሄድ፣ ለመገረፍ ዝግጁ መሆን አለብኝ» ብላ፣ ከራሷ ጋር ቃል ኪዳን ገባች።

*　　*　　*

ከሎ ሆራ ልቡን የሰረቀችውን የሐመር ውብ ለማግኘት ብዙ መድከሙ አልቀረም። ካርለትም ብትሆን የሐሳቡን መናወጥ ስላጤነችና ለጥናቷም እገዛ ይኖረዋል ከሚል እምነት በመነሣት ያችን ውብ ኮረዳ ማፈላለጉ ላይ አልሰነፈችም። ሻንቆና ላላ መንደር አለመኖሯን ግን ሁለቱም በየፊናቸው አረጋግጠዋል።

እንደ ተለመደው ከሎ ሆራና ካረለት በየመንደሩ በመዞር ጥናትን ለማጠናከር ሲንቀሳቀሱ፣ ከዲመካ ከተማ ወደ አምስት ኪሎ ሚትር እራቅ ብላ ከምትገኘው ኮረብታማ መንደር ወሮ ሄዱ። ከዚያ እንደ ደረሱ ወንዶች ወደ ወንዝ፣ ሴቶችም እርሻና ማሳ ጥበቃ ሄደው ስለነበር፣ መንደሯ ውስጥ ያገኙት የሚያላዝኑ ውሾችንና አሮጊቶችን ብቻ ነበር። መሸትሸት ሲል ግን ከብትና ኗሪው ከየውሎው ወደ መንደሯ መጠረቃቀም ጀመረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ትዕይንት ለካርለት እንግዳ አልነበረምና ከመንደሯ ወጣ ብለው የአካባቢውን ውበት ሲቃኙ፣ ከሎ ደንገጥ ብሎ ዓይኑን ወደ አንድ አቅጣጫ ደገነ። እንዴት ልጃገረድ ስታርስበት የዋለችበትን ምፈርና ቀንበር ከበሬዎች ጫንቃ ስታላቅቅ፣ ከበስተኋላ ተመለከቱ። አገሮቿ ግጥም፣ ዳሌዎቿ ኮራ ከወገቧ ሰርጎድ ያለችውን ኮረዳ ሁለቱም ከበስተኋላዋ በማየት ብቻ ማንነቷን አወቁ። ልጅቷ በሬዎቹን ፈትታ ዘወር ስትል፣ ሁለቱም ዓይናቸው እሷ ላይ ነው። ኮረዳዋ እንዳችም የመደነጋገር ሁኔታ ሳታሳይ ፈገግ ብላ በዚያ ኩራ ባለው አረማመዷ ወደነሱ ሄደች።

ከሎ ምራቁን ቶሎ ቶሎ ከማንጐራጐጭ በስተቀር የሚመለከተው ልጅቷን ነው። ካርለት ደግሞ በተመስጦ የምትከታተለው እሱን ነው።

በልጅነቷ ወንድና ሴት ተቃቅፈው አልጋ ላይ ሲተኙ የሚያደርጉትን ለማወቅና ብዙ ጊዜ ለማየት ትጓጓ ነበር። ነፍስ ካወቀች ጊዜ ጀምሮ የምትተኛው በግል መኝታ ቤቷ ሲሆን፣ አንድ ቀን ታዲያ የናቷ ጓደኛና ባሏ በእንግድነት እቤታቸው ይመጣሉ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ለእንግዳ የተዘጋጀው የመኝታ ክፍል ተይዞ ስለነበር እንግዶች ካርለት መኝታ ክፍል እንዲያድሩ ተደረገ፣ እሷ ከወላጆቿ መኝታ ቤት ካለው ትንሽ ክፍል እንድትተኛ ይደረጋል። ካርለት ግን እንቅልፍ ከመተኛት ይልቅ አንድ ለብዙ ጊዜ ለማወቅ ትጓጓ የነበረውን ሁኔታ ለመፈጸም አሰበች። እናም፣ የቆየ የልጅነት ፍላጎቷን ለማሟላት እንግዶች እሷ ከምትተኛበት ክፍል ገብተው ከመተኛታቸው በፊት አልጋው ሥር ገብታ ተደበቀች። ባልና ሚስቱ በመጠጥ ኃይል ሞቅ ብሏቸው ነበርና እየተሣሣቁ ተደጋግፈው ገብተው አልጋ ላይ እንደ ወጡ ተያያዙ።

ካርለት የአልጋ ላይ ጨዋታቸውን ሁሉ ልቅም አድርጋ ሰማች። ከዚያ በኋላ ሰዎቹ ሲተኙ፣ ወላጅ እናቷ ካርለት ከተኛችበት ክፍል ልታያት ስትገባ ድንገጥ አለች። ቀስ አድርጋ እጇን ልጇ አልጋ ላይ ስትጭን ጨርቅ ብቻ ሆነባት። በድንጋጤ ጮኸች። አባት፣ እንግዶች ሳይቀሩ እየተሯሯጡ ሲመጡ የለችም። ቤቱ ቢታሰስ፣ ብትፈለግ በቀላሉ ልትገኝ አልቻለችም። በመጨረሻ ግን አልጋ ስር እንደ ውሻ ተጠቅልላ ተገኘች። እና ዛሬም እንደ የዛኔው እንዲታወቅባት

t.me/OLDBOOKSPDF

ስላልፈለገች የኮረዳዋንና የከሎን ሁኔታ በጥንቃቄ መከታተል ቀጠለች።

ከሎና ካርለት ከልጅቱ ጋር ፊትና ኋላ ወደ መንደሩ እንደ ደረሱ፣ ከልጅቷ መኖሪያ ቤት ትይዩ ድንኳን ለመትከል እንደ ፈለገች ለከሎ ሆራ ሆን ብላ አማከረችው። «ኢህ» ብሎ ፈቃደኛነቱን ገለጸላት። ለነገሩማ እንሂድ ብትለውስ መቼ በጄ ይል ነበር።

ከሎ፣ ስለ ብዙ ነገር እንዳላወጣ እንዳላወረደ አሁን የሚፈልገውና የሚያየው ውብ ልጅ ነው – የሐመሯን ኮረዳ። አጠገቧ ካለው ድንኳን ውስጥ ሆኖ እሩቅ ያለች ይመስል አለማት። ከሎ ሴት አያውቅም ለማለት አይቻልም። በተለይ በገንዘብ የሚገኘውን የስሜት እርካታ በሚገባ ያውቀዋል። የሴት ጓደኛም ለመያዝ ብዙ ሞካክሮ ነበር። ግን፣ ከሙሉ ስሜቱ እንዲህ እንደ አሁኑ ነፍሱ ምንጥቅ እስክትል ወዶ አያውቅም።

ልጃገረዷ ደግሞ በሕይወቷ እንደ ወንድ ጓደኛ ግንኙነት የጠገበችው የለም። ከሚጠይቋት ወንዶች ውስጥ ከመረጠቻቸው ጋር ብቻ ተዝናንታለች፤ ዕድሜ ለሐመር ደንና ጫካ።

እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ልጃገረዷ ወላጆቿን በሥራ በመርዳት ስታገለግል ቆይታ ለምሽት ጭፈራው መሰናዳት ጀመረች። የጕረምሶችን ጩኸት እንደ ሰማች ከጓደኞቿ ጋር ለመደነስ ስትሄድ፣ እነ ከሎ ተመለከቷት። አባቷ እንዳያገኛት ተጠንቅቃ አለፈች።

ልጃገረድ በኢቫንጋዲ (የምሽት ጭፈራ) መካፈሏን ባህሉ የሚፈቅድ ቢሆንም ወደ ጭፈራ ቦታ ስትሄድ ግን አባትየው ሳያይ ሲሆን፣ ከጕረምሳ ጋር ስትዳራ ካገኛም አባት ተቈጥቶ ጕረምሳውን እስከመግደል ድረስ መብት አለው። ይህ መብት እንጂ ያደርጋል ማለት ግን አይደለም። ስለዚህ፣ ለደንቡ ያህል ጭፈራውም ሆነ ድሪያው አባት በማያየው መንገድ እንዲሆን ልጃገረዶች የራሳቸውን ጥናቃቄ ይወስዳሉ።

በአጋጣሚ ግን እሷ ባህሉ ያደገችበት ሆነና ብትጠነቀቅም፣ አባቷ ግን ከሌሎች የሐመር ወንዶች ለየት ያለ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

በኢቫንጋዲ ጭፈራ ልጃገረዷ ኮከብ ደናሽ ስትሆን፣ የከሉሉ ጉረምሶች በፍቅር ሲያጫውቷትና ወደ ጫካ ሄድ መለስ ስትል፣ ከሉን ግን ለዳንስ እንኳን ሳትጋብዘው ቀረች። ወደ እኩለ ሌሊት አካባቢ ሲሆን የወንዶች ድምፅ ተሰማ። በመንገድ ላይ የሚያልፉ ገበያተኞች እግረ መንገዳቸውን ለጭፈራ ሲመጡ የተለመደ ነበርና ጨዋታው ቀጠለ። ካርለት አሁንም ከትትሏን እንደ ቀጠለች ነው። ጭፈራው ደመቀ፣ ውዝዋዜው ጦፈ፣ ከዚያ የመጨረሻው የዳንስ ሰልት ጊዜ እነ ካርለት የሚከታተሏት ኮረዳ ከአንድ መልከ መልካም ሸበላ ጋር መርፌና ክር ሆኑ። ካርለት ያ ሰው ማን እንደሆነ ለመገመት ጊዜ አልፈጀባትም። መጀመሪያ እንዳልነበረ እርግጠኛ ነች። ከገበያ ከተመለሱ መንገደኞች ጋር እንደ መጣ አወቀች። ደልቲና ኮረዳዋ ወደ ጫካው ሲሠወሩ፣ ከሉና ካርለት ተፋጠጡ።

ውቢቷ ልጃገረድ ጎይቲ አንተነህ ትባላለች። በሐመርኛ ጎይቲ ማለት መንገድ ሲሆን፣ የስሟ ትርጓሜ ከመንገደኛ የተወለደች ለማለት ነው። ካርለትና ከሉ የሐመርኛ ቋንቋ አቀላጥፎ የሚናገረውንና በአኗኗሩም ሆነ በአለባበሱ ሐመር የሆነው የጎይቲ ወላጅ አባት ጠዋት ከከብቶች በረት ሲመለስ፣ እንግዶች ከቤቱ ፊት ለፊት ድንኳን ተክለው አየ። አንተነህ (ጋልታምቤ) እንግዶቹን እንዳየ በጨዋ መልክ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ፣ ጨዋታ ቢጤ ጀማመሩ። የመጡበትን ጉዳይና ማንነታቸውን ከገለጸለት በኋላ፣ «ሸፈሮ ቡና እንጠጣ» ብሎ፣ ወደ ቤቱ ይዟቸው ገባ።

ቡናውን ያፈላችውና የምትቀዳው ውቧ ልጃገረድ ጎይቲ አንተነህ ከአባቷ ፊት በጣም ጨዋና ረጋ ያለች ናት። ካርለትና ከሉ በጣም ጠባብ ወደ ሆነው የጎጆው በር በየተራ ገብተው ከተነጠፈው ቁርበት ላይ እንደ ተቀመጡ፣ ጎይቲ በሾርቃ ሞልታ ሸፈሮ ቡናውን ለካርለት አቀበለቻት፤ ቀጥላ ለከሉ ስትሰጠው በአጋጣሚ እሷን እሷን እያየ ነበር፤ እሷ ደግሞ ሾርቃውን የያዘ መስሏት ስትለቅለት ከመሬት ወርዶ ተሰበረ። ሁለቱም በጣም ደነገጡ። ካርለት ድንገተኛ ሣቅ አፈናት፤ የልጃገረዷ አባትና ሌሎች ሁለቱ ሐመሮች ግን ጸጥ ብለው ሁኔታውን አረጋጉ።

ቡናው የውኃ ጥምን ስለሚከላከል ማንኛውም ሐመር በየመንደሩ ቡና በእንስራ ተጥዶ፣ ሁለትና ከሁለት በላይ ሾርቃ ሳይጠጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመንደሩ የሚርቅ የለም። አንተነህ ይመር ኀይቲ (ሴት ልጁ) ቡናውን አጠጥታ ስትጨርስ፣ «ረሃብ፣ ችግር ከሐመር ምድር ይራቅ፤ ከብቶች ይጥገቡ፤ ንቦች አበባ ይቅሰሙ፤ ሰማዩ ውኃ ያውረድ፤ ፍቅርና ሰላም ለሐመር ሕዝብ ቦርጆ ያውርድ፤ አንቺም ተባረኪ፤ የተባረከ ባልና ትዳር ይስጥሽ፤ ሁላችሁም ተባረኩ» ብሎ ሸፈሮ ቡናውን ወደ አራቱም አቅጣጫና ወደ ኀይቲ፣ «ፕስስ...» አለና አማተበ።

ኀይቲና ሌሎች እንግዶች ሲወጡ፣ ጋልታምቤና ሁለቱ እንግዶች ብቻ ቀሩ። ካርለትና ከሎ ይህ ሰው ለየት የሚል ሆኖ አግኝተውታል። ስለዚህ፣ ሊጠይቁት የፈለጉት በመጀመሪያ ማንነቱንና ሕይወቱን በተመለከተ ነው። ሰውየውም እንዲያውም ከሚረካበት ትልቁ ነገር ስላለፈው ሕይወቱ ማውራት ስለነበር፣ ጉሮሮውን ጠራርጎ ጨዋታውን ጀመረ። «ስሜ አንተነህ ይመር ይባላል። ትውልዴ መንዝ ነው። የመጣሁት ለአደን ነበር። አውሬ ገድሎ ጀግና ለመባል...ሁሉም ቀረና ጓደኞቼ ሞቱ...በጦርነቱ ወቅት ከሐመሮች ወግኜ ተዋጋሁ። የሐመሮችን ወንድምነት፣ ፍቅርና እምነት ወደድኩት። ከዚያ ወደ ትውልድ ቦታዬ መመለሱ ከበደኝ።

«ባህላዊ ደንቡን አሟልቼ ሐመር አገባሁ። ሴት ልጅም ወለድሁ። እስካሁን በኑሮዬ ደስተኛ ነኝ» አላቸው። በረጅሙና አስገራሚ ታሪኩ ተደነቁ። እንዲያውም ካርለት፣ ስለ ሰውዬው ሁኔታ በጥልቅ አሰበች፤ ሰውዬው በሐመሮች ኑሮ ደስተኛ ነኝ ብሏታል። ስለዚህ፣ ምናልባት በሰውዬውና በሐመሮች ባህል መካከል የባህል ልዩነት ሊኖር ይችላል። ልዩነቱ ግን እንደኔ የማይገናኝ ላይሆን ይችላል» በማለት አሰበች።

ሰውዬው ከሐመሮች ጋር ለመኖርና ለመጋባት የቻለበት የራሱ ምክንያት ቢኖረውም፣ አብሮ በመኖሩና ጋብቻ በመፍጠሩ ደስተኛ ሆኗል። እሷም ለዓላማዋ ስኬት ስትል አብራ መኖርና መጋባት እንዳለባት ወስናለች፤ ስለሆነም በዚህ ተመሳሳይነት አላቸው።

ሌላው ያጓጓት ነገር ግን በከሎና በልጃገረዷ መካከል ሊኖር የሚችለው ግንኙነት ነው። ከሎም ቢሆን በዚህ ጉዳይ ከማንም በላይ መባዘኑ አልቀረም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሎ፣ የሚያስበው የተወሳሰበ የፍቅር ድራማ ነው፤ ተዋናዮች ገና ተግባብተው መከወን ያልጀመሩት። ካርለት ግን፣ ግንኙነቱ የሚሳካበትን እያወጣች እያወረደች ሳለ፣ አንድ ቁለፍ ጥያቄ እንደሚቀር ተገንዝባለች።

በሐመር ባህል ደንብ መሠረት፣ አንድ ወንድ ከብት ከዘለለ፣ ጨርቆሌ ማዝ ከሆነ በኋላ ከሸያው (ሚዜው) ጋር ደም፣ ወተትና ማር እየተመገበ በየመንደሩ እጮኛ ፍለጋ ይዞራል።

በየመንደሩ የሚኖሩት ልጃገረዶች ደግሞ ከማይፈለግ ቤተሰብ ጋብቻ እንዳይፈጠር በወንድሞቻቸው ስለሚጠበቁ፣ እጩኛ ፈላጊዎች ውኃ ልትቀዳ፣ እንጨት ልትለቅም ወይምንም በሌላ ምክንያት ወደ ኋላ የቀረች ልጃገረድ ሮጠው ሄደው ይይዙና እጮኛ ፈላጊው ልጃገረዷ ፊት ለፊት ላይ ከ«ተሪ» (ዲክዲክ) ቆዳ የተተለተለ ጠፍር መሳይ ነገር ያጋድማል። ከዚያም ይዞት ከሚዞረው ኩርኩፋ (ከማሽላ የተሠራ) ያጐርሳታል። ይህን ካደረጉ በኋላ እጮኛ ፈላጊና ሚዜው፣ ወደ ጫካ ይፈተለካሉ። ልጅቷ ታለቅሳለች፣ ትጮሃለች። ሁኔታውን የሰማ አባት፣ ወንድም፣ ዘመድ መሣሪያውን እየያዘ ለፍለጋ ይሰማራል። ከአንድና ከሁለት ቀን በኋላ ሽማግሌው ከወንድ ወገን ይመጣና አስፈቅዶ፣ ኮይታ (ጥሎሹን) በማስወሰን ከፍያው ይጀመራል። አንድ ልጃገረድ የተሪ ቆዳ ፊት ለፊቷ መሬት ላይ ከተጋደመና ኩርኩፋ ከጐረሰች፣ ከዚያ ካጐረሳት ሰው ውጭ ሌላ አታገባም» ብለው ሽማግሎች ያጫወቷት ካርለትን ትዝ ብሏታል።

ስለሆነም፣ አንተነህ ይመርን (ጋልታምቤን)፣ «ጎይቲ እጮኛ አላት ወይ?» ብላ ጠየቀችው። ከሎ ውስጥ ለውስጥ ይጨነቅበት የነበረው ጥያቄ በመጠየቁ ደስ ብሎት መልሱን ከአንተነህ ለመስማት ጓጓ። «መቼም ልጅቱ ንቁ ናት፤ በዚያ ላይ የእናቷ ዘመድ የሆኑት ኮረምሶች ሲጠብቋት ነበር» ሲል፣ ከሎ ፊቱ ወደ አመድነት ተቀየረ። ካርለት እንኳን ደልቲ ገልዲን ማታ ስትነጥቃት የነበረችውን ጎይቲን ከሎ እንዲያጣት ስለማትፈልግ እሷም የጭንቀት መልክ ታየባት። አንተነህ ይመር ነገሩን በመቀጠል፣ «...እስካሁን እንግዲህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ኩርኩፋ ያጉረሳት የለም። ይህ ግን መቼም የሚቀርላት አይደለም»
ሲል፣ ከሎና ካርለት ሁለቱም እፎይታ ተሰማቸው።

ከሎ ሆራ፣ መሠረታዊው ጥያቄ ከተመለሰለት በኋላ፣ ስሚቱ መጋለብ ጀመረ። «ጎይቲን ለማግኘት ሁለት መንገድ ይኖረዋል። አንደኛው በባህላዊ ደንቡ መሠረት፣ ካሊያም በአቋራጭ ከአባቷ ጋር ተስማምቶ፣ ከባህላዊ ደንቡ ውጭ ጋብቻ መፈጸም ነው። ለእኔ ሁለተኛው ሐሳብ የተሻለ ይመስለኛል። ሁለተኛውን አማራጭ ለመከተል ግን አቶ አንተነህ ይመርን ማግባባት አለብኝ። ልጁ እንድትማርለትና እንድትሻሻልለት ስለሚፈልግ፣ ሁኔታው አመቺ ሊሆንልኝ ስለሚችል ብጠይቀውስ» ብሎ ከሎ አሰበ። መፍራቱ ግን አልቀረም። ከሎ ከብዙ የሕሊና ጭንቀት በኋላ አንተነህን ሲጠይቅ ያገኘው መልስ የጠበቀው አልሆነም።

«መወለድ ወሬ ነው፣ ወላኙ አብሮ ተቻችሎ መኖሩ ነው።» ሐመሮች ወንድሞቼ፣ እኅቶቼ ሆነው ተንከባከበው፣ ልዩነት ሳያደርጉ፣ ድረውና ኩለው፣ ሸልመው፣ ለትዳርና ለንብረት አብቅተውኛል። ተስፋ የቈረጥሁትንና በሞት ጥርስ የተያዝኩትን፣ ከሞት አፍ ፈልቅቀው ተስፋዬን አድሰው ከዚህ አድርሰውኛል።

«እኔ አሁን ሐመር ነኝ። ባህሌና ቋንቋዬ ሐመር ነው። ስለዚህ ልጄን የምድራት በባህሌ ነው። በሐመር ባህል ደንብ ልታገባና ለተሻለ ሕይወት ወደ ከተማ ይዘሃት ልትሄድ ትችላለህ። ይህ የእኔ ትብብር ይሆናል። የባህል ደንቡን ካላሟላህ ግን ቃሌንና ባህሌን አልጥስም» አለ አንተነህ ይመር ኵስተር ብሎ። ከሎም ራሱን ቀብሮ ሲያስብ ቆየና ውቢቱን ልጃገረድ የራሱ ለማድረግ የባህላዊ ደንቡን ለመፈጸም መስማማቱን አስታወቀ። ግን ከብት ዘሎ ቀሪውን ባህላዊ ደንብ እስኪፈጽም ጎይቲ ትጠብቀው ይሆን?

ከሎ ሆራ የአንተነህ ይመርን (ጋልታምቤን) ልጅ ለማግባት ሽማግሌ ከመላኩ በፊት አንድ ባህላዊ ደንብ መፈጸም ነበረበት። ይኸውም በልጅነቱ ወድቆ ጥርሱ በመውለቁ ሚንጊ (ገፊ) ተብሎ ተጥሎ ነበር። አሁን ግን ከሞት ተርፎ አድጎ ወደ ቤተሰቡና አካባቢው በሥራ ምክንያት ተመልሷል። ያ ሐመር አይደለህም ተብሎ



t.me/OLDBOOKSPDF

የተማለው ሕፃን ዛሬ ሐመር ነህ ለመባል ዝም ብሎ እንደ ከብት አይቀላቀልም።

ለዚህም፣ ከሉ ሽማግሎችን አማክሮ ከብት ታርዶ በደምና ፈርስ እንዲታጠብ ተደረገና ወደ ሐመር ማኅበረሰብ መቀላቀሉ ተበሠረ። ከዚያ ቀጥሎ ትንሽ እራፊ ቆዳ በመልበስ «ኡከሊ» ሆኖ በየዘመዶቹ ለመዞር የወንድ ብልት መሳዩን አጭር ከእንጨት የተጠረበ «ቦኮ» ያዘ። ከዚያም በሐመር ቆላማና ደጋማ አካባቢ በእግሩ መዞር ጀመረ። ኡከሊ ማለት በሐመርኛ አህያ ማለት ሲሆን፣ ኡከሊ የተባለው ወጣት ለሴት ያልደረሰ ማለት እንደሆነ ይታመናል። ከሉ ሆራ ቦኮውን ይዞ በየዘመዶቹ ሲዞር በመጀመሪያ «ዳውስ» ይላል፤ ሠርጉ እንደተቃረበ ለመግለጽ። ቀጥሎ «ክርክሴ» ይላል። አሁንም ሠርጉ መድረሱን ለማብሠር። በሦስተኛው ቀን የሠርጉ (ከብት መዝለያው) ቀን የቀረውን ጊዜ የሚያሳውቅ ቋጠሮ ለዘመዶቹ ይሰጣል። አምስት ቋጠሮ አምስት ቀን፣ አራት ቋጠሮ አራት ቀን፣ ...አንድ ቋጠሮ አንድ ቀን ይሆንና ቀጠሮውን በቋጠሮ ያበሥራል። ዳውስ፣ ክርክሴ፣ የተቋጠረ ልጥ ይዞ ሲዞር የሚበላውንና የሚጠጣውን ዘመዶቹ ያዘጋጁለታል።

እናቱና ዘመዶቹም ከብት በሚዘልበት ቦታ (ራፂ) ለሚሰበሰበው ዘመድና የአገር ሰው፣ የሚጠጣ ቦርዴ፣ ምግብ አዘጋጁ። በዚህ በኩል ክርለት ወጪውን አሟላች። ሚስቱ ገና ሳትታጭ፣ ሠርጉ ተደገሰ ማለት ነው።

ከብት ከሚዘልልበት ቦታ (ራፂ) ዳስ ቢጤ ተዘጋጅቷል፤ ሰፋፊ ቅጠልም እየተቈረጠ ከላዩ ተረብርቦበታል፤ እንደናሱ (እናት ሚዜው)፣ ሽያው (አንደኛ ሚዜው) ጋር፣ ስም የሚሠየምባት ትንሽ ጥጃ፣ ዘመዶቹና እንግዶች ተሰብስበዋል።

ልጃገረዶች ከብት ለሚዘለው ዘመዳቸው ለግርፊያ እየተዘጋጁ ሲሆን «ፀንጋዞች» (ባዕዳን) የተባሉት ገራፊዎችም «ስሌንት» የተባለውን ቦታቸውን ይዘዋል።

ከልጃገረዱ መካከል በመልኳ ለየት ያለችውና በፍርሃት ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠ ያስቸገራት ሴት አለች። ሁሉም ልጃገረዶች አምናና ታች አምና ለወንድ ዘመዶቻቸው ከብት ሲዘሉ ተገርፈው በግርፋት ቻይነታቸው እንደሚወደሱት ሴቶች ለውደሳ ለመብቃት ስሌንት ወደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተባለው ቦታ እየሄዱ ፀንጋዞች (ባዕዳን) የሚባሉትን በነገር ይተነኳኰሳሉ፣ «ግርፊያውን ለምን አትጀምሩም። ፈራችሁ እንዴ ...መግረፍ የማትችሉ ከሆነ፣ ልበ ሙሉ ለሆኑት ወንዶች ስጧቸው» እያሉ ገራፊዎችን መጥተው እንዲገርፏቸው ያደፋፍራሉ።

መልኳ ለየት ያለችው ልጃገረድ ግን የሚሉት ቢገባትም በምትሠራው ድርጊት ራሷን «አውቆ አበድ መሆን አለብኝ...» እያለች፣ አብራ ትመላለሳለች። በባዶ እግሯ ላይ ታች ስትል፣ የቈሰለው እግሯ ሕመም በጣም እየተሰማት ነው። ለልጃገረዶች እንደሚሰፋው ሁሉ ዙሪያውን ዛጐልና ጨሌ ክፍክፍ ያለበት ጥቁር የፍየል ቆዳ ከወገቧ በታች ለብሳ፣ ከለበሰችው ቆዳ ውጭ ያለው ጭኗና ከወገቧ በላይ ራቁት የሆነው ሰውነቷ ለጋ ጥብስ መስሏል። አንገቷ ላይ ጨሌ፣ እጆቿ ላይ ደግሞ አምባር ደርድራለች። ጸጉሯ አጠር ብሎ ቅቤና የአሰሌ አፈር በስሱ ተቀብታ፣ በፀሐይ ሙቀት የሚቀልጠው ጆሮግንዷ ላይ ሲወርድ ይታያል። በበዓሉ ቦታ ከተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ በፍርሃትና በድንጋጤ የተዋጠችው ይችው ሰው ብቻ ነበረች። የሚያሳዝነው፣ ጭንቀቷ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ሁሉ ሰው ውስጥ ጭንቀቷን ካለ አንድ ሰው በስተቀር የሚያውቅላት አለመኖሩ ነው። ያ ሰውም የዕለቱ ክብት ዘላይ እሱ በመሆኑና ልምምዱም አጭር በመሆኑ በራሱ ችግር እየተዋጠ ይዘነጋታል።

ይህች ለየት ያለች ሰው ትናንት በሥልጣኔ ሕዋ ውስጥ ከተሰነ ቀሩት ምዕራባውያን አባል የነበረች፣ በቅምጥልና በድሎት ያደገች፣ ተንከባካቢ ቤተሰቦቿ አሁንም ድረስ የሚሳሱላት ናት። ዓላማዋ ግን የማታውቀውን እያሰቦካት ነው።

ከጫማ ጫማ አማርጦ የሚጫማ እግር ለእንቅፋትና እሾህ፣ ለጋሬጣና ለቃጠሎ ተጋልጦ ደም ያገፍል። ከአገር አገር፣ ከፋሽን ፋሽን ተመርጦ ዘመናዊና ውድ ልብስ የሚሸፈነው ገላ በቀላሉ በእጅ በተውሰበሰበ የፍየል ቆዳ ሩቡ ተሸፍኖ ሦስት አራተኛውን ውርጭና ሙቀት የደረቀ ባሕር ዛፍ ቅርፊት አስመስሎታል። ይህም ብቻ አይደለም፣ በለስላሳ እጆች በጥንቃቄ የሚዳሰሰው ጀርባ ለግርፋት ተዘጋጅቷል፤ የሐር ነዶ የመሰለው ጸጉር፣ በአፈርና ቅቤ ተለውሷል።

ይህች ለየት ያለችው ልዩ ፍጡር ካርለት አልፈርድ፣ እንግሊዛዊቷ ተመራማሪ ነበረች። እናት ሚዚው፣ ማዞች (በአለፈው ዓመት የዘለሉት)፣ የሚጨፍረው ሕዝብ፣ ልጃገረዶች፣ ወደሚጕርፍበት ሲሄድ ፀንጋዞች (ባዕዳን) የሚባሉት ገራፊዎች መግረፊያቸውን



t.me/OLDBOOKSPDF

(ባሪዛ አርጩሜውን) እየያዙ ተጠጉ። አርጩሜው ረጃጅም ከመሆኑ አልፎ ከመሰበር ይልቅ ገላ ላይ እንዲጠመጠም ተቀብሮ የቆየውን ባንዛቶች እያንዳንዳቸው በብዛት ይዘዋል። አንድ አርጩሜ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ ገራፊው ተንጠራርቶ ሲገርፍ አርጩሜው ተጠቅልሎ ሰምበር ከፊትና ኋላ ማውጣት አለበት።

ካርለት ልጃገረዶች ግረፉን እያሉ ፀንጋዞችን እያናናቁ ሲፎክሩ፣ የቤ ሰውነት በላብ ራሰ። የምትራመደው እየተንሻፈፈች ነው፤ ቀሰሏን ግር በነካው ቍጥር ስፍስፍ ትላለች፤ ጠዋት ብርዷ አሁን ደግሞ ሙቀቱ ሰውነቷን እንደ እሳት እየለበለባት ነው፤ በዚያ ላይ ደግሞ ልትገረፍ ነው። ጨሂ ጨሂ አሰኛት። ከዚህ ሁሉ የሚያድናት ሰው የለም። ስለዚህ፣ «አምላኬ የዛሬን ከመከራ አውጣኝ» ብላ ተማጸነች።

እንዲህ ስትብረከረክ ግርፋቱ ተጀመረ፤ ከሎ ሆራ ለካርለት ከልቡ አዘነላት፤ እሱም ጭንቀት ላይ ነበር። ሦስት ጥንድ በከብት ከብቶ ሳይወድቅ መሮጥ አለበት። ከወደቀ ለእሱም ለዘመዶቹም ጀርባ ውርደት ነው። ምልምል ራቁቱን ሆኖ እናት ሚዜው በልጥ መሳይ ነገር ሰውነቱ ላይ በሁለት ወገን አሰር አድርጎ፣ በአበት ሰውነቱን ቀባ ቀባ አደረገለት። እሱም እበት በመሃል እግሮቹ ነካ ነካ አድርጎ መሬት ላይ እሸት እሸት አደረገና ከአንደኛው ሚዜው በስተኋላ በመሆን የሚዘልባቸው ከብቶች መሃል ገባ።

ማዝ የተባሉት በከብቶች ዙሪያ በርከክ ብለው አማተቡና እየዘለሉ የከብቶችን ጅራትና ቀንድ ይዘው በአንድ ረድፍ ደረደሯቸው።

ካርለት በባራዛ አርጩሜ ገና አንድ ጊዜ በፀንጋዛው ስትገረፍ፣ ነፍሷ ከሥጋዋ የተለየች መሰላት፤ አርጩሜው ሥጋዋን ይዞ ሄደ፣ ደም በጀርባዋና በጡቷ አካባቢ ፍጭጭ አለ። ወደ ላይ ዘለለች፤ ከላይ ስትመለስ ደግሞ ሣሩ የእግሯን ቍስል ነካባት፤ ቁጭ ስትል የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ሣቅ በሣቅ ሆነ። ነፍሷን ስታውቅ መላ ሰውነቷን ጠዘጠዛት፤ በሁኔታዋ ሐፍረትም ተሰማት። ምክንያቱንም ሳታውቅ ከተቀመጠችበት ተነሣች፣ ግርፋቱ እየቀጠለ ሲሄድ ካርለት ራሷን ሳተች። ሰውነቷ ደም በደም ሆነ። አብረዋት የተገረፉት ልጃገረዶች እንደሷ ባይሆንም ደም በደም ሆነዋል። የሁሉም ሰምበሩ ያስፈራል፤ የሷ ግን ልዩ ነው።

ከግርፋቱ በኋላ ራሷን ስታ ብትወድቅም ልብ ያላት አልነበረም፤ ሁሉም በዕለቱ ከብት ወደሚዘለልበት ቦታ ሄዱ። ከሎ ሆራ ለመንደርደር እንዲያስችለው ራቅ ብሎ አሁንም ምልምል ራቁቱን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከአንደኛ ሚዜው በስተጀረባ ቆሟል። እናቱ፣ ወንድሙ፣ ዘመዶቹ ሰምለም ቅጠል ቄርጠው ይዘው፣ «ይቅናህ፣ አይዞህ» እያሉ መልካም ዕድል እንዲገጥመውና ከውርደት እንዲድኑ ይመኛሉ።

ሁሉም ዝግጁ መሆኑን እናት ሚዜው ሲረዳና ምልክት ሲያሳየው ከብት ዘላዩ ከአንደኛ ሚዜው ጀርባ ወጣ ብሎ ወደፊት ተንደረደረና ጋር በምትባለው ትንሿ ጥጃ ላይ ዘሎ ወጥቶ በተደረደሩት ከብቶች ጀርባ ሮጠ። መሃል አካባቢ ሚዛኑን ለመጠበቅ ቢንገዳገድም እንደ ምንም ብሎ መሬት አረፈ። እንደገና ዘሎ ወጥቶ አሁንም በከብቶች ጀርባ ሮጠ፤ ሦስት ጥንድ ሮጦ ሊጨርስ ሲል ከብት ዘላዩን እናት ሚዜው ጠበቀው፤ ከሎ ዝላዩን ሊጨርስ እንደ ተቃረበ ወደ እናት ሚዜው በአየር ላይ ሲዘል፣ እናት ሚዜው ከአየር ላይ ቀለበው። ደንብ ነዋ!

ከሎ ሆራ ዝላዩን በሚገባ ሲፈጽም ዕልልታው፣ ደስታው፣ ፈንጠዝያውና ዘፈኑ ቀጠለ። ጸጥ ብሎ የነበረው አካባቢ በጩኸት ድብልቅልቅ ሲል ካርለት ከነበረችበት ነቃች። ሰውነቷ በደም ተበክሏል። ከዚህም በተጨማሪ ሰውነቷን ማንከላወስ ተሳናት። እንደ ምንም ብላ ከተኛችበት ስትነሣ አንዲት ልጃገረድ ጀርባዋን ለጋ ቅቤ ቀባችላት፤ ቀና ብላ ስታያት ኀይቲ አንተነህ ናት። ጎባኗ። ካርለት ኀይቲን አመስግና እንደ ምንም እንድትደግፋት ነገረቻትና ለእህል ውኃ ወደ ዳሱ ከሚገባው ሰው ራቅ ብላ ዛፍ ስር ተኛች። ዝንቦቹም ትኩስ ደም ከቍስሏ ላይ በመምጠጥ ቁም ስቅሏን አሳይዋት።

በዚህ ወቅት ከሎ ሆራ ካለምንም ልብስ ብልቱን እያማታ ወደሷ መጣ። ልትሥቅ ሞከረች፤ «እንኳን ደስ አለህ!» ብላ እጇን ልትዘረጋለት ብታስብም እጇን ማዘዝ ተሳናት። እሱም እንዳያት በሁኔታዋ ድንግጥ ብሎ አዘጋጅቷ ያመጣችውን አልኮልና ጂቪ እያቃሰተች ቁስሏን ጠራረገላትና ቀና ሲል ኀይቲ አንተነህ ኩራ ብላ ስታየው ተመለከታት። ዘወር ሲልም ደልቲ ገልዲን አየው። ጎንበስ ሲል የካርለትና የከሎ ሆራ ዓይኖች ተገናኙ።

ሁለቱም የተግባቡ ይመስላሉ። የሚፈልጉትን ለማግኘት አስፈላጊውን ሁሉ መፈጸም እንደሚያስፈልግ አንዱ ለሌላው መንገር ኣላሻቸውም። ለዚህ ምሳሌዎች ናቸዋ!



t.me/OLDBOOKSPDF

# 10

ከሎ ሆራ ጨርቆሎ ማገዝ ሆኖ ደም፣ ወተት፣ ሥጋና ማር እየተቀለበ፣ ከሰልና ቅቤ ተቀላቅሎ ፊቱንና የተላጨውን ራሱን ተቀብቶ፣ ከሚዜው ጋር ውሎው ጫካ ነው። ከሎ የወገኖቹን ባህላዊ የጋብቻ ሥነ–ሥርዓት ለመጀመር ምክንያቱ አንድ ነበር – ፍቅር። ሥነ–ሥርዓቱን እያሟላ ሲመጣ ግን፣ አዲስ ስሜት አእምሮው ማፍለቅ ጀመረ።

ወገኖቹ የሆኑት ሐመሮች በአንድ ወቅት ከማኅበረሰባቸው አግልለውት ነበር። ያውም ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ፣ እንዲሞት ተደ ርጎ ተጥሏል። ከሚወዳቸው ወላጆቹና እኅት ወንድሞቹ፣ ከሚያፈ ቅረው የፍየልና ጥጃ ጥበቃው፣ ከቦረቀበትና ከተጫወተበት ማራኪ የሐመር ምድር ተጎትቶ ተወስዶ፣ በጦር ተወግቶ፣ ወደ ገደልም ተገፍቶ፣ የሞትን ጽዋ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀምስ ተደርጎ ነበር።

የሕፃንና የወጣትነት አእምሮው ይህን የደረሰበትን መራራ ጽዋ ጠንጥኖ በገዛ አእምሮው የዛን ጊዜውን መሪ ተዋናይ ሲያስታውሰው አፉን ደም ደም ይለዋል፤ ልሳኑ ይዘጋበታል፤ ሕይወቱ የላሸቀ፣ የተበላሸ እንቍላል ሆኖ ባለመጥቀሙ ተሸቀንጥሮ የተወረወረ ይመስለዋል።

የዛኔው የቍስል ስሜት ምልክት ጥሎ ካለፈ ዓመታት ቢቈጠሩም ሁሌም አጋጣሚውን ባስታወሰ ቍጥር ሥቃዩ ይጀምረዋል። ሞት ጉሮሮው ላይ ቆሞ ስለታም ሰይፉን ጉሮሮው ውስጥ ሊቀረቅርበት ሲመጣ ይታየውና ይባባል፤ መሸሻ፣ መደበቂያ፣ ማምለጫ መንገድ ያጣል። ከራስ ሕሊና የሚፈጠር አስፈሪ ነገር በምን አንቀጽ ይከሰሳል! ምን ዓይነት ጠንካራ በር ያግደዋል?



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኮ ለምን? ምን ባደረኳቸው በእንቦቀቅላነቴ ወቅት ልሸከመው የማልችለውን ሞትና ፍርሃት አሸከሙኝ። ምን ባደረኳቸው ከእናቴ ጉያ ነጥለው፣ አብሬአቸው ከምዘላቸው ጓደኞቼ ለይተው ለመከራ ዳረጉኝ?» ባለፈው ሕይወቱ ከሉ ሆራ ራሱን በራሱ እየጠየቀ መልስ ያጣበት ጉዳይ ነው። ለብዙ ዓመታት የዕለት ተዕለት ትዕይንት ሆኖ የሚቀርበውን የቆየ ትዝታ ባስታወሰ ቍጥር የመጨረሻውን ረድፍ ይዘው የሚደረደሩት ጥያቄዎች ከላይ የተዘረዘሩት ሲሆኑ መልሳቸው ግን ሰው ወይንም መዝገበ ቃላት ሳይመልሰው እስከ ዛሬ አብረውት ዘልቀዋል።

ከሉ ሆራ በሕይወቱ ሙሉ ያምንበት የነበረው አሁን ግን እንደ ጉም እየበነነ አልጨበጥልህ ይለው ጀምሯል። ወደ ወገኖቹ ብቻም ሳይሆን ወደ ሐመር ምድር ለመመለስ አልሞም አያውቅም። የኖረው እነሱን ሲረግምና ሲሸሽ ነው። አሥራ ሁለተኛ ክፍል እንደ ጨረሰ በአገር አቀፍ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻውም ወቅት፣ ከዘመቻው መቅረት ወይንም መለወጥ አልቻልህ ብሎት እንጂ እግሩንም ለማንሣት አያስብም ነበር። የዛኔም ቢሆን ደግሞ፣ «ጌታዋን የተማመነች በግ...» እንዲሉ፣ መንግሥትን ተማምኖ እንጂ እንኳን የከፍተኛ ትምህርት ዕድሉ ሌላው ሁሉ ነገር ቢቀር ወደ ሐመር ተመልሶ ለመምጣት አያስብም። በቆይታውም አይጥና ድመት ሆነው ቆዩ እንጂ አልተቀራረቡም።

አሁን ግን ከሉ ሆራ አይጡም ድመቱም እሱ እንደሆነ በመቍጠር ወደ ቤቱና ወደ ባለቤቶቹ መመለስ ይከጃጅለዋል።

ከሉ ሆራ በእርግጥ አሁን ያለው ሐመር ነው። ሐመሮች በተለይም ዘመዶቹ ባዩት ቍጥር ይሳሱለታል። ወላጅ እናቱ ልክ እንደ ልጅነቱ እጆቹን እያፍተለተሉ እንባቸውን ያፈሱለታል፤ ያላቸውንና ቤት ያፈራውን ጎጆው ድረስ ተሸክመው ያመጡለታል፤ ከብት ለመዝለል በየዘመዶቹ ቤት ሲዞር እንደ ብርቅ ስመው አስተናግደውታል፤ ከብት በሚዘለልበትም ወቅት ዘመዶቹ ዝግጅቱን በማሟላትና በለምለም ቅጠል መልካም ዕድልን በመመኘት አብረውት ተጨንቀዋል፤ ልጃገረድ ዘመዶቹም የዝምድና ምልክት የሆነውን ግርፋት በወኔና በፍላጎት ተገርፈውለታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሎ ሆራ ይህን ሁሉ ካመዛዘነ በኋላ ለዘመናት በአእምሮው ተቀብረው የኖሩትን ጥያቄዎች ከመቃብራቸው እያወጣ መጣል ጀምሯል። እናቱ እንደ ብርቅዬ ልጃቸው፣ ወንድምና እኅቶቹ እንደ ተወዳጅ ወንድማቸው አድርገው ይቈጥሩታል። ታዲያ ማንን ይጥላ? ለሥቃዩ ሁሉ ተጠያቂው ማን ሊሆን? ለምንስ እንዲሞት አድርገው ጣሉት?

ከሎ ሆራ አእምሮው ለጥያቄዎቹ መልስ አገኘ። ለመጣል ያበቃው ባህል ነው። እሱን ለመጉዳት፣ ከእናቱ ጉያ ለመነጠል የደፈሩት የአገር ሽማግሎች አንኳን ለሱ ከሚዳ ተነሥተው ከፉ አላሰቡም።

* * *

የሐመር ሕዝብ ባህሉን አክባሪ፣ ካለ ዘመናዊ ሕግና ደምብ በባህላዊ ደምቦችና ሥርዓቶች የሚመራ፣ ተፋቅሮና ተዛዝኖ የሚኖር ማኅበረሰብ ነው። ማንንም የማያገል፣ ባህሉን ከመከተል ዝንፍ የማይል ሕዝብ መሆኑን አረጋግጧል። «ታዲያ ወገኖቼ በእኔ ላይ ብቻ ልዩ ቅጣት አልፈጸሙብኝማ። ባህላዊው ደንብ መሟላት ነበረበትና ተገደልኩ! ከሙትነት ተነሥቼ ስመጣ ግን ተቀበሉኝ። አሁን የተቀበሉኝ ስለ ተማርሁ፣ ከእነሱ የተለየ ሕይወት ስላየሁ አይደለም! ባህሉ ስለሚፈቅድ ብቻ ነው። ታዲያ ባህል ባመጣው ጦስ ወገኖቼን መጥላት አለብኝ?» ጨርቆሌ ማዝ ተብሎ ጫካ ለጫካ የሚዞረው ከሎ ሆራ ዕድሜ ልኩን አእምሮውን ሰንገው ይዘው ያስጨንቁት የነበሩትን ጥያቄዎች መመለስ ጀመረ።

* * *

ሰው ራሱን ማስተማር የሚችል ታላቅ ፍጡር ነው። በተለይም ታታሪ ሰዎች ከአምላክ የተሰጠውን ቃል ተግባራዊ ለማድረግ እየተጣጣሩ ናቸው። እየተሳካላቸውም ነው።

በምርምር እንደ እብድ ያልለፈለፈ ፈላስፋ፣ ቀንና ሌሊት በምርምርና በሙከራ እልሁን ያልጨረሰ ሳይንቲስት፣ እንደ ሚፈጥራቸው ገጸባሕርያት ስቅስቅ ብሎ ያላዘነ አሊያም በደስታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያልተፍነከነከ ደራሲ፣ የሚሥለውን ሥዕል የተዋጣ ለማድረግ ረቂቁን የተፈጥሮ ምሥጢር ለማወቅ በመጣጣር ያልዳከረ ሠዓሊ ሊኖር አይችልም። ካለም ከነሆድ አምላኩ ወገን የሆነ አስመሳይ መሆኑ ነው።

ካርለት የሐመር ሴቶችን ሕይወትና ማኅበራዊ ተሳትፎ የምታጠና ወጣት አንትሮፖሎጂስት ናት። ያለችበት ዘመን ሳይንስና ተክኖሎጂ የመጠቀበት፣ የሰው ልጆች በአዲስ ግኝቶች የሚንበሸበሹበት ወቅት ነው።

«እንደ ዱሮው ዘመን ይህን – ይህን ማድረግ ያስቸግራል የሚል አዳማጭም ሆነ ተመልካች አያገኝም። መሆን አለበት ብዬ ብዙ ሞከርኩኝ፤ ፈተናና ሥቃይም ገጠመኝ፤ በመጨረሻ ግን ተሳካልኝ ሲባል አድናቆታዊው ጭብጨባ መቅለጡን አውቃለሁ። የሰው ልጅ በውኃ ውስጥ በባቡር መጓዝ በቻለበት፣ ሕዋ ላይ ከተማ በከተመበት፣ አይጥና ድመት አብረው እንዲጫወቱ በተደረገበት ወቅት እኔስ ሰውነቴ ቢቈስል፣ የአእምሮ ጭንቀት ቢደርስብኝ፣ ብገረፍ፣ ባል ባገባ ምኑ አዲስ ነገር ነው። ከዚህስ የቀለለ የዓላማ መሥዋዕትነት ምን ሊኖር ይችላል?» ካርለት መኝታዋ ላይ ተጋድማ የምታስበው ነበር።

ካርለት ለአንድ ወር ያክል በከብት ዝላይ ወቅት የተገረፈችው ቍስል አሠቃያት፤ ጫማ የለመደውን እግሯንም እንቅፋቱና እሾሁ እየተተካካ አንሰፈሰፉት። እየቆየ ሲመጣ ግን ይህ ሁሉ ሥቃይ እየታገሠ፣ ቍስሉም እየደረቀ፣ እግሯም እየደነደነ መጣ።

ካርለት በቃን በማይሉት ማስታወሻዎቿ የየዕለት ገጠመኞቿን እያሰፈረች፣ በካሜራዋ እይታዋን እያጠናከረች፣ በድንኳኗ አካባቢ አገገመች።

ካርለት አልፈርድ ልብሶቿን በሻንጣዋ ቆልፋ፣ ቆዳዋን በመልበስ፣ በባዶ እግሯ በጨሌና አንባር አጊጣ ስትወጣ ብዙ አዲስ ሁኔታ አጋጠማት። የሐመር ልጃገረዶችና ሴቶች ከልብ ቀረቧት። ጕረምሶች ያሽኰረምሟት ጀመር። እነሱ የእኛ ናት፣ እሷ ደግሞ የእነሱ ነኝ የሚል ስሜት ፈጠሩና ከልብ መቀራረብ ጀማመሩ። ለካርለት አዲሱ ቍልፍ በሩን ከፈተላት።



t.me/OLDBOOKSPDF

በተለይም ካርለት እንጨት ለመልቀም ወደ ጫካ ስትሄድ እንቅፋቱም፣ እሾሁም የለቀመችው እንጨት ክብደትም፣ ስቅስቅ ብላ እስከማልቀስ ቢያደርሳትም ከልጃገረዶችና ካገቡ ሴቶች ጋር በኩንኩር፣ አጋም፣ ጨውሊንባ፣ እንኮይ፣ ሾላ፣ ዋንዛ...ወደ ተሞላው ጫካ በሄደች ቍጥር የሚያወሩት፣ የሚዘፍኑት፣ ምሥጢራቸውን የሚያካፍሏት ሁሉ ማር ሆኖላታል — ጣፋጭ!

«ባልሽን ትወጅዋለሽ?» ካርለት አንድ ጊዜ አንዷን ባለትዳር ነጠል ብለው እንጨት ሲለቅሙ ጠጋ ብላ ጠየቀቻት።

«ይእ!» በሣቅ እየተፍለቀለቀች ራሷን በአወንታ አወዛወዘች።

«...ይገርፍሻል?»

«ይእ!—ባል ሆኖ እህ ላይገርፈኝ ነው!» በካርለት ጥያቄ እየተገረመች መለሰችላት።

«ለምንድነው የሚገርፍሽ?» ሌላው የካርለት ጥያቄ ነበር።

«ሳጠፋ፣ በትክክል እንድሠራ፣ እሱ ካልመታኝማ አጠፋለሁ።» የታፈነ ሣቋን ለቀቀችው።

«ሲመታሽ አትጠይውም?»

«ይእ!—ለምን? ወንድ ሆኖ ሴትን ካልምታት ታዲያ ስታጠፋ እያየ ዝም ሊል ነው?»

«ከባልሽ ወንድም ጋር የግብረ—ሥጋ ግንኙነት ትፈጽሚያለሽ?»

«ይእ! —ታዲያ ሊቀር ነው! ከባለቤቴ ታናሽ ወንድም ጋር።» ሣቋ ቀደማት።

ይህንና ይህን መሰሉን ውይይት ካርለት ከባለትዳር ሴቶች ጋር ባደረገች ቍጥር መልሳቸው ተመሳሳይ ይሆንባታል። ካርለት ከልጃገረዶች ጋር ስትጫዋወት ደግሞ ለየት ያሉ ነገሮችን ትሰማለች።

«ዕድሜሽ ስንት ነው?» ካርለት ልጃገረዷን ጠየቀቻት።

«ይእ!» በእሉታ አንገቷን ግራና ቀኝ አወዛወዘችላት።

«እጮኛ አለሽ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እ!» በአወንታ አንገቷን ላይና ታች አወዛወዘች።

«እጮኛሽን ታውቂዋለሽ?» ካርለት ጠየቀቻት።

«እ!» ልጃገረዷ የካርለት ጥያቄ ግር አላት።

«ከእጮኛሽ ጋር ተገናኝታችሁ ታውቃላችሁ?» ልጃገረዷ በአሉታ አንገቷን ወዘወዘች።

«ከወንድ ጋር የግብረ–ሥጋ ግንኙነት ጀምረሻል?»

«ይእ! ያማ ይጠፋ ቃል! በደንብ ነዋ» በሣቅ ፍርስ አለች ተጠያቂዋ ልጃገረድ። ልጃገረዷ በካርለት የሞኛሞኝ ጥያቄ ስትሥቅ ውላ ብታድርም አይወጣላትም። ሆኖም ካርለትን ባለማወቋ ብቻ ስሜቷን ካለገደብ ለቃ ልታሳቅቃት አልፈለገችም።

«ግንኙነት ስታደርጊ እንዴት ነው?» ካርለት ጥያቄዋን ቀጠለች። ልጅቷ ያን ጊዜስ ሣቋን ልትቈጣጠር ተስኗት ከርቀት ያሉ ጓደኞቿ እስኪደነግጡ ድረስ በሣቅ ተፍለቀለቀችና የፍየል ቆዳዋን ከኋላ በኩል ለዐመል ያህል ከፍ አድርጋ፣ ጎንበስ በማለት ያደራረግ ስልቷን አሳየቻት።

«እስከ አሁን ከስንት ወንድ ጋር ቀበጥሽ?» ቊጥር አለማወቋን ካርለት ዘነጋች።

«ይእ–ብዙ ነዋ!» መለሰች ልጃገረዷ።

«ካገባችና ካላገባች ልጃገረድ የየትኛውን ኑሮ ትወጃለሽ?»

«ሁለቱም ጥሩ ነው። ልጃገረድነት እንደ ልብ ለመጫወትና ከጐረምሳ ጋር ለመዳራት፤ ባል ማግባትም ልጅ ስለሚወለድ ደስ ይላል» ብላ መለሰች ልጃገረዷ።

ካርለት፣ ልጃገረዶች ሆኑ ያገቡ ሴቶች በባህላቸው የሚረኩ፤ ባህላቸውን የሚያከብሩና የሚወዱ ሆነው አገኘቻቸው። ካለሐፍረትና መሳቀቅ ከልባቸው የቀረቧት ሴቶች ከጓደኛ የሚደብቁት ምሥጢር የሚባል ነገር እንደሌላቸውም በተግባር አረጋገጡላት።



t.me/OLDBOOKSPDF

ክርስት እንደ ክልሉ ኗሪ ሕዝብ ባህል ራሷን ለማኖር በገባችው የራስ በራስ እምነት መሠረት ቆዳ እንደ መልበሱ፣ በባዶ እግር እንደ መሄዱ፣ እንጨት እንደ መልቀሙ ሁሉ ለማረስም ሞካከረች። ስለዚህ እርፍን የሚጨብጡ የእጇ ጣቶችና መዳፏ ለስላሳና ገና ያልገበረ በመሆኑ፣ መላላጡ ወደ እጇ ተሸጋገረ። በዚያ ላይ ከብቶች ወዲያና ወዲህ ሲያላጓት አቅመ–ቢስ በመሆኗ መውደቅ፣ መነሣት ቀጠለች።

ያም ሆኖ ግን፣ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ እጆቿ ጠነከሩ፤ የአካል ጥንካሬዋም ዳበረ። ሌላው ያስቸገራት ልምድ ደግሞ ላሞችን ማለቡ ነበር። በሐመር ባህል የምታርስ፣ ከብት የምታልብ ልጃገረዷ ናት። ክርስትም መጀመሪያ ማለብ ስትሞክር መልኳና ወዟ አዲስ የሆነባቸው ከብቶች አላስጠጋሽ አሏት። ይባስ ብለውም በቀንዳቸው ይደስቋት ጀመር።

አንድ ጊዜ እንዲያውም የጎን አጥንቷን አንዷ ላም ወግታት ለሁለት ሳምንት ያህል ውጋት እያጣደፋት ታማ ቆየች። ሲሻላት ደግሞ ሙከራዋን እንደ ምንም ቀጥላ ከብቶችን በመላመድ ላሞችን ማለብ ጀመረች።

* * *

ከሎ ሆራ በጩርቆሌ ማዝነት በደንብ እየተቀለበ ከቆየ በኋላ ሚዜው ሰውነቱ እንደ ተመለሰ አረጋገጠ። ስለዚህ ከሎ ሆራና ሚዜው ከተሪ (ዲክ–ዲክ) ቆዳ የተተለተለ ቀበቶ መሳይና ኩርኩፋ ይዘው በደንቡ መሠረት ጎይቲ አንተነህን በድብቅ ማሳደድ ጀመሩ።

ጎይቲ አንተነህ ከሎን አልወደደችውም፤ እሷ ልቧ የጠፋባት ለዚያ ጀግና ለደልቲ ገልዲ ነው። መሬቱን በልበ–ሙሉነት እየረገጠ ሲንጎማለል፣ የሷንም ልብ እንደ ጠረማመሰው ሁሉ በፍቅር ታቃስታለች።

በኢቫንጋዲ ጭፈራ ወቅት አንዳንዴ መንደራቸው ብቅ ካለ ስሜት ቀስቃሽ የሆኑትን ሌሎቹን የዳንስ ምቶች ከሌሎች ጋር



t.me/OLDBOOKSPDF

ብትጨፍርም ጭንን በጭን የማግባቱ ጊዜ ቀድማ የምትጋብዘው እሱን ነው። ጭኑን በጭኗ ውስጥ ሲያስገባ የአእምሮዋን እንቅስቃሴ ያዛባና በቍጥጥሩ ስር ያደርጋታል። ከወገቧ ልጥጥ ብላ ወንድ ብልቱ ላይ ትለጠፍበታለች። በዚያ ወቅት ስሜት እንደ ቅቤ ይቀልጥና እሱም እሸት፣ እሷም እሸት፣ እሱም እሸት...ሲደራረጉ ይቆዩና ሁለቱም ሲሸነፉ፣ ውጥረት ሲበዛባቸው ተያይዘው ወደ ጫካ፣ ወደ ልዩው የተፈጥሮ መኝታ ከፍል ጉራ ይላሉ።

ጫካው ውስጥ ወፎች፣ አራዊት፣ እባቦችና ሰዎችም ጭምር ፍቅ ራቸውን በነፃነት ይለዋወጣሉ። ጫካ ውስጥ ትርዒት አቅራቢ እንጂ፣ ተመልካች አይኖርም። «ሁሉም ለየራሱ...» ብቻ መባባል ነው።

ኀይቲ አንተነህ ታዲያ ያ አራዊትን፣ ሰውን የገደለ ጀግና የፍቅርም ጀግና ሆኖ አግኝታዋለች። ጠምዘዝ አድርጎ በጠንካራ እጆቹ ወደ እሱ እያስጠጋ ትንፋሿ እስኪቋረጥ የሚስማትና እንደ ሕፃን ልጅ አቅፎ የሚያጫውታት ሁሉ ትዝታን ያልፈጠረባት ‹እፎይታን ያልሰጣት› ጊዜ የለም።

ከሎ ሆራ፣ ኀይቲ አንተነህን ባየ ቍጥር ከፍቅሩ ፅናት አንፃር ሰውነቱ እየተልፈሰፈሰ ቢርበተበትም ተፈቃሪዋ ግን ኵሩ ሆና ኵሩ ወንድ፣ ጅንን ጀግና፣ ስሙ የገነነ ወንድ ፈላጊ ነበረችና እሱ ለእሷ ሲል ልብሱን አውልቆ ራቁቱን ቢሄድም፣ ሊያደርገው ያላሰበውን እንዲያደርግ ፍቅሯ ቢያስገድደውም፣ እሷ ግን ለሱ ቁብ የማይሰማት ሆነችበት።

የኀይቲ አንተነህ ልብ ያለው ደልቲ ገልዲ ላይ ሲሆን፣ የከሎ ሆራ ልብ የማለለው ደግሞ፣ ለኀይቲ አንተነህ ነው። ቢሆንም ከሎ ሆራ እሷን የማግኘት ተስፋው አልጨለመበትም። እሱም ሆነ ሽያው (ሚዜው) ከቀናቸው ኀይቲ አንተነህን ብቻዋን ሰከም ሰከም ስትል ሊያገኟት ይችላሉ።

አንድ ቀን በሬ ጠምዳ ስታርስ፣ አጥማጆቿ በርቀት ቍጥቋጦው ውስጥ ተደብቀው ሲከተሏት ዋሉ። መቼም እንደዚያን ቀን በከፊል የተመቻቸ ቀን ከዚህ በፊት አላጋጠማቸውም። በሬዎችን በጅራፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽንቶት በማድረግ፣ ከወገቧ ወደ ጎንና ጎን ለጠጥ፣ ዳሌዎቿን ወጣ ገባ...እያደረገች ስለ ሐመር ጀግኖች፣ ስለ ክስኪ ወንዝ፣ ስለ በልጉ ታንጐራጕራለች። አጠገቧ የአጎቷ ልጅ ብቻ ነው ያለው! እሱ ዘወር ካለላቸው ፈጥነው ሊይዟትና የልባቸውን ሊያደርሱ ይችላሉ — አጥማጆቿ። እሱ እያለ ግን ምንም መሥራት አይችሉም። ጎይቲ የተዘጋጀላትን ወጥመድ በጭራሽ አላወቀችም። ዝም ብላ እርሻዋን ታርሳለች። አፍቃሪዋም፣ ከዘምባባው ዙሪያ ካለው ሰንበሌጥ ውስጥ ሆኖ በገዛ ምራቁ ይታነቃል።

አጥማጆቿ፣ የአጎቷን ልጅ ቦርጆ (አምላክ) ከዚያ አካባቢ ዘወር እንዲያደርገው ይመኛሉ። የአጎቷ ልጅ ደግሞ፣ ጎይቲ አንተነህ ልጃገረድ በመሆኗ ብቻዋን ትቷት ቢሄድ ሊደርስባት የሚችለውን አጋጣሚ አሰበ። ኋላ እሱና ሌሎች ጐረምሳ ዘመዶቿ መጠበቅ ተስኗቸው ጀግንነት፣ ሀብት ከሌለው አንዱ ቢተናኮላት የሌሎች ልጃገረዶች ማሽሚጠጥና በጓደኞቿ «ፈሪ» ተብሎ መናቁ፣ እሱንና ዘመዶቿን ስለሚያናድዳቸው ብቻዋን ትቷት ለመሄድ አልፈለገም። ስለዚህ አዳኞች ታዳኟን በቍጥጥር ሥር እንዳያውሉ የአጎቷ ልጅ «የጕሮሮ አጥንት» ሆኖባቸው ሳይሳካላቸው ቀረ።

በሌላ ቀናትም ውኃ ለመቅዳት ስትሄድ፣ ገበያ ስትመላለስ ትከለ ቁመናዋን፣ ፈገግታዋን፣ የሚነጥረውን መቀመጫዋን ቀምሶ ያልጠገበውና እያየ በመሳሳት ላይ ያለው የመንደሯ ጐረምሳ፣ እንደ ሴት ውሻ ከቦ ስለሚከታተላት በድብቅ ለሚከታተሏት እንቅፋት ሆኖባቸው ሰነበተ።

ከሎ ሆራ ከሚዜው ጋር ሜካ ለሜካ ሲዞርና ጎይቲ አንተነህን ሲከታተል ጕሮሮው ሲጮህበት ቢውልም፣ እየቆየ ግን መሰላቸት ጀመረ። ፊት ለፊት ሄዶ የደንቡን ለመፈጸም ያስብና ባህሉን ባለማ ከበሩ የሚደርስበትን ውግዘትና ቅጣት እያሰበ፣ ሐሳቡን ከሕሊናው አውጥቶ ያሽቀነጥራል።

አንድ ቀን ግን፣ ጎይቲ አንተነህ ደንገዝገዝ ባለ ምሽት፣ ከቤቷ ወጥታ መንገዱን ስትነካው እነከሎ ተከተሏት። ከመንደሯ ዘወር እንዳለች የመሮጥ ያህል እየተራመደች ወደፊት ገሰገሰች። ከሎ ሆራ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«የት እየሄደች ይሆን? ብቻዋን ካለፍርሃት እንዴት ትሄዳለች» በማለት ግራ ገባው። ከወር ራቅ ብለው ካሉት መንደሮች ለመድረስ ከመቻሏ በፊት ግን እነሱ ያቀዱትን ከመፈጸም የሚያግዳቸው የለም።

«አቤት–ለስንት ጊዜ እንዳለፋን በግላጭ አገኘናት» ተባብለው ከሎና ሚዜው ተቃቅፈው ደስታቸውን ተገላለጹና ፍጥነት ጨምረው ለመያዝ ወደ ፊት ሽምጥ ሮጡ። እሷ ዘንድ ከመድረሳቸው በፊት ግን ሁለቱም ሩጫቸውን ገትተው ቆሙ።

ከግራር ጥላው ሥር መሣሪያ የያዘና በርኮታው ላየ የተቀመጠ ሰው ያዩ መሰላቸው። አበሽቃቸው፣ ገረማቸውም፣ «ማን ይሆን?» ጠየቀ ከሎ፣ «እንጃ!» አለ ሚዜው። ስለዚህ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ወደ ቃሚው ተከል ገባ ብለው አደፈጡ። ጎይቲ አንተነህ ወደዚያ ሰው እየቀረበች ስትሄድ እየተደነባበረች የሰካራም ጉዞ ጀመረች። ሰውየው መጀመሪያ አላያትም ነበር። ዱካዋን ሲሰማ ግን ከተቀመጠበት ፈንጠር ብሎ ተነሥቶ መሣሪያውን ሲደግን፣ ወደሱ የምትገሰግሰው ጎይቲ አንተነህ ናት። መሣሪያውን አቃንቶ፣ እጇን ከፍቶ ጠበቃት፤ ያው እንደ ልማዱ እንደ ቀንድ የቆመው ጡቷን ከሰውነቱ ስታሻሽለት፣ እሱም የኩራውን ዳሌዋን በሁለት እጁ ወደ እሱ ይበልጥ እየሳበ፣ ትንፋሿ እስኪቈረጥ ድረስ ሳማት። እሷም ሆነ እሱ በተፈጠረው ሙቀት እንደ ቅቤ ቀለጡ።

ከሎ ሆራ፣ ይህን ትርዒት ራሱ እንደሚሠራ ሁሉ፣ እሱም ባለበት ደነዘዘ። ሰውነቱ ሁሉ ባለበት ሲወጣጠር ታወቀው። በእሱ ላይ የተለጠፈችበትና አቅፎ የሚስማት መሰለው። ዋና ተዋናዮቹ ግን ወደ ዋናው እርካታ ጉዟቸው ለመሄድ አንዱ በሌላው ውስጥ ዘልቆ ሲገባ ከሎ ከሰመመኑ ነቃ። የሚወዳት ጎይቲ አንተነህ ከሱ ጋር ሳይሆን ያለችው ከሌላ ሰው ጋር ነው። እሱ ያቀፈውና የሳመው ለካ ግንዱን ነው። እሱ ግንድ አቅፎ ሲስም፣ እሷ ሰው አቅፋ ትቃበጣለች፣ «ዳሚት» አለ ከሎ፣ ሊቈጣጠረው በማይችለው ስሜት ተወጥሮ።

ከሎ ሆራ ሰውዬውን በደንብ ቢያስተውለውም ሊለየው አልቻለም። ሚዜው ግን ነገረው፣ «አያ ደልቲ ገልዲ ነው» አለው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘሎ! «እዎ እሱ ነው፤ ካለሉ እሷን እንዲህ የሚያደነባብራትና ትንፋሿን የሚያሳጣት ወንድ የለም» በማለት፣ በእልህ ወደ ተዋጠ ስሜት ውስጥ ገባ። ሚዜው ግን፣ ከርቀት የሚታየው ቅብጠት አፉን አስከፍቶታል።

ፍቅረኛሞች የፍቅር ጥማቸውን ለማርካት እየደጋገሙ ሲጫወቱ ፉና ተለያዩ። ጎይቲ አንተነህ ወደ መንደሯ ስትመለስ ከኋላ የቀረባት ሰው እንዳለ ሁሉ ልቧ ተንጠልጥሎ አልፈጠነችም። መንደሯ ልትደርስ ስትል ግን አጥማጆቿ እንደ ጥንግ ተወርውረው ያዟት። ዘሎ ሆራ አቅፎ ይዞ፣ እየታገለችውም ቢሆን ኩርኩፉውን አጎረሳት፤ ሚዜውም የተረውን ቀጭን ቋርበት ከፊት ለፊቷ አጋደመባት። በቃ ቃልኪዳኑ ታሠረ፤ ከእንግዲህ ጎይቲ አንተነህ የእሱ እንጂ የሌላ አት ሆንም። ይህ ደግሞ ጎይቲ አንተነህን እልክ ውስጥ ጣላት። ይሆናል ብላ ያላሰበችው ከተሜ መሳይ፣ ልፍስፍስ የሱ ሊያረጋት ነው።

አጇን እያወራጮች ጮኸች፤ አለቀሰች። የመንደሩ ሰው፣ ዘመዶቿ! «አወይ ተደፈርን» እያሉ፣ መሣሪያቸውን እያቀባበሉ ደረሱላት። አባቷ አንተነህ ይመር ከሁሉም ቀድሞ እንደ ደረሰ ልጁን ምን እንደ ሆነች አወቀ። ስለዚህ ምን ሆንሽ ማለት አላስፈለገውም። ከዚያ ይልቅ፣ «ማነው አንቺ ጉድ የሠራኝ?» ብሎ ጠየቃት። ጎይቲ አንተነህ ሳግ እየተናነቃት፣ «በቀደም...የጨርቅ ጎጆ ከእኛ ፊት ለፊት» ብላ ሳትጨርስ፣ አንተነህ ይመር በእፎይታ ተነፈሰ። እንሂድ እንግደል የሚሉት ጐረምሶችም የአንተነህን መቀዝቀዝ ሲያዩ ልጓሙ ወደ ኋላ እንደ ተሳበ ፈረስ ባሉበት ተቅበጠበጡ።

ጎይቲ አንተነህ፣ አባቷና ዘመዶቿ እነዚያን ልፍስፍሶች ለምን ሳያራውጧቸው እንደ ቀሩ ግራ ገብቷት ጠላቻቸው፣ «ምነው ደልቲ ገልዲ በኖረ ኖሮ፣ ይህን ሁሉ በቅጧ ልክ ያስገባልኝ ነበር። ወይኔ ወይኔ...» እያለች ደረቷን እየደቃች፣ አምርራ አለቀሰች።

ማንኛውም አባት በልጁ የወደፊት የሕይወት ዕጣ ማሰቡ የማይቀር በመሆኑ አንተነህ ይመርም ልጁ የወደፊት ዕድሏ ተስፋ ያለው እንዲሆንላት በልቡ ተመኝቶላታል። በተለይም፣ እነካርለት ወደ ወሮ መንደር መጥተው ከእነሱ ጎጆ ፊት ለፊት ድንኳናቸውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ተከለው በነበረበት ወቅት በሕሊናው ውስጥ ተፈጥሮ የማያውቅ አዲስ ተስፋ ወደ ሕሊናው ገብቷል። ከሎ ሆራ፣ «ልጅህን ከሰጠኸኝ አስተምራታለሁ...» እያለ አስጐምዥቶታል። አንተነህ ይመር ያ ሊበላ ያልደረሰውን ተስፋ በማሰቡ ብቻ ወስፋቱ ተልወስውሶ በአፉ ምራቅ ሞልቶበታል።

«ልጂ! አንዷ ልጂ ተምራ፣ እውነት ቀለም ለይታ ማየት ብችል ምን ይሰማኝ ይሆን? አይ የማያልቅብህ አምላክ! እኔ ለሷ የማውቀውን ስመኝላት አንተ በመለኮታዊ ኃይልህ የተሻለ መረጥክላት። ላንተ ከቶ ምን የሚሳንህ ነገር አለ! እኔን ከሞት አፋፍ መልሰህ፣ ከቅዱስ ሕዝቦችህ ጋር አገናኝተህ፣ ጤንነቴንና ሰላሜን ጠብቀህ ለዚህ ያደረስከኝ አንሶ እውነት ልጂ ለቁም–ነገር ልትበቃልኝ? ለዘመናት የተለየኋቸውን ዘመዶቼን ወረቀት ጥፋ ልታገናኘኝ? – እፁብ ነገር!» በማለት አንተነህ እጆቹን ወደ አምላኩ ዘርግቶ አማተበ።

ነገር ግን ይህን ባሰበበት አእምሮ ደግሞ አዲስ ተረኛ ሐሳብ እንደገና ይስተናገድበታል፣ «መቼም የልጂ ቤተሰብ ካርላ ነው። ስለዚህ ልጂ የምታገባው ከፀንጋዞች (ባዕዳን) ወገን ነው። ያለችኝ ልጅ አንድ እሷ ብቻ በመሆኗ የማገኘው ጥሎሽ በርከትትከት ያለ ካልሆነ በረቴ ላይሞላ ነው፤ ከጓሮዬ ጋጥ የማሰማራው በግና ፍየል ላጣ ነው። ማሩስ ቢሆን መጥቀሙ ቀረ። ኧረ ስንቱ ወንድሜ! ይህን ሁሉ ካጣሁ የሐመር ኑሮዬ አስጊ ሁኔታ ላይ መውደቁ ነው።» አንተነህ ይመር ልጁ ጎይቲን እንደሱ ፍላጎትና የወደፊት ዕጣ ዕድል ለደህና ቤተሰብ (ሀብቱ ለሚያስተማምን) ቢድራት እሷም ጠግባ ታድራለች፤ እሱም በረቱን በከብት ይሞላል፤ ሁሌ የሚመኘውንም ጥይት ገዝቶ በዝናሩ ላይ ሻጥ ሻጥ ያደርግበታል። ታዲያ ይህን ሁሉ እምነቱንና ፍላጎቱን ሰቅሎ ሌላ መዓት ወርዶ፣ የፈራው ከደረሰ ምን ሊሆን ነው? ማንንስ ሊወቅስ ነው?

ይህ አቀበቱን የሚጎትት፣ ቁልቁለቱን እየገፋ የሚያሽከረክረው ሐሳቡ እንቅልፍ ነሳው። እንዲያውም በሕይወቱ ሙሉ እንደዚህ የተጨነቀበትና እንደ አንዳንድ ነገረ ፈጅ መንገድ ለመንገድ የሚያወራበትን ምክንያት አላጣውም። ይህ ሁሉ ለልጁና ለራሱ ሲል ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

አንተነህ ይመር ልጁ የጮኸችት ድምፅ እንዳሰማች ነፍሱ በጭንቅላቱ የወጣች መስሎት ነበር። መልሷን ከሰማ በኋላ ግን ለልጁ ኩርኩፉ ያጕረሳትና የተተለተለውን የተሪ ቆዳ ያጋደመላት ከሎ ሆራ መሆኑን እንዳወቀ እንደ እንቦሳ እየዘለለ ሊቦርቅ አማረው፤ እንደ አዕዋፍ ክንፍ እጆቹን እያርገበገበ መብረርም አሰኘው።

‹ደግሞም አስተምራታለሁ› ብሎ ቃል ገብቶለታል። በዓይነ– ሕሊናው ልጁ ተምራ ትልቅ ሰው ስትሆን ታየው። ሐመር ዘመዶቹም ቢሆኑ እንግዲህ ከሎ ሆራና ጎይቲ አንተነህ የፈለጋቸውን ቢሠሩና ያሻው አካባቢ ይዟት ቢሄድ በግል ንብረቱ ጠያቂ የለበትም። እንኳን ባህላዊ ሥርዓቱን አሟላ፤ እንኳን እምነቱን ተከተለ! አንተነህ ይመር ይህን እንዳሰበ አሁንም አንድ ነገር አእምሮውን ቆንጠጥ አደረገው። «ኮይታውስ (ጥሎሽስ) እንዴት ሊሆን ነው? ከብት የለው፤ መሣሪያ የለው። ልብሱ ቢበዛ ለኔ ምኔ ነው? እዚህ ላይ ነገር ይበላሽ ይሆን?» እውነትም አንተነህ ይህን ባሰበ ቍጥር ጉንፋን ሊይዘው ማስነጠስ ጀመረው። ከሴት ልጁ ጋብቻ ኮይታ ካልተቀበለ ታዲያ ነገ ማን ሊደርስለት ነው? በረቱ ባዶ፤ ዝናሩ ጥይት አልባ መሆኑ ቀረ! ደንቡን መጣሱ መሆኑን ሲያስብም ሆዱን ባር ባር አለው።

* * *

ደልቲ ገልዲ በካርለት ባህል አፍራሽነት ቆሽቱ አርሮ የነበረውን ያህል አሁን ግን አእምሮው መዝናናት ጀምሯል። መቼም እሱ የያዘው ነገር መስተካከሉ የማይቀር በመሆኑ እንግዳዋ እሱን መቅረብ ከጀመረችና ግንኙነት ካደረጉ በኋላ ብልጭልጭ ቅራቅንቦዋን አወላልቃ ጥላ ቆዳ መልበሷ፤ በባዶ እግሯ ካለ ጫማ መሄዷ፤ እንደ ሐመር ልጃገረዶች ጸጉሯን አሳጥራ በጨሌና አምባር ማጌጥ መጀመሯ፤ እሱን ፍርሃት እንጂ ሌላ ምንም ምክንያት እንደማይኖ ራት ስለ ተገነዘበ ደስታ እየተሰማው፤ «ኧረ ገና ይቀራታል» ብሎ ፎክከሮባታል።

ካርለት የከሎ ሆራ ከብት ዘለላ ወቅት ከልጃገረዶች መሃል·ሆና ፀንጋዞች ሲገርፏት ግርፊያውን ፈርታ ስትንቀጠቀጥ የነበረውንና ከተገረፈችም በኋላ የጮኸችውን ደልቲ ገልዲ ሰምቶ ሐፍረት



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰምቶቷል፣ «ባለጌ! ልጃገረድ እንዴት ለግርፋት ትንቀጠቀጣለች? ...ቆይ ብቻ ልክ ሳላገባት ከቀረሁማ እኔ አይደለሁም!» እያለ ተማርባታል።

ደልቲ ገልዲ የእንግዳዋ ልጃገረድ አቀራረብ ልቡን የሚያራራ ሆኖ ቢያገኘውም፣ የሐመር ልጃገረዶች የሚያሟሉትን ባህላዊ ደንብ ባለማሟላቷ ግን ቅር መሰኘቱ አለቀረም። ደልቲ መቼም አንዴ ከአፉ አውጥቶ ሊያገባት በመወሰኑ እንጂ ልቡ ያለው ከሌላ ልጃገረድ ጋር ነው። ያችን ልጃገረድ ሊያገባትና የግሉ ሊያደርጋት ቢችል ኖሮ መቼም በሕይወቱ ቀረኝ የሚለው ነገር ባልነበረም ነበር። ግን ልጃገረዲን ሊያገባት አይችልም። አንድ ቤተሰብ ናቸው፤ የልጅቷ እናት የካርላ ጎሳ አባል ናት። እሱም ከዚሁ ቤተሰብ ነው። የካርላ ጎሳ የጉለትን ጎሳ ሊያገባ ይችላል። የካርላ ጎሳ የካርላን ጎሳ፣ የጉለት ጎሳ የጉለትን ጎሳ ግን ሊያገባ አይችልም። ሊጋቡ የሚችሉት ፀንጋዞች (ባዕዳን) ብቻ ናቸው። ይህም ሆኖ ግን ደልቲ ሊያገባት ባይችልም ሊወሽማት ይችላል! ችሏልም። ጉድ የሚፈላው ግን ባል አግብታ የሄደች እንደሆነ ነው።

ባል እንዳታገባ ደግሞ ሊያግዳት አይችልም። ይህን ላድረግ ካለ አባትየው አይቀበለውም። አባቷ ከልጁ ባል ጥሎሽ ማግኘት አለበት። ጥሎሹን ካገኘ ደግሞ የሷ ጉዳይ «ጉም መዝገን» መሆኑ ነው። በእርግጥ ደልቲ ሌላ ባል መጥቶ ከሚወስዳት እጥፍ የሆነ ጥሎሽ ከፍሎ ሊወስዳት ይችል ነበር። ችግሩ ግን ይህ አልነበረም! የሱ ችግር እሷና እሱ የአንድ ጎሳ አባል በመሆናቸው ጋብቻ ሊፈጽሙ አለመቻላቸው ነው። ከሎ ሆራ ግን የጉለት ጎሳ በመሆኑና ጎይቲ አንተነህ የካርላ ጎሳ በመሆኗ ሁለቱ ፀንጋዞች (ባዕዳን) ስለሆኑ መጋባት ይችላሉ።

ጎይቲ አንተነህም እንደ ደልቲ ገልዲ በውኗ መቃዣቷ አልቀረም። ብዙ ወንዶች ታውቃለች፤ እንደሱ ግን ልቧን የሰረቀባት ወንድ የለም። መጀመሪያም ቢሆን ከእሱ ጋር አካል ለአካል ከመነካካታቸው በፊት የወሮን መንደር ኗሪ እንደ አውሎ ነፋስ በነፈሰው ወሬ የደልቲ ገልዲ ጀግንነት እየተወራ፣ ዘፈኑና ሙገሳው ሲቀልጥ፣ በዝናው በእጅጉ መጉምዧቷ አልቀረም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከልጅነቷ ጀምሮ ከአባቷ እየሰማች ያደገችው የጀግንነት ታሪክ፣ የጀግንነት ውሎ፣ የጀግንነት ሞት ነው። ስለዚህ፣ ጀግና ትወዳለች፣ ገዳይ ታከብራለች። በየወንዙና በየእንጨት ለቀማው፣ ማንነቱን ገና የለወቀችውን ጀግና ስም በሐመር ሚካና ተራራ ድምፅዋ እያስተጋባ ዘፍናለታለች። ከልጃገረዶች ጋርም ገና ሳያዩት እየተሟሟቁ፣ «የኔ ነው! የኔ ነው» ተባብለው ተነታርከውበታል።

ጎይቲ እንተነህ ይህን ሰው የምትወደውና የምታደንቀው ከልቧ ነበር። የሌሎችን ልጃገረዶች እውነተኛ ስሜት ግን አታውቅም። ያ ሰው ግን እንዲያ በቀላሉ ሊከሰትላትና ልታየው አልቻለችም።

አንድ ቀን ከሌሎች ልጃገረዶች ጋር ገበያ ውላ ስትመለስ ግን ከወንዶች መሃል ሳዳጉራውን (ሽርጡን) ለብሶ፣ በላዩ ላይ ዝናር የታጠቀ፣ በአንገቱ ልጃገረዶች የሸለሙትን ጨሌ ለማስታወሻ አጥልቆ፣ ከናዱ ላይ አንባር፣ ጣቱ ላይ ደግሞ የመዳብ ቀለበት ያጠለቀ፣ ጸጉሩን በባህሉ መሠረት ተሠርቶ የሰጎን ላባ የሻጠ ሸበላ ላይ ልጃገረዶች ሲጠቋቆሙ፣ «ይእ! ምንድን ነው? ማነው?» ብላ ጠየቀች – ጎይቲ። ልጃገረዶች፣ «ይእ! አታውቂውም ማለት ነው?» ተሟሟቁባት። አፈረችና፣ «በቃ አላወቅሁትም ንገሩኝ» አለቻቸው። «ደለቷ ገልዲን ነው የማታውቂው? ይልቅስ አታሹፊብን» አሏት።

ያን ሁሌ የምታልመውን ሰው፣ እንዲህ እንደ ዘበት አይታው ልታልፍ፣ «እሱ ነው ለካ፣ አፈር በሆንኩት!» አለች ጎይቲ፣ ለምን እንደዚያ እንዳለች ግን አልገባትም። «አሁን ይሄ እውነት ሰው ነው? አቤት ውበት! አቤት ቁመና!» በማለት አፏን ከፍታ ማየቷን ቀጠለች። ጓደኞቿ እርስ በርስ እየተጫዋወቱ፣ እሷም አብራ ያለች መስሏቸው የተለመደ የወሬ ፍትፍታቸውን መጉራረስ ቀጠሉ።

«እከሌን ታውቂዋለሽ?»

«ይእ! እንዴት ነው ታውቂዋለሽ?»

«ግንኙነት አላችሁ?»

«አዎና!»

«አንችስ?»

«እኔም አዎን አውቀዋለሁ።» ይሟሟቃሉ። ደግሞ እንደገና ሌላውን ይጠያየቃሉ። መቼም በሐመር ልጃገረዶች አንድ ላንድ ብቻ መወሰን ጥላቻንም ሊፈጥር ይችላል። የኔይቱ ቆንጆ ባትሆን ነው፣ የኔው ቆንጆ ባይሆን ነው፣ ሌላው (ሌላይቱ) ያልፈለገው (ያልፈለገ



t.me/OLDBOOKSPDF

ችው) ስለሚባባሉ መራራቅ በመሃላቸው ሊፈጥር ይችላል። በሐመር ማኅበረሰብ ፍቅር ነፃ ጨረታ ነው። የጨረታው ዕጣ ግን በሴቷ ፍላጎት ይወሰናል። ስለዚህ አንዲት ልጃገረድ ለብዙ ወንዶች፣ ብዙ ልጃገረዶች በአጠቃላይ ለመንደሩ ጐረምሶች ይሆኑና መቃበጥ ነው።

ጎይቲ አንተነህ ከልጃገረዶች ተለይታ ደልቲ ገልዲን እንደ ተአምር ስትመለከት፣ ጓደኞቿን ረሳቻቸው። ደልቲ ገልዲ ይህ ሁሉ ሲሆን አላያትም ነበር፤ በኋላ ግን ድንገት ዓይኑን ወርወር ሲያደርግ ዓይኗን ቀድሞ ተመለከተው። አያት፤ አየችው፤ እንደገና አያት፣ እሷም አየችው። ብዙ ከቆዩ በኋላ ለሰላምታ አንገቱን አወዛወዘላት። እሷም አጸፋውን መለሰች።

በሐመር ባህል ሰላምታ ከዕረፍት በኋላ ነው። ወዳጅም ሆነ ዘመድ ድንገት ሲገናኝ ሮጦ አይተቃቀፍም፤ ሰላምታ አይለዋወጥም። የሚደረገው ራቅ ራቅ ብሎ መቀመጥ ወይንም መቆም ነው። ከሩቅ አካባቢ የመጣ ከሆነ እንዲያውም ካለምንም የቃል ልውውጥ ቁርበት ይነጠፍለትና ለመቀመጫም፣ ለትራስም የሚገለገልበትን በርኮታ ተንተርሶ ይተኛና ዕረፍት ይወስዳል። በሐመር ማኅበረሰብ መንቀዥቀዥ፣ መዘባረቅ የለም። ሁሉም የሚፈጸመው በሥርዓት ነው።

ስለዚህ እንግዳው፣ «እንደምን ናችሁ?» ይላል።

«ደህና ነን፤ እናንተስ እንደምን ናችሁ?» ይላል አባወራው፥ ወይንም የቤተሰቡ አባል።

«ደህና ነን። ከብቶችስ ደህና ናቸው?» እንግዳው ደግሞ ይጠይቃል።

«ደህና ናቸው። የእናንተስ?»

«ደህና ናቸው።»

«የአባካቢያችሁ ሰላምስ እንዴት ነው?»

«ደህና ነው። እናንተስ ዘንድ?» እየተባባሉ ጨዋታቸውን በሥርዓትና በእርጋታ ይቀጥላሉ እንጂ አፍ እንዳመጣ መዘላበድና «ሲበሉ እንደላኩት» ያንንም ይህንንም ያዝ ለቀቅ ማድረግ የለም። ከዚያ በኋላ የሚበላ ይቀርብና ሚስት ለብቻዋ ወይንም ከልጆች ጋር፣ ባለቤቷና እንግዳውም ለየብቻቸው ቤት ያፈራውን ይቀማምሳሉ።

ጎይቲ አንተነህና ደልቲ ገልዲም ገና እንደተያዩ ጸጥ በማለት አንዱ የሌላውን ሁኔታ ከርቀት ተጠናኑ። በእርግጥ፣ ደልቲ ገልዲም ጎይቲን እንዳየ ሰውነቱ ለሁለት ስንጥቅ ያለ መስሎ ተሰምቶታል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይሁንና ባህልና የወንድነት ወኔው እንዲበረታታ አደረጉት። ደልቲ ኮራ ብሎ ከርቀት ሲያስተውላት፣ ጎይቲም እንደዚሁ መላ አካላቷን ከለችበት ሳታንቀሳቅስ ስታማትር ትቆይና፣ «ይእ!—እንዲህ ነው እንጂ ወንድ!» ትላለች። እሱ ኰስተር ብሎ ያያታል! እሷ ፈገግ ብላ ታየዋለች። ወጉም ይኸው ነው! ሴት ሣቂታ፣ ወንድ ኰስታራ እንዲሆን ይፈቅዳል።

ሌሎች ገበያተኞች በተለይ ልጃገረዶች እሱን፣ ጐረምሶች ደግሞ እሷን እያዩ፣ እያደነቁ ቢያልፉም ሁለቱም ሌላ ነገር ማየቱን ትተው ዓላማቸውን በማጥበብ ሁለቱ ብቻ አንዱ ሌላውን እያደነቀ ማሰላሰል ያዙ። በመጨረሻም ደልቲ ገልዲ ከበርኮታው ላይ ተነሥቶ ወደ ልጃገረዷ አዘገመ።

«መንደርሽ የት ነው?» አላት።

«ወሮ ነው» አለችው።

ከዚያ በኋላ፥ «የማን ልጅ ነሽ? ከዚህ ቀደምስ ተያይተን እናውቃለን?» እያለ ሲጠይቃት ቆየ።

«አዎን፣ በአካል ባላይህም በስምህ ግን አውቅሃለሁ። አባቴ ጀግና ስለሆነ የሌላ ጀግና ሰው ስም ስሰማ ልቤ ይጠፋል። እንዲያውም ስላንተ ሳልዘፍን ውዬ ያደርሁበት ቀን የለም። እንዴት እንደማመልከህ ልቤን በምን ከፍቼ ላሳይህ ይሆን? መቼ ይሆን የማየው? እያልኩ ስመኝ ኖሬ ዛሬ ሳይህ ደግሞ በጣም የምታምር! ከባቴ የበለጥህ ቆንጆ ሆነህ አገኘሁህ» አለችው።

«ይእ! እውነትሽን ነው?» ብሎ፣ ያ ያበጠው ልቡ ይበልጥ ገዘፈበት።

«ለመሆኑ እንዴት እያልሽ ነው የዘፈንሽልኝ?» አላት። የልጃገረዶች ዘፈን ለእሱ አዲስ አይደለም። ልጃገረዷ የምትለውን ለመስማት ብሎ ግን ጥያቄውን ጠየቃት።

«ና እንሂዳ ወደ ጨውሊንባው፣ ዘንባባው፣ ሰንበሌጡ...?» አለችው፣ በጣቷ እየጠቆመች፣ ያን ጊዜ፣ «ቆይኝ መጣሁ» ብሎ የሚሰናበተውን ተሰናብቶ ተመለሰ። ከዲመካ ገበያ ከራቁ በኋላ መንገዱን ለቃ ወደ ጫካ ይዛው ገባች። ካለ ወፍ ዝማሬ ምንም አይሰማም! ከዕፀዋት ዕፀዋት ቱር ቱር የሚሉትም እነዚሁ ወፎች ብቻ ነበሩ።

«እ፣ ህ ልዝፈንልህ አይደል?» አለች ጎይቲ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዳልሽ» አላት። ድምፅዋን አለስልሳ በማውጣት ግጥሟን መደርደር ጀመረች–ክሱ አጠገብ ቆጭ ብላ።

ሰዎች አትዋሹኝ
አልሞተም አንበሳው
አልሞተም ቀጭኔው
ጎሹም እንዲሁ ነው...
የሞተው መች ጠፋኝ
የሞተው ልቤ ነው
ከፉኛ ተጎድቶ
ገዳይ እያለመ በፍቅሩ ተወግቶ...

ብላ በሚስረቀረቀው ድምፅዋ ስትዘፍንለት የሠራ አካላቱን ነሸጠውና:-

«ነይ ተነሽ ጭኔ ላይ ቁጭ በይ» አላት፣ ደልቲ ገልዲ። እንዳላት ሄዳ ጭኑ ላይ ቁጭ ስትል፣ የጭኑ ሙቀት ቆዳዋን አልፎ ተሰማት። አንገቱን እቅፍ አድርጋ ዘፈኗን ቀጠለች።

ትንሽ ከዘፈነችለት በኋላ፣ «ልሳምህ?» አለችው።

ጎይቲ፣ ስሙን በጠራች ቍጥር የፍትወት ፍላጎቷ ስለ ጨመረ፣ «እንደ ፈቀድሽ» አላት እሱም።

ከንፈሯን አሞጥሙጣ ስትጠጋው፣ እሱም በተጠንቀቅ ጠበቃት። ከልቧ ሳመችው። እሱም ትንፋሿ ይቋረጣል ብሎ ሳይሠጋ ጭምቅ አድርጎ ሳማት። ከተላቀቁ በኋላ ጎይቲ አንተነህ ዓይኖቹን፣ አፍንጫውን፣ መልኩን በአጠቃላይ ሁለመናውን ስትመለከት ቆየ ችና ከጭኑ ላይ ተነሥታ ቆመች። ደልቲ ትክለ ቁመናዋን እየተመ ለከተና እያደነቀ አንጋጦ ይመለከታታል።

ጎይቲ አንተነህ በትክክል ውስጣዊ ስሜቷን፣ የጋለውን ፍላጎቷንና ያደረባትን ፍቅር በእርጋታ አጤነች። ከዚያም ያንን ጀግናና ወላንሳ ዝቅ ብላ አየችው። አዎ፣ ለእሱ ነው የዘፈነችለት፤ እሱን ነው ያመለከችው፤ አዎ፣ እሱው ነው፤ ቀስ ብላ የለበሰችውን ቆዳ ገልባ ፊቷን ዞረችለት። ደልቲ በዚህ ወቅት ከሷ ምንም የሚጠብቀው ቃል አልነበረም። ስለዚህ፣ ሳዳጎራውን (ሽርጡን) ፈቶ ጣለውና የፍየል ቀንዱን አቁሞ ጎንበስ ወዳለችበት ተጠጋ፤ አዕዋፍ ዝማሬና ድሬያቸውን በነፃነት ቀጠሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጎይቲ አንተነህና ደሉቲ ገልዲ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ብዙ ጊዜ እየተገናኙ ተጨዋውተዋል። ከሁለቱ አንዳቸውም እንኳን የመሰ ለቶች ስሜት ተሰምቷቸው አያውቅም። ሁሌም መነፋፈቅ፣ ሁሌም መተቃቀፍ ነው የሚያሰኛቸው።

አሁን ግን ጎይቲ አንተነህ ይህን የምታፈቅረውን ሰው ልታጣ ነው። «ምኝነቱ ነው እንጂ መቼም ከእሱ ጋር ዕድሜ ልኬን አልኖር፣ መጋባት እንደሁ አንችል። ምነው ከእሱ ጎሳ ባልተፈጠርኩ ኑሮ» እያለች ራሷን ስታበረታታና ስትጨነቅ ከርማለች። ይባስ ብሎ አሁን ደግሞ እንኳን ማፍቀር ከጅላው የማታውቀው ሰው እጮኛው እንድትሆን አድርጓታል።

ከዚህ በፊት ከዚሁ እንግዳ ሐመር ጋር ወሰለትሁ ያለች የሐመር ልጃገረድ ሰምታ አታውቅም። ሰውየውን ከዚያች ነጭ ጋር አይታዋለች! ጭንቀቱንና ገላውን በጨርቅ ሸፍኖ ተመልክታዋለች። «ይእ! እስኪኮ አይድረስ ነው! አውሬ አልገደለ፣ የሐመር ጠላት የሆነ ሰው አላጠፋ፣ ከሐመር ጠላቶች ሄዶ ከብት አልዘረፈ፣ ጦርነት ገጥሞ ወንድነቱን አላሳየ። እስኪ ከኔ ከሴቷ በምን ተለይቶ እኔን ሚስት ሊያደርገኝ ነው? ከብት፣ ፍየል፣ በግ የለው። እኮ ከምኑ አምጥቶ ጥሎሽ ሊከፍል ነው?» እያለች በብሽቀት ተትከንክናለች። አንዳንዴም የጋብቻው መሥመር ያጠራጥራታል።

«ደግሞ እኮ የገረመኝ የአባቴና የአጎቶቼ ልጆች ይህን ሴታ ሴት ዝም ብለው መልቀቃቸው ነው። የኔ ውርደትና ሥቃይ አልገባቸው ብሎ ነው መሣሪያቸውን እንደ ጭራሮ አንጨፍረው የተመለሱት። ምነው በያዙት መሣሪያ ልሳኑን ዘግተው ባሳረፉልኝ ኖሮ። ወይኔ! ደሉቲን ብዬ ሄጄ ጉድ ተሠራሁ አይደል። ያማ ባይሆን የታባቱ ይደፍረኝ ነበር። ብቻዬን መሆኔ ነው ያስጠቃኝ። እሽ አሁን ሴት ለሴት እንዴት ሆነን አብረን ልንኖር ነው? ልጆቻችንስ በማን ጀግንነት ሊወጡ ነው? የሁለት ሴት ልጆች እየተባሉ መሰደባቸውስ ይቀራል?» እጇን እያፍተለተለች አነባች።

«ወይ ጀግኔ! እንደዚያ ያገር ያለህ እያልሁ ስሙህ እንዚያ በቅቧቶች ከሚሰሙ ምናለ ደሉቲ ሰምቶኝ በነበር! ዋጋውን ሰጥቶ ያሳርፈው አልነበረም? ደሉቲ እንኳን ለእንደሱ ዓይነቶች ቀርቶ ለሌሎች ጀግና ተብዮዎችም መድኃኒት ነበር» እያለች ብታዝንም፣ ከሎ ሆራ ግን በደንቡ መሠረት ሽማግሌዎችን በበነጋው ልኮ ጋብቻው እንደ ተፈቀደለትና በሳምንቱ ኮይታው (ጥሎሹ) እንደ ተወሰነ አረጋገጠች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 11

ካርለት ቆዳ ለባሽ፣ በባዶ እግሯ ተጓዥ፣ እንጨት ለቃሚ ብትሆንም ከዓለም ሕዝብ በመንፈስ አልራቀችም። ሕይወትን እስከ ሥሯ ድረስ ጠልቀው በማየት የኪተኑና የሰው ልጅን ውድቀትና ድል፣ ሽንፈትና ግብ፣ የሕይወትን ለስላሳና ሻካራ፣ አቀበትና ቁልቁለት ጉዳና እየለዩ ሳያሳርሩ ወይም በረዶ ሳያደርጉ የቀመሩትን የታታሪ ሰዎች የሕሊና ጭማቂ የሆነውን መጽሐፍ ታነባለች። አዲሳባ ከከሉ ጋር ስድስት ጊዜ ደርሳ ስትመለስ ይዛቸው የምትመጣቸው መጽሔቶችም በዓለም ላይ በመከናወን ላይ ያለውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ለውጥ እንድትገነዘብ አስተዋጽኦ ከማድረጉ ሌላ ከተለያዩ ጣቢያዎች የሬዲዮ ፕሮግራሞችን ትከታተላለች።

ካርለት በሐመር ለጥናት ለመቆየት ያሰበችው ጊዜ ስላነሳት እንዲራዘምላት ጠይቃ የተፈቀደላት ሲሆን፣ ለዓለም የሴቶች ድርጅት ያቀረበችው የፕሮጀክት በጀትም ተቀባይነት በማግኘቱ በጀቷ ተጨምሮላታል። ይህም ከሉና ጎይቲን የእንግሊዝን አገር እንዲጎበኙ ስቲቭ የተቻለውን ሁሉ እንዲጥርላት ለመንገር አደፋፈራት።

ካርለት በሐመር ኑሮዋ መጽሐፍ ከማንበቡ ሌላ ሙዚቃ ማዳመጥ የምትወድ ሲሆን ከሦስት መቶ ዓመት በፊት የኖረውን የሐይደን ሲንፎኒ፣ የጀርመናዊው የባህን የባሮክ ሙዚቃ የሞዛርትንና የቤቶቨን ፒያኖ ሶናታና ኮንቸት ከጥንቱ ሙዚቃ የምታዳምጥ ሲሆን፣ የተለያዩ ባለ ስርቅርቅ ድምፃውያን የአገረሰብ፣ ሮክና ሮል ሙዚቃ ከማዳመጧም ሌላ በዘመናዊ መንገድ በኮምፒውተር፣ በሒሳባዊ ቀመርና በአጋጣሚ የተቀነባበሩ «አጥንት በሽ» ሙዚቃ ሰው ሠራሽ እጅ ካልገባበት የተፈጥሮ አካባቢ ሆና ስታዳምጥ እሷም እውነተኛው ስሜት ይሰማትና እንባዋ በእርጋታ እየተንኳለለ ሲወርድ ትንሽ ወንዳር እንዳለች ሁሉ ኮለልታው ይሰማታል። ከስሜቷ ታዳምጣለች፤



t.me/OLDBOOKSPDF

ትመሰጣለች፤ ትረካለች፤ ታነባለች፤ ወደ ታች ጠልቃ ወደ ላይ መጥቃ ትጓዛለች። ትክክለኛ ስሜት ንጹሕ አየር ይፈልጋል፤ የተፈጥሮ መዓዛና ውበትን ይሻል። የሐመር ተፈጥሮ ደግሞ ለዚህ የተፈጠረ ነው፤ አዕዋፍ በነፃነት የሚያዜሙበት፣ ዕጽዋት ጎንበስ ቀና የሚሉበት፣ ንጹሕ አየር እንደ ጊሸጣ የሚገመጥበት ነው–የሐመር ምድር!

በዓለማችን ስንቱ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አሮጊቶች…በጦርነት የእሳት ላንቃ ተጠበሱ፤ ስንትና ስንት ሰው በተፈጥሮ አደጋ አለቀ፤ ስንቱስ በረሃብ ላንቃ ተቀጠፈ፤ አቤት ይህች ዓለም ስንት ዋይታ ተሰማባት? ስንቱ እንባውን አፈሰሰባት? እነዚያ ሁሉ እንባዎች እስከ አሁን ብዙ ውቅያኖስና ባሕር ፈጥረዋል፤ ወደፊትም ለቁጥር የሚታክት ውቅያኖስ መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። የዘመናችን ውጣውረድና ጠባሳ ከቶ በምን ይለካ ይሆን?

ካርለት ዋይታው፣ ለቅሶው፣ የዝናቡ ነጠብጣብ ሳይቀር ሕሊናዋን እየሰረሰሩ የሚገቡ እስኪመስላት ተመስጣ ታነባለች። የሙዚቃ ቃናዎችን ትረዳለች። አዎ ማየትማ ሁሉም ያያል፤ መስማትማ ሁሉም ይሰማል። ሁሉም አምስት የስሜት ሕዋሳት አለው። ብዙዎቻችን ግን አምስቱን ሕዋሶቻችንን የምንጠቀመው ለየቅል በተናጠል ነው። ጥቂቶች ብቻ አንድ አድርገው ያዩትን ይዳስሱታል፤ ያሸቱታል፤ ይቀምሱታል፤ ይሰሙታል።

ካርለትና ከሎ ሆራ የታደሉት ይህን ጸጋ ነው። የሚፈልጉትን ነገር በሙላ ሕዋስ መፈተሽ፣ በሥራ መበርታት፣ ለዓላማ ስኬት መሞት፣ ያሰቡትን ከፍጻሜ ማድረስ መቻልን ከልምድ ተማሩ። ስለዚህ ሲጀምሩት ራሳቸውን የወቀራቸው ጭንቀት በአእምሮ ፈውስ ተተካ። ዛሬ ዛሬ ከነበሩበት ይልቅ እየፈሩ የገቡበት ሕይወት ጥልቅና እውነተኛ ነው። ካርለት የደልቲ ገልዲ ሚስት ሆና ለመገረፍ፣ በእንብርክኳ ትንባሆ ለማቀበል፣ ሽፈሮ ቡና ለማፍላት፣ የከብት አዛባ ለመዛቅ ቸኩላለች። ካርለት አሁን የእውነተኛ አንትሮፖሎጂስትነት ስሜት እየተሰማት፣ ራሷን በራሷ የማትደልል፣ ከሕሊና ወቀሳ የራቀችና ከአምላክ የተሰጠውን ጸጋ የተላበሰች ናት። ሁሉን ለማወቅ፣ ከባዱን ለመሞከር መቻሏን ፈትናለች። ከእንግዲህ በዚህ ውድድሯ

t.me/OLDBOOKSPDF

አሸንፋ ለመውጣት ከቻለች፤ «ለመሆኑ በማሸነፍሽ ለምን ደስ አለሽ?» ተብላ ብትጠየቅ መልሷ፣ «ምክንያቱም ውድድሩ አስቸጋሪ ስለሆነ ነው» ብላ መመለሷ አይቀርም። ማሸነፍ የሚያረካው ደግሞ የውድድሩ ውጣ ውረድ ሲበዛና ተወዳዳሪዎችም ጠንክረው ሲገኙ ነው።

«በሕይወት ውድድር ላይ ያለ ሰው ውድድሩ ከራሱ ጋር እንጂ በምድራችን ያሉትን ቢሊዮን ሕዝቦች በማሰብ መሆን የለበትም። ይህን ካሰበ ግን በጭንቀት ብቻ ተደናቅፎ ይወድቃል» በማለት ካርለት ከሉን ደጋግማ መክራዋለች።

* * *

ደልቲ ገልዲ ካርለትን ለማግባት ኮይታው በሽማግሎች እንዲወሰን አስደረገ። ጥሎሹ ብዙም ከባድ አልነበረም፤ ቢያንስ አራትና አምስት ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ሊጨርስና እንግዳዋን የራሱ አድርጎ ያኔ በሚያውቀው ባህላዊ ደንብ ደህና አድርጎ ይገራታል።

ካርለት አሸዋማና ገላጣ ስፍራ ላይ፣ ዙሪያውን የፌጦ፣ የኩንኩሮ፣ የጠዬ የዝግባና ዋንዛ ዛፍና የሻንቆ መንደር ባለበት የኢቫንጋዲ ጭፈራ ቦታ ከደልቲ ገልዲ ጋር ሲጨፍሩ በተለይም ወደ ጫካ ሲገቡ የምታወልቀው የውስጥ ሱሪ፣ ወደ ላይ ከፍ አድርጋ የምትገልበው ልብስ፣ አሁን የላትም። የውስጥ ሱሪዋም ሆነ ልብሷ ቆዳዋ ነው፤ በውኃ መታጠቧን አቊማለች፤ ጸጉሯን በቅቤ የተለወሰ አፈር ትቀባለች። ይህን በማድረጓ የደረሰባት የጤና ችግር የለም። በእርግጥ መጀመሪያ አካባቢ ቆዳዋ ለብ–ለብ የተደረገ ለጋ ስጋ ጥብስ፣ ቀጥሎ ተዘልዝሎ የደረቀ ቋንጣ መስሎ ጠቁሮ ታይቷል። በተረፈ የቈሰለው ሁሉ ድኖላት፣ ወዟ እንደ ሐመር ልጃገረዶች ነው፤ ሕሊናዋም ደስተኛ ነው።

ደልቲ ገልዲ ግን አሁንም ብዙ የምታስተካክለው እንዳለ ያምናል። ያ–ደግሞ የሚሆነው እሱ እሷን አጠቃሎ የራሱ ካደረገ በኋላ ነው። ስለሆነም ጥሎሹን በቶሎ ለመጀመር ወስኗል።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሸንፋ ለመውጣት ከቻለች፣ «ለመሆኑ በማሸነፍሽ ለምን ደስ አለሽ?» ተብላ ብትጠየቅ መልሷ፣ «ምክንያቱም ውድድሩ አስቸጋሪ ስለሆነ ነው» ብላ መመለሷ አይቀርም። ማሸነፍ የሚያረካው ደግሞ የውድድሩ ውጣ ውረድ ሲበዛና ተወዳዳሪዎችም ጠንክረው ሲገኙ ነው።

«በሕይወት ውድድር ላይ ያለ ሰው ውድድሩ ከራሱ ጋር እንጂ በምድራችን ያሉትን ቢሊዮን ሕዝቦች በማሰብ መሆን የለበትም። ይህን ካሰበ ግን በጭንቀት ብቻ ተደናቅፎ ይወድቃል» በማለት ካርለት ከሉን ደጋግማ መክራዋለች።

* * *

ደልቲ ገልዲ ካርለትን ለማግባት ኮይታው በሽማግሌች እንዲወሰን አስደረገ። ጥሎሹ ብዙም ከባድ አልነበረም፤ ቢያንስ አራትና አምስት ዓመት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ሊጨርስና እንግዳዋን የራሱ አድርጎ ያኔ በሚያውቀው ባህላዊ ደንብ ደህና አድርጎ ይገራታል።

ካርለት አሸዋማና ገላጣ ስፍራ ላይ፣ ዙሪያውን የፌጦ፣ የኩንኩሮ፣ የጠዬ የዝግባና ዋንዛ ዛፍና የሻንቆ መንደር ባለበት የኢቫንጋዲ ጭፈራ ቦታ ከደልቲ ገልዲ ጋር ሲጨፍሩ በተለይም ወደ ጫካ ሲገቡ የምታወልቀው የውስጥ ሱሪ፣ ወደ ላይ ከፍ አድርጋ የምትገለበው ልብስ፣ አሁን የላትም። የውስጥ ሱሪዋም ሆነ ልብሷ ቆዳዋ ነው፤ በውኃ መታጠቧን አቊማለች፤ ጸጕሯን በቅቤ የተለወሰ አፈር ትቀባለች። ይህን በማድረጓ የደረሰባት የጤና ችግር የለም። በእርግጥ መጀመሪያ አካባቢ ቆዳዋ ለብ—ለብ የተደረገ ለጋ ስጋ ጥብስ፣ ቀጥሎ ተዘልዝሎ የደረቀ ቋንጣ መስሎ ጠቁሮ ታይቷል። በተረፈ የቈሰለው ሁሉ ድኖላት፣ ወዟ እንደ ሐመር ልጃገረዶች ነው፤ ሕሊናዋም ደስተኛ ነው።

ደልቲ ገልዲ ግን አሁንም ብዙ የምታስተካክለው እንዳለ ያምናል። ያ—ደግሞ የሚሆነው እሱ እሷን አጠቃሎ የራሱ ካደረገ በኋላ ነው። ስለሆነም ጥሎሹን በቶሎ ለመጀመር ወስኗል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቋት ምንም ተቃውሞ አላቀረበችም። እንደ አባቴ ጠላቶች እንደ ማትዋሽ ደግሞ እርግጠኛ ነኝ»አለው ደልቲ ኩስተርና ረጋ ብሎ።

ከሉ ሆራ አንገቱን ቀና አድርጎ ነገሩን ካወጣ ካወረደ በኋላ፤ «ከሐመሮች ጋር በጥቅም ድርድርና በሌሎች ተመሳሳይ ማግባቢያ ዎች መስማማት አይቻልም። እነሱ የኖሩትና ወደፊትም የሚኖሩት በአባት ደንብና ባህል ነው» ብሎ አሰበና ከሉ ሆራ የካርለት ፍላጎት ባለመሟላቱ እያዘነ ወደሷ ተመለሰ።

ከሉ ሆራ ሁኔታውን ለካርለት ሲነግራት መጀመሪያ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች። ስታለቅስ ሲያያት ሁኔታው አላስችለው አለ። ሆኖም ግን አስተያየቱን ከመስጠቱ በፊት ከሉ ካርለት ያስጠነቀቀችውን ነገር አስታወሰ፤ ይኸውም፣ «ሳለቅስ በመካከል ጣልቃ አትግባብኝ፤ የማለቅሰው ደስ ሲለኝ ወይንም በጣም ሲከፋኝ ነው፤ ደስታና መከፋቴን በልቅሶ ስቀበል ሰውነቴ እንግዳውን ገጠመኙን በጸጋ ይቀበልልኛል» ስላለችው ስታለቅስ ጣልቃ አልገባባትም።

ካርለት ትንሽ ቆይታ ደግሞ በሣቅ ተፍለቀለቀች። ከሉም የሕሊናው ውጥረት ትንሽ ቀለል ብሎለት አብሯት ፈገግ አለ። ካርለት ተመልሳ ደግሞ ጸጥ ብላ ማሰብ ቀጠለች።

«ከሉ ስላስጨነቅሁህ ይቅርታ አድርግልኝ። ያለቀስኩት በደልቲ ገልጺ ንጹሕ ሕሊና ነው። ዓለማችን በስግብግቦች የተሞላች ናት። ይህች ደንታቢስ ዓለም አንዱ ሌላውን የሻጉራ የሚያይባት ናት። የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ራሱ ኅብረ–ትርጓሜ ያጣ፣ በሚያ መጣው ጥቅም ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ሰው ግን የሚኖረው ለጥቅሙ ሳይሆን ለእምነቱ ነው። አምስት ዓመት ሙሉ እየተጨነቀ የሚከፍለው ጥሎሽ ይቅርልህ ስንለው አሻፈረኝ አለ። ለራሱ ሊያደርግ የሚፈልገውን በስጦታ ሊቀበል አልፈለገም። ይህን ማድረግ ሕሊናውን እንደ መግደል ቈጠረው፤ ትክክል ሆነም አልሆነም የሚኖረው በሕሊናው ፍርድ ነው። እራሱን ሆኖ፣ እምነቱን ሆኖ ነው የሚኖረው። አጋሰስ ሆኖ ሕሊናውን ለጥቅሙ ሲል ጨፍልቆ ያልገደለ ሰው ነው–ትክክለኛ ሰው።»



t.me/OLDBOOKSPDF

«የማቅሁት ግን ደልቲ ገልዲ እኔ ባሰብሁት አንፃር የሐመር ሴቶችን የጋብቻ ሕይወት በራሴ ላይ ደርሶ ማየት ባልችልም አንተ ጎይቲ እንተነህን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንድታገባ የሚጠየቀውን ጥሎሽ ወዲያው እንክፈልና እኔም ከጎይቲ ጋር ባህላዊ ሥርዓቱን አብሬ መሳተፍ መቻሌን በማሰቤ ነው የሣቅሁት» አለችው።

ከሎ ሆራ «ዳሚት» ብሎ አላመናጨቃትም። የትላንቱን ከሎን ትናንት ከልብሱ ጋር አውልቆ ጥሎታል። ፍቅር የራበው ከሎ ዛሬ የሚያፈቅረው መሃል እጁ ውስጥ ሊገባለት ነው፤ ብቸኛው ከሎ ዛሬ ከሰው ጋር ነው። ከሎ ሆራ ዛሬ አምርሮ የሚጠላው የለውም። አዲስ ልምድ፣ አዲስ የሕይወት ተሐድሶ፣ አዲስ ወኔ በሕሊናው ታጭቋል። አዲስ የተስፋ ሕይወት መኖር ጀምሯል። ካልፈሩት ሁሉም ነገር ቀላል ነው። ብቻ መቻል፣ መጣር...

* * *

ከሎ ሆራ በሦስት ወራት ውስጥ ጥሎሹን ከፍሎ ጨረሰ። ስድስት በሬ፣ አራት ላም፣ ሦስት ጊደር፣ ሰባት ፍየል፣ አራት ዋንኬ በግ፣ ሁለት ስልቻ ማር ለአንተነህ ይመር (ጋልታምቤ) ሽማግሎች የወሰኑትን አቀረበ።

ይህን ጉድ ድፍን የላላ፣ ሻንቆ፣ የወሮ መንደር ኗሪ ሕዝብ አፉን ከፍቶ በአድናቆት ተመለከተው። በሦስት ወራት ውስጥ በካርለት ትብብር ከሎ ሆራ የአንተነህ ይመርን በረት ሞላው።

ደልቲ ገልዲ የጥሎሹን ስጦታ በዝርዝር ሲሰማ ሞራሉ በመጠኑም ቢሆን ተሽኮሽኮ ወደ ታች ወረደ፣ «ይእ! በሦስት ወር ውስጥ ከይታ ከፍሎ መጨረስ መቼም በሐመር እምብዛም ያልተለመደ ነው። እኔ መቼም እንኳን በቅርብ ጊዜ ብዙ ጨረቃ ወድቃና ተነሥታ እንኳን ጥሎሹን ከፍሎ ይጨርሳል፣ አላልሁም ነበር። የዘረፈ እንኳን እንዲህ በአንዴ አይሟላለትም፤ እንኳን ተነጋዴ ተሸምቶ!» ብሎ ለጎይቲ ሲያጫውታት፤

«እኔስ ብሆን ይህ ይሆናል ብዬ መቼ አስቤ? ይህ መናጢ እንግዲህ ከአንተ ሊነጥለኝ ነው አይደል? እንግዲህ የሱና የታናሽ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድሞቼ ብቻ ሆኜ መቅረቴ ነው። ከእንግዲህ ልቤ ከከጀለው ጋር መጫወቱ ሊቀርብኝ ነው። በኢቫንጋዲ ጭፈራ ከልጃገረዶች ጋር እንዳልሄድ መታገዴ ነው። ስንቶች የኔ ታላላቅ ልጃገረዶች፣ እጮኛ ከያዙ በኋላ እንኳን ስንትና ስንት ጨረቃ ሲቀብጡና ሲደሰቱ እኔ ግን ዕድሌ ሆኖ እንደ በቆሎ ደስታዬን በሦስት ወር ተሸለቀቅሁ አይደል!» እያለች እንባዋን መንታ በመንታ አፈሰሰችው።

«እንግዲህ በቃሽ ብዙ አትዘኚ። እኔ መጀመሪያ ፍርሃቴ የነበረው ከሎ ጥሎሹን መክፈል ላይችል ለምን የእሷን ዕድል ይሰብራል ብዬ ነበር። አሁን ጥሎሹን በጣም ፈጥኖ ጨርሷል። ምንም እንኳን ለኛ ባይገልጥልንም ብዙ ሀብት እንዳለው አያጠራጥርም። ስለዚህ መጽናናት አለብሽ።»

«ይእ! አያ ደልቲ ገልዲ፣ አንተ የማገባውን ሰው አላወቅኸውም ማለት ነው። የማገባው ሰው እኮ ሴት ነው። ሴት፤ አይጥ ያልገደለ፤ በጨርቅ ተጀቡኖ የኖረ፤ ፍርሃቱ ከሴት የባሰ፤ እስከ አሁን ከአንድ ልጃገረድ ጋር እንኳን ተጫውቶ ምንነቱን ያላስመሰከረ ሴት እንዳገባ አንተም ጨክነህ ልትፈርድ?» አለችው፣ ጎይቲ ልቅሶዋን በእልህ ተክታ።

«ይእ! እሱ ላይስ ልክ ነሽ። እንኳን የአባቱን ጠላቶች ሊገል፣ ታላላቅ አውሬዎች ሊፈንግል፣ መተኮስ እንኳን የሚያውቅ አይመስ ለኝም» ሲል ጎይቲ ከአፉ ነጠቅ አድርጋ፥ «መተኮስ ከጀመረማ ወንድ ነው! አይጥ ለመግደል ጦር እንኳን ወርውሮም አያውቅም ነውእኮ የምልህ። እና፣ ከዚህ ሰው ጋር እንዴት እንኳኋናለን?»

«ይእ! እንግዲህ ምን መላ አለው። ባለቀ ነገር ነው እኮ የምታስ ጨንቂኝ። ከብት ዘሎ፣ ጨርቆሌ ማገዘ ሆኖ፣ አንችን የተሪ ቆዳ አጋድሞና ኩርኩፉ አጉርሶ፣ ከዚያም አልፎ ጥሎሹን ከፍሎ ከጨረሰ በኋላ ጀግና ባለመሆኑ አንቺን ከወሰደ በኋላ ለአደን በረሃ ይወርዳል፤ በጦርነትም ዘምቶ የአባቱን ጠላት ይገድላል፣ ወይ ይሞታል። እንግ ዲህ ወዲያ ማሰብ ያለብሽ፣ መውደድ ያለብሽ፣ መውለድ ያለብሽ ለሱ ነው» አላት በሕሊናው ውስጥ ሲመላለስ የነበረውን ሐሳብ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኀይቲ አንተነህ ደልቲ ገልዲ በመጨረሻ የሰጣትን ማጠቃለያ እንደ ሰማች ተመስጣ አጤነችው። የሐመር ዕጽዋት ከፊሉ ጠው ልገው ጥቂቶቹም አብበዋል፤ ንፋሱ እንደ ወትሮው ሁሉ አሁንም ወደ ሐመር ይነፍሳል።

ኀይቲ አንተነህ ለምለም ቅጠሎችን ይዛ በንፋስ የምትወዛወዘውን ዛፍ ስታይ በርቀት የማይታዩ የደረቁና የጠወለጉ ቅጠሎች አልፎ አልፎ ይወዳድቃሉ። ወፎቹ፣ ንቦቹ ለምለሟን ቅጠልና ማራኪ አበባዎችን እየዞሩ፣ እየዘመሩ፣ እየቀሰሙ ይበራሉ። ሆድ ባሳት፤ ኀይቲ አንተነህ ልትወድቅ የተቃረበች መሆኗን ጠርጥራለች።

«ደልቲ አቀፈኝ፤» አለችው።

ደልቲ እንደ ታዘዘው ሳዳጎራውን አውልቆ ተጠጋት። እንደ ተለመደው ጠበቅ አድርጎ አቀፋት።

እሷ ግን ጠራችው፣ «ጠበቅ አድርገህ እቀፈኝ፤ ትንፋሼን ሳትጠ ብቅ ሳመኝ፤ ትጨነቃለች፣ መተንፈስ ያቅታታል ብለህ እንዳታስብ። እቀፈኝ፤ ሳመኝ...አካሌ ካንተ ገላ ጋር አንድ እስኪሆን ወዳንተ ለጥፈኝ። በእቅፍህ ውስጥ እንደ ተደሰትኩ፣ በእቅፍህ ውስጥ ነፍሴ ትለፍ» አለችው።

ደልቲ እንደ ተባለው አቀፋት፤ በመካከላቸው አየር እንኳን የሚያልፍበት ቀዳዳ አልተወም። ሁለመናዋን ከፋፍታ ሰጠችው፤ እሱ ደግሞ ሁለመናዋን ዘጋጋላት። በጣም አጥብቆ ዘጋው። እሱ የዘጋውን ማንም ሰው ሳይከፍተው ዘላለም ዝግ እንደሆነ እንዲኖር ኀይቲ ተመኘች።

* * *

ካርለትና ከሎ ሆራ አስፈላጊውን ጥሎሽ ለጋልታምቤ ከሰጡ በኋላ በአንዳንድ ነገሮች ላይ በቂ ውይይት አደረጉ፤ በእነሱ አካባቢ መሟላትና መስተካከል የሚገባውንም አሳክተው ጨረሱ።

ከሎ ሆራ ለጊዜው አጎቱ ቤት እንዲኖርና ሚስቱ ወደዚያ መጥታ ሻላ ላይ እንድትደበቅ፤ ካርለትም ሁኔታውን በቅርብ እንድትከታተል


t.me/OLDBOOKSPDF

አብራት እንድትሆን፤ ካርለትና ጎይቲ ሌሊት ሌሊት እየተነሡ የፍየሎችን በጠዋ እንዲጠርጉና ሽፈሮ ቡናውን አፍልተው፣ ሌሎቹን ሴቶች በመቀስቀስ እንዲደበቁ ሆኖ ባህሉ የሚጠይቀውን ሁሉ ከሉ እንዲያሟላና ጎይቲን ፊት ለፊት ሲያገኛት እንዲገርፏት ተመካከረው ካርለት፣ የከሎ ሆራ እናትና ሌሎች ሴት ጐረቤቶች ጎይቲን ለማም ጣት ወደ አንተነህ ይመር ዘንድ ወደ ወሮ ሄዱ።

አንተነህ ይመርና ሚስቱ ለእንግዶች ልጃቸውን ሲያስረክቡ አደጋ የደረሰ ያህል ሁሉም በያሉበት ለቅሶ በለቅሶ ሆኑ። ከእንግዲህ ጎይቲ አንተነህ ለእናቷ ውኃ አትቀዳላትም፤ እንጨት አትለቅ ምላትም፤ አብራት ውላ፣ አታድርም። ሲደክማት አታበረታታትም። ወልዳ፤ አጥብታ፤ ለአካለ መጠን አድርሳ የኔ ናት ስትላት፣ «ሁለት ዓመት፣ ሦስት ዓመት የምሳሳላት ልጀ ከአጠገቤ አትሄድም» እያለች ስትጽናና ያ ሁሉ ምኞቷ የውኃ ሽታ ሆኖ ሳታስበው ድንገት ጥላት ልትሄድ ነው። ቤታቸው ሊቀዘቅዝ፣ መንደሩ ጭር ሊል ነው።

አንተነህ ይመር በበኩሉ ስቅስቅ እያለ ፊቱን ዞሮ አለቀሰ። እሱ የሚያለቅሰው ግን ለራሱ ነው። ልጁም፣ ሚስቱም፣ እንግዶቹም አያዩትም። ውስጥ ለውስጥ ሲንሰፈሰፍ፣ እንባው ግን እንደ ቀልድ በዓይኑ ፍጭጭ ፍጭጭ ብቻ ይላል። እንባውን እንደ ሚስቱ አያወር ድም። ብዙው ወደ ራሱ አካል እየተስረገረገ ይቆጠቁጠዋል፣ ያቃጥለዋል።

ጎይቲ አንተነህ ለሱ ልጁ ብቻ አይደለችም፤ እኅቱም፣ እናቱም ናት። እንደ እኅት መካሪው፣ እንደ እናት አዛኙ ናት። የሐመሯ ባለቤቱና የሐመር ኑሮው ድልድይ ልጁ ናት። የመኖር ተስፋውና መጽናኛውም እሷው ነበረች። ደግሞ ሆዱን ለመብላት ጥርሶቿና ዓይኖቿ የሱን ስለሚመስሉ የራሱን ምስል በልጁ የሚያይ ይመስለዋል። ስለዚህ፣ «መስተዋቴ ነሽ» ይላት ነበር፤ ድሮ ሕፃን እያለ አንድ ጊዜ ብቻ በመስተዋት መልኩን ያየውን እያስታወሰ።

ጎይቲ አንተነህ የስሙ መጠሪያ፤ የህብቱ ምንጭ ብቻ አይደለችም። ለእሱ ምኑም ናት። መደሰቻ፤ መተከዣ፤ ተስፋው ሆና ኖራለች። አሁን ግን ከአጠገቡ መሄዷ ነው። ጎጆው መቀዝቀዝ ሊጀምር ነው። ከእንግዲህ ዓይን ዓይኗን እያየ ያፈላችውን ቡና



t.me/OLDBOOKSPDF

አይጠጣም፤ «እግርህን ልጠብህ» ብላ፤ እግሩን ስታጥበው ፍቅር ሽቅብ ወደ ሆዱ መፍሰሱ ሊቆም ነው። የረሳው የሕሊና ቅዠትና ውጥረቱ ደግሞ ሊያገረሽበት ነው።

ጋልታምቤ እንግዲህ ለልጁ ለጎይቲ ብሎ የሚኖረውን ሕይወት ዘግቶ እንደገና የራሱን ሕይወት ባለፈው ከቆመበት መጀመር አለበት።

«በቁርጥ ቀን ወንድ ልጅ ቀበቶውን ማጥበቅ አለበት። እስከ አሁን ምትን ለእሷ ስል ስሸሽ ኖሬያለሁ። አሁን ግን የምኖረው ለራሴ ነው፤ ያኔ እኔም እናቷን አይጌን ሳገባ አባቷ ሲሸማቀቁ፣ የእኔ ልብ በደስታ እየዘለለ ፈርጦ አልነበረም? ‹ብድር በምድር› ይሏል ይህ አይደል! በሉ ይብቃ» አለና ሁሉንም በቀላው ዓይኑ ቃኛቸው። ውስጣዊ ስሜቱ ግን ያነባ ነበር።

«መስተዋቴ» አላት አንተነህ ልጁን።

«ይእ!» አለች ጎይቲ በርከክ ብላ ኩማዋ ላይ በመቀመጥ፣ እንባዋን በመንታ—በመንታ እያንዠቀዠቀች ዓይን ዓይኑን በማየት።

«ተይ የኔ ልጅ...ተይ ምርር ብለሽ አትዘኝ። ከወላጅ ጉያ ወጥቶ ወደ ባል መሄድ የአባት ደንብ ነው። የኔ ልጅ ቦርጆ ከከፋ ስንት የደም እንባ እሚያስለቅስ መከራ አለ መሰለሽ» አላት ትከሻዋን ይዞ።

«ይእ...እ! ባል አልኸው፤ ወንድ መስሎህ እኮ ነው...ወንድማ ቢሆን በማን ዕድሌ — ለሴት ዕድሜ ልኬን መሰጠቴን አሁን እውነት አጥተኸው ነው። የኔስ ይቅር፣ ይብላኝ ለልጆቼ...» አለች ጎይቲ፣ ገና የሚወለዱት ልጆች የጀግና ልጅ አለመባላቸው እየከነከናት።

«አይ ምኝት! አንድ ወንድ ጀግና እሚባለው በረፋድ ውሎ እኮ ነው። ይህ ሰው ወጣት ነው፣ ወደፊት ጀግና ለመሆን ጎሽ ወይንም አንበሳ...መግደል ያቅተዋል ብለሽ ሠጋሽ? የማያስጨንቅሽን ነው ልጄ ያሰብሽው» አላት በአባታዊ ተግሣፅ።

«እስቲ እንግዲህ የአንተ ቦርጆ ይርዳው እንጂ እኔማ እንግዲህ ምን እሆናለሁ» አለች፣ ዓይኗን በቀኝ እጇ መዳፍ ግራና ቀኝ እየሞዠቀች።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ቦርጆ ሦስት ምስክሮች አሉት መስተዋቴ–ምድር–ዐሐይና ጨረቃ። እነሱ ይታደጉሽ ልጄ–ንቀት ደግ አይደለም፤ ተነሽ» ብሎ ልጁንና እናቷንም ተቆጥቶ ሸኛት።

ካርለት ጎይቲ ባለቀሰች ቁጥር እሷም ስፍስፍ ብላ አላቀሰቻት፤ «ለካ ሁሉም ከለመደው ሲለይ ማዘኑ፤ ማልቀሱ አይቀርም።» እረ ይህ አብሮ መኖር ምን ያለ ጠንካራ ሰንሰለት ነው» እያለች ጎይቲን ሊያመጡ ሄደው የሆኑትን ለከሎ ነገረችው። ከሎ ይህን ሲሰማ ስሜቱን ፈንቅሎ አንድ ነገር ልውጣ እያለ ሲተናነቀው ቆየና፣ «ካርለት፣ ሰው መማር የሚችል ፍጡር መሆኑን አምናለሁ፤ ዛሬ የአንድን ነገር ውጤቱን ብቻ ሳይሆን ምክንያቱንም ለማወቅ መጣር እንዳለብኝ በመረዳቴ በሕይወቴ ሙሉ እሷንና ወገኖቿን፣ እንዲሁም ጠቅላላውን የሰው ልጅ በሙሉ እያስደሰትሁ ለመኖር ቃል እገባልሻለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ የምጠላውና የምንቀው ሕዝብ የለም። ሁሉም ያስባል፤ ሁሉም እምነት አለው፤ ሁሉም ፍቅር አለው» ብሎ ከሎ መናገር አቃተው። ለመጀመሪያ ጊዜ ዓይኑን እያጠበ የሚወርድ ደስ የሚል እንባ በጉንጮቹ እየተንኳለለ ወረደ። ያ ከሕሊናው የፈለቀው የፈውስ ጠበል የነተበ አስተሳሰቡን አጥቦ አስወገደለት።

ካርለት ተሸበረች፤ ልቧ ለሁለት የተተረተረ መሰላት፤ ሕሊናዋ ዞረባት፤ ስለዚህ እጇን ዘርግታ ከሎን አቀፈችውና ሁለቱም በጋራ አነቡ። የቃል ኪዳን እንባ፤ እውነተኛ ንጹሕ እንባ ወደታች ፈሰሰ። አዎ! የሐሳብ መጣጣም ከሒሳብ ስሌት ቀመር ውጭ ሁለቱን አንድ ያደርጋል። የተራራቀውን ያቀራርባል።

* * *

ጎይቲ አንተነህ ከሎ ሆራ አጎት ቤት እንደ መጣች ፈጽሞ መንፈሷ ሊረጋጋላት ባለመቻሉ ካርለት የምታደርገውን አጣች። ጎይቲ ጽጉሯን ስትላጭ ካርለት ብቸኝነት እንዳይሰማት አብራት ተላጨች። በከሰልና በቅቤ የተለወሰውንም ቅባት መላ ሰውነቷን ስትቀባ፣ ካርለትም አብራት ተቀባች።

ጎይቲ አንተነህና ካርለት አልፈርድ ቆጥ ላይ ከተደበቁ በኋላ ካርለት ጎይቲን ለማጽናናትና ለማደፋፈር ብትጣጣርም አልሳካልሽ አላት። ጎይቲ እንዲያውም ፊቷን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዞረችባት።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት ሁኔታው አስደንጋጭ መሆኑን ብታውቅም ሦስት ወር እስኪሞላቸው ድረስ ቆጡ ላይ መቆየት ነበረባቸውና እስከዚያ ድረስ በመከከላቸው እርቀ—ሰላም እንደሚወርድ ተመኘች።

ቀኑንና ምሽቱን ቆጥ ላይ ከቆዩ በኋላ ለአንድ አፍታ ወረድ ብለው ከሎ ከመምጣቱ በፊት ለመናፈስ ወጡ። ጎይቲ አንተነህ ቆጥ ላይ መውጣቱ አልዋጥልሽ ብሏታል።

«አሁን እሱ የወንድ ልብ አግኝቶ እኔን ሊመታኝ፣ በየትኛው ወኔውና ጀግንነቱ፤ ወይ ሲያየኝ እሱ ራሱ ባልተርበተበተ አይደል? ወይኔ ጎይቲ የወንድ ልጅ ዱላም ይናፍቃል ለካ?» አለች ለካርለት ይሁን ለማን እንደ ተናገረች ሳይታወቅ።

ወደ ጎጇቸው ሲመለሱ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከከሎ ሆራ ጋር ፊት ለፊት ተገናኙ። ከሎ ሆራ ሁለቱንም ሲያይ ደንገጥ ብሎ ቆመ። ካርለት በዓይኗ ጠቅሳ እንዲመታት ልትነግረው ፈልጋ ነበር። ለእሱ «ና ምታት» ብላ በዓይን ለማመልከት እንዴት እንደምታደርግ እስከታስብ ግን እሱ ከቆመበት ደረሱ። ከሎ ሆራ መንገዱን ለቆ አሳለፋቸው። ካለፉ በኋላ ግን ተሰማው፤ በባህሉ መሠረት እንዳያት ደህና አድርጎ መግረፍ ነበረበት። ያን ሲያስብ የብሽቀት ስሜት ታየበት፤ ጎይቲ አንተነህን ይወዳታል፣ ባህሉንም ያከብራል፤ የሚያፈቅሩትን መምታት ቢከብድም ተመችው ባለመመታቱ ቅሬታና ቂም የሚይዝ ከሆነ አካል በማይጎድልበት መንገድ መምታቱ የሚያመጣው ችግር የለም።

«ወደፊት ግን ይህን ጥፋት መድገም የለብኝም። በመምታቴ ጎይቲ አንተነህን የሚሰማት ነገር የለም። እንዲያውም እሷን ባለመደብደቤ ቅሬታ ሊያድርባት ይችል ይሆናል» እያለ፣ ራሱን ወቅሷል።

ካርለትም በበኩሏ ትንሽ በሽቋታል። ከሎ ሆራ ጎይቲ አንተነህን ፊት ለፊት ባገኛት ጊዜ ሁሉ እንዲገርፋት ተመካክረዋል። ጎይቲ አንተነህ ደግሞ የከሎን የፍቅር ፍርሃት ባለመረዳት ሲርበተበት ስታየው ባሕርይው ያስጠላታል። ከሎ ወንድ ወንድ አልሸትሽ ብሏታል።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከሎ ትክክል አልሠራም። እሱ ጎይቲን ልክ ከተማ እንዳየው ብዙ ሕይወቱን እንዳሳለፈበት በጠባይ ሊያግባባት፣ ሊያቀርባት፣ ፍቅሩን ሊገልጽላት ይፈልጋል። ጎይቲ ግን ከወንድ ልጅ በቅድሚያ የምትፈልገው ኩስታራነት ነው፤ ዥሩ ወንድ፣ ሽንቆጥ የሚያደርግ ወንድ፣ እሷን በፍቅር ገርቶ፣ በፍቅር አብሯት መጋለብ ይችላል። ሴት ልጅ ዱላ ሲያርፍባት የሴትነት ፍላጎቷ ከአሸለበበት ይነቃል። እምጭ እምጭ የሚላት፣ ፍቅር የሚናፍቃት፣ ድሪያ የሚታወሳት ያኔ ነው፤ ከሎ ደግሞ ይህን አልተረዳውም። እንግዳ ነገር ሆኖበታል። ሕጉን እያወቀ በተግባር ግን አያከብርም። ይህ ደግሞ ስሕተቱ ነው።» ካርለት በእንግሊዝኛ ለጎይቲ ነገረቻት። ጎይቲ አንተነህ ግን ያለችው በጭራሽ አልገባትም፤ እንግሊዝኛ ደግሞ የት አውቃ!

ጎይቲ አንተነህ አጠገቧ ያለችው ቀውስ ብቻዋን ስትለፈልፍ ብትደነቅም፣ እሷም ተመሳሳዩን ፈጸመች።

«ይኸዋ ይህ ቦቅቧቃ! እንኳንስ ሲያየኝ እንደ ወንዶቹ ሊገርፈኝ ይቅርና መንገድ ለቆ አሳለፈኝ። ባል እኔ ነኝ! እሱ ሚስት ነው። እንዴት ሆኜ ከዚህ ሴት ጋር እኖራለሁ? ምነው ያን ቀን ደልቲ ገልዲን ብዬ ባልሄድሁ ኖሮ፤ እሱን ብዬ በመሄዴ ቀናው እንኳ የታባቱ ያገኘኝ ነበር– ይህ ሴት። ሴት ልጅ የባሏ ዱላ ሕይወቷ፣ ፍቅሯ ነው። ታዲያ ይህ ሰው እኔንኮ ሕይወቴን እያጠፋ ነው። እሺ የኔስ ነገር ይቅር ነገር ግን የሚወለዱት የሁለት ሴት ልጆች መባላቸው አይደል? ወይኔ ያልታደሉት። ወይኔ ወይኔ» እያለች፣ እንባዋን ታወርደው ጀመር።

ካርለት ትንሿን ቴፕ ከፍታ የምትለውን እየቀዳች፤ በማስታወሻ ደግሞ የሚሰማትን ትከትባለች። ካርለት በአንዳንድ ሁኔታ ላይ እሷም ራሷ እየተስማማች መጣች። በአገሯም፣ አንዳንድ እውቅ ሴቶች ስለ ወንድ ፍቅረኛቸውና ከእሱ ስለሚጠብቁት ባሕርይ ሲያወሱ ነካ አድርገው የሚያልፉት ነገር አለ፣ «ከፍቅረኛዬ ጋር ስንላፋ፣ ስንታገል፣ የፍቅር ዱላ ገላዬ ላይ ሲያርፍ ልቤ እስኪጠፋ ድረስ ራሴን እሰጠውና የሱን ደግሞ ለመውሰድ ሙሉ ፍላጎት አሳያለሁ። ከዚያ በኋላ የምንሠራው የፍቅር ጨዋታ ሁሉ እንደ ‹አይስክሬም› እየጣፈጠኝ፣ መላ አካሌ ከጸጉር እስከ እግር ጥፍሬ በርካታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲንበሸበሽ ይሰማኛል። እንደዚህ አድርገው ከኔ ጋር የተጫወቱ ወንዶች የፍቅር ዙፋኑን ማንም ሲነጥቃቸው አይችልም» ብለው የተለያዩ ሴቶች አስተያየት ሲሰጡ ሰምታለች።

እሷም ቢሆን አንዳንድ ልምዶችን አሳልፋለች። አንድ ጊዜ፣ ሰማ ጃክ ነው ብሎ የተዋወቃት አሜሪካዊ፣ ማንችስተር ውስጥ ለጉዳይ መጥቶ አንድ የምሽት ዳንስ ላይ ይተዋወቃሉ። ካርለት በእርግጥ ወደ ዳንሱ ቦታ የሄደችው ከወንድ ጓደኛዋ ከዴቪድ ጋር ነው። ታዲያ አሜሪካዊው አንድ ሁለት ጊዜ በትእዛዝ መልክ ዳንስ ጋበዛትና ሰውነቷን በጠንካራ እጆቹ ጠበቅ አድርጎ እያሸ፣ እያሻማት። ቀደም ብላ ባሳለፈችው ሕይወቷ ወንዶች እንደዚያ ሰው አድርገዋት አያውቁም። ሰውነቷን የሚደባብሱት ቀስና ላላ አድርገው ነው። ሰውዬው ግን መሞረዱ አንሶ በረጅም እጁ መቀመጫዋን ደህና አድርጎ ቸብ ቸብ አደረገላት። «ተው» ማለት እየፈለገች፣ ቃሉ ግን ከጉሮሮዋ አልወጣልሽ አላት። በእርግጥ፣ ዴቪድም ከሌላ ሴት ጋር እየደነሰ ስለነበር እንሱን ልብ አላላቸውም።

አሜሪካዊው ፍጹም በማታውቀው መንገድ ሰውነቷን እየመ ታታ፣ እየሞረደ፣ ልቧን ስልቱን አስቀየረው፤ ከንፈሯን እንኳን ሲስማት የንክሻ ያህል ሆኖባት እግሯን አንሥታ ለመጮህ ትንሽ ቀርቷት ነበር። ግን አልጮኸችም። ዳንሱ አብቅቶ ሲለያዩ ካለልብ ወደ ቦታዋ ተመለሰች፤ እንደ ምንም ታግሣ ሁለት ጨዋታዎችን አሳልፋ ልቧን ወደ ቦታው ለመመለስ ወደ አሜሪካዊው ሰው ሄደች። «ቶንጅት እንደምትመጪ አውቅ ነበር...» ብሎ አሜሪካዊው ተመጻድቆባታል። ግን ፊቷን አዙራ አልተመለሰችም፤ ተመልሳ ከነና እጆቹ መሃል ወደቀች። ሞራርዶ፤ ቸባችቦ፤ ብድግ አድርጎ ተሸክሟት ወደ አንድ ክፍል ሲገባ፣ እግሮቿ አልተፈራገጡም። እጆቿ አልተወራጩም፤ አፏም አልቀባጠረም።

ካርለት ይህንን አሜሪካዊ እስከ አሁን ድረስ በዚያች ለሰዓታት በቆ በዘለቀች የፍቅር ጨዋታ የማትረሳው ትዝታ አስታቅፏት ኮዷል። ያንን ሰው ለብዙ ጊዜ የተካው ወንድ አልነበረም። ኖራ ኖራ ግን ሐመር ላይ ተመሳሳዩን አገኘች። የሷም ብቻ ሳይሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

የጎይቲም የሆነው ሰው በእርግጥ ለየት ያለ በመሆኑ ሳይወዱ በግድ ሌላ ወንድ ቢያስንቃቸው አይፈረድባቸውም።

ካርለት ቆጥ ላይ እንዳሉ እንዲህ በሐሳብ ተዘፍቃ ቆየችና እናቷ ትዝ አሏት። ስለዚህ፣ ደብዳቤ ለመጻፍ ብዕርና ወረቀቷን አስተካከለችና መጻፍ ጀመረች።

ውድ እናቴ፣

ምን ጊዜም እንደማፈቅርሽ፤ እንደማልምሽ የምትዘነጊ አይመስለኝም። «እማ፣ አንቺን በማጣቴ እንዴት ጎደሎ እንደ ሆንኩ ልገልጽልሽ ይከብደኛል። እኔና አንቺ አሁን ያለነው በተለያየ ዓለም ነው። የምትዪኝ ቢገባኝም፣ የምልሽ ግን ሊገባሽ አይችልም። ልጅሽ አሁን ሌላ ሰው ነኝ። ከድሮው እኔነቴ የአሁኑ ሕይወቴ ትርጉም ያለው ሆኖ ይሰማኛል። እማ! እንዴት ብዬ አሁን ያለሁበትን ሕይወት ልግለጽልሽ ይሆን? ከበደኝ። እማ! ይህ ልዩ ዓለም የራሱ የሆነ ተፈጥሯዊ ፍቅርና ደስታ ያለው ጣፋጭ ዓለም ነው። ገና ያልተበረዘ፣ ንጹሕ ዓለም! ብክለት ያልደረሰበት ድንግል ምድር ነው። ማንም ከርቀት የሚመስለውን ሊል ይችላል። እኔ ያየሁትን ያየ ግን መቼም ከዚህ የተሻለ ግሩም ዓለም ይኖራል ብሎ ማሰቡ ያጠራጥረኛል። ሰዎች የሚኖሩት በሕገ–ልቦና ነው። ተካፍሎ መብላት! ተከባብሮ መኖር! መግባባት እውነተኛ መኖሪያቸው እዚህ ነው። ሌላው ግን ውሸት–የውሸት ውሸት ነው።

እማ! አሁን አሁን ምን እንደሚሰማኝ ታውቂያለሽ? የሌላው አካባቢ ብክለት ወደዚህ ሲገሰግስ እያየሁ እወራጫለሁ። ምን ልበልሽ? ለመሆኑ የምልሽ ይገባሻል?...

ካርለት

ካርለት ደብዳቤውን አጣጥፋ ከመከተቷ በፊት የእንባ ዘለላዎች ዱብ ዱብ አሉባት። አሸገችው።

ጎይቲ ሌሊት ስትነሣ፣ ካርለትም ከእንቅልፏ ነቃች። ጎይቲ አንተነህ ከቤት ወጥታ ወደ ፍየሎች ጋጥ ስትሄድ ተከተለቻት። ጎይቲ የፍየሎችን በጠጥ ማጽዳት ስትጀምር፣ ካርለትም እንደሷው


t.me/OLDBOOKSPDF

ማጸዳዳት ጀመረች። ካርለት ጎይቲን እየተከተለች ወደ ከብቶች በረትም ሄዳ የከብቶችን እበት ጠረገች። ከዚያ ተመልሰው የሸፈሮ ቡና ማፍያውን እንስራ ጎይቲ ስትጥድ፣ ካርለት እንጨቱን አቀራረበ ችላት። ጎይቲ አሁን አንድ ነገር መጠርጠር ጀመረች። ግን እንዴት ሊሆን ይችላል? ከሆነም ግን የሚረዳት አገኘች ማለት ነው። ጎይቲ አንተነህ ካርለትን የከሎ ሆራ ሁለተኛ ሚስት እንደ ሆነች ገመተች። ስለዚህ፣ ማንኛውንም ሥራ ተካፍለው መሥራት አለባቸው ማለት ነው። ጎይቲ አንተነህና ካርለት ሥራቸውን ጨርሰው ቡናውን ካፈሉ በኋላ ቆጣቸው ላይ ወጡ። ቆጥ ላይ እንዳሉ ጎይቲ አንዳንድ ነገሮችን ማውጣትና ማውረድ ጀመረች።

«ይህ ሰው ምን ያለ ሰው ነው? የኔን ሦስት አዲስ ጨረቃ ብቻ ገና እንደታየ ጥሎሹን ከፍሎ ጨረሰ። ሌላው ሐመር ግን ለጥጥር የሚታከት አዳዲስ ጨረቃ ወጥቶ እንኳን ላይሳካለት ይችላል። ደግሞ ይህ አንሶ፣ በአንድ ጊዜ ሁለት ሚስት አምጥቷል። ለእኔ አባት የከፈለውን ኮይታ ለዚችኛዋም ሴት አባት መቼም መክፈሉ አይቀርም። በእርግጥ ሁለት፣ ሦስት ከዚያም በላይ ሚስት ያላቸው ሐመሮችን አውቃለሁ። ሁለት ሚስት ባንድ ጊዜ ያገባ ግን እንኳን ላይ ሰምቼም አላውቅም። ደግሞኮ ይህች ሁለተኛ ሚስቱ አስባ በሐመር ባህል መሠረት አትሠራም። የምትሠራው እኔን እያየች ነው። ስለዚህ፣ የመጀመሪያ ሚስት በመሆኔ ደስ ሊለኝ ይገባል። ለሷም የማደርገውን ሁሉ እንድትፈጽም አደርጋታለሁ» ብላ ጎይቲ አሰበች።

ካርለት፣ ጎይቲ አንተነህ በባህሉ መሠረት የምታደርገውን ሁሉ በማስታወሻዋ ትለቅማለች። ጎይቲ አንተነህም የምታሳያትን ትፈጽማለች። ካርለት፣ ጎይቲ ይህን እናድርግ፣ ያንን እናድርግ ስትላት የተግባቡ እየመሰላት ሌላ ሌላ ጨዋታም ልታጫውታት ስትፈልግ መልሳ ኩርፍ ትልባታለች። ጎይቲ አንተነህ እንዲያውም የከሎ ሚስት ስሙን የማታውቀውን ነገር ይዛ በነጭ ነገር ላይ ስትጫጭር ስታያት፣ ምኒቱ የአዋቂ ጅል ናት በሉ! ገና መጫዎቻዋን ያልጣለች» ብላ አንድ ጊዜ ብዕርና ማስታወሻዋን ወርውራባታለች። እንዲህ በመሆን ሁለት ሳምንት እንዳለፋቸው ግን ካርለትና ጎይቲ መግባባት ጀመሩ። እንዲያውም ጎይቲ ሐመርኛ ለካርለት


t.me/OLDBOOKSPDF

ስታስተምራት፣ ካርለት ደግሞ የእንግሊዘኛ ፊደልና ቃላት ለጎይቲ ማስተማር ጀመረች።

ከሎ ፊት ለፊት ካገኛቸውም ሁለቱንም በተለይ ካርለትን ለከፍ ጎይቲን ደግሞ ጠበቅ አድርጎ ይገርፋል። ካርለት ግን እሷን ለከፍ እያደረገ መምታቱን ስላልወደደችለት ጠበቅ አድርጎ እንዲመታት ጠይቃዋለች።

ጎይቲ አንተነህ እሷን የከሎ ሁለተኛ ሚስት አድርጋ መገመቷም በቀላሉ የጋብቻውን ሥነ–ሥርዓት ለመከታተል አመቺ መሆኑን አልተጠራጠረችም። ካርለትና ጎይቲ በወራቸው እጅግ በጣም የተግባቡ ሆኑ። መሣቅ፣ መጫወት፣ መላፋትም ቀጠሉ። ጎይቲ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቃላትን መጻፍና ማንበብ ጀመረች፤ በዚህም ከካርለት ጋር መግባባት ቀጠሉ። ካርለትማ ሐመርኛውን የራሷ ቋንቋ አደረገችው።

ጎይቲ አንተነህ ዘጠና ቦታ የቋጠረችውን ቋጠሮ በቀን በቀን አን ዳንዱን ፈትታ ጨረሰች። ይህ ማለት ደግሞ ሦስት ወር ሞላት ማለት ነው። ስለዚህ በቋጠሮው የተያዘው ቀጠሮ፣ ቋጠሮው ሲያልቅ አለቀ።

ልክ በሦስተኛው ወር ላይ ከሎ ሆራና ጎይቲ አንተነህ አካል ላካል ከመገናኘታቸው በፊት ጎይቲ አንተነህ አንድ ቅል ወተትና አንድ ቅል አሸዋ ይዛ በና ማኅበረሰብ ክልል ሙቀጫ ከተባለው መንደር ከካርለት ጋር ሄዱ። ሽማግሌው ሌሎችንም የዕድሜ እኩያዎቻቸውን ጠርተው ሸፈሮ ቡና ሲጠጡ ቆዩና፣ «ችግርና ረሃብ ከእኛ ይራቅ፤ ፍቅርና ሰላም አይለየን፤ የሰማይ አፎች አይዘጉ፤ ፀሐይ መውደቅ መነሣቷን አታቋርጥ፤ ከብቶቻችን ይርቡ፤ አንቺም ውለጅ ከበጅ» ብለው የቡናውን ውኃ በራሷ ላይ አርከፈከፉባት። ከዚያም ወተት የያዘውን ቅል ሰጥታ፣ አሸዋ የያዘውን ግን ተቀብላ እንደ ጨረሰች ካርለት ለሽማግሌዎቹ ያመጣችውን ሸፈሮ ቡናና አንድ ጀሪካን አረቄ ሰጥታ በመመረቅ የመልስ ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ሻንቆ መንደር እንደ ደረሱ ጎይቲ አንተነህ አሸዋ የያዘውን ቅል ግርግም ላይ ሰቀለችና ከሎ ሆራ ከሚተኛበት ግርጌ በቆሎ በተን አደረ ገች። ይህ ማለት ደግሞ፤ «ሰውነቴ አምሯል፣ አሁን አንተን ለማገዝና



t.me/OLDBOOKSPDF

ናትና ለማስደሰት ዝግጁ ነኝ። ከዛሬ ወዲያ በውቢቱ የግል ንብረትህ ኮርተህ የፈለገህን ልታዛት ትችላለህ» የማለት ምልክትና የሴቷን የማበረሥጋ ግንኙነት ፍላጎት የሚገልጽ መሆኑን ከሎ ሆራ ያውቃል።

ከሎ ሆራ፣ በተቻለው ሁሉ ሌሎች ወንድ ወገኖቹ የሚፈጽሙትን ለማድረግ ዝግጁ ስለ ነበረ ከኀይቲ በስተቀር ማንም ወደሌለበት የአጎቱ ጎጆ ሲሄዱ ልቡ ዳንኪራ መታበት።

ያችን የሚያፈቅራትን የሐመር ውብ ቀንበጥ ሰውነቷን ሊዳስሰው ነው። ቀንና ሌሊት ያለማትን ቆንጆ ዛሬ ያላትን ሁሉ ለመፈጸም እየጠበቀችው ነው። ወደ ጎጆው በተቃረበ ቁጥር እናቱን እንዳየ ሕፃን ቦርቅ፣ ዝለል፣ አየሮፕላን ሄደህ ሳማት፣ እቀፋት፣ ይዘሃት መሬት ላይ ዥዋ ብለህ ውደቅ አሰኘው።

ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ ለማድረግ ባህሉ አይፈቅድለትም። ስለዚህ ራሱን ለመቆጣጠር እየሞከረ ወደ ጎጆዋ ውስጥ ዘለቀ። ኀይቲ አንተነህ ከሎ ሆራ ወደ ቤት ሲገባ አንገቷን ቀልበስ አድርጋ ፊቷን ሳታዞር ቆማለች። የአንድ ሰው ዓይን ብቻ የምታደርገውን በቀዳዳ ሆና ይከታተላታል።

ከሎ ፊቱን ዞር አድርጎ በተነጠፈው የከብት ቁርበት ላይ በጎኑ ተኛ። ኀይቲ አንተነህ ቀስ ብላ ዞራ ስታየው፣ ፊቱን ዞር መጋደሙን አረጋገጠች። ከውጭ በኩል ሳታየው የሚከታተላት ዓይን ግን አሁንም በጉጉት መከታተሉን አላቆመም።

ኀይቲ አንተነህ ቀስ ብላ መራመድ ቀጠለች። ከሎ ሆራ ልቡ እንደ ታምቡር እየደለቀ አስቸገረው። ለዓመታት ባለችበት ቆማ የቀረችም መሰለው። ስለዚህ፤ «ዞረህ እያት፣ ዞረህ ቃኛት፣ ዞረህ እምጣት» አሰኘው፤ እንዲህም እንዲያደርግ ግን አይችልም።

ኀይቲ አንተነህ ቀስ ብላ እየተራመደች ሄዳ አጠገቡ እንደ ደረሰች ከወገቧ በታች የለበሰችውን ቆዳ ገለብ አደረገች። ያ ከውጭ በኩል ትርዒቱን የሚመለከተው ሰው ስሜቱ ቢወጣጠርበትም ማየቱን ቀጠለ፤ ፊቱን ማዞሪያው ጊዜ እንደ ተቃረበ አልጠፋውም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሎ በጭንቀት ሊሞት ነው። እነዚያ ግጥም ያሉ እግሮቿ፣ ኮረብሎ ነጠር ነጠር፣ ወዝወዝ የሚለው ዳሌዋ ወደሱ እየተጓዘ ነው! በሙሉ መብት ሊያቅፈው ተቃርቧል! ውብ ጥርሶቿና የሚያባብለው ዓይኗ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እሱን እሱን ሊያዩት ነው። ስለዚህ ስሚቱ አካሉን ጥሎ ሰገረ! አካሉን ሊያስከትል ሲል ግን ከጎኑ ጋደም ስትል አዳመጠ። ገላዋ ገላውን ነካ አደረገው! ንክኪው ከሎን ከፉኛ ናጠው! ሁለቱም ግለኛል። የሱ ትዙሳት ለሷ፣ የሷ ለሱ ፈውስ እንደሚሰጣቸው ያ በጉጉት የሚከታተላቸው ሰው እየገመተ ነው።

ከሎ ሆራ ፊቱን ዘወር ሲል የጎይቲ አንተነህን ዓይን ለአመል ያህል ተመለከተው። እንደ ንጋት ኮከብ ጠይም ፊቷ ላይ ይንቦገቦጋል። እጁን ሰደድ አድርጎ አቀፋት፣ እሷም አቀፈችው። ከንፈሩ ወደ ከንፈሯ፣ ከንፈሯ ወደ ከንፈሩ ተጓዙ። የጎይቲ የንብ አውራ መሳይ ወገብ ወደፊት ተለጥጦ ከከሎ የፍየል ቀንድ ጋር ፍልሚያ ገጠመ። አንዱ ወደ ኋላ ሲያፈገፍግ ሁለተኛው ተንደርድሮ ሄዶ ሲወጋ፣ እንደገና ሲያፈገፍግ ሌላው ሲንደረደር፣ ከላይ አንዱ ሌላውን ሲጎርስ ትንሽ ቆዩና ጎይቲ አንተነህ ፊቷን ዞራ ጀርባዋንና መቀመጫዋን ለከሎ አዞረችለት! በዚህ ጊዜ ከሎ ሆራ እየተመቻቸ ሲጠጋ፣ ቁርበቱ ዝማሬውን ቀጠለ።

ካርለት በሕይወቷ እንዲህ የሚማርክ ሕይወት አይታ አታውቅም። ያየችውን ሁሉ ልክ እሷ የምታደርገው ይመስል ሳይታወቃት ወገቧን ሰብቃለች! መጨረሻ ላይ ግን ሌሎች ወደ ማራኪው ዓለም ሲነጠቁ እሷ ግን ተመልካች ኖራ ደረቅ መሬት ላይ እንደ ቆመች ስትቀር፣ «አምላኬ!» ብላ ዓይኗን ጨፈነች።

ከሎ ሆራና ጎይቲ አንተነህ አካል ለአካል ተገናኝተው ከተጫወቱ በኋላ የፍትወት ስሜታቸው ረግቦ ትንሽ ተንፈስ እንዳሉ ዕድሜዋ አጭር የሆነ እንቅልፍ ሸለብ አረገቻቸው። ጎይቲ ከተኛችበት ስትነሣ የታጠፈውን ቆዳዋን ወደ ታች ስትለው እንደ ፍየል ጅራት ግራና ቀኝ ውን ውን አለ።

ከሎ ሆራ ሳዳጎራውን በአጭሩ አገልድሞ ሲነሣ ጎይቲ በእጇ መዳፍ የያዘችውን ትንባሆ ለመስጠት ተንበርክካ እጇን ዘረጋችለት፣ ከሎ በደንቡ መሠረት እሷን ሳያይ ትንባሆውን ተቀብሎ መሄድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበረበት። እሱ ግን አልቻለም። ዓይኖቿን እያቁለጨለጨች አንጋጣ በአክብሮት ትንባሆ የምታቀብለውን ሴት ከልቡ ያፈቅራታል፤ ፍቅሯ ረትቶ ልብሱን ጥሎላታል፤ ሐሳቡ እየባዘነ እንደ ኢንሹ ቁጥቋጦ ለቁጥቋጦ ተሸሎከሎኮላታል።

ከሎ ሆራ ጎይቲን ለአፍታ ትክ ብሎ አያት፤ ጭኖቿ ግጥም ብለው፤ መሃል ለመሃል አጭር ቆዳ ተንጠልጥሎበታል፤ በቆሙት ጡቶቿ መሃል እንብርቷ ተሰርጉዷል፤ በትከሻና በትከሻዋ እንደ ሸለቆ እየጠበበ ወርዶ ዳጉስ ያለው ዳሌዋ የዓይኑን አቅጣጫ አስቀየረው።

ጎይቲ አንገቷን አቀርቅራ ቆይታ ቀና ስትል ደሟ ሞልቶ እንደገና አሟረባት። ከንፈሮቿ የንቡጥ ፅጌረዳ ቅላት ያዙ። ጎይቲ የከሎ ሁኔታ ገባት፤ አባቷ የመከራትንም አስታወሰች፤ «ሴት ልጅ ሣቂታ፣ ወንድ ኰስታራ ነው» ብሏታል፤ እሷም ዕድሜ ልኳን በዚህ ስታምን ኖራለች። ስለዚህ ሣቅ አለች። ከሎ ግን ፈገግታዋን ሲያይ ልቡ ስንጥቅ አለ። በሽተኛ ሆነ፤ ስለዚህ አስታማሚውን ይዞ እንደገና ቁርበቱ ላይ ወጣ።

ጎይቲ ሌላ ትንባሆ ይዛ ለመምጣት የታጠፈ ቆዳዋን ዘርጋ ዘርጋ አደረገች፤ ከሎም አንድ ጊዜ በጥፊ መቶ የተቀበላትን ትንባሆ ይዞ ወጣ። ጎይቲ አንተነህ፣ ከሎ በጣም ይመታኛል ብላ ጠብቃ ነበር፤ እሱ ግን ለአንዱም አንጀቱ አልቻለለትም ነበር።

ጎይቲ አንተነህ ከሎ ሆራ ሥራው ሁሉ እንደ ናቀችው ሆኖ አላገኘችውም። አስተቃቀፉ የላላ ቢሆንም፣ ልቧ እስኪጠፋ ድረስ በደንብ አድርጎ ስሟታል፤ የወንድነት ጥንካሬውም እንደ ደልቲ አንጀት አርስ ባይሆንም የሚያስከፋ ሆኖ አላገኘችውም።

ከጎይቲና ከሎ የፍቅር ጨዋታ በኋላ ጎይቲና ካርለት ሲጨዋወቱ ካርለት ጎይቲን አንዳንድ ነገር ጠየቀቻት።

«ጎይቲ ምነው ደስ ያለሽ ትመስያለሽ?» ካርለት ጎይቲን ጠየቀቻት።

«ይእ!—ተቃበጥኳ» አለች፣ ጎይቲ ፈርጠም እያለች።

«ከማን፣ ከከሎ ጋር?» ካርለት ጉሮሮዋ የጮኸባትን ጨዋታ ቸውን አስታውሳ የተሰማትን ስሜት እያፈነች።

«አዎን» አለች፣ አገጯን ወደ ላይ እየለጠጠች፣ አናቷን ወደ ኋላ በማስተኛት።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ከሉን ወደድሽው?»

«ይእ! ወድጂ ነው።» ጎይቲ የሚያማምሩ ጥርሶቿን በሙሉ እያሳየች ሣቋን ለቀቀች።

«የግብረሥጋ ግንኙነት አደረጋችሁ?» ጎይቲ አንተነህ ካርለት ቂል ሆና እሷንም የተደጋገመና የቂል መልስ እንድትመልስ በመጠየቋ፣ የካርለትን ትከሻ በቀኝ እጇ መታ በማድረግ፣ «ቅድም ነግሬሽ–አዎን ተቃበጥን» አለች። ካርለት እንደ ነገረቻት አስታወሰች፤ በመርሳቷ ግን እራሷን ታዘበች።

«ከከሉ ሆራ ጋር በስሜት ግንኙነት አደረግሽ?»

«ይእ! ድርስ–ከእንግዲህ ወዲያ ስሜቴን ለማን እሰጣለሁ? እሱኮ ከአሁን በኋላ የእኔ ጌታ ነው። ስለዚህ ሁለመናዬን በፍላጎቴ መስጠቴ አይቀርም።»

«...አርጋችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ከሉን ወደድሽው ማለቴ ስሜትሽ ረካ?»

«አዎ– ግን ሳይደጋግም ተወኝ» ብላ፣ ሁለት ጠጠር ከመሬት አንሥታ አሳየቻት፤ ሁለት ጊዜ አረግን ለማለት።

«ለምን አንቺ እንዲደጋግም አትነግሪውም ነበር?»

«ይእ! ልጃገረድ ብሆን ኖሮ እንዳልሽው የፈለኩትን ጠይቄ ወንዶች እንዲፈጽሙ አደርግ ነበር። የሐመር ወንዶች ልጃገረድ ያለቻቸውን ከመፈጸም ወደ ኋላ አይሉም። አሁን ግን ልጃገረድ አይደለሁም፣ ባል አግብቻለሁ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ «እንዲህ አድርጊ» ስባል ማድረግ እንጂ «እንዲህ አድርግ» ብዬ ባሌን መጠየቅ አልችልም።» ጎይቲ አንገቷን ደፍታ ለካርለት መለሰችላት።

«ከሉ ሆራ፣ አይዞሽ አትፍሪ፤ የምትፈልጊውን ሳትሳቀቂ ጠይቂኝ ቢልሽ እሽ ትያለሽ?» አለቻት ካርለት።

«ይእ! ከባህሉ ውጭ? አሁን አንቺስ ይህን አጥተሽው ነው? አንችስ ሴት መስለሽኝ?» አለች ጎይቲ፣ ኩስተር ብላ።

«ጎይቲ እኔ የከሉ ሚስት መስየሽ ነበር?»

«አዎ! የዛኔ ቆጥ ላይ አብረሽኝ እያለሽ ሁኔታው ግር ቢለኝም፣ የሱ ሚስት መስለሽኝ እኮ ነው ሥራ አብረሽኝ ስትሠሪ ዝም ያልኩት።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ግን አለመሆንሽን አወቅሁ። ምነው የሱ ሚስት በሆንሽ ኖሮ፣ ጉልበት ቢያንስሽም አዛባና አበት ለመዛቁ ንገሩኝ ብለሽ ልብ እታወልቂም» አለቻት ጎይቲ፣ በሣቅ እየተንከተከተች።

«ከሉን ለምንድነው እሱ የምትይው፣ በስሙ አትጠሪውም?»

«ይእ!– ገና አንድ እንኳን ሳልወልድ መጥራቱን እፈራለሁ» አለች ጎይቲ ፈርጠም ብላ።

ካርለት ስለ ጎይቲ አንተነህ ባሕርይና ድርጊት ብዙ ነገር ተከታተለች። ስለዚህ ስለሷ የምታውቀው ብዙ ነው። እሷ ደግሞ የሐመር ልጃገረዶችንና የአገቡ ሴቶችን ባሕርይ የምትወክል ናት።

«ጎይቲ፣ ደልቲ ገልዲን ትወጂው ነበር?» ካርለት ጎይቲን ጠየቀቻት።

«ይእ! ነፍሴ እስኪጠፋ ነዋ!» አለች ጎይቲ።

«ለምንድነው ከሌሎች ወንዶች ሁሉ እሱን ነፍስሽ እስኪወጣ የምትወጂው?»

«ይእ!–ጀግና ነዋ፤ ጉበዝ ነው፤ በፍቅር ጨዋታም ጠንካራ ነዋ! ኧረ እሱ ምን የማይሆነው አለቴ። እሱ ሲይዘኝ ልቤ በደስታ ይሞላል። በዚያ ጠንካራ እጁ ወደ ደረቱ እየሳበ ሲለጥፈኝ፣ እኔም ጀግና የሆንሁ ይመስለኛል» አለች ጎይቲ፣ አሁን የምታደርገው ይመስል ዓይኖቿ እየቦዙና እንባዋ ዓይኗ ላይ እየተንግላለለ።

«ጎይቲ እኔና ደልቲ ገልዲኮ ተቃብጠናል፤ እኔም እንዳንች ሳልወደው የምቀር አይመስለኝም» አለች ካርለት በቅናት ገፅታዋ ይቀየር ይሆን ብላ ጎይቲ አንተነህን እያስተዋለች።

«ይእ! እንግዲያው እኔን ብቻ ለምን ትጠይቂኛለሽ። አንችም ከእሱ ጋር ተቃብጠሻል ለካ!» አለች ጎይቲ።

«ጎይቲ ከፍቅረኛሽ ጋር ግንኙነት በማድረጌ አትቀየሚኝም?» ካርለት ጎይቲን ስትጠይቃት፣ ጎይቲ አልገባት አለ። ስለዚህ ካርለት እንደገና፣ «ከደልቲ ጋር በመቃበጤ አትናደጅም?»

«ይእ! ለምን? ልጃገረድ አይደለሽም እንዴ? ካሰኘሽ ጋር ብትቃበጭ ደሞ ጥላቻውና ንዴቱ ምንድን ነው? እሱም ወንድ ነው፤



t.me/OLDBOOKSPDF

ከፈለጋት ሴት ጋር ቢቃበጥ ጠያቂ የለውም። ልጃገረድና ወንድ ደግሞ ለመቃበጡ ማን ከልካይ አለበት? እንዴት እንዴት ጠየቅሽኝ ደሞ?»

ካርለት በሐመር ማኅበረሰብ የአባለዘር በሽታ ችግር እንደሌለ አረጋግጣለች። በሐመር ውስጥ ትልቁ ገዳይ በሽታ ወባ ነው። ሐመሮች ለብዙ በሽታ እንደ መድኃኒት የሚጠቀሙበት ላት ቆርጠው፣ ጨው ይጨምሩበትና አሥረው ጥቂት ጊዜ በማቆየት ጠጣሩ ላት ሲሟሟ ያኔ በቀሰም እየሳቡ ይጠጡታል። ለቁርጠትም የጨፌ ሣር ሥር እንደሚጠቀሙ አይታለች።

ካርለት በጎይቲ መልስ እጅግ ተመስጣ፣ ባህላዊ የግብረሥጋ ግንኙነት ወደፊት ሊያስከትል የሚችለውን ጠንቅ ስታስብ ጎይቲ ደግሞ በተራዋ ጠየቀቻት፣

«ለምንድነው ገላሽ የነጣ?»

«የፀሐይ ቃጠሎ ከማይበዛበት አገር ስለመጣሁ።»

«የመጣሽበት ከኮንሶ ይርቃል?»

«ጎይቲ ኮንሶማ እዚህ እናንተ ጥግ፣ እናንተ አገር እኮ ነው ያለው! እኔ ግን ብዙ አገር አቋርጬ፣ በአውሮፕላን ሰማይ ላይ ሲበር ድምፁ በሚሰማው ነው የመጣሁት።»

«ይእ! አንቺ ደግሞ ቀልደኛ ነሽ። እኔ የእውነቴን ጠየኩሽ፣ አንቺ ግን ትቀልጃለሽ» አለች ጎይቲ።

«ጎይቲ እውነቴን እኮ ነው።»

ጎይቲ አንተነህ ካርለት ያለቻትን እውነት ነው ብላ መቼም መቀበል አትችልም።

«ሰው በሰማይ በሚበረው ይሄዳል ብዬ ባምን አገር በኔ ዓመት አይሥቅም?»

ጎይቲ ትንሽ ቀየም አለች። ካርለትም ጎይቲ አንተነህን ለማስረዳት መጣሩ የማይሳካ ስለሆነባት፣ «አሁን ባታምኚኝም፣ ወደፊት ወስጄ ሳሳይሽ ያኔ ታምኚኛለሽ» አለቻት። ጎይቲ ግን ከአጠገቧ ዞርፍ ብላ ሄደች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 12

ከሎ ሆራና ጎይቲ አንተነህ ሁለት ዘንግ ይዘው ሥጋ ዘመዶቹ ባሉበት ሁሉ መዞር ጀመሩ። አንዱ አጠር፣ ሌላው ረዘም ያሉት ዘንጎች አዲሶች ሙሽሮች ወደፊት የሚወልዷቸው ልጆች ሴትና ወንድ እንደሚሆኑ የሚያበሥር ሲሆን በማኅበረሰቡ «ወንድ ወተት፣ ሴት ልጅ ዝናም ናት» ተብሎ ይታመናል — ሁለቱም የማኅበረሰቡ ዋልታና ማገር መሆናቸውን ለመግለጽ። የሐመር ማኅበረሰብ የሀብት መለኪያ ከብት፣ ለሕልውናቸው መሠረቱ ደግሞ ወተት፣ የከብት ደም፣ በቆሎ፣ ማሽላና ሌሎች የዱር ቅጠላ ቅጠልና ፍራፍሬዎችን የሚያበቅለው፣ የከስኪ ወንዝ ምንጭም ዝናብ ነው።

ስለዚህ፣ ማንኛውም አዲስ ሚስት ያገባ ወንድ ወደፊት ልጅ ወልዶ በሴቶች ልጆቹ ከባሎቻቸው በሚያገኘው ጥሎሽ፣ ከአጐራባች ማኅበረሰቡም ወንድ ልጁ በሚዘርፋቸው ከብቶች በረቱን ስለሚሞላ ሀብታም መሆኑ የማይቀርና ለሌሎቹም ዘመዶቹ ያኔ ሊጠቅም መቻሉን ዘመዶቹ ስለሚያረጋግጡ ለመቋቋሚያ በሬ፣ ወይፈን፣ ጊደር፣ ጥጃ፣ ማር፣ ቅቤ ይሰጡታል። እንዲህ በመረዳዳት በሁለት እግሩ ከቆመ በኋላ እሱም በተራው ሌሎች ዘመዶቹን ሳይማረር ያቋቁማል። ለዚህ ደግሞ ከአዲሷ ሚስቱ ጋር ሁለት ዘንግ ይዞ በመዞር በኮይታ (ጥሎሽ) የተሟጠጠውን ጓዳውን ይጠግናል።

ከሎ ሆራም፣ በዚህ ባህላዊ ደንብ መሠረት ግልድሙን በአጭሩ አገልድሞ፣ የመዳብና ንኬል አንባሩን በቀኝና ግራ እጁ አድርጎ ጥቁር፣ ሰማያዊ፣ ነጭ፣ ቀይ፣ ጨሌዎቹን በአንገቱ አጥልቆ፣ በርኮታውን በመያዝ በኵራ አረማመድ፣ ዳሌዋን ዳንኪራ እያስረገጠች፣ ጡቷን እያስነጠረች፣ ሁለት ዘንግ ይዛ ከምትጓዘው ጎይቲ ኋላ አርጩሜውን ይዞ ይከተላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሎ ሆራ ጥሩ ጥሩ የባራዝ አርጩሜ ይዞ እሱና ጎይቲ በሚዞሩበት መንደር ሲጓዙ በየምክንያቱ ጎይቲ አንተነህን በአርጩሜ ይገርፋታል። ለሽንት ስትቆም ለምን ቆምሽ፣ እንቅፋት ሲመታት ለምን መታሽ፣ ደከሟት ቁጭ ስትል ለምን ቁጭ አልሽ እያለ በየምክንያቱ እንዲገርፍ ባህሉ ያስገድዳል። ሴት ልጅ በኋላ ከቁጥጥር ውጭ ሆና እንዳታስቸግር፣ ባሏ እየገረፈ በማሽቆጥቆጥ ቅን ታዛዥ፣ ሽር ያለች አገልጋይ እንድትሆን ያደርጋል።

ካርለት አልፈርድ ማስታወሻ፣ ካሜራ፣ ድንኳኗን በጨርቅ ከረጢት ይዛ፣ የፍየል ቆዳዋን በመልበስ አብራቸው እየተጓዘች ከሎና ጎይቲ የሚያደርጉትን ትቃኛለች፤ የከሎ ዘመዶች ለከሎ የሚያደርጉለትን ስጦታም ትመለከታለች።

ከሎ ሆራ እናቱ ዘንድ ስጦታ ለመቀበል ላላ መንደር ሲሄድ፣ ካርለት እጅግ በጣም አዘነች። ከሎም በጣም ተሰማው። እናትዬዋ እንዳዩት አቅፈው፣ አንገቱን ሲያሻሹ ቆዩና ካርለትና ሚስቱን ሰላም ብለው ትክዝ ብለው ቁጭ አሉ። ለልጃቸው ምን እንደሚያደርጉለት ጨነቃቸው። ለሱ ስጦታ ያዘጋጁለት መካከለኛ መጠን ያለው ሁለት ቅል ቅቤና አንድ ቅል ማር ብቻ ነው። ከሎ የእናቱን ሁኔታ አይቶ ኃዘን ተሰምቶት ዘወር ሲል፣ ካርለት ተጠጋቻቸው።

«ለምን ያለቅሳሉ?» አለች ትንሽ ዐረፍ ካለች በኋላ።

«ይእ! ልጄ የሚያስፈልገውን ያህል ስጦታ አላገኘማ።»

«እርስዎ ለልጅዎ የሚሰጡት ከብት፣ ፍየል... የለዎትም?»

«የለኝም»

«ለምን?»

«ይእ! እኔ ከብት፣ ፍየል... ኖሮኝም አያውቅም። ወደፊትም አይኖረኝም። በልጃገረድነቴ ከብቶች፣ ፍየሎች፣ በጎች የአባቴ ነበሩ። ባል ሳገባ ደግሞ፣ የባሌ ነበሩ። አሁን ባሌ ሞቷል፤ የከሎ አባት ቢኖር ለልጄ ብዙ ሀብት ይሰጠው ነበር።»

«የባልዎትን ሀብት አልወረሱም?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይእ! ሚስት እንዴት የባሏን ሀብት ትወርሳለች? ባሏ ሲሞት ለወንድሙ በውርስ ትተላለፍና ወንድሙ ሌላውን ሀብት እንደ ወረሰ ሁሉ እሷንም ይወርሳል። እኔም፣ ለባሌ ታናሽ ወንድም እያገለገልኩ እኖራለሁ።» አሁንም ባልቴቷ ፍዝዝ እንዳሉ ናቸው።

«ባልዎ የሞቱ ጊዜ መቼም እንዳሁኑ የበለተቱ አይመስለኝም፤ ከታናሽ ወንድምየው ጋር ይቃበጡ ነበር?»

«ይእ! ይሄማ ይጠየቃል፤ ባሌ እያለም ቢሆን ከታናሽ ወንድምየው ጋር እንጫዋወታለን። እንዲያውም ከሎን የወለድኩት ከሆራ ቬላ ታናሽ ወንድም ነው።» ባልቴቷ ፈርጠም አሉ፣ የሞጨ የጨውን ዓይናቸውን ወደ ካርለት እየመለሱ።

«ምን? ማለቴ የከሎ ወላጅ አባት ሆራ ቬላ አይደለም ነው የሚሉኝ? የሚጠራው እኮ ከሎ ሆራ ተብሎ ነው።» ካርለት መልሱን ለመስማት ጓጓች።

«ይእ! በኛ ባህል አንድ ሴት ከባሏ ታናሽ ወንድም ልጅ ብትወልድ የልጁ አባት የሚሆነው ባሏ ነው። ባሏ እንኳ ሞቶ ከሌላ ወንድ ብትወልድ የልጁ አባት ስም በሟቹ ባሏ ስም ነው የሚሆነው።»

«እና የከሎ እውነተኛ ወላጅ አባት በሕይወት አለ?»

«አዎን አለ።»

«አሁን እርስዎን የሚጦርዎ ማነው?»

«እሱና ልጆቹ።» ካርለት ይህ ለሷ እስከ አሁን ያልሰማችው አዲስ ነገር ነው። ከሎ ሆራም ስለ ወላጅ አባቱ የሚያውቅ አልመሰላትም። ምክንያቱም የግል ታሪኩን ሲነግራት አባቴ ሞቷል ብሎ ነበር።

ካርለት ወደ ከሎ ሄዳ ጉዳዩን ስትነግረው በጣም ተገረመ። ይህን ምሥጢር እሱ ቀደም ብሎ አያውቅም። ወደፊትም ለማወቅ የሚችል አልመሰለውም።

«ካርለት አሁን የምትነግሪኝ ሁሉ ለኔ አዲስ ነገር ነውኮ፤ በጥረትሽ ወላጅ አባቴን እንዳውቅና እንዳገኝ እያደረግሽኝ እኮ ነው» አላት ከሎ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት፣ «ምንም አይደለም፣ ይልቁንስ አባትክን ማግኘት ይኖርብናል» አለችው።

* * *

ጂሚ ሼላ ብዙ አላረጀም። ምቾት ስላለው ሰውነቱ ጠንካራ ቢሆንም ዕድሜው ከ60 በላይ ነው። ካርለትና ከሉ ሆራ እሱ ዘንድ ሲመጡ ከጎጆው ፊት ለፊት በርኮታው ላይ ቁጭ ብሎ ፀሐይ እየሞቀ አገኙት። ካርለት ጂሚን ስታየው ደንገጥ ብላ ከሉን ዞራ አየችው። ከሉ ሆራና ጂሚ ሼላ በጣም ይመሳሰላሉ። ካርለት ጂሚን እንዳየች ከሉ ሆራ አርጅቶ ከፊት ለፊት የተቀመጠ መሰሏት ነበር።

ጂሚ ሼላ ከሉ ሆራን ለመጠየቅ ሻንቆ መንደር ሄዶ ሳለ ካርለትን አይቷታል። ስለዚህ እንዳያቸው አወቃቸው። እነሱም ሄደው አጠገቡ ቁጭ አሉና በሐመር ባህል መሠረት ዕረፍት ከወሰዱ በኋላ፣

«እንዴት ነዎት?» አሉት።

«ደህና ነኝ። እናንተስ እንዴት ናችሁ?» አለ ጂሚ ሼላ።

«ከሉ ለእርስዎ ምንዎ ነው?»

«የወንድሜ ልጅ ነው።» ጂሚ ካርለትን በተመስጦ ተመለከታት።

«መልኩ ግን ቁርጥ እርስዎን ነው የሚመስለው?»

«ሆራ ሼላና እኔም እንመሳሰል ነበር እኮ።»

«ከሉ የእርስዎ ልጅ እንደሆነ ሰምቻለሁ። እንዴት ነው?» ካርለት ዋናው ነጥብ ላይ ዘላ ጥቡልቅ አለች።

«እንዴት ተደርጎ?» ጂሚ ሼላ መልሶ ጠየቃት።

«እርስዎ ከከሉ እናት ጋር... ያረጉ አልነበረም?»

«ያማ ባህል ነው።»

«እና እንዴት ከሉ የማን ልጅ እንደሆነ ያጡታል?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ይሕ! በሐመር ባህል ልጅ ከወንድም ተወለደም፣ ከውሽማ በአባትነት የሚታወቀው ባል ነው። እኔም ከከሎ እናት ጋር ወንድሜ እያለም ሆነ፣ ከዚያን ወዲህ ግንኙነት ቢኖረኝም ከሎ ከማንኛችን እንደ ተወለደ የምታውቀው እናቱ ብቻ ናት።»

ካርለት ነገሩ ገባት። «በሐመር ማኅበረሰብ የልጁን ትክክለኛ ወላጅ አባት የምታውቀው እናት ብቻ ናት ለካ!» ብላ፣ ተደንቃ ቆየችና፣ «ለምን ስምዎ ጂሚ ተባለ?» አለችው፣ ጂሚ ሼላን።

«አንድ ጂሚ የሚባል ፈረንጅ እዚህ መጥቶ፣ ከአባቴ ጋር ተዋውቆ ነበር። እንዳጋጣሚ እናቴ እሱ ከዚህ ሳይሄድ እኔን ወለደ ችኝ። በሐመር ባህል እንግዳ መጥቶ በአጋጣሚ ልጅ ቢወለድ ስሙ በዚያው ሰው ስም ነው የሚጠራው።»

ካርለት ነገሩ ወዲያው ገባት። ምክንያቱም በዚህ መልክ በሷ ስም የሚጠሩ ሁለት ሕፃናት ታውቃለች።

«የከሎ ሆራ እናት፣ የከሎን ትክክለኛ አባት ጠይቂያቸው እርስዎ እንደሆኑ ነገሩኝ» ስትለው፣ ጂሚ ምንም መልስ ሳይሰጣት ከሎ ሆራን ዓይን ዓይኑን ሲያይ ቆየና እጁን ጎተት አድርጎ ያዘው። ከሎ የወላጅ አባቱ ጣቶች እጁን ሲነኩት፣ ደስታ አይሉት ኃዘን ቅጡ የጠፋ ስሜት በመላ አካሉ ተስለከለከበት። ትንሽ ቆይተው አባትና ልጅ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ተቃቀፉ። የወላጅና ልጅ ፍቅር በመካከላቸው ታየ፤ ካርለትም የደስታ እንባ አነባች። የሐመር ፀሐይ ግን ወደ መሠወሪያዋ ወደቀች።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 13

ከሎ ሆራ በፈቃድ ከዩኒቨርሲቲው በተገለለ በሁለተኛ ዓመቱ ትምህርቱን ለማጠናቀቅ አዲስ አበባ ሄደ። ከሎ አዲሳባ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ትምህርቱን ከጀመረ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ለስቲቭ ስልክ ደወለለት። ቀጠሮ ተሰጣጡና እሑድ ዕለት ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ከሎ ከስቲቭ ቀድሞ በቀጠሮው ቦታ ተገኘ። ስቲቭ ልክ በሰዓቱ ሲገባ፣ ከሎ ገና ከበሩ ወደ ቀኝ ሲታጠፍ ተመለከተው። ስቲቭ፣ የሆነ ፖስታ ይዞ የመሮጥ ያህል ሲራመድ፣ ከሆቴሉ ማዕዘን ላይ ካለው ሶፋ ላይ ነጫጭ ጥርሶቹን የሚያብለጨልጨውን ከሎን ተመለከተው። ስቲቭ ፈገግ እያለ ተጠግቶ የእጅ ሰላምታ ተለዋወጡና፣ «ስላንተ በማስብበት ወቅት ላገኝህ በመቻሌ በጣም ተደስቻለሁ» አለ ስቲቭ፣ የፈገግታውን መጠን እየጨመረ።

«እኔም እንደገና ላገኝህ በመቻሌ ደስ ብሎኛል» አለ ከሎ በተራው። በመካከሉ የሆቴሉ አስተናጋጅ በትሕትና ቀርቦ፣ «ምን ልታዘዝ?» አለ። ስቲቭ ማኪያቶ አዘዘና፣ «ከሎ ይህ ፖስታ ለአንተ ከኢንግላንድ የተላከ ነው» ብሎ ሰጠው።

«ለእኔ?» ብሎ፣ ከሎ ስቲቭን በመደነቅ ተመለከተውና የታሸገውን ካኪ ፖስታ ከፈተው። ከሎ ይሆናል ብሎ ባይገምትም ከካርለት ጋር ተመካክሮ ለእንግሊዝ አገር የአፍሪካ ቀንድ አንትሮፖሎጂስቶች ፕሮጀክት ያጭር ጊዜ የትምህርት ዕድል ሐሳብ አቅርቦ ነበር።

«ይገርማል! የአፍሪካ ቀንድ አንትሮፖሎጂስቶች ፕሮጀክት የስድስት ወር የሙያ ማሻሻያ የትምህርት ዕድል ማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንዳገኘሁ የሚገልጽ ነው» አለ ከሎ ስቲቭን ፈገግ ብሎ እያየ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ! አውቄያለሁ። ባለፈው ካርለትና እኔ በአንተ የትምህርት ዕድልና በባለቤትህ የኢንግላንድ ጉብኝት ብዙ አስበንበት ነበር። ሆኖም ግን ስለ መሳካቱ እርግጠኞች አልነበርንም። አሁን ግን ሊሳካ ችሏል።» ብሎ፣ ስቲቭ የእንግሊዝ ቪዛ የተመታበትን ፓስፖርት ሰጠውና፣ «የባለቤትህ ፓስፖርት ዘግየት ቢልም ይደርሳል» አለው።

«ኀይቲ የኖረችበት ዓለም ወደፊት ከምታየው ዓለም የተለየ ነው። ለጭር ጊዜ ቀሪውን ዓለም እንድታይ ማድረጉ ባስተሳሰቧ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል። ኀይቲ በመማር ለማኅበረሰቧ ጠቃሚና የሌሎች እኅቶቿ አርአያ መሆን አለባት» ብሎ ከሎ በተመስጦ ሲያስብ፣ ስቲቭ በጥሞና እየተመለከተው ማኪያቶውን ጠጣና በሌላ ጊዜ ለመገናኘት ስልክ እንደሚደዋወሉ ተነጋግረው ተለያዩ።

ከሎ ሆራ፣ መልሱን በማያውቀው ጥያቄ ለዓመታት በሐሳብ ዥዋዥዌ ሲጫወት፣ አቅሉን ስቶ የወደቀ ሲመስለው፣ በፍርሃትና መራራ ጥላቻ ሲነከር ኖሯል። ጊዜ የምሥጢሮች ሁሉ ቁልፍ በመሆኑ፣ የጠወለጉት እምነቶቹ በሕሊናው ትክክለኛ ፍርድ እየተጠረጉ ሲወጡ፣ በጊዜ የለመለሙ ሐሳቦቹ በሕሊናው ውስጥ ስፍራ ስፍራቸውን ያዙ። ጊዜ ደካማ ሐሳቦቹን ጠገነለት፤ አደሰለት፤ ወለወለለት፤ አጸዳለት።

እራሱን የደበቀውን ከሎን ከመሸገበት የተሳሳተ ምሽግ እንዲመለስ የተጋፈጠው እውነት አስተዋጽኦ አደረገለት። ዛሬ ከሎ የተደበቀ እውነት በማያሰልስ ብርቱ ጥረትና ፍለጋ ከተቀበረበት ማውጣት የሚቻልበትን ልምድ አግኝቷል።

‹ጥቁርን ጥቁር› ከሚሉት ይልቅ ‹ጥቁሩን ነጭ ብንልስ› የሚሉት እውነት ላይ ለመድረስ የተሻሉ እንደሆኑና እነዚህኞቹ ከእነዚያኞቹ የማወቅ ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን ተገንዝቧል።

ዓለማችን እሾህ እንደ ቁጠማ የተንዘነዘባት አይደለችም። እሾህ ግን አለባት። እሾሁ ለሰው ልጆች ችግር እንዲያስከትል አልተ ፈጠረም። ባጋጣሚና በራስ ጥፋት ግን ችግር ሊያደርስ ይችላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዋናው ቁም ነገር ግን የሾሁን ጉዳትና ጥቅም በሚገባ ማወቅና ሊጠቅም የሚችልበትን ዘዴ መፈለጉ ነው። ከነአባባሉስ፣ ‹እሾህን በሾህ› አይደል የሚባለው? ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን በሕይወት ቅንጣቢ ላይ በደረሰ ጥፋት ከጓደኛ፣ ከዘመድ፣ ከሰው፣ ከአገርና ከዓለም ለመሸሸ መሞከር፣ ሕዝብን መናቅ እርካታ ወደማይገኝበት ያዘቅት ሕይወት መንሸራተት ይሆናል።

ከሎ አሁን ልብሱ ሳዳጎራ (ግልድም) ነው፤ የሚጓዘው ካለሚግ፣ የሚተኛው ቆዳ ላይ ነው። ሕሊናው ግን ብስለትን፣ ማስተዋልን፣ መቻልን ተለማምዶ ስለ ደነደነ ደስተኛ ነው። ደስታ የቁስ ውጤት ሳይሆን የሕሊና ትርጉም መሆኑን ከሎ በራሱ ላይ አረጋግጧል።

የእናትን ጡት እየጠቡ ዕድሜ ልክ የማይኖርባት ዓለማችን ለእኛ ብዙ ሽፍንፍን ገፀ–በረከት ታድለናለች። ሽፍንፍኑን ከመፍታታችን በፊት ግን አንድ ልናስተውለው የሚገባ የሕሊና ፍርድ መኖር አለበት። ሽፍንፍኑ ውስጥ የምንፈልገው ወይንም የማንፈልገው በረከት ሊኖር እንደሚችል ማወቅና የማንፈልገው ከደረሰን ሕሊናችን እስኪደማ ድረስ ላለመማረር ራሳችን ለራሳችን ቃል መግባት አለብን። ያገኙትን የሕይወት ዕጣ ለማሻሻል ሁሌም መጣር፣ መድከም ግን ይጠበቅብናል።

ካርለትና ከሎ ሆራ አንዱ ከሌላው ብዙ ተምረዋል። ሁለቱም ለሐመር ሕዝብ ልዩ ፍቅር አድሮባቸዋል። አብሮ መኖር፣ የሕዝብን ሥነ–ሕይወታዊ ቀመር መረዳት ፍቅርን ማስከተሉ የማይቀር ሲሆን ‹መወለድ ቋንቋ› መሆኑን አረጋግጠዋል።

የከሎ ሆራ የመመረቂያ ቀን ሦስት ቀን ሲቀረው ካርለት ኅይቲን ይዛ አዲስ አበባ መጣች። ኅይቲ አዲስ አበባ እንደ መጣች ከሎ ስቲቭ መኖሪያ ቤት ሄዶ ተገናኙ። ኅይቲ ጉድጓድ ውስጥ እንደ ኖረ ውሻ በምታየው ነገር ሁሉ በርገግ–በርገግ ማለቷን ሰውነቷ ሲርበተበት አይቶ ቢረዳም፣ ከሎ አንድ ነገር በሕሊናው ተመላለሰ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሐመር ላይ ልብስ የለበሰ ሰው ‹የደረቀ ዛፍ› ይመስል ከርቀት እንደሚታየው ሁሉ፣ አዲሳባም ለየት ያለ አለባበስ ለብሶ መታየት እንዳሻንጉሊት ያስቈጥራል» ብሎ ከሎ አሰበ። ጎይቲ ደግሞ እንዲያ እንድትሆን ፈቃዱ አልሆነም። ስለዚህ ጉዳይ ከካርለት ጋር ቲመካከር፣ በሐሳቡ ከተስማሙ በኋላ፣ «የከተማ ሰዎች የሚለብሱትን አይተሽ የለ? አንቺም የዚያ ዓይነት ልብስ ልበሺ፤ ወደ ሐመር ስንመለስ ግን የራስሽን ልብስ ትለብሺያለሽ» ብሎ ጠየቃት ጎይቲን።

«ይእ! ለማን ብዬ፣ ያባቴን የወግ ልብስ ትቼ የከተማ ጨርቅ ለምን እለብሳለሁ?» አለችው።

«ለተወሰነ ጊዜ እኮ ነው እንጂ እኛስ ብንሆን ሐመር የምንለብሰውን አይተሽው የለም! እዚህ ከከተማው ሰው ለየት ያለ ልብስ ከለበስሽ የሰው ሁሉ ዓይን አንቺ ላይ ስለሚያርፍ ያሳፍርሻል ብለን ነው» አሳት ከሎ ለማግባባት ያህል ምክንያቱን ዘርዝሮ።

«ይእ! እንዴት ነው ያሳፍርሻል? እነሱ ቢያጠፉ፣ እኔም ልሳሳት፤ እኔ በአባቴ ደንብ ሰው አየኝ ብዬ የማፍር አይደለሁም። በገላዬ የሚያስቀይም ነገር ስለሌለኝ በጨርቅ አልሸፈንም» አለች ጎይቲ ኰስተር ብላ።

ከሎና ካርለት ጎይቲ ባቀረበችው ምክንያት ተቀጥቶ አፍህን ያዝ የተባለ ሕፃን ሆኑ። ጎይቲ፣ ከሎና ካርለትን የኃፍረት ምንጩ ራሱ የተሳሳተ የሕሊና ማነስ ትርጉም ውጤት መሆኑን አስተማረቻቸው። ስለዚህ፣ ሁለቱም ጥያቄያቸውን አነሡ።

ጎይቲ፣ ካርለትና ስቲቭ በከሎ ምረቃ ከተገኙ በኋላ የማስታወሻ ፎቶ ተነሡ። ከዚያም ስቲቭ ቤት ፊት ለፊት ካለው ለምለም ሣር ላይ ቁጭ ብለው ከሎና ስቲቭ ቢራ፣ ካርለትና ጎይቲ ሚሪንዳ እየተጎነጩ፣ የተጠበሰ የከብት ሥጋ ከመጥበሻው ላይ እያነሡ ሲመገቡ እንደ ቆዩ ስቲቭ ወደ ቤቱ ገባና ሲመለስ፣ ለከሎና ካርለት አዲስ ዜና አበሠራቸው።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጎይቲ በቱሪስት መልክ ወደ እንግሊዝ አገር እንድትሄድ በፓስፖርቷ ላይ የእንግሊዝ ቪዛ አስመትቻለሁ» ብሎ ፓስፖርቱን ለከሉ አቀበሉ፤ በግራ እጁ የያዘውን ሻምፓኝ ከፈተ።

ካርለት ከመቀመጫዋ ተነሥታ ትዊስት እየደነሰች፣ ሣቋን ለቀቀችው። ከሉም ለስድስት ወር አጠገቡ በመሆኗ ፊቱ በደስታ «የቀለጠ ኑግ» መስሎ አንፀባረቀ። ጎይቲ ግን በሷ ጉዞ የሚፈነድቁትን ግራ ገብቷት እየተመለከተች ፈገግ አለች። ከዚያ ካርለት ጎይቲን ጠራቻትና፤ «ጎይቲ ከኔ ጋር ለንደን ትሄጂለሽ?» አለቻት።

«እናንተ አሁንስ ብላችሁ ብላችሁ ባህሌን ልታስፈርሱኝ ነው። እኔ በራሴ ፈቃድ የትም የትም አልሄድም፤ እሱን ጠይቂው» አለቻት ጎይቲ አንተነህ፣ ፊቷን ቅጭም አድርጋ።

ከሉ ሆራ፣ «ጎይቲ ፈቅጂልሻለሁ፣ ሂጂ» አላት።

«ይእ! እሱስ አይሄድም? እኔ ብቻ ነኝ የምሄደው?» አለች በድንጋጤ ትከሻዋን ሰብቃ።

«ጎይቲ ከሉን ታፈቅሪዋለሽ?»

«ይእ! አዎና ከእንግዲህ ካለሱ ማን አለኝ» አለች፣ ጎይቲ አንገቷን ቀበር አድርጋ ከሉን ሰርቃ እያየች።

«ደስ ይበልሽ፣ ሦስታችንም አብረን እንሄዳለን» አለቻት። ከሉ ሆራ ሳይታወቀው በሐሳብ ጀት ገብቶ ተሳፈረ። ወዲያው ሦስቱም ስቲቭን ተሰናብተው በመኪናቸው ወደ ሐመር በረሩ። አዕዋፍ ሲዘምሩ፣ ንቦች አበባ ሲቀስሙ፣ ኮርማዎች ሲያገሱ ሦስቱ ጓደኛሞችም የተፈጥሮው ትርዒት ዕድምተኛ ሆነው ተቀላቀሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 14

ካርለት የሁለት ዓመት ከሦስት ወር የሥራ ፈቃዷን ልትጨርስ ቀራት አንድ ሳምንት ብቻ ነው። ከዚህ በፊት ከአንድም ሁለት ጊዜ ጥናት ፈቃዷን አራዝማለች። ዘመናዊው ሕይወቷን በመዘንጋት ለሐመሩ ንጹሕ ሕይወት ረከታለች። ዛሬ የሐመር ሕዝብ ለሷ የለንደን ሕዝብ ነው። ከእንግዲህ ወዲያ ካርለት ኢትዮጵያዊት ነች። ለንደን ሥጋ ዘመዶቿ፣ ሐመር ደግሞ የመንፈስ ወዳጆቿ የሚገኙበት ነው። ዚህ ቀን ካርለት ከከሎ ጋር ስለ ማኅበረሰቡ የወደፊት ዕጣ ነጋግረው ነበር። ካርለት፣ «ሐመሮች በእርግጥ የሚያውቁት ሳቸውን ነው። ከነሱ ውጭ ያለው ዓለም ምን እንደሚመስል ያውቁም። ይሁን እንጂ ከዓለማችን ውጭ በራሳቸው ደሴት ተጠልለው ዝንተ ዓለም መኖር አይችሉም። ተወደደም ተጠላ ከልላቸው ሳይንስ የፈጠራቸው ተሽከርካሪዎችና በራሪዎች ያልፋሉ። ስለ እነሱ ሌላው ሲያውቅ፣ እነሱም ስለ ሌላው ለማወቅ መቻል አለባቸው። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ድልድይ የሐመር ወጣቶች ሊሆኑ፣ የዘመኑን ትምህርት መቅሰም መቻል አለባቸው» ብላ ነግራዋለች። ከሉም ሐሳቧ የሱም እምነት እንደሆነ አረጋግጦላታል።

ካርለት፣ ሐመርን ለመልቀቅ የተወሰኑ ቀናት ሲቀራት ሆዷ እየተሸበረ ተጨነቀች። የገርሲ፣ ፌጦ፣ ኩንኩሮ፣ ጨዋንዛ፣ ግራር፣ ዘንባባ፣ አጋም፣ ጠዬ፣ አንቃ፣ ሌሊሚ፣ ጨውሊምባ፣ ሾላ፣ ዋንዛ፣ የእንኮይ...ደኑ፣ የአሰሌ፣ የካራ ሰንሰለታማ ተራራ፣ የላላ፣ የሻንቆ፣ የወሮ...መንደር፣ የሐመር ልጃገረድ፣ ጐረምሳ፣ አዛውንት፣ ሽማግሌ፣ ባልቴት፣ ቀብራራው ደልቲ ገልዲ በአእምሮዋ እንደ ፔንዱለም ባለማቋረጥ እየተመላለሱ ‹ጨከነሽ ጥለሽን ልትሄጂ› እያሉ፣ ልቧን አንጠለጠሉባት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ካርለት ቀሪውን ጊዜዋን ከብቱን፣ ሰውን፣ ሜካውን ፎቶ ስታነሣ ሰነበተች። ልቧ ግን እንደ ታረደ ዶሮ እየተነሣ ፈረጠባት፤ ስትመጣ ዳር ዳር ቆመው የተመለከቷት ሐመሮች የጉዞዋን ዜና ሲሰሙ ሕሊናቸው ኩምሽሽ ብሎ ዓይናቸው በእንባ ሲሞላ ተመለከተች፤ ስትቀርባቸው ሊወጓት ቀንዳቸውን ያዞሩባት የነበሩት ከብቶች ጠረኗን እየፈለጉ ተጠግተው እጆቿን ላሷት።

ካርለት በሕይወቷ እንዲህ ልብ ሰራቂ የሆነ የሰውና የተፈጥሮ ፍቅር አጋጥሟት አያውቅም። ስለዚህ፣ ልቧ ደረቷን ሲረግጥ፣ ሕሊናዋ አነባ፤ ዓይኖቿም አለቀሱ።

ካርለት ሐመርን ልትለቅ አንድ ቀን ሲቀራት የኢቫንጋዲ ጭፈራውን ለመካፈል አሸዋማ፣ ገላጣና ዙሪያውን በለመለሙ የሐመር እፅዋት ተከቦ ፍቅር እየተቦካ ወደሚጋገርበት፣ ንብ አበባ ወደምትቀስምበት፣ አዕዋፍና ሰዎች ጥዑም ዜማቸውን ወደሚያዜሙበት፣ የእፅዋት፣ የአራዊት፣ የአዕዋፍ፣ የሰው ዳንኪራ ወደሚረገጥበት ስፍራ ተጓዘች።

ካርለት በኢቫንጋዲ ጭፈራ ወቅት ሁሌም እንደምታደርገው ጀግናውን በዓይኖቿ አማተረች። ጀግናው እየዘለሉ አየሩን ከሚቀዝፉት ጉረምሶች መካከል የለም። ካርለት፣ «አምላኬ!» ብላ፣ እንደ መኪና ጎማ ተነፈሰች። በጭንቀት ዓይኖቿ ሲቅበዘበዙ ግን ደልቲ ገልዲ ካለወትሮው ተክዞ፣ ራቅ ብሎ ቆሞ አየችው። ጀግናውን ተክዞ አይታው አታውቅም። ቀጭኔ፣ አንበሳ...የገደሉት አነጣጣሪ ዓይኖቹ ቦዘው ስታይ ሰውነቷ ተዝለፈለፈባት። ጭንቀት ያዘለው ዶፍ ዝናብ ሊያለብሳት መጣሁ ወረድሁ እያለ አጉረመረመባት። ካርለት በደመ ነፍስ ወደ እሱ እየተንቀሳቀሰች፣ «ምን ሆኖ ይሆን?» ብላ ራሷን ጠይቃ ፊት ለፊቱ ሄዳ ቆመች።

«ካርለት» አላትና ዝም ብሎ ዓይን ዓይኗን ተመለከተ።

«ምን ሆንክ ደልቲ?» ብላ ጠየቀችው።

ዝም ብሎ ዓይኖቹን ከሷ ላይ አንሥቶ ወደ ጨረቃዋ ወረወራቸው። ካርለት ዘለሽ እቀፊው እቀፊው አሰኛት።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ካርለት» አለ ደልቲ ዓይኖቹን ሳያወርድ።

«አቤት» አለችው።

ደልቲ ገልዱ ግን ዝም አለ ተመልሶ።

እንደ ባልጩት ድንጋይ እያብለጨለጨ የተከፋፈለው የጭኑና እጁ ጡንቻ፣ ሣንቃው ደረቱ፣ የሚንቦገቦጉት ትናንሽ ዓይኖቹ በጨረቃዋ ብርሃን ካርለት ስታይ የምትይዘው የምትጨብጠው ጠፋት። መላ አካሏ እሳት ላይ የወደቀ ቋንጣ ይመስል ኩምትርትሩ ወጣ።

«ወይ አምላኬ፣ ምናለ የልቡን በነገረኝ፤ ምናልባት መለያየታችን አስጨንቆት ይሆን? መቼም ማለት የፈለገው ነገር አለ፤ ከአንደበቱ እንዳያወጣው ግን እየተናነቀው ነው» ብላ አሰበች።

ይህን ስታስብ፣ «ካርለት–መሄድሽ ነው?» የሚል ከደልቲ ጉሮሮ አፈትልኮ ወጣ።

«አዎ መሄዴ ነው» አለች ካርለት፣ «ምን ሊለኝ ይሆን አምላኬ» ብላ ዓይን ዓይኑን እየተመለከተችው። ደልቲ ግን አሁንም ጸጥ አላት።

«ትወደኝ ነበር?» ብላ የምኝ ጥያቄ ጠየቀችው፤ ደልቲ ግን ትክ ብሎ አይቷት፣ «አይ» አላት፣ በምፀት። ካርለት መልሱ ከልቡ እንዳልሆነ በሚገባ ተረዳች። ካርለት ያኔስ ከቁጥጥሯ ውጭ ሆነች። ጀግናው እንደገና ጣላት። ስለዚህ፣ እጇን ሰዳ እጁን ያዘችውና ወደ ሰንበሌጡ ይዛው ገባች። ከዚያ ጭፈራው በዓይነት በዓይነት ቀጠለ፤ ዳንኪራው ተመታ። አሁንም እንደ ባለፈው ተመልካች በሌለበት የተፈጥሮ አዳራሽ ትርዒታቸውን ለራሳቸው አሳዩ። ዳንኪራው ግን እንዳለፈው ተስፋ ሰጪ ሳይሆን ለየት ያለ፣ የሰቀቀን፣ የኃዘን፣ የህምታ ውዝዋዜ ሆነ።

በነጋታው ፀሐይ ከወደቀችበት ተነሥታ ወደ መሃል ሰማይ ስትገሰግስ ካርለት ዕቃዎቿን በስቴሽን ዋገን መኪናዋ ላይ ከከሎ ጋር አስተካከለው ጭነው እንደ ጨረሱ ሐመሮች ከየመንደሩ ተሰባስበው



t.me/OLDBOOKSPDF

ሴቶቹ ደረታቸውን እየደቁ ሲያለቅሱ፣ ወንዶቹ በርኮታቸው ላይ ተቀምጠው ተከዙ። ካርለት ዓይኗ በእንባ ሊጠፋ ተቃረበ። የሁለት ዓለም ዘመዳሞች ሲለያዩ አምርረው አዘኑ።

ካርለት፣ ከሎ ሆራና ጎይቲ በሽማግሎች ተመርቀው፣ ጀርባቸው በከብት እበት ከተቀባ በኋላ ሦስቱም መኪና ውስጥ ገብተው መኪናዋ ትንቀሳቅሳ አቧራው ሲነሣ የሐመር ጭንቅላቶች ወደ መሬት አቀረቀሩ። ካርለት ትንሽ ከተጓዘች በኋላ ኢቫንጋዲ የጨፈረችበትንና የቦረቀችበትን የሐመር ጫካ ለመሰናበት መኪናዋን አቁማ ስትወርድ፣ ከሎና ጎይቲም አብረው ወረዱና እንባቸውን አወረዱት። ወፎች ግን እየዘመሩ፣ ቱር እያሉ እየበረሩ፣ እየተጻሩ ምግባቸውን መፈለጋቸውን አላቆሙም።

*  *  *

በዋናው የመኸር ወቅት የሐመር የተፈጥሮ ውበትና ልምላሜ የከ ቱን አውጥቶታል። እፅዋት ለምልመው አብበዋል፤ የከስኪ ወንዝ ከአሸዋ በላይ ሆኖ ይፈሳል። የቡስካ ተራራ አሁንም ከቦታው ሳይንቀ ሳቀስ የሐመሮች የታሪክ ሐውልት ሆኖ ፈገግታውን በልምላሜ ያሳያል።

ከአሰሌ ሰንሰለታማ ተራራዎች እስከ ኬንያ ጠረፍ፣ ከኤርቦሬ እስከ አሪ ማኅበረሰብ የሐመሮች ዘፈንና ዳንኪራ አሁንም ከጫፍ እስከ ጫፍ ያስተጋባል። የሐመር ተፈጥሮ ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ከድንቢጥ ወፍ እስከ ጥንብ አንሳ ጆፌ አሞራ፣ ከትል እስከ ተሳቢው ዘንዶ...ከከብት እስከ ሚዳቋና ድኩላ ይፈነጭበታል።

ሁሉም የተፈጥሮ ድምፁን ባሰማ፣ እንቅስቃሴ ባደረገ ቁጥር ውብ የሙዚቃ ቅማሬ ከጋራ ጋራ፣ ከቋጥኝ ቋጥኝ ይስተጋባል። የሐ መር ምድር ለሚመጡትም ለሚሄዱትም ሁሌም ያው ነው። መለም ለም፣ ማበብ፣ መጠውለግ፣ መድረቅ...ተመልሶ ደግሞ መለምለም።

ደልቲ ገልዲን መኪናዋ የሚወዳቸውን ጭና በአራት እግሯ ከቡስካ በስተጀርባ ተሠውራበታለች። መዝናኛዎቹ፣ መደሰቻዎቹን


t.me/OLDBOOKSPDF

ሌባዋ ይዛ በአቧራ ደመና ገብታ ጠፍታበታለች። ደልቲ አሁን ሁለት እግር ያለው፤ ከሌላ ፍጡር ያልተለየ መሆኑን ሳይረዳ አልቀረም።

የጎሽን ጀርባ በአንድ ምት ብቻ አከርካሪውን አድቅቆ የሚያንበረክከው አንበሳ መጨረሻ የዝንብ መዝናኛ መሆኑ የማይቀር እውነት መሆኑን ደልቲ የግድ ሊመለከተው፣ ሊደርስበት ነው።

ያ ከቀጭኔ እይታ ውጭ አልፎ ብብት ስር የሚገባ ፈጣን ሯጭ ፍቅረኞቹን ለመያዝ አቅም አነሰው። ሲሄዱ አላይም ብሎ ከስኪ አሸዋ ገብቶ ተሠወረ። ደልቲ የመለየትን መጥፎ ዕጣ ተጋተ።

ደልቲ አሁን የሚወደውን የማጣት ዕጣ ደርሶት የትካዜ አባዜን እያስተናገደ ነው። እነሱ ጥለውት ሄዱ፤ እሱ ግን ያለው እዚያው ነው። ነገ ልጃገረዶች ለሱ የዘፈኑለት የዘፈን ዜማና ግጥም ለሌላ አዲስ ጀግና ሲተላለፍ ህምታ ሰፍኖበት መቆዘሙ ላይቀር ነው።

አይ ሕይወት! የሞላ መስሎ ይቆይና መፍሰስ ይጀምራል። ፍቅር ሲጀምሩት የጥቅምት ማር ይሆንና ሲያልቅ ግን ይመራል፤ ያስከፋል፤ ያስደምማል። ጀግናው ደልቲ ላይ እንኳን የወደዱትን የማጣት አባዜ እየተንበራቸ እየተጠጋ ነው።

ሁለቱ ፍቅረኞቹ ሲያዩት እንደ በሰለ ድንች በፍቅር ትርከከ ብለውለት ነበር። ‹እቀፈኝ፣ ጠበቅ አድርገህ ወደ ሰውነትህ ለጥፈኝ› እያሉ አዝናንተውታል። ከዚያና ከዚህ እየተቀባበሉ ዘፍነው፣ በጭፈራ ልባቸው ጠፍቶ፣ ልቡን አጥፍተውታል። አሁን ግን እነሱ የሉም። አሁን ተራው የሌላ ነው። ለዛሬ ትናንት ትዝታ ነው። በትናንት እሱ ተውቧል፤ ዛሬ የትዝታው ቀን ናት፤ ነገስ የማን ትሆን?

ደልቲ ገልዲና አንተነህ ይመር ከሐመር አለኝታ፣ ከሐመሮች ሕይወትና ተስፋ ከከስኬ ወንዝ ዳር ተጋድመዋል። ሁለቱም ከተስፋ ይልቅ በትዝታ ይንቦጫረቃሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 15

ልክ በስድስተኛ ወሩ እንግሊዝ አገር ውስጥ በሚገኘው የማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ አዳራሽ ሁለት ቆዳ ለባሽ ሴቶች፣ አንድ ሳዳጎራ ያገለደመ ወጣት፣ ተቃቅፈው በመግባት ቦታቸውን ይዘዋል። አፉን ከፍቶ የነበረው አዳራሽ ቀስ በቀስ ሞልቶ ተጨናነቀ። የዕለቱ አንትሮፖሎጂካዊ ጥናት አቅራቢ የአፍሪካ ውስጥ ምርምሯን ይዛ ወደ መድረክ ወጣች።

«...ከቡራትና ክቡራን፣ በተመራማሪነቴ የሠለጠነው ዓለም ከረሳው ተፈጥሮና ሕዝብ መካከል ተገኘቼ፣ ለዘመናት የዳበረ ባህልና ጥበብ ያለውን ክልል ለማየትና ሕይወቱንም ለመኖር ችዬ እኔ ያገኘሁትን ዕውቀት ለቀሪው ዓለም ሕዝብ ለመግለጽ በመብቃቴ ደስታዬ ወደር የለውም።

«የሐመር ተፈጥሮ፣ ሰው ሠራሽ ብክለት ያልተጠናወተው ንጹሕ ተፈጥሮ ነው። በዓለማችን ፍጹም ደስታ ያለው ሕዝብ አለ የሚል እምነት የለኝም። ደስተኛ ሕዝብ አለ ከተባለ ግን ከሐመር ሕዝብ የበለጠ ደስተኛ፣ ግልጽ፣ በመካከሉ ጠንካራ መፈቃቀር ያለው ያለ አይመስለኝም።

«በዘመናችን እንደ ብርቅ የሚታየው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሐመሮች ለብዙ ዘመናት የሕልውናቸው የማዕዘን ድንጋይ አድርገ ውት ኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ የሐመሮች የዳበረ የከብት አረ ባብ ዘዴ፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ ብሒሎችና ትውፊቶች ወዘተ. ዝብርቅርቁ የወጣውን የዘመነውን ዓለም ዓይን–ልቦና የሚስብ እንደሆነ አምናለሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«...ለማጠቃለል ያህል፣ እኔ የምናገረው የማውቀውን ብቻ ሳይሆን የሚሰማኝንም ጭምር ነው። በእርግጥ ሐመር ላይ ሊሻሻሉ፣ ሊያድጉና እገዛ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ቁም ነገሮች እንዳሉ አምናለሁ። ሆኖም ግን ከሠለጠነው ዓለም የአካባቢ ብክለት ችግር፣ የበሽታ መስፋፋት፣ ተፈጥሮአዊ ካልሆነ የአኗኗር ሥርዓት ችግር አንፃር የሐመር ተፈጥሮ ማራኪ ነው። ሕዝቡም ንጹሕ ሕሊና፣ የዳበረ የአኗኗር ልምድ፣ ተፈጥሮአዊ ፍቅርና በራሱ የሚተማመን ሕዝብ መሆኑን ሳረጋግጥ በዓለማችን እውነቱን በመመስከር ከታወቁት ምስክሮች ራሴን እንደ አንዱ እቈጥረዋለሁ።

«...ቀሪው ዓለም አፍሪቃውያንን መርዳት ብቻ ሳይሆን፣ አሁንም ከአፍሪቃውያን ብዙ የሚማረው እንዳለ ማወቂያው ጊዜ አሁን ነው» የሚለው፣ በጽሑፍና በተንቀሳቃሽ ሥዕል የተደገፈው ጥናቷ ተመልካቿን ከመቀመጫው ናጠው።

ተመራማሪዋ በባዶ እግሯ፣ ቆዳዋን እንደ ለበሰች ጥናቷን ስታቀርብ ቆይታ ስታጠቃልል ያችን ችግርና ሰቆቃ ተቋቁማ፣ የሁለቱን ዓለም ልዩነትና አለመግባባት አስወግዳ፣ እውነተኛ ሰብአዊ ፍቅርንና ሕይወትን ያሳየች ተመራማሪ የአድናቆት ጭብጨባና ጩኸት ለደቂቃዎች በዩኒቨርሲቲው ታሪክ ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ መልክ ቀረበላት። ካርለት አልፈርድ ተባባሪዋንና ጓደኞቿን ይዛ ወደ መድረክ ስትወጣ ጭብጨባው ይበልጥ ጋለ። ከሎና ጎይቲም ሕሊናቸው በደስታ ረካ።

ሦስቱም ጓደኛሞች በሐመር ደን መካከል እንዳደረጉት ሁሉ፣ በማንቸስተሩ የጉባኤ አዳራሽም ተቃቅፈው አነቡ—እየሣቁ አለቀሱ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# 16

በአውሮፓ ሕይወት ከሎ ብዙውን ጊዜውን በትምህርት አሳለፈ። ጎይቲ ግን ከካርለት ቤተሰቦች ጋር ተቀመጠች። ጎይቲ በዓይን ማየት ቀርቶ በወሬ እንኳን በአሳለፈችው ሕይወት ያልሰማችው ጉድ ውስጥ ስትገባ በእውኗ መቃዠት አበዛች።

ከካርለትና ከከሎ ጋር መጀመሪያ ከሐመር ሲነሡ የመኪናው ጉዞ ደስ ብሏት ነበር። ከካርለት ጋር በመኪና ዲመካ፣ ቱርሚ፣ ጂንካም ሄዳ ስለነበር እንደ ልማዷ መኪናዋ ስትጓዝ የሐመር ሰዎችና እፅዋት ወደ ኋላ ሲሮጡ እሷ በሣቅ ፍርስ ብላለች። አንዴ ወደፊት፣ አንዴ ወደኋላ ስታይ እንደ ቆየች ግን የሆነ ነገር ሆዷን አሸበራት። ወዲያው ለካርለትና ለከሎ፣ «ይእ!—አያችሁልኝ የኔን ነገር አገሩን ሁሉ ስሰናበት አያ ደልቲን ግን ሳልሰናበተው ስመጣ? ምናለ እናንተዬ ብትመልሱኝ? አሁን ባል በማግባቴ አንጀቱ የተኰማተረው አንሶት መሄዴን ሲሰማ ሆዱ መንቦጫቦጩ ቀረ! ጀግና ሰው ልቡ ቶሎ ይቀየማል» አለች።

«ጎይቲ አሁንማ ብዙ ርቀን መጥተናል። ቀደም ብለሽ አስበሽው ቢሆን ኖሮ ብንመለስም አይከብድም ነበር። አሁን ግን ብዙ ርቀናል። አንቺስ አያ ደልቲ የሚገኘው ከስኬ ወንዝ አሸዋ ላይ ተጋድሞ መሆኑን እያወቅሽ ለምን ሄደሽ ሳትሰናበችው ቀረሽ?» አላት ከሎ።

«ይእ! እናንተ ልቤን አጠፋችሁታ። እንዲህ አሁን ሆዴን ሊያጥወለውለኝ እዚች መኪናይቱ ላይ መውጣቱም አጓጓኝና እረሳሁት እንጂ! ምነው እናንተዬ ኧረ ኃዘኑ ቅስሙን ይሰብረዋል። ጀግና ሰው ዕድሜው አጭር ነው! መርቀኝ፣ ላገርሽ ያብቃሽ በለኝ ሳልለው ወጥቼ ስመለስ ባጣው ጸጸቱ ዕድሜ ልኬን ይወጣልኛል?» አለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጎይቲ አያ ደልቲን አሁንም ታልሚዋለሽ ማለት ነው። ድሮ የተቃበጣችሁት አይበቃም?» አላት ከሎ ፈርጠም ብሎ።

«ይእ! ኧረ አይልኝ—የአያ ደልቲ ጨዋታ እንደ ከተማ ልብስ የሚወልቅና የሚታጠብ መሰለህ! ሆድ—ዕቃ ውስጥ ነው የሚቀመጥ። አያ ደልቲ አንፈራጦ ብቻውን ይዞት የነበረውን ሰፍራ አንተ ገብተህ እሱን ወደ ጥግ ወሰድከው እንጂ ከሆድ ዕቃዬ አውጥተህ አልጣልከው። እኔና እሱ የአንድ ጎሳ ልጅ መሆናችንና አንተ ባዕድ መሆንህ እኔና አንተን አገናኘን እንጂ የዚያ ጀግና ሎሌ ሆኜ ብኖር ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር» ብላ በሣቅ ስትፍለቀለቅ፣ ካርለትና ከሎ አብረው አጀቧት።

ካርለት ጎይቲ በሐመርኛ ቋንቋ የተናገረችውን ካዳመጠች በኋላ፣ «ምነው ሰው ሁሉ እንዳንቺ ግልጽ በሆነ፣ እውነተኛ ስሜቱን ባልደበቀ። በዚህ ወርቅ መሳይ ብልጭልጭ ዓለም እውነተኛው ወርቅ ሕይወት ሐመር ላይ አለ ቢሉት ማን ጆሮውን ይሰጣል። መተማመን ቀርቶ መጠራጠር ዘውድ በጫነበት በዚህ የውሸት ዓለም እስከ መቼ መኖር ይቻላል?» ብላ፣ ስታስብ ካይኖቿ ስር መጀመሪያ ጉም የመሰለ ነገር፣ በኋላ ተከታትሎ እየተስረገረገ የሚንኳለል ትኵስ እንባ ዓይኗን ሲሞላ፣ መኪናዋን አቁማ መሪው ላይ ተደፍታ መንሰቅሰቅ ጀመረች።

ጎይቲ መጀመሪያ ካርለት እየሣቀች መስሏት ነበር። የቀላውን ፊቷንና የራሰውን ዓይኗን ስታይ ግን ልቧ በኃዘን ተሰብሮ ቆየችና፣ «ይእ! ምነው አይደክማት እሷ ብቻዋን ደፋ ቀና እያለች እኛ ዝም አልናት። በይ አንቺስ ከምታለቅሺ ዕርዱኝ አትይም? እንደ እርፍ ወዲያ ወዲህ የምታማስይውን እንደሁ አያቅተኝም። መዘወሩንም ቢሆን አላጣውም» አለቻት።

«ጎይቲዬ አመሰግናለሁ። መንዳቱ ለአንቺ እንኳ ይከብድሻል! ባይሆን መኪናውን ከሎ ያሽከርክር፣ ወደፊት ግን አንቺም ታሽከረክሪያለሽ» ብላ በታዋን ለቀቀችለት።

ጎይቲ አንተነህ ደስ ያላት ጉዞ እያንገሸገሻት ሄደ። አንገቷን ደፍታ የማታውቀው ጎይቲ ሆዷን አቅፋ፣ አንገቷን አዘነበለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ኀይቲ በአውሮፐላኑ ጉዞም ሆነ በአውሮፓው ሕይወት ቋንቋውን፣ ገጽታውን የማታውቀው ትያትር ተመልካች ሆና ሁሉም ነገር ታከታት። ዙሩው አረማመዷ ስብር ስብር አለ፤ ጥርሶቿ በከንፈሮቿ በጥብቅ ተጋረዱ። የሐመሯን ሸጋ ህምታ ሰፈነባት። ፀሐይ ከእሷ በጣም ርቃ ሙቀቷ ሳይሰማትና ብርሃኗ ሳያስደስታት ወጥታ ገባች። ጨረቃን ከናካቴው ከሰማይ ላይ አጣቻት። ሲያዩት የሚያብለጨልጨውና የሚያምረው ሰው ሠራሽ ውበት፣ እየቆዩ በሄዱ ቁጥር እያፈናት መጣ። መለምለም፣ ጠውልጎ መድረቅ፣ ተመልሶ መለምለም የማያውቀው የተፈጥሮ ቅመም የጎደለው የቴክኖሎጂው ዓለም ለውጥ አልባ በመሆኑ እጅ እጅ አላቸው። ንጹሕ አየር፣ ተለዋዋጩ የተፈጥሮ ውበትና የሚያውደው መዓዛ፣ የአዕዋፍ ዝማሬና የአውሬዎች ጩኸትና ግሳት፣ የጨረቃ ወቅት ዳንስና ጣፋጩ የጫካ ውስጥ ፍቅር በእዝነ ሕሊናቸው ውል እያለ አስቈዘማቸው።

ካርለት በሐመር ሕዝብ ግልጽነትና እሷ በምታውቀው የተጠራጣሪነት ድብቅ ዓለም ያለው ልዩነት ሰፋባት። እንደበት እምነትን የማይገልጽበት፣ ስሜት በቃላት ሾኬ ተመትቶ የሚልወሰወስበትን፣ ችሎታ በፍቅረ–ንዋይ ተተብትቦ የሚንቦራችበትን ዓለም ታዘበችው። የድብብቆሽ ሕይወት፣ ገሐዳዊ እምነት የጎደለው፣ ተፈጥሮአዊ ቅኝቱ ያልተጣጣመና ዝብርቅርቁ የወጣ ሕይወት መሆኑን አረጋገጠች።

የአውሮፓ ሕይወት የተፈጥሮ መሥመሩን የሳተ፣ ሰዎች ተፈጥሮን ለማዛባት የሚፍጨረጨሩበት ጨው አልባ ሕይወት ሆነባት። ስለዚህ ካርለት ጠባይዋ ቀጠነ፣ መነጫነጭ አበዛች። የድሮ ጓደኞቿም አላረካሽ አሏት። ከእሱ ፍቅር ሳይዘኝ አይቀርም ያለችው ሰልካካ አፍንጫ፣ የሚያማምሩ ዓይኖችና መካከለኛ ቁመና ያለው ዴቪድ ጋር እንኳ ፍቅሯ ከሥሩ እንደ ተነቀለ ዕጌረዳ ቀን በቀን እየጠወለገ መምጣቱን አስተዋለች። አንድ ቀን እንዲያውም ካርለትና ዴቪድ በመዝናኛ ክፍላቸው ውስጥ ሲጫዋወቱ፣ «ፍቅሬ! ለምን ሽቅርቅር ማለቱን ተውሽው?» አላት።

«ተፈጥሮ የምታምረው ራቁቷን፣ የሰው ልጅ ባዶ ሙገሳ ጣልቃ ሳይገባባት መሆኑን በመረዳቴ ይሆናላ» ብላ መለሰችለት። ዴቪድ



t.me/OLDBOOKSPDF

በስስ ከንፈሮቹ ጆሮግንዷን፣ ጸጉሯን እየሳመ ቀየና የግራ እጇን ጣቶች በቀኝ እጁ ጣቶች አስገብቶ፣ በቀኝ እጁ ጆሮግንዷን እየዳሰሰ፣ በከንፈሮቹ ከንፈሯን፣ ጉንጯን፣ ዓይኗን፣ ጡቷን...እየሳመ ውስጥ ሱሪዋን ወደ ታች ሲጎትት፣ ካርለት አጠገቧ ሳይሆን ሐመር ትታው የመጣችው ሰው ታወሳት። አዎ! ደልቲ እያሻሸ፣ እያባበለ፣ ውስጥ ሱሪዋን በማውለቅ ወደ ፍቅር ዓለም አይዶላትም። የሷ ስሜት ሲግል፣ የሱም ስሜት ሲግል አንዱ ሌላውን እንደ ሕፃን ሳያባብል፣ አንዱ እየሰማ ሌላውን ለማስተኛት ሳይሞክር፣ አንዱ አውላቂ ሌላው አጥላቂ ሳይሆን፣ የጋራ በሆነ ቅኝት የፍቅር ዳንኪራው ከተፈጥሮው የሙዚቃ ቃና ጋር ተዋሕዶ እየተስረቀረቀ ይንቆረቆራል። የፍቅር ማር ጫካ ካለው ቀፎ ላይ ሁለቱም አፋቸውን ከፍተው፣ ወለላው ምላሳቸው ላይ ጠብ—ጠብ ይላል። ካርለት ያ የሐመሩ ማር ናፈቃት። ስለዚህ ዴቪድን ገፍተር አድርጋ ፊቷን ዞረችበት።

«ዴቪድ አዝናለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ቁልፍ አስገብቶ ሞቶሬን በማስነሣት እንደ መኪና የሚያሽከረክረኝ ሾፌር አልሻም። የጋራ ቁልፍ፣ እኩል የስሜት ምልክትና እርካታ ነው የምሻው። ስለ ጠላሁህ ይቅርታ አድርግልኝ፤ የፍቅር ሚዛኑ የተስተካከለውን ስሜቴን ከእንግዲህ ማዛባት አልሻም።»

«ፍቅሬ፤ አበድሽ ልበል! ዴቭ ነኝኮ! በፍቅሬ ተይዘሽ፣ እኔንም ወደ ፍቅር ዓለም የዘፈቅሽኝ እኮ አንቺ ነሽ። እኔኮ ፍቅርሽን ስራብ ነው የኖርኩት። ትዳር ይዘን፣ ተደጋግፈን፣ ገቢያችንን በማዳበር ጥሩ ሕይወት እንኖራለን እያልኩ የማልም ፍቅረኛሽ ነኝ» አላት ዴቪድ፣ በቀዘቀዘና አንጀት በሚበላ አንደበቱ።

«ፍቅረኛሽ ነኝ አልከኝ ዴቪድ፤ ትዳር እንመሠርታለን ብዬ የማልም ነኝ አልከኝ፤ ይህን ያሰብነውና ያለምነው ትናንት መሆኑን እርግጠኛ ነኝ። ትናንት ደግሞ ለእኔ በሕይወቴ ላይ የተዛባ ፍርድ ስበይንበት የነበረበት ወቅት ነው። ትናንት ዞ ባለ አንበሳ የረካሁበት ጊዜ ነው። ዛሬ ግን ስሜቴ ለዚህ ቁሳዊ ዓለም፣ የሸንገላ ሕይወት እየተማረከ እንዲያሽልብ አልፈልግም። ሐቀኛውን ሕይወትና የጫካውን አንበሳ ከነግርማ ሞገሱ ለማየት በቅቻለሁ። ዴቪድ! ፍቅር ያለው በጫካ ከሚኖሩት ወፎች ነው» አለችው።


t.me/OLDBOOKSPDF

«ካርለት የምትዪኝ አይገባኝም።»

«ስላልገባህ እኔም አልገረምም።»

«እስኪ በፈጠረሽ ታዲያ አፍቃሪሽን–እኔን እንዴት ግፍ ትሠሪብኛለሽ?»

«ዴቭ! ፍቅር ከፋብሪካ የተፈበረከ ሸቀጥ አይደለም። ፍቅር ከላይ የሚለበስ ሳይሆን ከውስጣችን አብቦ የሚፈካ ነው። ስለዚህ ውስጣዊ ስሜቴን ስገልጽልህ ለምን የፍቅር ግፍ ፈጻሚ አድርገህ፣ ፍቅር አልባ ስሜቴን ለመቀበል ትፈልጋለህ?»

ሐሳቧን ከመጨረሷ በፊት ዴቭ ፊቱ ደም መስሎ፣ የደም ሥሩ ተገታተረና የግራ እጁን በቀኝ እጁ በቦክስ አንዴ ነርቶ፣ በሩን በርግዶ አጨሆ በላይዋ ላይ ዘግቶባት ሄደ። ካርለት ጆሮዋን ይዛ፣ አንገቷን ወደ ታች ዘንበል አደረገች።

ጊዜው እየተንተተ ሰባት ወራት ሞላቸው። የካርለትን እምነት ቤተሰቦቿ፣ ፍቅረኛዋና ምቾት ያለው ዘመናዊ ሕይወቷ ሊያስቀ ለብሷት አልቻሉም።

የለንደን ሰማይ በጉም ተሸፍኖ፣ በረዶው በስሱ ያካፋል። የለንደን ኗሪም እንደ ልማዱ በየአቅጣጫው ደፋ ቀና በሚልበት ወቅት፣ ከለንደኑ ሒትሮ አይሮፕላን ማረፊያ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይሮፕላን እያጉረመረመ፣ የለንደኑን ዳመና በአፍንጫው እየሰቀሰቀ ወደ ኢትዮጵያ ሲያቀና ካርለት፣ ጎይቲና ከሎ በሐሳብ ወደነደልቲ ቀዬ ወደ ፊት ቀድመው ተጓዙ – ሐመር...



t.me/OLDBOOKSPDF

ሦስት ፍቅሮች በአንድ ተጋምደው ፥ ነፍስ ዘርተው አካል ገዝተው የሚታዩበት ልብወለድ ነው - የሰው ፥ የሙያ ፥ የማንነት። ሦስቱም ከንጹሕ ልቦና ፥ ከብርቱ መንፈስ ከሐቅ የመነጩ ናቸው። በነዚህ በሦስቱ ተቈራኝተው የሚንቀሳቀሱት ገጸባሕርያት የማንነታቸው ቀለም ሳይፈዝ ፥ የሰብዕና ብርሃናቸው ሳይደበዝዝ እነሱነታቸውን ይዘው በአንድ ላይ ሲኖሩ ይታያሉ።

እንግሊዛዊቷ ካርለት አልፈርድ ፥ ኢትዮጵያውያኑ ከሉሆራ ፥ ደልቲ ገልዲ ፥ አንተነህ ይመርና ውብ ልጁ ጎይቲ አንተነህ በሐመር ማኅበረሰብ ውስጥ በእውነተኛ ፍቅር ሕይወትን በአንድ ሲቋደሱ እናገኛቸዋለን። የሐመሮች ባህልና ወግ ተፈጥሯዊ የአኗኗር ስልት የለንደኗን ወጣት የሥነሰብዕ ተመራማሪ ከቡስካ ተራራ በስተጀርባ የሚፍለቀለቀው ሕይወት ምርኮኛ ያደርጓታል።

የአንድን ማኅበረሰብ ማንነት ለመገንዘብ ቈርጦ የሚነሣ አጥኚ ዓላማውን እግቡ ለማድረስ የሚጓዝባቸውን ጠመዝማዛ መንገዶችና የሚፈጥራቸውን ሰዋዊ ግንኙነቶች እናያለን።

ፍቅረማርቆስ በዚህ ቀዳሚ ድርሰቱ ከሐመሮች ጋር ኖሮ፥ ማዕዳቸውን ተቋድሶ ፥ ውኃቸውን ጠጥቶ ፥ በአፋቸው ተናግሮ በአጠቃላይ እነሱን ሆኖ መልሶ ይሄው እንዲህ ናቸው ይለናል። ባልተወሳሰበ አገላለጽ የተተረከ ብሩህነት ያለው ፥ የገጸባሕርያቱ ድርጊትና ማንነት የሚታይበት ፥ ታሪኩን እስከ ማብቂያው እንድንከታተል የሚያደርጉ አጋጣሚዎችና ሁነቶች ያሉበት ልብ–ሰቃይ ድርሰት ነው።

ዘሪሁን አስፋው
ረዳት ፕሮፌሰር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ዋጋው ብር 10.00

በት·መ·ማ·ማ·ድ· ታተመ

t.me/OLDBOOKSPDF